
ከሀዲዎቹ

ኢትዮጵያን በባርነት ለመግዛት እየተፈፀመ ያለው የክፍለ-ዘመኑ አደገኛ ሴራ!!



ወርቅአፈራሁ አሰፋ

ከሀዲዎቹ

ከወርቅአፈራሁ አሰፋ

ሰኔ 2008 ዓ.ም

ስጦታ

ለሄል

(ጸባየ ሰናይ)

እንደቅርብ ጓደኛሽ ከልብሽ የምትወጂያት
ሶስና (ሶሲ) ይኸው እውን ሆነች..... ‹ኮንግራ!›

ለመጪጊያሽወርቅ

(ዘለአለማዊ እናት)

እርኩስ መንፈስ በላይህ ላይ እያንጎበበ
ሊያስፈራራህና በቁጥጥሩ ስር ሊያውልህ
ቢሞክርም፤ ፈጣሪህን እስከያዝክ ድረስ ምንም
አትሆንምን አትፍራ!

ክፍል አንድ

- 1 -

ፕሪንስተን፣ ኒውጀርሲ

ደቡብ ኢሊኖይስን፣ ምዕራብ ኬንታኪንና ደቡብ ምስራቅ ሚሱሪን ለሚያገለግለውና የABC ተባባሪ ለሆነው WSIL-TV በትርፍ ጊዜዋ የቴሌቭዥን ጋዜጠኛ የሆነችው ሶስና አለማየሁ ከአለቆቿ በተላለፈላት አስቸኳይ ትእዛዝ መሰረት ፕሪንስተን፣ ኒው ጀርሲ ተገኝታለች። አለቃዋ "የውጭ ሀገራት የግል ኢንቬስትመንት ኮርፖሬሽኖችን የስራ ሂደት በተመለከተ ቃለ-ምልልስ የምታደር ጊለት ከፍተኛ ባለሙያ ይጠብቅሻል" ነበር ያላት።

በአፍሪካ የልማት ባንክ ውስጥ የመጀመሪያዋ አፍሪካዊ የዩናይትድ ስቴትስ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር በመሆን አገልግላለች። የውጭ ሀገራት የግል ኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽን (Overseas Private investment Corporation-OPIC) ምክትል ፕሬዚዳንት ሆናም ሰርታለች። በዩናይትድ ስቴትስ ሴኔት (የህግ መወሰኛ ምክር ቤት) ውስጥም ጉልህ የሆነ የሙያ ተሞክሮ ያላት ሶስና በትርፍ ጊዜዋ የቴሌቭዥን ጋዜጠኛ ለመሆን የፈለገችው ለጋዜጠኝነት ካላት ፍቅር እና አክብሮት ነው።

ሰአቷን ተመለከተች። ሶስት ደቂቃዎች ብቻ ቀርተዋታል። ቀድማ መገኘት ያደገችበት ልምድ ነው። ስሟ ሲጠራ ሰማችና ዘወር አለች።

አጠርና ደልደል ያለ ሰውነት ያለው ራሰ-በራ ጎልማሳ ነው፡፡ ጥቁር የጸሃይ መከላከያ መነጽር አድርጓል፡፡ እጹን ለሰላምታ ዘረጋላት፡፡ "ዮናታን ወልዴ እባላለሁ፡፡ ስላገኘሁሽ ደስ ብሎኛል" አላትና አያይዞም "ለቃለ-ምልልሱ ወደተዘጋጀልን አዳራሽ እንሂድ?" ሲል ጠየቃት፡፡ አሳንሰሩን ተጠቅመው ወደ ሆቴሉ አምስተኛ ፎቅ የስብሰባ አዳራሽ አመሩ፡፡ ሙሉ ጥቁር ልብስ የለበሰ የደህንነት ሰራተኛ በአክብሮት ይገቡ ዘንድ ጋበዛቸው፡፡ ሃያ ሰዎች ያህል የሚይዝ መለስተኛ የስብሰባ አዳራሽ ነው፡፡

ዮናታን በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ገባ፡፡ "የመጣሁት ፍሬድሪክስበርግ ቨርጂኒያ ውስጥ ከሚገኘው ስከል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር ቅርንጫፍ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ (እርከን) ስልጣን ያገኘሁት በቅርቡ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በምስጢር ልንጀምረው ላሰብነው የማህበሩ እንቅስቃሴ የበላይ ጠባቂና ተቆጣጣሪ ሆኜ የተሾምኩት እኔ ነኝ፡፡ ኢትዮጵያዊ ረዳት ያስፈልገኝ ነበርና የብዙዎችን ታሪክ ላጠና ያንቺ ሚዛን ደፍቶ በመገኘቱ ልመርጥሽ ችያለሁ፡፡"

አንዱም ነገር አልገባትም፡፡ "ኦ.....አንድ ጊዜ ይቅርታ፡፡ እያልክ ያለኸው ነገር ምኑም አልገባኝም፡፡ አለቃዬ የነገረኝ በውጭ ሀገራት የግል ኢንቨስትመንት....."

አቋረጣት፡፡ "ሶስና፣ አሱኛውን አጀንዳ እርሺው፡፡ ዋንኛው እቅዳችን በመላው ዓለም ላይ ተግባራዊ ልናደርግ ያሰብነውን የአንድ ዓለም አስተዳደር ስርአትና ሀግ ኢትዮጵያ ውስጥም ተግባራዊ ማድረግ ነው....."

"እንዴ አቶ ዮናታን፡፡ ለመሆኑ ማህበራችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊያከናውን ያሰበው ዕቅድ ምንድነው?"

"እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እምነቱን ጠብቆና በፍቅር ተሳስቦ የሚኖር ህዝብ መኖሪያ ናት፡፡ በራሱ ጥበቅ ባህልና ወግ የሚመራን ህዝብ ወደ አንድ ዓለም አስተዳደር፣ ወደ አዲስ ስርአትና ሀግ ማምጣት የሚታሰበውን ያህል ቀላል አይደለም....."

"አንድ ዓለም አስተዳደር?.....አዲስ ስርአት?.....አዲስ ሀግ? ይቅርታ እየገባኝ አይደለም፡፡ እስቲ አብራራልኝ አቶ ዮናታን?"

"ለጊዜው የበላይ አለቆቼ አጠቃላዩን እንጂ ዝርዝር ሃሳቡን አሳውቅሽ ዘንድ አልፈቀዱልኝም። ለግንዛቤ ያህል የተወሰኑትን የዕቅድ ሃሳቦች ላሳውቅሽ.....እና እንዳልኩሽ አንድ የሆነን ህዝብ ለመከፋፈል ወሳኝ የሆኑ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ግድ ይላል።"

"ይቅርታ ህዝብን ለመከፋፈል?"

"አዎን፣ ህዝብን ለመከፋፈልና ህዝቡ የአንድ ዓለም አስተዳደሩን ተግባራዊነት በጸጋ እንዲቀበል በቅድሚያ የማሳመን ስራ መሰራት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ብቸኛው አማራጭ ሚዲያ ነው። በሚዲያ አማካይነት የህዝብን በተለይም ደግሞ የወጣቱን አእምሮ መቆጣጠር ይቻላል። ቀደም ሲል ሲሰራበት የኖረና አሁንም ድረስ እየተሰራበት ያለ ዘዴ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ድሃ ሀገራት ወጣቶችን አእምሮ በባህር ማዶ የመዝናኛ እና ስፖርታዊ ወሬዎች በቀላሉ መቆጣጠር እንደሚቻል እናምናለን። አብረሽን ለመስራት እንደምትፈቅጂ እምነቴ ነው። በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት ስልክሽን እጠብቃለሁ።"

"ቆይ....ቆይ እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ። የኢትዮጵያን ኃያልነትና አንድነት ያልፈለጋችሁበት ምክንያት ምንድነው?"

"ነገርኩሽኮ። ጥብቅ እምነትና አንድነት ያለውን ህዝብ፣ ኃያልነትን መለያውን ያደረገን ዜጋ ወደ አንድ ዓለም አስተዳደሩ አዲስ ስርዓትና ህግ አምጥቶ መግዛት እና ማስተዳደር ይከብዳል። እናም አንድነቱን፣ ኃያልነቱንና ጽኑ እምነቱን ማናጋት ግድ ይላል።"

የሶስና ጠይም ፊት በንዴት አጋም መሰለ። "አቶ ዮናታን! ገባኝም አልገባኝም ከዚህ በላይ ላዳምጥህ አልፈልግም። የምትለውን በሀገሬ ላይ ሸፍጥ እንድሰራ፣ በሀገሬ ወጣቶች ላይ ደባ እንድፈፅም፣ ዕድገቷን፣ አንድነቷን፣ መሻሻሏን የምናፍቀውን ሀገሬን ለዝንተ-ዓለም ከማትወጣበት ጥልቅ ገደል....."

"በቃ፣ በቃ ሶስና። ሃሳቤ ገብቶሻል ማለት ነው። እየሽ፣ እንቺ ፈለግሽም አልፈለግሽም እንኳን ኢትዮጵያን የመሰለች ድሃና

ኋላቀር ሀገር ቀርቶ በመላም ዓለም ላይ የአንድ ዓለም አሰተዳደር ተግባራዊ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ በዚያ ላይ የጠየቅሽውን ያህል ብር እንሰጥሻለን፡፡"

"ምን ያህል ቢከፍሉህ ይሆን?" በንቀት ተመለከተችው፡፡

"ለምስጢር ማህበር አባልነት ከተመለመልሽ በኋላ ከገንዘብ ይልቅ የማህበርሽ ቅን አገልጋይ እንድትሆኚ የሚያስገድድሽ ኃይል አለ፡፡ አባል ካልሆንሽ የዚህን ኃይል ምንነት አትገነዘቢውም፡፡"

ሶስና ንዴቷን መቆጣጠር እየተሳናት መጣ፡፡ "ድንቁም የማህበር አገልጋይ!! ይልቅ በዶላራቸው ሰብዕናዬን ገዝተውታል፣ እንደ አሻንጉሊት ይጫወቱብኛል ብትል ይሻልሃል.....ለማንኛውም በከንቱ አትልፋ፡፡ እኔ መቼም ቢሆን ተባባሪያችሁ አልሆንም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው....."

"አ.... ተረጋጊ ሶስና፡፡ ተረጋጊና አስቢበት...."

ድንገት እመር ብላ ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ ብድግ አለችና ቦርሳዋን አነሳች፡፡

ዮናታንም ከተቀመጠበት ጅንን ብሎ ተነሳና እጁን ለስንብት ዘረጋላት፡፡ በጥላቻ ስሜት ተመለከተችው፡፡

"የማ-ስ--ብ--በ---ት ምንም ነገር የ-ለ--ም! መቼም ተባባሪያችሁ ልሆን አልችልም!"

የፊዝ ፈገግታ አሳያት፡፡ ወደ መውጫው በር ተንደረደረች፡፡ በምጸት ሳቅ የታጀበ ድምጹ ከኋላዋ ተከተላት፡-

"እናያለና!"

መኪናዋን ያቆመችበት ስፍራ እስክትደርስ መንገዱ በጣም የራቀባት መሰላት፡፡ መሪ ብትጨብጥም የምታሽከረክረው በደመ-ነፍስ ነበር.....

- 2 -

ጣሊያን፣ ሚላኖ

አሌክሲስ ሮቢንስ፣ የኤቢሲ ተባባሪ ለሆነው WSIL-TV ቴሌቭዥን ጣቢያ ሪፖርተር ሆኖ ከመመደቡ በፊት ዋሽንግተን ፖስት፣ ቢዝነስ ዊክ፣ ስፖርት ኢሉስትሬትድ እና ፎርልድ ሪፖርት ላይ በአዘጋጅነት ሰርቷል። በተለይ የቢዝነስ ዊክ አዘጋጅ ሆኖ ለስራ በተላከባት የጣሊያን ውብ ከተማ ሚላኖ ያጋጠመውን ክስተት በሕይወት ዘመኑ ሙሉ ፍፁም አይረሳውም።

በወቅቱ ከተማዋ ውስጥ የተዘጋጀ የንግድ ትርኢት ዘግቦ እንዲመጣ ነበር የተላከው። በከተማዋ ውበት ‹ሙቀት› የተሰማው መልኩ-መልካሙ አሌክሲስ በፕሮግራሙ ላይ ተገኝቶ፣ በንግድ ትርኢቱ ይዘት ተደስቶ እና ለጋዜጣው ግብአት የሚሆነውን መረጃ ሰብስቦ እንደጨረሰ በትእይንቱ ላይ ከተሳተፉት የንግድ ትርኢቱ አቅራቢ ቆነጃጅት መሃል ብዙዎች አድናቆታቸውን ከለገሷት የሃያ አራት ዓመት ፊረንሳዊት ጋር ቃለምልልስ አደረገ። በወጣቷ ውበት አፉን ከፍቶ እንደነበር ትዝ ይለዋል። የሰበሰበውን መረጃ ሊያጠናቅር ወደያዘው ሆቴል መኝታ ክፍል ዓመራ። እሩብ ሰአት እንኳን አልቆየም። የመኝታ ክፍሉ በር ተንኳኳ። "ማነው?" አለ በዚህ ሰአት ፈልጎት ከፍሉ ድረስ ሊመጣ የሚችለውን ሰው ማንነት ለመገመት እየሞከረ። መገመት አልቻለም። "ይቅርታ እንዴ ልታናግረኝ ፈቃደኛ ነህ?" የወጣት ሴት ድምጽ። ይህን ድምጽ የት ነበር የሰማው? በሩን በመጠኑ ገርበብ አድርጎ ከፈተው። ቃለምልልስ ያደረገላት ፊረንሳዊት ቆንጆ በሚያማልል አለባበስ በሩ ላይ ቆማለች። ሀልም መሰለው። ሀልም ያለመሆኑን የተረዳው "መግባት እችላለሁ?" የሚለውን ጥያቄ ካቀረበችለት በኋላ እሺታውን እንኳን ሳትጠብቅ ወደውስጥ መራመድ ስትጀምር ነው።

"የሆቴል ክፍሌን በምን አወቅሽው?" ተገርሞ ጠየቃት።

"የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ነገሩኝ" በግድየለሽነት ሰሚት መለሰችለት፡፡ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጣ ንግግሯን ቀጠለች፡፡ "ለምን እንደሆን እንጃ ገና እንዳየሁህ ነው ከሁለት አመት በፊት የተለየሁትን ፍቅረኛዬን ያስታወስኩት፡፡ እሱም እንዳንተ መልከ-መልካም ጋዜጠኛ ነበር፡፡ የአፍጋኒስታንን ጦርነት ሊዘግብ ሄዶ....." እምባዋ አላናግር አላት፡፡

ፍቅረኛዋን በግዳጅ ላይ ሳለ በሞት እንዳጣችው መገመት አልተሳነውም፡፡ በርካታ ጋዜጠኞች በጦር ግንባር ላይ እንደተሰዉ ያውቃል፡፡ ከእነዚህ ጋዜጠኞች መሃል አንዱ የዚህች ፈረንሳዊት ቆንጆ ፍቅረኛ በመሆኑ ከልቡ አዘነላት፡፡

"እና ምን ልተባበርሽ?" አላት ጉጉት በሚነበብባቸው አይኖቹ መላ ሰውነቷን እየቃኘ፡፡ እጹን ለመስጠት ዳር ዳር እያለ እንደሆነ አውቃለች፡፡

"ፍቅረኛዬን ከሚመስል እና የረሳሁትን ትዝታ ከቀሰቀሰብኝ ጋዜጠኛ ጋር መልካም ለሊት ባሳልፍ ችግር አለው?" እንባዋን እያበሰችና ውብ ፈገግታዋን እያሳየች ጠየቀችው፡፡ ቀን በልቡ የተመኛትን ቆንጆ አሁን እቤቱ ድረስ መጥታ በፍቃዷ በግላጭ ስትጠይቀው እምቢ የሚልበት ወኔ አጣ፡፡ እናም አስደሳች ለሊት አሳለፉ፡፡ ቁርስ በልተው ሲለያዩ ያሳለፉትን ለሊት እስኪሚሞት እንደማይረሳው እየማለና እየተገዘተ ነገራት፡፡ ከዚህ በኋላ እንደማይለያዩ ቃል ገባችለት፡፡ አድራሻ ተለዋወጡ፡፡ በሚላኖ ባሳለፈው አስደሳች ቆይታ እየፈነጠዘ ወደመጣበት ተመለሰ፡፡ ያጋጠመው ነገር ፈጽሞ ያልጠበቀው ነው፡፡ ቢሮው በገባ ማግስት የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ጠራውና እጪውን ዱብ የሚያደርግ መረጃ አሳየው፡፡ ከፈረንሳዊቷ ቆንጆ ጋር እርቃኑን ሲያብድ የተነሳው ፎቶ ነው፡፡ "ከዚህ ቀደም የጠየቅንህን ጥያቄ የማትቀበል ከሆነ ፎቶውን ለሀጋዊ ባለቤትህ ከመላካችን በተጨማሪ በምትሰራበት ጋዜጣ ፊት ገጽ ላይ...."

በቃ! ወጥመዳቸው ውስጥ ወደቀ፡፡ ፈረንሳዊቷን ቆንጆ ያሰማሯት እነሱ እንደሆኑና የነገረችው ታሪክ ሁሉ ፈጠራ እንደሆነ

ደረሰበት።። ያዘዙትን እሺ ብሎ ከመቀበል ውጭ አማራጭ አልነበረውም።። ከሰምቹ ወጥመድ ማንም ማምለጥ እንደማይችል እርግጠኛ ሆኗል።። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በምስጢር ማህበር አባላት ስብሰባ ላይ እየተገኘ ባያምንበትም፣ አጀንዳቸውን በሚሰራባቸው የሀትመት ውጤቶች እና የቴሌቭዥን ጣቢያ ላይ እያስተጋባ ነው።።

- 3 -

በጂሰን ምስጢራዊ ቡድን አዳራሽ፣ አሜሪካ

ከኤም አይ ስድስት፣ ከሞሳድ እና ከሲ.አይ.ኤ ተወክለው የመጡት የስለላና የመረጃ ሰዎች በጂሰን ምስጢራዊ የሳይንቲስቶች ቡድን ውስጥ ከታቀፉት እውቅ ሳይንቲስቶች መሃል አንዱ የሆነውን ከርስቶፈር ስቲቨንስ በማባበልም፣ በማስፈራራትም የሰው ልጆችን ቁጥር በፍጥነት ለማመናመን የሚያስችለውን መድሃኒት ቀመር (ፎርሙላ) ይፋ እንዲያደርግላቸው ቢለምኑትም ፍቃደኛ ባለመሆኑ እርምጃ ለመውሰድ ጥቂት ትእግስት ብቻ እንደቀራቸው እየነገሩት ነው። በቡድን ተከፋፍለው መድሃኒቱን ለመስራት የሚያስችለውን ቀመር ከሰሩት ሳይንቲስቶች መሃል ዋናው እና ባለቀመሩ እሱ በመሆኑ ነበር ሙጭጭ ያሉበት። ጸጸት ላይ ላለመውደቅ በመፈለጉ እና በሰው ልጆች ላይ የሚያደርሰው ጥፋት ከወዲሁ ስለታየው ከርስቶፈር ስቲቨንስ ሃሳቡን ቀየረ።

ከመረጃ ሰዎቹ መሃል እጅግ የተበሳጨው እስራኤላዊው ቤንጌሪዮን ሶሎሞን ሌባ ጣቱን ቀስሮ "ስማ ሂንሪ፣ ኪሲንጀር የስነ-ምህዳሩን ቀውስ ለመቆጣጠር ዘጠና ከመቶውን የዓለም ህዝብ ማስወገድ ይኖርብናል ያለው እኮ ያንተን ቀመር ተማምኖ ነው። የዓለምን ህዝብ ለማረጋጋት በየቀኑ ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ያህል ህዝብ ማስወገድ ይኖርብናል ሲል በ1991 ዓ.ም ከዩኔስኮ ኮሪየር ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ ላይ የተናገረው ጃኪውስ ኮስቲዩም ቢሆን በጂሰን ምስጢራዊ የሳይንቲስቶች ቡድን ላይ ጽኑ የሆነ እምነት ነበረው። አንተ ግን የሃያላን መሪዎቻችንን እምነት ገደል ለመክተት እየሞከርክ ነው። ነው ወይስ የስነ-ምህዳሩን ቀውስ ለመቆጣጠር በተወጠነው ሃሳብ ላይ አትስማማም ማለት ነው?"

ክርስቶፈር እነዚህን የሰይጣን መልእክተኞች በውይይት ማሳመን እንደማይችል በማመኑ ገምታን መርጧል። ከመሪጃ ሰምቫ እና ከክርስቶፈር ስቲቨንሰ በስተቀር ማንም የለም። ብዙ ለምነውታል። ብዙ አስፈራርተውታል። የተሰወረ ነገር ባለመኖሩ ፊቱ ምጥጥ ያለው የሲአይኤው ሰውዬ አሚሩን እና ደንዳና ሰውነት ያለውን የእይ ኤም ስድስቱን ሰውዬ ጠቀሰው። ጊዜ አላጠፋም። ከጀርባ ሆኖ በሚማግ ፈላሽ የያዘውን መርፌ አንገቱ ላይ ሰካው። ከአንድ ቀን ራስ መሳት በኋላ የተዳከመ ሰውነቱን በህክምና መሰማሪ ስትሬቸር ላይ አገኘው። ደረቱ ላይ አነስተኛ መጠን ያላት ቲዩብ መሳይ ነገር ተለጥፋለች። እጅግ ደነገጠ። ምን እንደሆነች አወቀ። በተስፋ መቁረጥ ስት ስት ብሎ አለቀሰ።

- 4 -

ኒውዮርክ፣ አሜሪካ

በሙዚቃ ስራዎቿ ዓለም አቀፍ እውቅናን የተጎናጸፈችው ሂዮንሴ ናውልስ በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ እንድታደርገው የተስጣትን ተልእኮ መመሪያ ለመቀበል ኒውዮርክ ውስጥ በሚገኘው የሃሪማን ፓሌይ ቢሮ ተገኝታለች፣፣ አይነ-ፈጣጣው ፓሌይ በሰፊው ቢሮው ሲንጎራደድ ስታይ፣ ሂዮንሴ በጥልቅ ሃሳብ ውስጥ መሆኑን አልተጠራጠረችም፣፣ ከእንቅልፉ እንደመባነን አለና፣

"ዋንኛው የጉዞሽ ምክንያት የሙዚቃ ዝግጅት እንዳልሆነ ቀደም ብዬ ነግሬሻለሁ"

በአምንታ ራሷን ነቀነቀች፣፣

"ጥሩ፣፣ የአንድ አለም አስተዳደርን ሀግና ስርአት ለማስፈን በቅድሚያ የቆየውን ባህልና ወግ መናድ ግድ ይላል፣፣ አቋራጭ መንገድ ደግሞ በብዙ ሃገራት ያስቆፋነውን የሰይጣን አምልኮ እዚያም ማስፋፋት ነው"

አሁንም በመስማማት እራሷን ነቀነቀች፣፣

"በመድረክ ላይ ከምታቀርቢያቸው ዘፈኖች ዋንኛው Sweet Dreams እንዲሆን እንፈልጋለን"

"እሺ" አለችውና በውስጧ እዜመችው፡-

"I am worthy...Hail Satan...I follow Lucifer.
I'm stuck in the fast living...
I'm Sorry for the end of Your Sins."

"የሀጻናት መርሻ ድርጅቶችንም እንድትጎበኚ ፕሮግራም ተይዞልሻል"

"እሺ"

"ለሀጻናቱ ሰይጣናዊ ምልክቶቹን ማሳየትሽን እንዳትረሺ! እሺ?"

"እሺ"

"የምትጎበኟው አንድ ቤተክርስትያንም ይናራል"

"ጥሩ"

"የህዝቡን አእምሮ ለመቀየርና በሃይማኖት አባቶች እና በአማኙ ህዝብ መካከል ልዩነትን ለመፍጠር ይረዳናል ብለን እናምናለን"

"መልካም"

"የመጀመሪያ ተልእኮሽ ዋና አላማ ህዝቡን ከሰይጣናዊ ምልክቶች ጋር ማስተዋወቅ፣ ሰይጣናዊ አምልኮን እንዲቀበል መቀስቀስና ከቆየ ባህልና ወግ እንዲሁም እምነት ጋር ማጣላት መሆኑን እንዳትዘነጊ!"

"ገብቶኛል"

"መልካም መንገድ"

- 5 -

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ዘወትር ምሳ ሰአት ላይ ጥቁር ቆብ ደፍቶ እና ጥቁር ቱሚሰ ለብሶ የጊዮርጊስ ስጋ ቤቶችን የሚያዘወትረው መልከመልካም ወጣት ቄስ ሰሞኑን በደረሰው መልእክት ፍንጥዝጥዝ ብሷል። የተሰጠው ተልእኮ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ቢሆንም ለእሱ በጣም ቀላል ነው። እንኳን እንዲህ አይነት በዋና ዋና ሰዎችና ባለስልጣናት ሽፋን የሚደረግለት ተልእኮ ይቅርና ከእየሩሳሌም እስከ አሜሪካ ስንትና ስንት አይሳኩም የተባሉ ተልእኮዎችን አሳክቷል። በወንጀል ተግባራትም ላይ ተሳትፏል። ውድ የአብያተ ክርስትያናትን ቅርሶች ዘርፎና አዘርፎ በውድ ዋጋ ሸጧል። ለሲ.አይ.ኤ እና ለሞሳድ አልመች ያለ ባለስልጣንን በተካነበት ሰይጣናዊ ድግምት በሱዳን በኩል እያስቀዘነ እንዳስወጣም ይነገርለታል። በቅርብ ለሚያውቁት የባለስልጣኑ በሱዳን ድንበር በኩል መውጣቱ አልነበረም አስገራሚው። በሚወጣበት ወቅት ያጋጠመው ሁኔታ እንጂ። አስቸጋሪው ባለስልጣን ዘንድ በሽምግልና የተላከው ቄስ "እሺ ብለህ ለምን በሰላም አትወጣም?" ሲል ለመነው።

"ሃገሬን ትቼማ.....ያውም ለሰላዮች ስል አላደርገውም። የሚመጣውን ሁሉ እዚሁ እጋፈጠዋለሁ"

"ተው" አለው ቄሱ። "ተው ኋላ ከሚቆጭህ..... "

ባለስልጣኑ ቱግ አለ። "የምን ማቃጠር ነው? ገና ለገና እስራኤልና አሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ወጪዎቼን ሸፍነው አስተምረውኛል ብለህ ነው? ቢገባህስ የምበጅህ የሃገርህ ልጅ

የሆንኩት እኔ ነበርኩ፡፡ ለነገሩ ለጥቅም አድረሀ ወገንህን የሸጥክ አንተብቻ አይደለህም፡፡ ስለዚህ አልፈርድብህም"

ቁሱ አሁንም በለሰለሰ አንደበት ሊያሳምነው ጥረት አደረገ "ጓላ ላይ ከሚመጣው ውርደት እና ሽንፈት ለመዳን....."

ባለስልጣኑ አሁንም እንደተጣደ ጀበና ገነፈለ፡፡ "አታቃጥር አልኩህ እኮ! አትሰ--ማ--ም!"

ቁሱ እዚህ ጋር ትእግስቱን ጨረሰ፡፡

"እንዲያውም ልንገርህ፤ የሚያስወጡህ እነሱ ሳይሆኑ እኔ ነኝ!"

"ም--ን!?" ባለስልጣኑ የምጸት ሳቅ ሳቀ፡፡

"ያውም ቅዘንህን እያስረጨሁህ!"

ቁስ በቹ ከበነጋታው ጀምሮ ባለስልጣኑ በሄደበት.....በየሰው መሃል ጡጥ.....ጢጥ.....ቡም ማድረግ ጀመረ፡፡ ንፋስ ሲያመልጠው የደነገጠው ባለስልጣን ለቤተሰቦቹ እና ለቅርብ ጓደኞቹ ከቁሱ ጋር የተነጋገሩትን ሁሉ ነገራቸው፡፡

"ግዴለህም ከሰይጣን ጋር ሲዶልት ውሎ ሲዶልት ከሚያድር ደብተራ ጋር እልህ መጋባቱ ይቅርብህ እና ነፍስህን አድን" አሉት፡፡

እያመነታ በነበረበት ወቅት "ነፋሱ" ወደጠጣር ፈሳሽ ተቀየረ፡፡ በየአደባባዩ በርጨቅ ማድረግ ጀመረ፡፡

"ይሄ ደብተራ እንደዛተው አዋረደኝ አይደል?" ሲል በንዴት ጸጉሩን እየነጨ በካርቱም በኩል አድርጎ ወደ ግብጽ ኮበለለ፡፡ ቅዘኑ የቆመለት ሲናይ በረሃ ውስጥ እንደነበር ያስታውሳል፡፡ እግዜር እና ሰይጣን የሉም ሲልየነበረው ባለስልጣን ከዚያ ጊዜ በጓላ በፈጣሪ መኖርም፣ በሰይጣናዊ ድግምትም ማመን ጀመረ፡፡ ዋናውን ተዋናይ ቁስ በቹን እየረገመ፡፡

- 6 -

ፍሬድሪክስበርግ፣ ቨርጂኒያ

በደርግ ዘመነ-መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረውና ኢህአዴግ ሀገሪቱን ሲቆጣጠር ወደአሜሪካ የተሰደደው ዮናታን ወልዴ ፍሬድሪክስበርግ፣ ቨርጂኒያ ውስጥ ወደሚገኘው ግዙፍ ህንጻ የመጣበት ምክንያት አልጠፋውም። በዬል የሀግ ዩኒቨርስቲ የኩፍል ጓደኛው የነበረውና ለምስጢር ማህበር አባልነት የመለመለው አሜሪካዊው ቤንጃሚን ፓተርሰን ሁሉንም ነገር በዝርዝር አስረድቶታል። ፓተርሰን ዮናታንን እንዲህ በቀላሉ አሳምነዋለሁ ብሎ ባያስብም ያለ እልህ-አስጨራሽ ደጅ ጥናት እጁን ሰጥቶታል። ቤንጃሚን ፓተርሰን ከዚህ እውነት ላይ የተገነዘበው ዮናታን ወልዴ ዳጎስ ያለ ገንዘብ እና ከፍተኛ ስልጣን እስካገኘ ድረስ ምንም ነገር ሁን ቢባል እምቢ እንደማይል ነው። ዮናታን ወልዴ ከ1996/2004 የዬል የሀግ ዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች መሃከል አንዱ በመሆኑ ዋንኛውን የመመልመያ መስፈርት አሟልቷል። በአሜሪካ ውስጥ ከፍተኛ እውቅና ያለው ስኩል ኤንድ ቦንስ አባል ለመሆን የግድ የታዋቂው የሀግ ዩኒቨርሲቲ ዬል ተመራቂ መሆን እንደሚጠበቅበት ያውቃል። ቤንጃሚን ፓተርሰንም ነግሮታል። ስለምስጢር ማህበሩ ከሚያወሱ መጽሃፍትም አንብቧል።

ዮናታን የስኩል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር አባልነት ጥያቄውን ከእሺታም አልፎ በደስታ በመቀበሉ ወደፊት ለሚያከናውነው ተግባር አምስት ሚሊዮን ዶላር ተመድቦለታል። በኢትዮጵያ ለታሰበው የምስጢር ማህበሩ እንቅስቃሴም የበላይ ጠባቂነቱን ስልጣን ተሸጧል። ዮናታንን በእጅጉ ያስደሰተው እና ራሱን ከዓለም ታላላቅ ባለስልጣናት መካከል እንደአንዱ አድርጎ እንዲመለከት ድፍረት የሰጠው ግንዘቡን የመደበለት ኒውዮርክ

የሚገኘው ፌደራል ሪዘርቭ ባንክ ፕሬዚዳንት አንቶኒ ሶሎሞን መሆኑ ነው። ከእነዚህ ሰዎች ጋር መስራት ማለት ማንንም መጨፍለቅ የሚችል መዳፍ ባለቤት መሆን ማለት ነው። ዮናታን ከግንዘቡ ይልቅ አጥብቆ የሚሻውሸ-ሙቱን ነው። ይህ ሹመት ደግሞ ተራ ሹመት አይደለም። ከምድረ አሜሪካ አልፎ በየትኛውም ሀገር ውስጥ ገብቶ የማዘዝ የመፍለጥና የመቁረጥ ኢ-መደበኛ መብትን የሚያጎናጽፍ የማይደፈር እና የማይገሰስ ሹመት ነው። ይህ ሹመት ከሃገሩ ከመውጣቱ በፊት እንዳሻቸው ሊያሹት እና ሊያሽከረክሩት የዳዳቸውን ባለስልጣናት እና የጊዜው ሰዎች በተራው እንዳሻው ሊያዛቸውና ሊያሽከረክራቸው የሚያስችለው ድንበር ተሻጋሪ ስልጣን ነው። እንደሱና እንደመለመሉት ሰዎች ጽኑ እምነት አለምን በበላይነት ከምትቆጣጠረው የዘመኑ ሃያል ሀገር አሜሪካ በላይ የምስጢር ማህበራት እና የማህበራቱ አባላት አሉ። ከዚህ መሃል ቀንደኛው ዮናታን ወልዴ የታጨበት ስከል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር ነው።

ዮናታን ወልዴንና ቤንጃሚን ፓተርሰንን ጨምሮ በስፍራው የተገኙት የምስጢር ማህበር አባላት ስነ-ስርአቱ የሚጀመርበት ሰአት በመድረሱ ወደህንጻው የምድር ቤት አመሩ። የምድር ቤቱ ባለሁለት ተካፋች መግቢያ በር ከግዙፍ የዋንዛ እንጨት የተሰራ ነው። በአንደኛው ግዙፍ ተካፋች በር ላይ የሰው ራስ ቅል ምስል የተቀረጸበት ሲሆን በሌላኛው ላይ ደግሞ የሰው አጥንት ምስል ተቀርጾበታል። አባላቱ ስነስርአቱ ወደሚካሄድበት ዋነኛ ክፍል ከመዝለቃቸው በፊት የእለቱ አስተናባሪ ስነስርአቱ ከሚካሄድበት ክፍል ፊት ለፊት ወዳለ ሌላ ክፍል መራቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ ተርታ በቆሙት የልብስ መስቀያዎች ላይ ኮሌታ አልባ ጥቁቁር ኮቶች እና ነጫጭ ሸሚዞች ተሰቅለዋል። አስተናባሪው ለራሱ ብቻ የሚሰማ በሚመስል ድምጽ የሆነ ነገርን ሲያልጎመጉም አባላቱ ለብሰውት የመጡትን ኮትና ጀኬት እያወለቁ የተሰቀሉትን ሸሚዞችና ኮቶች መልበስ ጀመሩ። የተለመደ ትዕይንት በመሆኑ በአስተናባሪው የማይሰሙ ቃላት ግራ አልተጋቡም። ለትእይንቱ እንግዳ የሆነው ዮናታን ወልዴም የጓደኛውን ቤንጃሚን ፓተርሰንን

እና የቀሪዎቹን የማህበሩ አባላት እንቅስቃሴ ተከትሎ ኮሊታ አልባውን ነጭ ሸሚዝና ጥቁር ኮት ለበሰ።

ከዮናታን በስተቀር ቀሪዎቹ አባላት በአስተናባሪው አማካይነት የሚያብለጨልጭ ብርማ ሻምላዎችን ታደሉ። በሁለት ረድፍ ከተሰለፉ በኋላ ሻምላቸውን በደረታቸው ፊት ለፊት ወድረው በወታደራዊ እርምጃ ስነስርአቱ ወደሚካሄድበት ክፍል አመሩ። በአስተናባሪው ትእዛዝ ወደኋላ እንዲቀር የተደረገው ዮናታን ወልዶ ዘግይቶም ቢሆን ስነስርአቱ ወደሚካሄድበት ክፍል መወሰዱ አልቀረም። በክፍሉ ሁኔታና በሚመለከተው ነገር ሁሉ ግራ ተጋብቷል። ቤንጃሚን ወደሀንጻው እየመጡ ሳለ የነገረውን ለማስታወስ ሞከረ። *"የመጀመሪያ ጊዜህ በመሆኑ በምታየው ነገር ግራ ልትጋባና ልትደነግጥ ትችላለህ፣ እየቆየህ መልመድህ አይቀርምና አይዞህ ለመረጋጋት ሞክር"*

እንዴት ብሎ? ቀደም ሲል አብረውት የነበሩት አባላት በሁለት ረድፍ ሆነው ሻምላቸውን እንደወደሩ በተጠንቀቅ ቆመዋል።ፊት ለፊታቸው ከሚታየው ዙፋን መሰል ወንበር ላይ የሰው ራስ ቅል፣ የሰው አጥንት፣ መጽሃፍ ቅዱስ፣ የዶሮ ላባ፣ ክፍቱን የተቀመጠ የቀለም ብልቃጥ፣ ያልተጻፈበት ቁራጭ ወረቀትና ብራና ተቀምጧል። ከወንበሩ በቅርብ ርቀት በሚገኘው ክብ ጠረጴዛ ላይ ደግሞ ወረንጠ፣ ቢላዋ እና የብረት ዋንጫ ይታያል። ዙፋን መሰሉን ወንበር ተደግፎ የቆመው ሰው ነጭ ጸጉሩን ልሙጥ አድርጎ ወደኋላው ልጎታል። አንገቱ ላይ ወርቅማ ጥልፍ የሚታይበት ረዥም ቀይ ቀሚስ ለብሷል። ዮናታን ከቤንጃሚን ፓተርሰን መረጃ ላይ በመነሳት ይህ ሰው ፊተናውን የሚያቀርብለትና ሰላሳ ሶስተኛ የማዕረግ ደረጃ ላይ የደረሰ ባለስልጣን መሆኑን ገምቷል። ግለሰቡ ግራንድ ማስተርነት ደረጃ የደረሰ ከፍተኛ ባለስልጣን ነው። በእንቷን ሌቪ የተፃፈውን እና 'Satanic Bible' የሚል ጉልህ ርእስ የሰፈረበትን መፅሃፍ ይዟል።

ጸጥታው የመቃብር ያህል ይከብዳል። ባለስልጣኑ በሻማ ማስቀመጫው ላይ የተሰካውን ሻማ ሲለኩስ አስተናባሪው ዮናታን

ወደባለስልጣኑ ተረብ ብሎ እንዲቆም በምልክት ነገረው። የተነገረውን ፈጸመ። ከፍት ሆኖ የተጋደመውን የሬሳ ሳጥን ሲመለከት ውሃ ሆነ። በፍቃደኝነት ገብቷል። የሚሆነውን በጸጋ መቀበል ግድ ነው።

ግራንድ ማስተሩ እንደደራሽ ውሃ በሚያስገመግም ድምጹ "ወንድም ለመሆን በፍቃደኝነት ወደ ፍሪድሪክስበርግ፣ ቨርጂኒያ የማህበር ቅርንጫፍ እንኳን በሰላም መጣህ። ፈተናውን አልፈህ የመጀመሪያ ደረጃ አባል መሆን ያለመሆንህ በቀጣዮቹ ውስን ደቂቃዎች የሚረጋገጥ ቢሆንም አባል ለመሆን ባሳየኸው ተነሳሽነት በማህበሩ አባላት ስም አመሰግንሃለሁ" አለው። በሌሎች ስፍራዎች ከንግግር በኋላ የሚሰማው ጭብጨባ እዚህ አልተሰማም። አባላቱ ትንፋሻቸውን ዋጥ አድርገው ሻምላቸውን እንደወደሩ በተጠንቀቅ ቆመዋል።

ግራንድ ማስተሩ ዮናታን በጉልበቱ ይንበረከክ ዘንድ አዘዘው። ተንበረከከ። ቁራጭ ወረቀትና የአይን መነጽር ካነሳ በኋላ አቀበለው።

"የአይን መነጽሩን አድርግ!"

የታዘዘውን አደረገ። ቁራጩን ወረቀት አይኑ ስር እያስጠጋ "አንብብ!" አለው። አጨንቁሮ የተጻፈውን ለማንበብ ሞከረ። ባዶ ነበረና ለማንበብ አልቻለም።

"ማንበብ ስላልቻልክ እንዳትሸበር። ሌላ ዘዴ አለ"

አይኖቹን በጨርቅ ጠረገለት። ዳግም እንዲዘጋጅ ነገረው። ወረንጦዎችን አንስቶ ተጠጋው። የተሰለፉት አባላት የበሩ ሻማዎቻቸውን ከፍ አድርገው ያዙለት። የዮናታንን ቅንድቦች መንቀል ጀመረ። ቀጣይ ሂደት እንደሚቀር ተናግሮ ከተንበረከከበት እንዲነሳ አደረገ። በቀጣይነት የቀረበለት ጥያቄ "ፊት ለፊትህ የሚገኘውን መጽሃፍ ቅዱስ ረግጠህ በማለፍ ክፍቱን የተጋደመው የሬሳ ሳጥን ውስጥ ለሰባ ለስንዶች ያህል በጀርባህ ተኛ" የሚል ነበር። እጅግ ቢከብደውም አምኖ ገብቶበታልና የታዘዘውን አደረገ።

ገብቶ እንደተኛ አባላቱ ሻምላቸውን አነሳስተው በአንድ ድምጽ "ወንድማችን እንኳን ደስ አለህ፣ የመጀመሪያ ደረጃ አባላችን ሆነሃል" አሉት፣ ማስተሩ የመጀመሪያ ደረጃ አባልነቱን አረጋገጠለት፡፡ ወዳልተዛፈበት ብራና በማምራትም የዶሮ ላባውን ቀለም የያዘው ብልቃጥ ውስጥ ነክሮ ካወጣ በኋላ የሚከተሉትን ቃላት ጻፈ፡፡

"ዮናታን ወልዴ የስከል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር የአንደኛ ደረጃ ሰልጣን አባል"

ከዚያን እለት አንስቶ ዮናታን ወልዴ በመላው ዓለም በርካታ አባላት ያሉት የስከል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር አባል ሆነ፡፡ ጀማሪ ደረጃ (ኖቪስ) ላይ እያለ በቤንጃሚን ፓተርሰን እና በቀሪዎቹ አባላት አማካይነት የምስጢር ማህበሩ አላማዎች ተነግረውት ተቀብሏቸዋል፡፡

አባላቱ በምስጢር ማህበር አባልነት ሲያጨት የደም ሀረጉ አላሳሰባቸውም፡፡ እንግሊዝ ውስጥ በሚገኙት ስመ-ጥር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሀሮው እና ሳንድኸርስት ከንጉሳውያን ቤተሰቦች ጋር የተማሩትና ከንጉሳውያን ቤተሰቦች ጋር የተጋቡት ስዩም አንተነህ የልጅ ልጅ እንደሆነ በማስረጃ ደርሰውበታል፡፡ መረጃውን ያቀበላቸው ከእንግሊዛዊው ወታደር እና መልእክተኛ ስዩም አንተነህን የተረከበውና እንደልጁ ተንከባክቦ ያሳደገው የጦር ጀኔራል ሰተን ጎልድ ስሚዝ የልጅ ልጅ ብራድ ሰተን ጎልድ ስሚዝ ነው፡፡ ስዩም አንተነህ በልጅ ኢያሱ ዘመነ መንግስት የልጅ ኢያሱ ደጋፊና የቅርብ ባለሟል ነበሩ፡፡ የሸዋ መሳፍንትና መኳንንት ግንባር ቀደም ተዋናይ የሆኑበት የልጅ ኢያሱን አልጋ የመገልበጥ ሕቡእ ሴራ ለመጀመሪያ ጊዜ መስከረም 16 ቀን 1909 ዓ.ም ይፋ ሲሆን "በጥጹም!" በማለት ተቃውሟቸውን ካሰሙት የልጅ ኢያሱ የቅርብ ሰዎች መሃል ግንባር ቀደሙ የዮናታን ወልዴ ቅድመአያት ስዩም አንተነህ ናቸው፡፡

አልጋቸውን ለማስመለስ በቱራ መስክ፣ በሰገሌ(ስሜን ሸዋ፣ በመቅደላ አምባና በደሴ ዙሪያ የአልሞት ባይ ተጋዳይ ፍልሚያ

እድርገው ድል የሸሻቸው ልጅ ኢያሱ በሽሽት ወደአዳል በረሃም ሲገቡ ስዩም እንተነህ አብረዋቸው ነበሩ። የኋላ ኋላ ግን በልጅ ኢያሱ አማካይነት በተዋወቁት እንግሊዛዊ ወታደር እና መልእክተኛ እርዳታ ወደ እንግሊዝ ተሻገሩ። መልእክተኛው ወታደር ስዩም እንተነህን ከእንግሊዛዊው የጦር ጄኔራል ሰተን ጎልድ ስሚዝ ጋር ሲያስተዋውቃቸው "ታማኝና ለወደደው ሟች" በማለት ነበር። ጄኔራሉ ስዩምን ከተመሰከረላቸው በላይ ሆነው አገኛቸው። በምግብ አብሳይነት እና በተላላኪነት ለሁለት አመታት ያህል ካስቀመጣቸው በኋላ ለንጉሳውያኑ ቤተሰቦች የፈረስ ግልቢያ አስተማሪ ሲፈለግ በእጩነት አቀረባቸው።

በወቅቱ የ27 ዓመት ወጣት ነበሩ። ኢትዮጵያ በነበሩበት ጊዜ የተመሰከረላቸው ጋላቢ የነበሩት ስዩም በእጩነት የቀረቡትን ሁሉ በልጠው የእንግሊዛውያኑ ቤተሰቦች የፈረስ ግልቢያ መምህር መሆን ቻሉ። በባህሪያቸውና በታዛዥነታቸው በእንግሊዛውያኑ ንጉሳውያን ቤተሰቦች ዘንድ ግርማ ሞገስ ያገኙት ስዩም ከቤተሰቡ አባላት እንደ አንዱ ተቆጠሩ። የግልቢያው ሰአት ተቀንሶ ትምህርታቸውን ይከታተሉ ዘንድ እድል አገኙ።

ሀገራቸውም ሳሉ ትምህርት ቀመስ ነበሩና ከእንግሊዝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በከፍተኛ ውጤት አልፈው ሀሮውንና ሳንድኸርስትን ለመቀላቀል ጊዜ አልፈጀባቸውም። በንጉሳውያኑ ቤተሰቦች በኩል ሄደዋልና ሀሮውና ሳንድኸርስት በሮቻቸውን አልዘጉባቸውም። በሀሮው ሳሉ ለእንግሊዛውያኑ እጅግ ተወዳጅ የነበረውን የሰር ዊኒስተን ቸርችል "The Duke of Marlbourough" መጽሃፍ አብዛኛውን ምእራፍ በቃላቸው በማነብነባቸው እንግሊዛውያኑ ተደሰቱባቸው። እራሳቸውን አጥብቀው ለሚያፈቅሩትና እንደ ልዩ ፍጡር ለሚመለከቱት እንግሊዛውያን ከበቂ በላይ ነበር። ባይወለደንም ዜጋችን ነው ብለው ተቀበሏቸው። በደም ኢትዮጵያዊ የሆኑት ስዩም እንተነህ በወረቀት እንግሊዛዊ ሆኑ። ሰር ዊኒስተን ቸርችል በተማሩባቸው ሀሮውና ሳንድኸርስት የተማሩት ስዩም ከንጉሳውያን ቤተሰብ ልጆች እንደ አንዱ ተቆጥረው ከንጉሳውያን

ቤተሰቦች የተገኘችውን ኬቲ ታቸርን ሲያገቡ የተቃወማቸው አልነበረም።

እንግሊዛውያኑ ከንጉላውያን ቤተሰቦች አባል እንደ አንዱ ቆጥረው ተቀብለዋቸዋልና በሃገራቸው ባህልና ወግ መሰረት ኬቲ ታቸርን አስረከቧቸው። በአመለካከትና በመንፈስ የተማሰኟቸው ስዩም በእንግሊዛውያኑ የዜግነት መዝገብ ላይ ሰፈሩ። ኢትዮጵያዊ መጠሪያቸውን ወደ ስፔንሰር ቤክሃም ስሚዝ ቀየሩና እንግሊዛዊነ ታቸው ለየላቸው። ከኬቲ ጋር በተጋቡ በአመታቸው አበራ ስፔንሰር ቤክሃም ስሚዝን ወለዱ። እስከ አሰር አመቱ ድረስ ሮን ስፔንሰር ቤክሀም ስሚዝ በሚል መጠሪያ ሲጠራ የቆየው ሮን አባቱ ማታ ማታ የሚያጫውቱት የጀርባ ማንነት ታሪክ መስጠት የማያውቃትን ሀገሩን ማስታወሻ ይሆነው ዘንድ ኢትዮጵያዊ መጠሪያ ስም ያወጡለት ዘንድ ወተወታቸው። ከቀረቡለት በርካታ የስም ምርጫዎች መሃል አበራ የሚለውን ስም በመምረጡ በዚህ ስም መጠራት ጀመረ።

እያደገ ሲመጣ የአባቱን ሀገር የመጎብኘት ፍላጎቱ በማየሉ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። በአምስት አመታት ቆይታው ፍጹም ደስተኛ ነበር። ወደ እንግሊዝ መመለስን ባይፈልግም አባቱ በመኪና አደጋ ህይወታቸው በማለፉ የቤተሰቡን ድርጅት ለማስተዳደር መመለስ ነበረበትና ቅር እያለው ተመለሰ። ከኢትዮጵያዊት ሴት በወለደው ውብ ሀገን ፍጹም ደስተኛ ስለነበር እጅግ ያፈቀራትን ሴት እና ልጁን ይዞ መመለስ ቢፈልግም ወላጆቹ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ብቻውን ለመመለስ ተገደደ። አበራ ለልጁ እንግሊዛዊ ስም ማውጣት አልፈለገም። ወልዴ አለው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ከእንግሊዛዊ አባቱ በሚላክለት ገንዘብ ተንቀባሮ ያደገው ወልዴ እድሜው ለአቅመአዳም ሲደርስ ከሀጋዊ ሚስቱ የወለደው የበኩር ልጁ ዮናታን ወልዴ ነው እንግዲህ በታሪክ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የስክል ሴንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር አባል ሆኖ የተመዘገበው - ያውም የአንደኛ ደረጃ ስልጣን አባል።

- 7 -

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ተንቀሳቃሽ ስልኩ ጮኸ፡፡ "ማን ልበል?" አለ ረድኤት ሃይላይ የደዋዩን ማንነት ሰላላወቀ፡፡

"ወላሂ ታዝቤሃለሁ፡፡ ስንት ነገር ተነጋግረን ስልኬም ጠፋህ? እህ... ጆሮ-ጠቢ ነህ ስልህ እንኳን...." አስታወሳቸው፡፡

"ይቅርታ አሁን አስታወስኩዎት፡፡ እ.....ጋሽ..." ስማቸውን ለማስታወስ ሞከረ፡፡ "ጋሽ ሙደሲር?"

"አዎ፣ ሙደሲር ነኝ.....ሙደሲር" ሰላስታወሳቸው ተደሰተዋል፡፡

ሃይላይ፣ አድልአ ካስመረራቸውና የዚህች ሀገር አካሄድ ካላማራቸው አዛውንት ጋር የተገናኘው ታክሲ ውስጥ ነው፡፡ ሽበት ጣል ያደረገባቸው አዛውንት የሚናገሩትን እያንዳንዱን ቃል ከአንደበታቸው የሚያወጡት በምሬት እያጀቡ ነው፡፡ ጫት ያበለዘው ጥርሳቸው የዛገ ቆርቆሮ ይመስላል፡፡ በንግግራቸው መሀል "እህ" የምትል የብሶት እስትንፋስ ያወጣሉ፡፡ "ወላሂ፣ አሁንስ ብሶታችንን ለማን እንደምንተነፍስ ነው ግራ የገባን፡፡ ጎረምሳ የለመዱ ሴት ልጆቻችን፣ ቤት ውስጥ ሰላም ይነሱናል፡፡ ሚስቶቻችን፣ ኑሮውን እኛ ያስወደድነው ይመስል በገባን በወጣን ቁጥር ይነጫነጩ ብናል፡፡ ሌላው ቀርቶ ተራ የቀበሌ ዘበኛ እንኳን ጉልበት የሚያሳየው እኛ ላይ ነው፡፡ እህ! አላህም ብሶታችን የሰለቸው ይመስል ችላ ብሎናል፡፡"

ሃይላይ እንደዘበት ተመለከታቸውና፣ "ኑሮ እጅግ የመረርዎት ይመስላሉ?" አላቸው፡፡ በቀሉት ዓይኖቻቸው ዘወር ብለው ተመለከቱት፡፡ ‹አንተስ ማን ሆንክና› ይመስላል አመለካከታቸው፡፡

"ተናግሮ ከሚያናግር አላህ ይጠብቀን፡፡ ጆሮ-ጠቢ ነህ መስለኝ፡፡ እና ብትሆንስ? ምን አገባኝ.....አሃ! ዲሚክራሲያዊ ሀገር ነው የምንኖረው እየተባለ አይደል? የተሰማኝን እናገራለሁ፡፡ ደግሞ ቦለቲካ አልተናገርኩም፡፡ አይደለ እንዴ ቆንጂት?" አጠገባቸው የተቀመጠችውን ዘመናይ ወጣት ተመለከቷት፡፡ በአራሷ ዓለም ውስጥ ነበረች፡፡ መልስ አልሰጠቻቸውም፡፡ የፊትም፣ የደፊትም ብሶት የፈነቀላቸውም መስለው ታዩት፡፡ ብሶት አለባቸው፣ ግን ደግሞ በነጻነት ለመተንፈስ ሙሉ ድፍረቱ የላቸውም፤ ነፋሳቸውን ለጥቅም የሸጡ ጆሮ-ጠቢዎችን ይፈራሉ፡፡

"አባባ....."

"አ-ባ-ባ? ልጄ ጋሼ በለኝ፤ ጋሼ ይበቃኛል፡፡ ጋሽ ሙደሲር...."

"እሺ ጋሽ ሙደሲር፣ እኔ ጆሮ-ጠቢ ሳልሆን በአንድ የግል ሚዲያ ተቋም በምትዘጋጅ መጽሔት ውስጥ የምሰራ ጋዜጠኛ ነኝ፡፡ የተሰማዎትን..." አላስጨረሱትም፡፡ ዓይናቸው ውስጥ ተስፋ ተመለከተ፡፡ ደስ ያላቸው መሰሉ፡፡

"ወላሂ ጋዜጠኛ ነህ? ጋዜጠኛ ጋር ማን ይውሰደኝ እያልኩ ባለበት ሰዓት ነው ያገኘሁህ፡፡ እኔ ደግሞ ተንቀልቅለህ ስትጠይቀኝ ጆሮ-ጠቢ መስለኸኝ፡፡ ምን ላድርግ ልጄ? የጆሮ-ጠቢው ቁጥር ከህዝቡ ቁጥር ሊበልጥ ምን ቀረው!? ደሞ ለረባ ገንዘብ መሰለህ? ለአርባ እና ለሃምሳ ብር እኮ ነው፡፡ አየህ፣ እንዲህ ዓይነት የከሀደት ዘመን ላይ ነው የደረስነው፡፡ ሰው እንዴት ለአርባና አምሳ ብር ብሎ ጓደኛውን፣ እህቱን፣ እና ወንድሙን አሳልፎ ይሰጣል!? እርግጠኛ ነኝ የሌለውን አለ፣ ያልሆነውን ሆነ እንደሚሉት እንዳንድ የሹማምንት አገልጋዮች ዓይነት ጋዜጠኛ አይደለህም?" አሉት ዓይን-ዓይኑን በተስፋና በጉጉት እየተመለከቱት፡፡ ሃይላይም በየዋህነታቸው እየሳቀ ራሱን ነቀነቀ፡፡ የዚያኑ ዕለት የተለያዩት ስልክ ተለዋውጠው፣ ሊጠያየቁ ቃል ተገባብተው ነበር፡፡ እነሆም አሁን አሳቸው ቀድመው ደወሉለት፡-

"ይቅርታ ጋሽ ሙደሲር.....የስልክ ቀፎዬን ቀየርኩና ስምምንም.....ቁጥርምንም....."

"እናንተ ምን አለባችሁ? እኛ የመናሪያ ቀኗችንን ሙቀየር አቅቶናል፡፡ እናንተ በየጊዜው የስልክ ቀፎ ቀያይሩ፡፡" እየሳቀ፣

"እንዴ ጋሽ ሙደሲር ቀፎማ ለንብ ነው፡፡ የሰው ልጅ ባይሆን....." አቋረጡት፡፡ ቶሎ ቶሎ ጣልቃ መግባት ይወዳሉ፡፡

"የሰው ልጅ ባይሆን.....ኮንዶሚኒየም ልትለኝ ነው? እሱንም ለማግኘት እኮ እድል ይጠይቃል፡፡ ባለጊዜ መሆን ግድ ይላል፡፡ ይኸው ሲጀመር የተመዘገብኩ እስካሁን ምንም የለም፡፡ እውነቴን ነው የምልህ፡፡ ከአስር ቤተሰቤ ጋር እጅብ ብለን የንብ ቀፎ የመሰለ ቤት ውስጥ ነው የምንኖረው.....ይልቅ እሱን ተወውና ወደዋናው ነጥቤ ልመልስህ?"

"ይሻላል....ይሻላል ጋሽ ሙደሲር" አላቸው፡፡ የሚነግሩትን ለመስማት ጓጉቷል፡፡

"እኔ የምልህ መጽሔትህ አሁንም በስራ ላይ ነው አይደል?"

"አዎ በስራ ላይ ነው"

"መልካም! የህዝብ አይን እና ጆሮ ነን ትሉ የለ?"

"እነማን....ማለቴ...?"

"ምን ያርበተብትሃል? እናንተ ጋዜጠኞች ናችሁ! ደግሞ ልብ በል እነዚህ የተበደለ ሲጠራቸው የሚያላግጡትን፣ ሽራተን እና ሂልተን ዝግጅት አለ ሲባሉ የሚሮጡትን የሹማምንቶቹን ጋዜጠኞች ማለቴ አይደለም፡፡ በግል የምትውተረተሩትን ማለቴ ነው"

"ለህዝብ እስከሰራን ድረስ የህዝብ አይን እና ጆሮ ነን ብንል እናፍርም፡፡ አደራ የሹማምንት ካሷቸው ጋዜጠኞች ጋር እንዳያጣሉኝ"

"ከእናንተም እኮ ከህዝብ ጥቅም ይልቅ ለግል ጥቅም የሚሮጡ አልጠፉም፡፡ ግና የነዚያ ይብሳል፡፡ እንዳያጣሉኝ ነው ያልከኝ? ተጣሉህ አልተጣሉህ ምን ያመጣሉ?"

"ምን አልባት የአየር ሰአት ወስጄ መስራት ባስብ እንኳን...?"

ያን ሰሞን ከአንድ ጓደኛው ጋር የቴሌቭዥን እና የራዲዮ የአየር ሰአት ወስዶ ለመስራት በዝግጅት ላይ ነበር።።

"እና ይከለክሉናል ብለህ ፈራህ?"

"ሃላቤ ገብቶዎታል"

በእልህ እና በንዴት እንደሚናገሩ ያስታውቃል።።

"ይክልክሉሃ! ቢከለክሉህ ምን ይቀርብሃል? የሚቀርብህ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ስክሪን ላይ ፍጥጥ፣ ግጥጥ ብለህ በማያስቀው መገልፈጥ።። ሰው ሰምቶ የሰለቸውን መረጃ ከሌላ ፕላኔት ላይ በምርምር ፈልገህ ያመጣህ ይመስል በእኛ ድርጅት ብቻ የሚገኙ መረጃዎችን.....ብለህ መኩፈስ።። ወላሂ ጠይቀህ ቢከለክሉህ ይሻላል"

"አልገባዎትም እኮ!"

"ገብቶኛል።። ያሰብከው ብቻ ሳይሆን ወደፊት የምታስበውም ይገባኛል።። ይልቅ በአዛውንትነቴ ልምከርህ።። ይክልክሉህና የተሻለ ትልቅ ነገር አትርፍ"

ጓጉቶ "ምን?" አላቸው።።

"የህዝብ ፍቅር! በየጣራው ላይ የበዛው ሳህን ያለምክንያት የተሰቀለ መስሎሃል?"

ተአምረኛ አዛውንት እንደሆኑ እየገባው ነው።።

"ምክንያቱን ይንገሩኛ?" አላቸው የሚሉትን ለመስማት ጓጉቶ።።

"ነገርኩህ እኮ።። ጨጓራ የሚልጥ ላቅ ከመመልከት፣ የቆረፈደ መረጃ ከማድመጥ አልበላም አልጠጣም ብሎ ሳህን መስቀሉ ይሻላል"

"አደዋወልዎ የሆነ መረጃ ሊነግሩኝ መስሎኝ?"

"ልክ ነህ ልጄ።። እባክህን ጭንቅ ጥብብ ብሎኛል"

"ምነው...ምን ገጠመዎት?"

"ጭንቀቱ እና መሳቀቂ ከመብዛቱ የተነሳ እንደሌባ አምሽቼ መግባትና ማለዳ መውጣትም ጀምሬያለሁ"

"እኮ በምን የተነሳ?"

"ጭንቀቱ ለእኔ ብቻ የተረፈ መሰለህ? ባለቤቴ እና ልጆቼም የሚሄዱበት ጠፍቷቸው እንጂ ጠዋት ወጥተው ውድቅት መግባትን በወደዱ"

"በምን የተነሳ አልኩዎት እኮ?"

"ሽሽት ነዋ ልጄ.....ሽሽት"

"አልገባኝም ሽሽቱ ከማነው?"

"በገዛ ሃገራችን ጉልበተኛ ነን ባይ የቀበሌ ሹሞችን ሽሽት ጠዋት ወጥተን ውድቅት እንገባ ዘንድ ተገደናል"

"በግልጽ ይንገሩኝ?"

"የዛሬ ሁለት አመት ገደማ ምን ሆነ መሰለህ? በህዝብ የተመረጥን ነን ያሉ ሶስት አራት ሰዎች ተሰባስበው መጡና የልማት ብር አምጡ አሉን። አንዱማ የቀበሌ ሊቀመንበርነቱን ከለላ አድርጎ ከአንድ ጓደኛችን የወፍጮ ቤት ጉዳይ አስጨርሰልሃለሁ ብሎ አስር ሺህ ብር ጭርግድ አድርጎ የበላ ነው"

"ግን እኮ ጋሽ ሙደሲር ልማት ይወደዳል እንጂ አይጠላም" አላቸው ጣልቃ ገብቶ። ተበሳጩ።

"ውይ የልጅ ነገር ከአፌ አትንጠቀኝማ። በህዝብ የተመረጥን ስትሉ ምን ማለት ፈልጋችሁ ነው? እኔስ ከህዝቦች መሃል እንዱ አይደለሁምን? እኔ መች መረጥኳችሁ? አልኳቸው። እመድህ ቡን ይበል ልጄ ከመሃላቸው አንዱ አመዴን ቡን አደረገችው። ድሮም እናውቅሃለን ጸረ-ልማት አይደለህ? ከጎንህ ታገኛታለህ ብላ ስታስፈራራኝ ያመንኩበትን ሳይሆን እነሱ ከአቅሜ በላይ የጣሉብኝን ክፍያ ማንቁርቴን ታንቄ ከፈልኩ"

"እና ልማት የተባለው ነገር ተሰራ ወይስ...?"

በብስጭት መለሱለት፡፡ "ተሰርቷል ይባል አይባል አላውቅም"

"ማለት?"

"ግንዘብ ያወጣነው ምስኪን ድሆች ሰፈራችን ላይ ምንም አላየንም፡፡ በህዝብ ተመረጥን ያሉት የቀበሌ ሹሞች ግን ደጃፋቸውን በኮብል ስቶን አሳምረው....."

"በእኛ ግንዘብ ተመረጥን ያሉ ሹሞች ሰፈር ለማ እያሉኝ ነው?"

"እንደዚህ አይነት ጉደኛ ሀገር ውስጥ ነው ያለነው ምን ታደርገዋለህ?.....ምን ይደረግ ልጄ እንዲህ አይነት የቀን ጅቦች ያሉበት ሃገር ውስጥ ነው የምንኖረው"

እጅግ ተበሳጭቶ ነበር፡፡

"ታዲያ ለምን ለሚመለከተው አካል....?"

አላስጨረሱትም፡፡

"የሰለቸኝን ጥያቄ አትጠይቀኝ፡፡ መጀመሪያውኑ የሚሰማህ ሲኖር አይደል፡፡ ፍትሃዊ አስተዳደር የምታገኘው፣ ብሶትህ ተደማጭ የሚሆነው፣ ችግርህን እንደየአግባቡ ለመፍታት ጥረት የሚደረገው ኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ላይ ነው፡፡ ወደምድር አውርደህ እውነቱን ስትመለከተው ግን.....ተወኝ ልጄ ጠግቦ ለመብላት ባልታደለ አንጀቴ አታስለፍልፈኝ....አታድርቀኝ፡፡ አንደኛው ጅብ ሲጠግብ ሌላ ጅብ ይልኩብሃል እንጂ <አካል> ያልካቸው መች ይሰሙሃል?!"

"ይህማ የአይን በአይን ዘረፋ ነው"

"እሱን ነው እኮ የምልህ፡፡ እኔና የእኔ ቢጤዎች በድርጊቱ እየበሸቅን፣ የሚሰማን አጥተን እያለቀስን፣ ሮሮአችንን ለአላህ ነግረን እንደተቀመጥን ሌሎች ጅቦች መጡልህና <የልማት?> አሉን"

"እሺ ምን ብላችሁ መለሳችሁ?"

"እየጮህኩ፣ እያጓራሁ፣ እየፎከርኩ ያለፈውን በደል ብናገር ማን ሰምቶኝ?"

"ጆሮ የሚሰጥዎ ጠፉ?"

"እንዲ ነገረኛ ፊት ያላት ልጅ ምን እንዳለችኝ ታውቃለህ? ያለፈው ብር መበላቱን ሰምተናል፡፡ እኛ ግን ሃቀኛ የልማት አስተባባሪዎች ነን"

"ጥሩ፡፡ ሃቀኛ የልማት አስተባባሪዎች ለመሆናችሁ ከሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ ይዛችሁ ኑ አልኳቸው፡፡"

"እና.....?"

"በተራዬ ማላገጥ ፈልጌ እንጂ ያልተለመደ ጥያቄ መሆኑን አላጣሁትም፡፡ ‹ኮሚክ ነገር ነዎት ልበል? ቀልዱን ይተውትና ገንዘቡን ይስጡን?› አለችኝ፡፡ ሃቀኛ የልማት አስተባባሪዎች ነን ያለችው ሴት፡፡.....ያው አምባገነኖች የበዙበት፣ ሰሚ የሌለበት ሃገር በብስጭት የበሽታ ጎሬ ከመሆን ውጭ ምንም ማድረግ እንደማልችል አውቃለሁና አሁንም የአቅሜን ሳይሆን እነሱ የወሰኑብኝን ከቤተሰቤ ጉሮሮ ነጥቄ ሰጠሁ፡፡"

"እሺ እነዚህስ ልማቱን ሰሩ?"

"የእነዚህ ትንሽም ቢሆን ይሻላል፡፡ የሆነ ቱቦ ነገር መቅበር ሲጀምሩ እውነትም ሃቀኛ የልማት አስተባባሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም አልን፡፡ ይህን ብለን ደስታችንን አጣጥመን ሳንጨርስ፣ የተቀበረው ቱቦ ላይ አፈር ሳይመለስ ሁሉም ነገር ቀጥ"

"ምነው ተባለ?" አለ በአግራሞት፡፡

"ኮሚቴዎቹ በገንዘብ ተጣሉ!"

"እንዴት ነው ነገሩ ማን ባዋጣው ገንዘብ ማን ይጣላል?"

"አልሰማኝ አልክ እንጂ ምን አይነት የጉድ ሃገር ውስጥ እየኖርን እንደሆነ እየነገርኩህ ነው፡፡ ተወኝልጂ የሚወራው ሌላ፣ የሚሰራው ሌላ፡፡ የሃገራችን ነገር እንዲህ ሆኖልሃል፡፡ በሚዲያ የሚሰብኩን ሌላ፣ በአይናችን የምንመለከተው ሌላ"

"ታዲያ የአሁኑን ሽሽት ምን አመጣው?" ታሪኩ እንደ ልብ ሰቃይ ድርሰት መስጦታል፡፡

"ልጄ ሙት እንደዚያ በቱሉቫሽሮን ማስታወቂያ ላይ አርሟለሁ እንዳለው ሰውዬ አደባባይ ወጥቼ አርሟለሁ እንጂ ለሶስተኛ ዙር የቀን ጅቦችማ እጄን አልሰጥም፣፣ እንዳያገኙኝ ብዬ እኮ ነው እንደሌባ ሌሊት ወጥቼ ሌሊት የምገባው"

"እስክመቼ እየሸሹ?"

"ለህዝቦቹ የሚያስብ እና የሚቆረቆር መሪ እስኪመጣ፣፣ ሙሰኞችን በወሬ እና በምላስ ሳይሆን በተግባር የሚቀጣ መሪ እስኪመጣ፣፣ ጉልበተኛ እና እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚል የቀበሌ ሹም፣ አምባገነን ባለ ወንበር የሚወገድበት ሰናይ ጊዜ እስኪመጣ .....እስከዚያው ጉልበተኛና ባለጊዜ የበዛበት ሀገር ነዋሪ እስካደረገኝ ምን አደርጋለሁ? በቃህ እስኪለኝ ስሸሽ እና ስደበቅ እናራለሁ"

"ለምን ከኮሚቴዎች ጋር በሰከነ እና በሚያግባባ ሁኔታ አትነጋገሩም? መቼም ልማት ለአንድ ሀገር አስፈላጊ ነው?"

"ወይ ምስኪን! ወይ መግባባት! አዎ አንተ እንዳልከው ልማት ለአንድ ሃገር እጅግ አስፈላጊ ነው፣፣ በልማት ስም ህዝብን የሚዘርፉ ጅቦች ግን አስፈላጊ አይደሉም፣፣ የሶስተኛው ዙር ኮሚቴዎች ደግሞ የሚገርሙህ ናቸው፣፣ ኪስህን የሚያውቁ፣ ፔሮልህን የተመለከቱ ይመስል የመሰላቸውን ሂሳብ ሰርተው ዱቅ አድርጋት የሚሉህ ናቸው"

"እኔ እስከማውቀው ህዝብ ለልማት የሚያዋጣው በፍላጎት እና እንደአቅሙ ነው" አላቸው እንግልታቸው.....ሽሽታቸው..... መሳቀቃቸው.....ጭንቀታቸው አሳዝኖት፣፣

"እሱማ ቀደም ብዬ እንዳልኩህ ኢቴቪ ላይ ነው"

"በገሃድስ?"

"በገሃድማ ተግባር ሌላ፣ ወሬ ሌላ"

"እሺ ምን እንድረዳዎ ነው የደወሉልኝ?"

"በመጽሄትህ ብሶቱን ህዝብ ዘንድ እንድታደርስልኝ፡፡ የሚሰማ የመንግስት አካል ባይኖርም ህዝብ ይሰማው"

"እሱማ የሙያ ግዴታዬ ነው"

"አላህ ይስጥልኝ፡፡ ይህን ብቻ አድርግልኝ፣ ከእኔም ባይሆን ከሰማይ ቤት ታገኘዋለህ"

"ችግር የለም ጋሽ ሙደሲር"

"አላህ ያክብርህ!"

"አሚን!"

"በገዛ ሃገርህ.....በገዛ ሰፈርህ.....አፈር ፈጭተህና ውሃ ተራጭተህ ባደግህበት መንደርህ ተንከራታች ከመሆን ያድንህ!"

"አሚን ጋሽ ሙደሲር...አሚን!"

"ከቀን ጅብ ከሽም ጉልበተኛ ይጠብቅህ!"

"አሚን!"

"ስልጣኑን መከታ አድርጎ ዘራፍ ከሚል፣ መጠየቅ ያለበትን በአግባቡ ከመጠየቅ ይልቅ በትእቢት ከሚያመናጭቅ ባለስልጣን አላህ ይሰውርህ!"

"አሚን! እርሶንም ከሽሽት እና ከጭንቀት ያድንዎ"

ተመራርቀው ተሰነባበቱ፡፡ ማን ያውቃል ይህን ታሪክ አንድ ቀን እንደ ግብአት ሊጠቀምበት ይችል ይሆናል፡፡

- 8 -

አሊኖይስ፣ አሜሪካ

ከካናዳ፣ አንታሪዮ ተነስተው በልዩ የግል አውሮፕላን አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ የደረሱት አይሁዳውያን ጥንዶች ባረፉበት ራዲሰን ብሉ ሆቴል ውስጥ ሆነው ይደርሳችኋል የተባሉትን ትእዛዝ በጠባበቁም የደረሳቸው ትእዛዝ አልነበረም። የላካቸው የሲቢኤስ ሚዲያ ሃላፊ ሃሪማን ፓሊይ "ትእዛዝ እስኪደርሳችሁ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ከማንኛውም አይነት ሰው ጋር መገናኘት በጥብቅ የተከለከለ ነው" ሲል አስጠንቅቋቸዋል። እቅዱ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ለአየር ተበትኖ እንዲከሽፍበት አይፈልግም። እቅዱ ተግባራዊ ከሆነ የበላይ አለቆቹ በእሱ ላይ ያላቸው እምነት ከፍ ማለቱ አይቀርምና ወደተሻለ የስልጣን ደረጃ ያሸጋግሩታል። ከደረሰበት የስልጣን ደረጃ ላይ ለመድረስ ሳይጠሩት አቤት፣ ሳይል ኩት ወዴት ማለት ነበረበት። የትጉህ ተላላኪነቱ፣ የቅን አሽከርነቱ ውጤት የታዋቂው ሲቢኤስ ቴሌቭዥን ጣቢያ የሚዲያ ሃላፊ ይሆን ዘንድ አስችሎታል። አሁንም በስልጣን መሰላሉ ተንጠላጥሎ ከፍ ለማለት የአለቆቹን ትእዛዝ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል። በችሎታ በልጠውት የበታቾቹ እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ሰራተኞች እንዳሉ ጠንቅቆ ያውቃል። ሃጊ ሚናሂም እና ሚስ ጁዲ ሚናሂም ለአብነት ይጠቀሳሉ። ጥንዶቹ ከሚዲያ ሃላፊው ሃሪማን ፓሊይ የተሻለ ብቃት እንዳላቸው ቢታመንም የእሱን ያህል እምነት የተጣለባቸው ባለመሆናቸው የበታቾቹ ሆነው እንዲሰሩ ተወስኖባቸዋል። በሃላፊዎቹ ዘንድ ከብቃት በላይ ታማኝነት ሚዛን ይደፋል።

ሃጊ እና ጁዲ በቨ.ያኑም ባለቤትነት ስር በሚተዳደረው ሲቢኤስ ጣቢያ ከሰባት አመታት በላይ አገልግለዋል። የፍቅርና የጋብቻ መሰረታቸውም ሲ.በ..ኤስ ነው። አሁንም ድረስ በትዳርም በስራም አብረው ናቸው።

ሃሪማን ፓሊይ ጥንዶቹ እትዱን ከዳር እንደሚያደርሱለት ጥርጥር የለውም፡፡ ለእትዳቸው ስኬታማነት ዮናታን ወልዴን እንደሚያገናኛቸውና አብረው እንደሚሰሩ ነግሯቸዋል፡፡ አይን የተጣለባት ኢትዮጵያዊቷ ጋዜጠኛም ከጥንዶቹ ይልቅ በሀገሯ መንግስትም ሆነ ህዝብ ዘንድ የተሻለ ተቀባይነት እንደምታገኝ አምኗል፡፡ የኒውዮርክ ፌዴራል ሪዘርቭ ባንክ ፕሬዚዳንቱን አንቶኒ ሶሎሞንን አሳምኖ አምስት ሚሊዮን ዶላር ቢያስመድብም አልተባበራችሁም እያለቻቸው ነው፡፡

በሶስና ግትር ባህሪ በእጅጉ የተናደደው ሃሪማን ፓሊይ በመጀመሪያ የWSIL-TV ስራ አስኪያጅ ወደሆነው አሌክሳንደር ሱልዝበርገር ቀጥሎ ደግሞ ወደ ዮናታን ወልዴ ስልክ ደወለ፡፡ "አጠገብህ ያሉች አንዲት ተራ ጋዜጠኛ ማሳመን አቅቶህ ትንገታገታለህ" ሲል አሌክሳንደርን ከወረፈው በኋላ "ሁለት ቀናት ብቻ ሰጥቼሃለሁ!" ሲል አስጠነቀቀው፡፡

"በሁለት ቀናት ውስጥ ተጨባጭ የሆነ አዎንታዊ ውጤት እፈልጋለሁ፡፡ እንኳን እንዲህች አይነቷ ተራ ጋዜጠኛ የአመታት ልምድ ያካበቱ አንጋፋ ጋዜጠኞችም አብረውን እየሰሩ ነው"

"አብረውን" ሲል እራሱን ወደላይ ማንጠራራቱና ከሃያላኑ ሰዎች የፊት ወንበር ላይ ማስቀመጡ እንደሆነ የገባው አሌክሳንደር ‹ይህ ሰውዬ እስከመቼ ነው እራሱን የሃያላኑ ሰዎች ፈታውራሪ አድርጎ የሚያስበው?› ሲል በውስጡ አጉተመተመ፡፡ የሶስና "ተራ ጋዜጠኛ" መባልም አላስደሰተውም፡፡ ተራ ጋዜጠኛ ብትሆን ኖሮማ ለእንዲህ አይነቱ ወሳኝ ተልእኮ ባልተመለመለች፡፡ ጉረኛው የሚዲያ ሃላፊ ሁልጊዜም እራሱን ከፍ አድርጎ መመልከትና ሌሎችን ማንኳሰስ እንደሚቀናው ስለሚያውቅ በውስጡ ታገበ አለፈው፡፡ በሁለት ቀናት ውስጥ ሶስናን ለማሳመን እንደማይችል በመገንዘቡ ግን ሃሳብ ላይ መውደቱ አልቀረም፡፡

"በእኔ ይሁንብህ ፓሊይ፣ በቅርቡ እናሳምናታለን፡፡ ቢበዛ አንድ ሳምንት ብቻ ታገሰን፡፡ ለአሌክሳንደር በግዴ ተባብራ የምትሰራበትን መንገድ እጠቁመዋለሁ"

የናታን ይህን የሚናገረው በናጹም እርግጠኝነት ነበር።

"እንዲህ በራስ የመተማመን ስሜት እንድትናገር ያደረገህ ምንድነው?" አለው ከንዴቱና ከቁጣው በረድ እያለ። "ሰዎች እጅግ የሚወዱትና ሊያጡት የማይፈልጉት ነገር ባሪያዎች ናቸው። ያንን መያዣ እድርገህ ብታስፈራራቸው ሳትጠራቸው አዘት ሳትልካቸው ወዴት ብለው ይሽቀጠቀጡልሃል። የሶስናን ነገር ለእኔ ተወው"

ሃሪማን ፓሊይ በየናታን ወልዴ እርግጠኝነት የተሞላበት ንግግር በከፊል ስለተማመነ "አንድ ሳምንት ብቻ እታገስሃለሁ ብሎት ስልኩን ዘጋው። የናታን ጊዜ አላጠፋም። ወዲ አሌክሳንደር ሱልዝበርገር ደወለና ፓሊይ ያለውን ሁሉ ነገረው።

"እኔም ጋር ደውሎ ‹አንዲት ተራ ጋዜጠኛ ማሳመን አቅቶህ ትንገታገታለህ። ሁለት ቀናት ብቻ ሰጥቼሃለሁ› ሲል ነው ሊያስፈራራኝ የሞከረው"

"ሶስናማ ተራ ጋዜጠኛ አይደለችም። ይህን ደግሞ እራሱም ጠንቅቆ ያውቃል። ተራ ጋዜጠኛ ነች ብሎ ካሰበ ለምን ትኩረቱን አሳረፈባት? የሆኖ ሆኖ አንገታችን ላይ እያጠለቀ ያለውን ሽምቀቆ ስቦ ከማጥበቁ በፊት እኔና አንተ በአካል ተገናኝተና እሷን የምናሳምንበትን መንገድ መነጋገር አለብን"

አሌክሳንደር ወዲያው ነበር ጥቃደኛ የሆነው። ጨንቆት ነበር። ‹ሁለት ቀናት ብቻ ሰጥቼሃለሁ!› ብሎ ካስጠነቀቀው በኋላ በድብርት መንፈስ እየታመሰ ነው። ከሃያላኑ አባላት ጋር መላተሙን አልፈለገም። በምን አቅሙ? በአቲገም ህመም የሚሰቃዩ ሁለት ልጆቹን በሰላም ማሳደግ የሚችለው የሃያላኑ ሰዎች ጥሜ እስካላረፈበት ድረስ ብቻ ነው።

"ግን እኮ ሁለት ቀናት ብቻ ነው ሰጥቼሃለሁ ያለኝ" አለ በጭላንጭል ተስፋ ውስጥ ሆኖ።

"እንደምንም አሳምኜው አንድ ሳምንት ሰጥቶናል። ዛሬ ልንገናኝና ልንነጋገር እንችላለን?"

አሌክሳንደር ደስ ብሎት የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈሰ። "በእርግጠኝነት ዛሬ ተገናኝተን መነጋገር እንችላለን"

ከሶስት ሰአታት በኋላ ቱሉቭሻርን ጣቢያው አጠገብ ካለው ካፍቴሪያ ውስጥ ለመገናኘት ተቀጣጠሩ። ዮናታን በሰአቱ ከተጠሮው ስፍራ ሲገኝ አሌክሳንደር አምስት ደቂቃዎች ያህል ቀድሞት ነበር። በመለስተኛው ካፍቴሪያ ውስጥ ብዙ ሰው አይታይም። ዮናታን ወንበር ስቦ አጠገቡ ተቀመጠ። ቡና ካዘዘ በኋላ የአሌክሳንደርን ፊት በተመለከተ እየተመለከተ "እንቅልፍ አጥተህ ያደርክ ትመስላለህ?" አለው። የአሌክሳንደር ፊት ያሳጣ ነበር። አይኖቹ ቀልተዋል። ቆዳው ገርጥቷል። ስሜቱ ተረብሿል።

"ሶስናን በፍጹም ላሳምናት አልቻልኩም። ወደፊትም እንዴት ላሳምናት እንደምችል አላውቅም። የበላይ አለቆቼን ጠንቅቄ አውቃቸዋለሁ። ያስተላለፉልህን ትእዛዝ ያላስፈጸምክ መስሎ ከታያቸው ድምጥማጥህን ነው የሚያጠፉት። ከእነሱ ጋር ያልተባበረና ትእዛዛቸውን ያላስፈጸመ ምንም የማይረባ፣ መወገድ ያለበት የምድር ካንሰር ነው። ካንሰር መሆን ደግሞ አልፈልግም። ያለ እኔ ማንም የሌላቸውን በሽተኛ ልጆቼን በሰላም ማሳደግ እፈልጋለሁ"

ዮናታን የአሌክሳንደር ጭንቀት ገብቶታል። የአሌክሳንደር ስጋት እና ጭንቀት ምንጭ ልጆቹ ናቸው። የዮናታን ደግሞ ስልጣኑ እና ገንዘቡ።

"ለዚህ እኮ ነው ተገናኝተን እንድንነጋገር የፈለግሁት። ያንተ ጭንቀት የእኔም ጭንቀት ነው። ይሰራበታል ብለው የሰጡኝን አምስት ሚሊዮን ዶላር ተነጥቄ ከታሔሀብት የሃላፊነት ስልጣን በቅሌት መባረርን አልፈልግም"

"ወደ መፍትሄው እንሂድ" አለ አሌክሳንደር። ዮናታን የሚነግረውን ነገር እስከሚሰማ ቸኩሏል።

"ሶስና እጅግ የምታፈቅረውን፣ የምትሳሳለትንና ልታጣው የማትፈልገውን ነገር ነግራህ ታውቃለች?" ዮናታን አሌክሳንደር ያልገመተውን ጥያቄ ሰነዘረ።

"እ-እኔንጃ? አላስታውስም። ይህን ማወቁ ምን ይጠቅመናል?"

"ይጠቅመናል" አለ ዮናታን፡፡ "ሰምች እምበ. ያለ·ት·ን ነገር እንዲተበለ· ማድረግ የሚቻለው በሚወዱ·ት ነገር ነው፡፡"

አሌክሳንደር የዮናታን አመጣጥ እየገባው የመጣ መሰለ፡፡ ሶስና እጅግ የምትወደውን እና ልታጣው የማትፈልገውን ነገር ለማስታወሰ ሞከረ፡፡ አንድ ቀን በጨዋታ መሃል ስራዋን እና ልጇን አጥብቃ እንደምትወድና ሁለቱንም ማጣት እንደማትፈልግ ነግረዋለች፡፡

"ልጇንና ስራዋን ማጣት እንደማትፈልግ ነግራኛለች"

በዮናታን አይኖች ውስጥ የተስፋ ጭላንጭል ታየ፡፡ ወደ አሌክሳንደር ጆሮ ተጠጋና ሌላ ሰው እንዲሰማው ያልፈለገ ይመስል ድምጹን ዝቅ አድርጎ፣

"መፍትሄን አገኘሁት፡፡ አሁን አማራጭ የላትም፡፡ አብራን ለመስራት ትስማማለች፡፡ ልጇን እናግተዋለን" ሲል አንሾካሾከለት፡፡

"ምን?" አለ አሌክሳንደር ደንግጦ፡፡ ሶስና ለልጇ፣ ለአንድ ልጇ ያላትን ጥልቅ ፍቅር ያውቃል፡፡ ከልጇ አባት ጋር እንዴት እንደተለያዩና እንዴት ብቻዋን እንደምታሳድገውም አጫውተዋ ለች፡፡ አሌክሳንደር፣ የሶስናን ልጅ ከእናቱ ጋር ቢሮ በተመላለሰበት ወቅት አይቶታል፡፡ የሚያምርና ያለእድሜው የበሰለ ልጅ ነው፡፡ ከእሱም ጋር የነበራቸው ቀረቤታ የአባትና የልጅ ያህል ነው፡፡

"አዎ እናግተዋለን፡፡ ከእዚህ የተሻለ አማራጭ አይኖረንም"

ዮናታን አሁንም በሃሳቡ እንደጸና ነው፡፡ አሌክሳንደር አልተዋጠለትም፡፡ ልጆቹን አስታወሳቸው፡፡ ‹ይህ ድርጊት እኔ ላይ ተፈጽሞብኝ ቢሆንስ ኖሮ?› ሲል አሰበ፡፡ መወላወሉን የተገነዘበው ዮናታን

"በዚህ ሃሳብ አልስማማም የምትል ከሆነ መ·ለውን ሃላፊነት ትወስዳለህ፡፡ ይህንንም ለሃሪማን ፓሊይ እና ለሌሎቹ የበላይ አለቆች አሳውቃለሁ" ሲል አስፈራራው፡፡ አሌክሳንደር ይህ እንዲሆን አይፈልግም፡፡ ሃላፊነቱን አይወስድም፡፡ ደጋግሞ

በእንደበቱ እንደሚናገረው ከሃያላኑ ሰዎች ጋር ያለአትሙ አይላተምም፡፡ ብዙዎች እራሳቸውን መስዋእት ከሚያደርጉ ይልቅ ሌሎችን ወደመሰዊያው ሜዳ መውሰድ ይቀላቸዋል፡፡ ለእሱም የሚቀለው ይህኛው መንገድ ነው፡፡ ቢዘገንነውም እሱና ልጆቹን መስዋእት ከሚያደርግ ይልቅ....

በዮናታን ሃሳብ ተስማማ፡፡

"የሶስና ልጅ ስሙ ማነው?" አለ ዮናታን ከደረት ኪሴ ባወጣው የማስታወሻ ደብተር ላይ እየጻፈ፡፡ "ሰለሞን" አሌክሳንደር መለሰ፡፡ "እይተኸው ታውቃለህ?"

"ብዙ ጊዜ ከእናቱ ጋር ቢሮ ይመጣ ስለነበር በደንብ እንተዋወቃለን፡፡ እንዲያውም በመሃላችን ያለው ግንኙነት የአባትና ልጅ ያህል ነው"

"ስለዚህ ፎቶግራፉን መፈለግ አያስፈልገንማ?" አሌክሳንደር በአዎንታ እራሱን ነቀነቀ፡፡

"የሚማረው የት ነው?"

"ራድክሊፍ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት"

"እርግጠኛ ነኝ ትምህርት ቤት የምታደርሰውና የምትመልሰው እናቱ ነች?" ዮናታን ሰለሞንን ለማገት ያስችላሉ ናቸው ያላቸውን ጥያቄዎች መጠየቁን ቀጥሏል፡፡

"እሷ ስራ ሲበዛባት የተቀጠረላት ሹፌር እንደሚያመላልሰው አውቃለሁ"

"በጣም ጥሩ" አለ ዮናታን ይጽፍበት የነበረውን የማስታወሻ ደብተር ወደኪሱ እየመለሰ፡፡ "ጊዜ መስጠት አያስፈልገንም፡፡ ነገውኑ ተግባራዊ እርምጃ እንወስዳለን"

ዮናታንም ሆነ አሌክሳንደር ትምህርት ቤቱን ስለሚያውቱት ያለጠያቂ ለመሄድ አይቸገሩም፡፡ የመውጫ ሰአቱንም ያውቁታልና በዚህ በኩልም ችግር የለባቸውም፡፡

"ሾፈሩንስ ታውቀዋለህ?" አለው ዮናታን የሆነ ሃሳብ መጥቶለት።

"ስለሞንን ቢሮ ይዞ በመጣባቸው ጊዜያት አይቼዋለሁ"

"እሱስ ያውቀኛል ብለህ ታስባለህ?"

"ይመስለኛል"

"ጥሩ። በመጀመሪያ ደረጃ በነገው እለት ከሰአት በኋላ ለሶስና ከቢሮ የሚያስወጣ ስራ ትሰጣታለህ። እኔና አንተ ወደትምህርት ቤቱ እንሄድና ለሾፈሩ እናቱ ስራ ስለበዛባት እግረ-መንገዳችንን ይዘነው ልንሄድ እንደመጣን ነግረን እናሰናብተዋለን። እርግጠኛ ነኝ ሰለሞን ይዤህ ልሄድ ነው የመጣሁት ብትለው እምቢ አይልህም"

አሌክሳንደር በአምንታ እራሱን ነቀነቀ።

****

የራድክሊፍ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወደቤታቸው ሊሄዱ የቀራቸው አስራ አምስት ደቂቃ ብቻ እንደሆነ በማወቃቸው ልባቸው ከወዲሁ ማኮብኮብ ጀምሯል። በተለይ የነሰለሞን ክፍል ተማሪዎች እንደዛሬው የመጨረሻው የትምህርት ከፍለ-ጊዜ የታሪክ ትምህርት ሲሆን ደቂቃው አልገፋ ስለሚላቸው የመጨረሻውን ደቂቃ የሚጠብቁት በናፍቆት ነው። በቅርብ እርቀት መኪናቸውን ያቆሙት ዮናታን እና አሌክሳንደር ነጭ ቀለም ከተቀባው ቼቭሮሌት መኪናቸው ውስጥ ሆነው ሰለሞንን የሚጠብቀውን ጃማይካዊ ሾፌር በዓይነ ቁራኛ እየጠበቁት ነው። ፈትለክ ብሎ እንዳያመልጣቸው አይናቸውን ከመኪናው ላይ አልነቀሉም። ብርማ ቀለም ቢ. ኤም ደብሊው። አሌክሳንደር ከመኪናው ወርዶ ወደ ሾፈሩ ተራመደና መስኮት አንኳኳ። ሾፈሩ ያነበው ከነበረው ጋዜጣ ላይ ቀና ብሎ ያንኳኳውን ሰው ተመለከተው። የሶስና አለቃ መሆኑን ሲያውቅ ወርዶ እጁን በትህትና ዘረጋለት። በሶስና አይን ነው የሚያየው። ያከብረዋል።

"ዛሬ ምን እግር ጣለህ?"

"ሶስና ስራ ስለበዛባት እግረ-መንገዴን ሰለሞንን ልወስደው ነው"

ከክፍል እንደወጣ ወደእናቱ መኪና ማቆሚያ ያመራው ሰለሞን መኪናዋን በማጣቱ የሾፌሩን ቢ.ኤም.ደብሊው መፈለግ ጀመረ። አሌክሳንደር እጁን ሲያውለበልብለት ተመለከተው። ተንደርድሮ አቀፈው።

"እናትህ ስራ ስለበዛባት ልወስድህ ነው የመጣሁት"

ግርታ ቢፈጥርበትም ከቀረቤታቸው አንጻር አልተጠራጠረ ውም። ወደነጫ ቼቭሮሌት አመሩ። የማያውቀውን እንግዳ የተመለከተው ሰለሞን ግራ በተጋባ ስሜት አሌክሳንደርን ተመለከተው።

"ጓደኛዬና የስራ ባልደረባዬ ነው። ዮናታን ይባላል። የእናትህም የቅርብ ጓደኛ ነው።"

ሰለሞን እጁን ለሰላምታ ዘረጋ።

ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ጉዞ ወደ ዮናታን ወልዴ የግል መኖሪያ ሆነ። ምስኪኑ ታዳጊ መጠለፉን ያወቀው እጅግ ዘግይቶ ነበር።

****

ዮናታን ለጥንቃቄ በሚል ሁለንም በሮች ቆለፈና ወደ ስልኩ አመራ። ለሶስና ደወለላት። "ሃሎ፣ ማን ልበል?" አለችው የታፈነ በሚመስል ድምፅ።

"ሶስና፤ ዮናታን ነኝ። ባለፈው ጊዜ ፕሪንስተን፣ ኒውጀርሲ ውስጥ ያገኘሽኝ የሀገርሽ ልጅ...." ንግግሩን እንዲቀጥል አልፈቀደችለትም። እያለቀሰች ለመነችው። ልጁን ከአሌክሳንደር ጋር የወሰደባት እሱ እንደሆነ ጠርጥራለች። የልጇ ሰዓት ማሳለፍ ስጋት ቢጭርባት ወደ ሾፈሩ ዳሚያን ደውላ የነገራት በድንጋጤ የጨው አምድ አድርጓታል። አሁንም ከድንጋጤዋ አልተላቀቀ

ችም፡፡ "አሌክሳንደር ከአንድ እንግዳ ሰው ጋር በነጭ ቮልቮሌት መኪና ይዞት ሄዱል" ነበር ያላት ዳሚያን፡፡ ነፍሷን ቮልቮሌት መኪና አስታወሰቻት፡፡ ፕሪንስተን፣ ኒውጀርሲ የተገናኙም ዕለት ይሏት ነበር፡፡ እንደዛተው አግኝኝ ስትል ከተጠበከነከነች በኋላ፣

"ዮናታን ስለፈጠረህ ልጄን፣ አንድ ልጄን፣ ያለአባት ያሳደግሁትን ልጄን ምንም እንዳታደርግብኝ!" ስትል ተለማመጠችው፡፡

"እመኚኝ ሶስና፡፡ ከልጅሽ ጋር ምንም ጉዳይ የለንም፡፡ በፍጹም አንጎዳውም፡፡ ጥያቄያችንን እስከተቀበልሽና አብረሽን ለመሰራት እስከተስማማሽ ደረስ ለምን ብለን እንጎደዋለን?"

"አሁንስ ምንም እንዳላደረጋችሁት በምን አውቃለሁ?"

"ይኸው.....አናግሪው" አላትና የያዘውን ስልክ ለሰለሞን አቀበለው፡፡

"ማም! ማምዬ! ባክሽ ቶሎ ላግኝሽ እፈልጋለሁ! አሁኑኑ! ካንቺ መለየት አልፈልግም! ጥያቄያቸውን ተቀበይ፡፡ መሞት አልፈልግም፡፡ ወደ ቤት መመለስ ነው የምፈልገው፡፡" እያለቀሰ ነበር ያናገራት፡፡

"ሃኒ፣ አይዞህ የኔ ውድ፤ አትሞትም፡፡ በጥያቄያቸው አሁኑኑ እስማማለሁ፣ ውዴ፡፡ ከዚያ ይለቁሃል፡፡ በፍጥነት እንገናኛለን፡፡" በተቻላት መጠን ልታግባባው ሞከረች፡፡ ዮናታን ስልኩን ከሰለሞን ተቀበለውና አናገራት፡፡

"ጥሩ፣ በጥያቄያችን ከተስማማሽ አሁኑኑ እንለቀዋለን፡፡ ታዲያ ልጅሽን ከለቀቅንልሽ በኋላ ሃሳቤን እቀይራለሁ ብትይ የልጅሽን ሬሳ ትምህርት ቤቱ በር ጋ ተዘርቶ ታገኚዋለሽ፡፡"

ልጇ አሁን የተገደለባት ይመስል እሪ!!!! ብላ ጮኸች፡፡ "ስለፈጠረህ ዮናታን.....አንድ ልጄን አትጉዳብኝ!!" ድምጽዋ በሳግ ጎርንኖ፣ በጩኸት ሻከሮ፣ በእልህና ቁጣ ተሞልቶ ያስገመግም ነበር.....

ክፍል ሁለት

- 9 -

ቶሮንቶ፣ ካናዳ

ከአስር ቀን በኋላ

በል መያዝ መፈናፈኛ ያጣችውና ጥያቄያቸውን የተቀበለችው ሶስና በኒውዮርክ ፌዴራል ሪዘርቭ ባንክ ፕሬዜዳንት አንቶኒ ኤም. ሶሎሞን ልዩ ትእዛዝ በተመደበ ወጪ በምስጢር ማህበራቱ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ካናዳ፣ ቶሮንቶ ገብታለች፡፡ ሁሉም ነገር እንግዳ ሆኖባታል፡፡ በከተማው ውበት ስለተማረከች አብሯት ከተመደበው ወጣት ጋዜጠኛ አሌክሲስ ሮቢንስ ማብራሪያዎችን እያገኘች ነው፡፡ ከምስጢር ማህበራቱ መሃል አንዱ በሆነው ቢልደርበርግ የአባላት ስብሰባ ላይ ደጋግሞ የተገኘው አሌክሲስ ስለቶሮንቶ በቂ ግንዛቤ ስለነበረው ማብራሪያ ለመስጠት አልተቸገረም፡፡ ቶሎ ከሰው የመግባባት ችሎታ ያላት ቆንጆዋ ኢትዮጵያዊት ጋዜጠኛ የምትከብድ ሰው ባለመሆኗ ደስ ብሎታል፡፡ ከዚህ ቀደም በቶሮንቶ ጉዞው ላይ ያጋጠሙት ጋዜጠኞች እራሳቸውን ከፍ አድርገው የሚመለከቱ እብራተኞች እንደነበሩ ያስታውሳል፡፡ ይህች ግን ለሰው ክብር ያላት፣ በበላይነት ስሜት የማትኮፈስ፣ ጥሩ አድማጭ ወጣት ጋዜጠኛ ስለሆነች እውቀቱን ሳይሰስት በደስታ ነበር የሚያካፍላት፡፡

ከኒውዮርኩ ዎል ስትሪት ጋር ብዙ ነገሮቿ በተለይ ደግሞ በንግድ እንቅስቃሴዋና ማዕከልነቷ እንደምትነጻጸር በተመሰከረላት

Bay Street (ቤይ ጎዳና) በኩል ሲያልፉ አሌክሲስ ማብራሪያውን በሰፈው ተጥሎበት ነበር፡፡ በቁጥር 161 የቤይ ጎዳና ላይ አስከ ግርማ ሞገሱ በኩራት የቆመውን ካናዳ ትረስት ታወር በጣቱ እየጠቆማት እንዲህ አላት "ሃምሳ ሶስት ፎቆች ያሉት ይህ ህንጻ ከተማዋ ከምትኮራባቸው ቅርሶቿ መሃል አንዱ ነው፡፡ አንድ ሺህ ስምንት ሙዩ ሃያ ፎማ ከፍታ ካለው CN Tower ተጥሎ በሁለተኝነት ደረጃ ላይ ያለው ካናዳ ትረስት ታወር የዩሮንዩ አሻራ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ግንባታው በ1990 ዓ.ም የተጀመረውን እና ለማጠናቀቅ አመታት የፈጀውን ይህን ማማ የሰራው ዝነኛው ስፔናዊ አርክቴክት ሳንቲያጎ ካላትራቫ ሲሆን ችሎታውን ሳይሰስት በተጠበበት በዚህ ህንጻ ከፍተኛ አድናቆትን አግኝቶበታል፡፡"

እግረ-መንገዱን የካናዳ ትረስት ታወር መንታ እህት ህንጻ የሆነውን ቤይ ዌሊንግተን ህንጻን አስጎበኛት፡፡ ባለአምስት ፎቁን ጋሌሪያንም ተመለከቱ፡፡

በጉብኝቷ እጅግ የተደሰተችው ሶስና "የዩሮንዮን ከተማ ህዝብ ቁጥር ማወቅ ይቻላል?" ስትል አሌክሲስን ጠየቀችው፡፡

"ከአምስት ሚሊዮን በላይ ይሆናል" ሲል ፊጣን ምላሽ ሰጣት፡፡ "የዩሮንዩ ከተማ ከንቲባ ሳትሆን አትቀርም" ስትል ሳቀችበት፡፡

ሰዎች ስለሚያውቀው ነገር እውቅና ሲሰጡት በእጅጉ የሚደሰተው አሌክሲስ "ዩሮንዩን በደንብ አውቃታለሁ" ሲል በኩራት መለሰላት፡፡ ሰዎች እየተሻሙ ወደሚገዙት ጋዜጣ መሸጫ ወሰዳት፡፡ ሁለት ጋዜጦችን ተሻምቶ ከገዛ በኋላ አንደኛውን ጋዜጣ እያቀበላት "አርኪ ቡና መጠጣት አላሰኘሽም?" ሲል ጠየቃት፡፡ በእሺታ አንገቷን ነቀነቀችለት፡፡ ወደአንድ ታዋቂ ቡና መሸጫ ካፌ አመሩ፡፡ ጥግ ስፍራ ላይ ወንበር ፊልገው እንደተቀመጡ አሌክሲስ የያዘውን ጋዜጣ ስም እያሳያት በካናዳ በሰፊው የሚነበብ ተጽእኖ ፈጣሪ ጋዜጣ መሆኑን ነገራት - ዩሮንዩ ስታር፡፡

ያዘዘችውን ቡና ፉት እያለች የጋዜጣውን የመጀመሪያ ገጽ ርእሶች መቃኘት ጀመረች፡፡ በአንደኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠውን አብይ ርእስ ስትመለከት ከመቀመጫዋ እንደመነሳት ታጣች፡፡

ቶሮንቶ ስታር በአብይ ርእሱ በነገው እለት በCIBC ሪሠርች ስለሚደረገው የቢልደርበርግ አባላት ስብሰባ በሰፊው ጽፏል። ይህ ሪሠርች እጅግ ውድ የሆነ የፊረሶች የእርባታ ቦታ እንዳለውና የእንግሊዝ ንጉሳውያን ቤተሰቦች ለጉብኝት የሚያዘወትሩት ትንሹ ሰፍራ እንደሆነ የጠቆመው ቶሮንቶ ስታር ለአራት ቀናት ያህል በስብሰባው ላይ የሚሳተፉትን ሃያላን ሰዎች ማንነትም ይፋ አድርጓል። ጋዜጣው ይፋ ካደረጋቸው አንድ መቶ ሃያላን ሰዎች መሃል የዩናይትድ ስቴትስ የመከላከያ ሃላፊ ዊልያም ፔሪ፣ የአውሮፓ ኮሚሽነር ማሪያ ሞንቶ፣ የቺስ ማንሃታን ባንክ ባለቤት ዴቪድ ሮክፌለር፣ የቀድሞ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሄንሪ ኪሲንጀር፣ ቀድም ሲል የካናዳ የፋይናንስ ሚንስትር የነበሩትና ኋላ ላይ የጠቅላይ ሚንስትርነቱን ወንበር የተረከቡት ፖወል ማርቲን በማንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ።

ጋዜጣው ይፋ ያደረገው ይህን ብቻ አልነበረም። የአባላቱ ዋነኛ አጀንዳ ድብቅ ቢሆንም ህዝብን ለማሳሳት እና የተዛባ መረጃ ለማስተላለፍ እንዲሁም የምንደብቀው ነገር የለም ለማለት የአባላቱ መግለጫ አሻንጉሊቶች የሆኑ ጋዜጠኞችም ቶሮንቶ መግባታቸውን ጽፏል። "የአባላቱ መግለጫ አሻንጉሊቶች" ተብለው ስማቸው ከሰፈረው ጋዜጠኞች መሃል የሰሰና ስም በዘጠነኛ ተራ ቁጥር ላይ ሰፍሯል። ስሟን ከተመለከተች በኋላ ከመቀመጫዋ እንደመነሳት ታጣች። ግራ በተጋባ ስሜትም አለክሲስን ተመለከተቸው። "አይዞሽ አትደንግጪ። ይህ ተለመደ ከስተት ነው። የመጀመሪያሽ ጊዜ ስለሆነ ይሆናል የተረበሸው። እኛ ለምደነዋል። ከቶሮንቶ ስታር ጋዜጠኞች የሚደበቅ ነገር የለም። ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት ስብሰባው የት እንደሚካሄድ እና በስብሰባው ላይ የሚሳተፉት ሃያላን ሰዎች ስም ዝርዝር እንዲሁም የጋዜጠኞቹን ማንነት የያዘ ዝርዝር መረጃ ይደርሳቸዋል። አስተማማኝ ምንጮች ያሏቸውና የሃያላኑን ሰዎች ተግባር አጥብቀው የሚያውጠ ጋዜጠኞች የጋዜጣው ዋነኛ ምንጮች ናቸው"

ሰሰና በቶሮንቶ ስታር ጋዜጣ "የአባላቱ መግለጫ አሻንጉሊት" ተብላ ስሟ መጠቀሱ እጅግ አበሳጭቷታል። አማራጭ የላትም።

ለሰለሞን ስትል እንኳን መሰደብ፣ እንኳን መዋረድ፣ እንኳን "መግለጊያ አሻንጉሊት" መባል የህይወት መስዋእትነትም ትከፍልለታለች፣ የምትኖረውስ ለማን ሆነና?

መበሳጨቷን ልብ ያለው አሌክሲስ "በዚህ አይነትማ እድሜ አይኖርሽም፣ በንዴት ትሞቻለሽ፣ ለልጅሽ ብትኖሪለት አይሻልም? እስቲ እይኝ እኔ ምን ሆንኩ? ሰንት አመት ‹መግለጊያ አሻንጉሊት› እየተባልኩ እንደኖርኩ ብታውቂ ኖሮ እንዲህ አትሆኚም ነበር"

በተራ ቁጥር 6 ላይ ስሙ የሰፈረው አሌክሲስ ሮቢንስ ሶስናን ሊያጽናናት ሞክሮ በመጠኑ ተሳክቶለታል፡፡ እነሱ ስንቱን ችለው እየኖሩ እኔ ገና ከአሁኑ ምን መለወጥ እችላለሁ? ስትል ከእራሷ ጋር ለመታረቅ እየሞከረች ነው፡፡ ቃሉን ባስታወሰች ቁጥር ግን መባነኗ አልቀረም፡፡ ያን እለት ያላዩትን ስፍራ ሲጎበኙና አንዳንድ እቃዎችን ሲሸማምቱ አምሽተው ወደተያዘላቸው ሆቴል አመሩ፡፡ አሌክሲስ ደህና እደሪ ሲል ተሰናብቷት በጠዋቱ ስብሰባ ላይ ንቁ ሆኖ ለመገኘት በማሰብ አንሶላ መሃል እንደገባ ነበር እንቅልፍ የወሰደው፡፡ እስከምሽቱ አምስት ሰአት ድረስ ጣቢያዎችን እየቀያየረች የተለያዩ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን ስትከታተል የቆየችው ሶስና ግን መከራዋን ነው ያየችው፡፡ ሽለባ ሊያደርጋት ሲል "የአባላቱ መግለጊያ አሻንጉሊት" የሚለው አባባል በእዝነ ልቦናዋ እየጮኸባት እንቅልፍ በአይኗ ሳይዞር ነጋ፡፡

****

መኝታ የተያዘላቸው ሆቴል ቁርሳቸውን በልተው ወደስብሰባው ስፍራ አመሩ፡፡ "እኔና አንቺ በስብሰባው ላይ የምንሳተፈው ዛሬና የመገዢያው እለት ነው፡፡ በመሃል ባሉት ሁለት ቀናት አናስፈልግም፡፡ ስብሰባው በዝግ የሚካሄድባቸው ቀናት ናቸው፡፡ ለጋዜጠኞችም ዝግ የሆነ ስብሰባ፡፡ ረፍት በምንሆንባቸው ሁለት ቀናት ቶሮንቶ ውስጥ ማየት የምትፈልጊውን ስፍራ ሁሉ አሳይሻለሁ፡፡" ከወዲሁ ታል ገባላት፡፡ ወደስብሰባው እያመሩ በነበረበት ሰአት በተመለከተችው ነገር ተደንቃለች፡፡ ስብሰባው

በሚካሔድበት ሪዞርት ፊት ለፊት በተከለለ ስፍራ ተሰብስበው የሚሥሡ ሰዎችን እየተመለከተች ነው። አብዛኛዎቹ የፎቶግራፍ እና የቪዲዮ ካሜራ ይዘዋል። ከመሃላቸው ረዘም ያለው እና ጸጉሩን ወደኋላ አበጥሮ የቋጠረው መልከመልካም ጎልማሳ ተሰብሳቢዎቹ ወደስብሰባ አዳራሽ በማምራት ላይ ሳሉ ፎቶግራፍ ለማንሳት እየሞከረ ነው። ሰዎቹ በስፍራው የነበሩትን የደህንነት ሰዎች ከምንም እንዳልቆጠሯቸው ልብ ብላለች። ማይክራፎን የያዘው ሰው በወኔ ተሞልቶ ድምጹን ከፍ በማድረግ የሃያላኑን ሰዎች ስብሰባ እየኮነነ ነው። አንዳንዶቹን በስማቸው እየጠራ ሲኮንናቸው ታገላለች። አጭርና ደልደል ያለ ሰውነት ያለው ሰው ነው።

"ሔንሪ ኪሲንጀር ካናዳን ለማፈራረስ የወጠንከበትን ድብቅ አጀንዳ ይዘህ መጣህ? ዴቪድ ሮክፌለር ግንዘብህን ምናለ ለበጎ ነገር ብታውለው? ሴራችሁን ደርሰንበታል። እየሰራችሁ ያላችሁት አለምን ለማፈራረስና በአንድ አለም አስተዳደር ስር ለማድረግ ነው። በፍጹም አይሳካላችሁም" ንግግሩን ገታ ያደርግ እና ወደግል ፎቶ አንሺው በማምራት "ያ የፊያት ካምፓኒ ሊቀመንበር ጆቫኒ አኞኔሊ አይደለም እንዴ? አዎ እራሱ ነው። በጥራት አንሳልኝ። ያውልህ ደግሞ ዋናው ተዋናይ የኔዘርላንዱ ልዑል በርንሃርድ በቅርበት አንሳው። የቢልጂየም ልኡል ጆርጅ ሶሮስ እንደምን አለህ እባክህ?" ከት ብሎ ይስቅና "መ·ድ" ሊይዝ ይሞክራል። ብዙዎቹ ላይ የብስጭት መልክ ቢታይም አንዳንዶች እንደተዋጣለት ኮሜዲያን እያዩት ስቀው ያልፋሉ።

ሶስና በሰውየው ድርጊት ተደንቃለች። "አሌክስ ጆንስ ነው" አላት መደነቋን ያስተዋለው አሌክሲስ። ይህን ስም የት ነበር የምታውቀው? አስታወሰችው። በምስጢር ማህበር አባላት ዙሪያ የጻፈውን ጽሁፍ አንብባለታለች። እንደዚያ አይነት አስደናቂ መረጃ የያዘውን ጽሁፍ የጻፈውን ሰው በቅርበት በአካል ለማየት በመቻሏ ደስ ብሏታል።

አሌክሲስ ተጥሏል "ጸጉሩን ወደኋላ አስተኝቶ የቋጠረው ደግሞ ዳንኤል ኢስቱሊን ነው። በምስጢር ማህበራቱ በተለይም ደግሞ

በቢልደርበርግ አባላት ዙሪያ በጻፋቸው መጻሀፍ፡ ይታወቃል፡፡ ሩሲያ ካናዳዊ ነው፡፡ በቢልደርበርግ አባላት ዙሪያ ከአስራሰባት አመታት በላይ ጥናትና ምርምር አድርጓል፡፡ ዘ ትሩ ስቶሪ ኦፍ ዘ ቢልደርበርግ ግሩፕ የተሰኘው መጽሃፉ በኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትን አትርፎለታል፡፡ በተለያዩ የአለም ሀገራት እየተዘዋወረ የቢልደርበርግ አባላትን የተመለከተ ገለጻዎችን ያደርጋል፡፡ በአውሮፓ ኮሚሽን ስብሰባ ላይ ላይ በመገኘት ስለቢልደርበርግ አባላት ንግግር ያደረገ የመጀመሪያ ጋዜጠኛ ነው"

ሶስና ስራዎቻቸውን ተመልክታ በእጅጉ ያደነቀቻቸውን ጋዜጠኞች በአካል በማየቷ ደስታዋ እጥፍ ድርብ ሆኗል፡፡ ከሰበሰበቻቸውና አንብባ ካደነቀቻቸው ስለምስጢር ማህበራት የሚያወሩ መጻህፍት መካከል አንዱ የኢስቱሊን "ዘ ትሩ ስቶሪ ኦፍ ዘ ቢልደርበርግ ግሩፕ" ነው፡፡ እነዚህን ጋዜጠኞች በቅርበት አግኝታ ትተዋወቃቸው ዘንድ ተመኘች፡፡ በስብሰባው አዳራሽ መግቢያ በር ላይ ደርሰው ነበር፡፡

"አሌክሲስ እነዚህን ጋዜጠኞች በአካል አግኝቼ ብተዋወቃቸው ደስ ይለኝ ነበር?"

"አሁን ስብሰባው የሚካሄድበት አዳራሽ ውስጥ እየገባን ስለሆነ ከስብሰባው በኋላ እንነጋገራለን"

ቦታቸውን ያዙ፡፡ ሌሎች "የአባላቱ መገልገያ አሻንጉሊት" ጋዜጠኞችን የተመለከተችው ሶስና "ብቻዬን አይደለሁም" በሚል የመጽናናት ስሜት እራሷን ልትሸነግል ሞከረች፡፡ ከሃሳቧ የተመለሰችው የመግቢያ ንግግሩ እንደተጀመረ ነበር፡፡ አሌክሲስ ተናጋሪው ከአመራር ኮሚቴው ሊቀ-መናብርት መሃል አንዱ የሆነው ፒተር ካሪንግተን እንደሆነ ነግሯታል፡፡ ከመግቢያ ንግግሩ በኋላ ስብሰባው በይፋ ተጀመረ፡፡ የምሳ ሰአት ረፍቱን ጨምሮ ሙሉ ቀን የፈጀው የአባላቱ የስብሰባ አጀንዳ በላይበር ጥቃት፡ ከኒዩክለር አደጋ ነጻ በሆነች አለም፡ በአፍሪካ፡ በሩሲያ፡ በገንዘብ አቅም፡በአሜሪካና በአውሮፓ አንድነት መካከል ባለው ግንኙነት፡ በአፍጋኒስታንና በፓኪስታን እንዲሁም በእስልምናና በኢራን ላይ

ትኩረት ያደረገ ነበር። አባላቱ አንስተው የተነጋገሩበት አጀንዳ ከፋት አልታየትም። በየጊዜው በዜና ማሰራጫዎች ላይ የምትከታተላቸው ርእሶች ናቸው። "ለምንድነው ታዲያ እነዳንኤል ኢስቱሊን፣ እነአሊክስ ጆንስ የሚታወሟቸው?" ጥያቄውን ለአራዒ ብታቀርብም አጥጋቢ ምላሽ ማግኘት አልቻለችም።

ከስብሰባው መጠናቀቅ በኋላ በለመደው የስብሰባ አይነት በእድጉ ተሰላችቶ የነበረው አሊክሲስ "ወዳረፍንበት ሆቴል ባር ሂደን ወይን እንጠጣ" የሚል ሃሳብ በማቅረቡ ወደዚያው አመሩ። እግራ መንገዱን የተለየ ስፍራ የተያዘላቸውን እና ወሳኝ የሆኑ አስተያየቶችን ይሰነዝሩ የነበሩ ግለሰቦችን ማንነት እያስተዋወቃት ነበር። የግሪክ ጠቅላይ ሚንስትር ኮስታስ ካራማንሊስ፣ የፊንላንድ ጠቅላይ ሚንስትር ማቲ ቫንሃነን፣ የስዊድን የውጭ ጠቅላይ ሚንስትር ካርል ቢልድት፣ የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት ሮበርት ዞሊክ፣ የአውሮፓ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ጆዜ ማኑኤል ባሮሶ እና ሌሎችም። እነዚህን ከመሰሉ የዓለማችን ሃያላን ሰዎች ጋር በመሰብሰቧ ኩራት ቢጤ ቢሰማትም መገልገያ አሻንጉሊትነቷ በታወሳት ቁጥር መበሳጨቷ እና ሙሽማቀቁ አልቀረም።

በሆቴላቸው ባር ምቹ ሶፋ ላይ ተቀምጠው ወይናቸውን ሲጎነፁ ሶስና እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበችለት።

"በተነሳው አጀንዳ ላይ ምንም አይነት መጥፎ ይዘት ያለው ሃሳብ አላየሁም። የነኢስቱሊን የተቃውሞ መንስኤ ምንድነው?"

ገና ምንም የገባሽ ነገር የለም በሚል አስተያየት ከተመለከታት በኋላ "ይህ ለዓለም ህዝብ በሚዲያ በኩልየሚለቀቅ የማሳሳቻ አጀንዳ ነው። ዋነኛው አጀንዳ የሚነሳው ነገ እና ከነገወዲያ በሚደረጉትገዢ ስብሰባዎች ላይ ነው። የሁለቱን ቀናት አጀንዳዎች ከእነሱ በስተቀር ማንም አያውቅም። ይህ ሴራ ስለገባቸው ነው እነአሊክስ ጆንስ ነጋ ጠባ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙት። ለህዝብ በሚዲያ የሚነገረውና እነሱ በገሃ ችሎት የሚመክሩበት አጀንዳ ይዘት የሰማይ እና የምድር ያህል ልዩነት አለው።"

"የድብቁን አጀንዳ ምንነት መገመት አይቻልም?"

"ከዚህ ቀደም አፈትልከው የወጡ መረጃዎች እንዳረጋገጡት እና እንዳጋለጡት ምናልባት ህዝብን በጅምላ ለመፈረስ ስለሚያስችሉ መሳሪያዎች፣ ላብራቶር ውስጥ ስለሚፈጠሩ አደገኛ የቫይረስ አይነቶች፣ ስለ ሀረ ክርስቶስ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች፣ ወደመስመራቸው አልገቡ ያሏቸውን ሃገራት ስለሚያጠፉባቸው ዘዴዎች እና የመሳሰሉት አጀንዳዎች ይወያዩ ይሆናል"

የሶስና አይኖች ተጎልጉለው ወጡ፣፣

"እም ሰዎቹ የዚህን ያህል ጨካኞች እና አደገኞች ናቸው" ሲል አረጋገጠላት፣፣

"ስለእነሱ ይህን ያህል በቂ መረጃ ካለህ እንዴት አብረሃቸው ለመስራት ፈቃደኛ ሆንክ?"

ራሷኑ መልሶ ጠየቃት

"አንቺ እንዴት አብረሻቸው ለመስራት ፍቃደኛ ሆንሽ? በፍላጎት? አይመስለኝም፣፣ ደግሞም የገባሽበትን አጣብቂኝ አሌክሳንደር ነግሮኛል"

ጥቂት እንደማመንታት ካለች በኋላ" በልጄ ስለመጠብኝ ነው አብሬያቸው ለመስራት ፍቃደኛ የሆንኩት" የሚል ምላሽ ሰጠችው፣፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የፍልቅልቁና የሳቂታው አሌክሲስ ሮቢንስ ገጽታ ሲጨልም ተመለከተች፣፣ አይኖቿን በጉጠጠ አድርጎ እየተመለከታት "እሄም ሳልወድ በግዴ ነው ተባባሪያቸው የሆንኩት" አላትና እንዴት በአንዲት ፈረንሳይት ቆንጆ መጥመዳቸው ላይ እንደጣለት አጫወታት.....

ሶስና በጽሞና ካደመጠችው በኋላ አዘነችለት፣፣ "ይኸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከምወዳት ባለቤቴ ላለመለየት፣ ትዳሬን ላለመበተን እና ሶስት ልጆቼን ላለማጣት ስል ያዘዙኝን ያለማንገራገር እየፈጸምኩ አለሁ" አለና አሳረገ፣፣

"አንተም እኮ በምትወዳት ባለቤትህ ላይ ክህደት መፈጸም አልነበረብህም"

"የሰው ልጅ ክህደትን የሚፈጽመው በሁለት መንገድ ነው፣ አንድም በምላሱ ሃሰት ተናግሮ ሁለትም በብልቱ የእሱ ያልሆነውን የሰው ንብረት "ዞሮ" አለና አሳቃት። በል ካለው ተልደኛ ነው። ድርጊቱን ከፈጸመ በኋላ መጸጸቱን አልደበቃትም።

"የሴትን ፊተና ለማለፍ ከአዳም የተሻለ ወኔና ብርታት ያስፈልጋል። ያን ደግሞ ብዙዎቻችን ወንዶች አልታደልንም"ም ብሏታል።

"ሁልጊዜ ታዛጎቸው ለመሆን ወዶ ፍቃደኛ ሆነሃላ!?"

"ፈጽሞ እኔን የሚያሳጡበትን መረጃ ሁሉ ደብዛውን እስካጠፉ ድረስ ብቻ ነው። በሂደት ያን እንደማደርግም እርግጠኛ ነኝ። ከዚያ በኋላ አፍንጫቸውን ሲልሱ ይችላሉ። ተቃራኒውን የነአሌክስ ጀንስና ዳንኤል ኢስቱሊንን የጋዜጠኞች ቡድን ተቀላቅዬ የምስጢር ማህበራቱን ሴራና ድብቅ አጀንዳ ማጋለጥ መጀመሬ አይቀርም። ሁልጊዜ የአባላቱ መገልገያ አሻንጉሊት መባልንማ አልፈልግም"

እንደሚናገረው ተላል እንደማይሆንለት መገመት አላቃታትም።

"ሰራህን ትተህ በምን ትተዳደራለህ?" እግረ-መንገዷን ለእራሷም ጥርጊያ መንገድ ለማመቻቸት መረጃ እየጠየቀችው ነው።

"ከአንዳቸው ጋር እየሰራሁ በቂ ገቢ ማግኘት አያቅተኝም። ችሎታው እስካለሽ ነጻ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር የመስራት እድሉም ይኖርሻል። በምስጢር ማህበራቱ ዙሪያ መጻህፍት ጽፌ መሸጥ እና ድረ-ገጽ ከፍቼ መረጃዎችን መሸጥ፣ የዶክመንተሪ ፊልሞችንም ማሰራጨት አያቅተኝም

"ሴላ አማራጭ መኖሩን ስለጠቆማት እፎይ ብላለች። ተደም ሲል የጠየቀችው ጥያቄ ትዝ አላት እና "እነዚያን ጋዜጠኞች በአካል አግኝቼ ብተዋወቃቸው ደስ ይለኛል"

በሁለቱ የእረፍት ቀናት እንደሚያስተዋውቃት ቃል ገባላት፡፡ "የኢስቴሊንም፣ የአሊክስ ጆንስም የግል ስልክ ቁጥር አለኝ፡፡ ደውዬላቸው በምስጢር እናገኛቸዋለን፡፡ ስብሰባው እስከሚጠናቀቅ ከቶሮንቶ እይወጡም" አላት፡፡

"ፊት ለፊት ማግኘት አይቻልም ማለት ነው?"

"መረጃ ታሳቢብላላችሁ ተብለን ጥቁር መገገብ ላይ ልንሰፍር እንችላለን፡፡ ግዴለም ከዚህ በፊትም የማደርገው ነውና በምስጢር እናገኛቸዋለን" ሲል ዳግም ቃል ገባላት፡፡ የጠረጠረችውን ነገር ፍርጥ አድርጋ ጠየቀችው፡፡

"አሊክሲስ ደብል ኤጀንት ነኝ እንዳትለኝ?" በአግራሞት ተመለከተችው፡፡

"ከነታሽ ምን ይደረጋል? ያውም በከፍተኛ ጥንቃቄ የምሰራ ደብል ኤጀንት፡፡ ያለውዴታሽ በግዴታ እንደምትሰሪ ስለማውቅ እንጂ አንገቴን ለገመድ የሚዳርግ ምስጢሬን አልነግርሽም ነበር' ተሳሳቁ፡፡ የወይናቸውን የመጨረሻ ጠብታ ጨልጠው ወደመኝታ ክፍላቸው ሲሄዱ ሶስና በአዲስ ተስፋና ምኞት ተሞልታ ነበር፡፡

አልጋዋ ላይ ተንጋላ በነገው እለት ስለምትተዋወቃቸው ጋዜጠኞችና ስለምታሳልፈው አስደሳች ቀን አሰላሰለች፡፡ እንደምታስበው ከተሳካላት ልጇን ሰለሞንን ይዛ አድራሻዋን በመቀየር ካደነቀቻቸው ጋዜጠኞች ጋር መስራት ትጀምራለች፡፡ አሊክሲስ የጠቆማትን መንገድ ተጠቅማ ለእሷም ሆነ ለልጇ መተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ ማግኘት አያቅታትም፡፡ የWSIL-TV ጋዜጠኝነቷ ሊቀር ይችላል፡፡ ሀገሯን ለማፈራረስ ሴራ ጎንጉነው ከተነሱ ወገኖች ጋር ከምትሰራ በተቃራኒው የሴረኞቹን ተንኮል የምታጋልጥ ጋዜጠኛ መሆን ትመርጣለች፡፡ ለእሷም፣ ለልጇም ክብርና ኩራት ነው፡፡ እራሷ በፈጠረቻቸው መሰል የደስታ ሃሳቦች ተጠምዳ እንቅልፍ ወሰዳት፡፡

የነታቸው አርፍዳ ነበር፡፡ ከጠዋቱ 3፡30 ላይ፡፡ አሊክሲስም የሚያስቸኩል አጣዳፊ ስራ ስላልነበረው ማለዳ መነሳት አላስፈለ

ግውም፡፡ ከአልጋው ላይ ሳይወርድ በአእምሮው የእለት ውሎውን መንደፍ ጀመረ፡፡ አብዛኛውን ሰአት የሰጠው የምስጢር ማህበራቱን ከሚቃወሙ ጋዜጠኞች ጋር ለሚኖረው ቆይታ ነው፡፡ ከዚያ የሚተር ፈውን ሰአት ከፍሉ ውስጥ ሆኖ በንባብ ለማሳለፍ ነው የወሰነው፡፡ ያውም ሶስና ሃሳቡን ካላስለወጠችው ነው፡፡ ከተማ መጓጓኘት፡ ያላየሁትን ማየት እፈልጋለሁ ካለች አማራጭ አይኖረውም፡፡ ደወለላት፡፡" ወደ ሬስቶራንት ሄደን ቁርስ አንበላም?"

"እንደውም እርቦኛል ሰውነቴን ለቅለቅ ብዬ እመጣለሁ እዚያው ጠብቀኝ"

ከአልጋው ተነስቶ ተጣጥቦና ለባብሶ ወደ ሬስቶራንቱ ከመሄዱ በፊት ለዳንኤል ኢስቱሊን ደወለለት፡፡

"እንዴት ነህ የሀገር ልጅ?" አለ ኢስቱሊን ሞቅ ባለ የወዳጅነት ስሜት፡፡ አሊክሲስ በስብሰባው ላይ እንደሚገኝ ቱደም ብሎ መረጃው ደርሶታል፡፡ ቶሮንቶ ስታር ጋዜጣም ላይ አንብቧል፡፡ ማወቅ የፈለገው ጋዜጣው በተራ ቁጥር 9 ላይ ስለጠቀሳት አዲስ ጋዜጠኛ ነው፡፡ በየአመቱ በሚደረገው ቢልደርበርግ አባላት ስብሰባ ላይ የሚገኙትን አብዛኞቻቹን ጋዜጠኞች ያውቃቸዋል፡፡ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ሁኔታ ተገደው እንደሚሰሩ ስለሚያውቅ ያዝንላቸዋል፡፡ ከብዙዎቹም ጋ መልካም ወዳጅነት አለው፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ የመረጃ ምንጮቹ ናቸው፡፡ "ይህችን ደግሞ ኬት አመጧት?" ብሏል የሶስናን ስም በጋዜጣው ላይ ከተመለከተ በኋላ፡፡ ከWSIL-TV መወከሏ አልጠፋውም፡፡ ከዚያ በፊት የነበረችበትን ሁኔታ ነውማወቅ የፈለገው፡፡

ኢስቱሊን ቃሉን ደገመው፡፡ "እንዴት ነህ የሃገር ልጅ? ለነገሩ እንደምንገናኝ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ቶሮንቶ ስታር መግባትህን ስላበሰረኝ እስክትደውልልኝ እየጠበቅሁ ነበር" ለኢስቱሊን በምስጢር መረጃ ከሚያቀብሉት ጋዜጠኞች መሃል አንዱ አሊክሲስ ሮቢንስ ነው፡፡ አሜሪካንና እንግሊዝን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት ውስጥ የኖረና የሰራ ቢሆንም በአባቱ በኩል ሩሲያዊ የደም ሃረግ አለው፡፡ ሩሲያ ካናዳዊው ኢስቱሊን ያን ስለሚያውቅ ነው

በተደዋወሉ ቁጥር የሃገር ልጅ የሚለው፣ "እሱ ጋዜጣ እኮ ስድቡ ከፋ እንጂ እድግ የሚደነት ጋዜጣ ነው፣፣ እንዲት መረጃ አታመልጠውም፣፣ መገልገያ አሻንጉሊቶች የሚለውን ስድቡንም ለምደነዋል" አለ አለሀከሲስ እየሳቀ፣፣

ኢስቱሊን ለአለሀከሲስ ንግግር ግድ አልነበረውም፣፣ ቀልቡ ያለው እንግዳዋ ጋዜጠኛ ላይ ነው፣፣ የእሱን ንግግር እና አስተያየት ችላ ብሎ "እኔ የምልህ እዲሲድ ባልደረባህ ማነች? ቶሮንቶ ስታር በዘገባው ላይ እንተ ከምትሰራበት ቴሌቭዥርን ጣቢያ እንደመጣች ጽፏል" ሲል ስለሶስና የማወቅ ጉጉቱ እያስታወቀ ጥያቄ አቀረበ፣፣

አሌክሲስ የታፈነ በሚመስል ድምጽ ሳቀ፣፣ የኢስቱሊንን ባህሪ ያውቀዋል፣፣ ለእዲስ ሰውና ለእዲስ ነገር ሁሌም ጉጉ ነው፣፣ ስለሁለቱም በቂ መረጃ እስከሚያገኝ ድረስ ረፍት አይኖረውም፣፣

"ሶስና ትባላለች፣፣ እሜሪካ ተወልዳ እና አድጋ ኑሮዋንም እዚያው ታድርግ እንጂ ቤተሰቦቿ ከኢትዮጵያ የመጡ ስደተኞች ናቸው፣፣ እሁን እኔ በምሰራበት የቴሌቭዥርን ጣቢያ በመስራት ላይ ትገኛለች፣፣" አጠር ያለ መረጃ ሰጠው፣፣

ኢስቱሊን ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ሲሰማ የተለያዩ ሃሳቦች በአእምሮው ተመላለሱ፣፣ መጽሃፉን እድ ያደነቁለት የኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ የክብር እንግዳቸው እድርገው ወደሃገራቸው በጋበዙት ጊዜ በጨዋታቸው መሃል ደጋግመው ያነሱለት ሀገር ብትናር ኢትዮጵያ ናት፣፣ ስለህዝቧ ጨዋነት፣ እግዚአብሄርን የሚፈራ ህዝብ እንደሆነ፣ ስለለምለምነቷ፣ እንግዳ ተቀባይነቱን፣ የሚዋደድና የሚፋቀር ህዝብ እንደሆነ እንድም አልቀራቸው፣፣ ብዙ ነው የነገሩት፣፣ ካስትሮ የነገሩት ነገር በሚዲያ ላይ ከሚያየው ጋር ፍጹም ተቃራኒ የሆነበት ኢስቱሊን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፣-

"ሚዲያ ላይ የማየው ግን ርሃብ፣ በሽታ እና ችግር ያለባት ሀገር እንደሆነች ነው"

ካስትሮ ለኢስቱሊን ንግግር እድ አልሰጡም፣፣ እንዲህ ሲሉ መለሱለት፣፣ "በሚዲያዎች ላይ የተመለከትካት አይነት ሀገር

አይደለችም፡፡ ሳታጣ ያጣች ሀገር ናት፡፡ መሪዎቿ በራስ ወዳድነት ስሜት በፈጠሩት ስህተት ከመላው አለም ጋር የተዋወቀችበትን አሉታዊ ገጽታ የፈጠረች ምስኪን ሀገር፡፡ መሪዎቿ ወደ እራሳቸው እና ዘመዶቻቸው ብቻ ማየት ትተው ወደሰፊው ህዝብ ማየት ቢጀምሩ፣ ከድንግል መሬቷ የተገኘውን ሃብት ለእራሳቸውና ለዘመዶቻቸው ብቻ ከሚያደርጉ ፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተ የሃብት ክፍፍል ዘዴን ቢጠቀሙ እውነት አልሃለሁ ዛሬ ምእራባውያን ሚዲያዎች ላይ የምንመለከታት አይነት ኢትዮጵያን ሳይሆን ተቃራኒዋን ነበር የምናያት፡፡ ደግሞም እኮ ምዕራባውያኑ ሚዲያዎች የሚያጋንኑትን ያህል የሲኦል ምድርም አይደለችም"

ከዚህ የካስትሮ ንግግር ጋር ተዳብሎ ሊላም ስለኢትዮጵያ ያነበበው ነገር ከአእምሮው ጓዳ ብቅ አለ፡፡ ከምስጢር ማህበራት መሃል ፊት አውራሪ እንደሆኑ የተመሰከረላቸው እየሱሳውያን በአጼ ሱስንዮስ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ መግባታቸውንና በኋላ ግን ልጁ ፋሲለደስ እንዳስወጣቸው ያነበበው ትዝ አለው፡፡ ያነበበው ይህን ብቻ አይደለም፡፡ ዱቼ ሙሶሎኒን መጠቀም የፈለጉት የሮም እየሱሳውያን በወኪላቸው ቂስ ዶን ስቱሩዞ እና የካቶሊክ ካህናት አማካይነት በምርጫት ሽንተው ኢትዮጵያን እንዳስወረሩም አንብቧል፡፡

ኢስቱሊን ከዚህች ታሪክኛ ሀገር ስለተገኘችው ጋዜጠኛ በይበልጥ ለማወቅ ፈለገ፡፡ ኢትየጵያዊት ትሁን እንጂ በኢትዮጵያ እንዳልተወለደች፣ እንዳላደገችና እንዳልኖረች አሊክሲስ ነግሮታል፡፡ መቼም በንባብም ሆነ በቤተሰቦቿ አማካይነት የሃገሯን ታሪክ ማወቋ አይቀርም፡፡ እና ከጥንት ጀምሮ ሀገሯን ከሚፈታተኑ የምስጢር ማህበር አባላት ጋር ጋር ለመስራት የተስማማችው በምን ምክንያት ነው?

"ሃሎ አሊክሲስ?" አለ ኢስቱሊን "ይህችን ጋዜጠኛ በአካል አግኝቼ ላነጋግራት እፈልጋለሁ?"

"እንተም ባትል እሷ እራሷ አግኝታህ ልትተዋወትህ ትፈልጋለች" ኢስቱሊን ደስ አለው፡፡ 8፡30 ላይ ከሚያውቱት አነስተኛ ካፍቴሪያ ሊገናኙ ተጠሮ ያዙ፡፡ አሊክሲስ እሱና ኢስቱሊን

እንዲሁም ጥቂት የምስጢር ማህበራቱ ጋዜጠኞች ብቻ የሚገናኙበትን ምስጢራዊ ስልክ ዘግቶ ወደ ሬስቶራንቱ አመራ። ሲበዛ ጠንቃቃ በመሆኑ ለኢህቱሲን እና ጥቂት ታማኝ ጋዜጠኞች ብቻ የሚደውልበት ምስጢራዊ ቁጥር አለው።

ሶስናን ቀድሟት ነበር የደረሰው። የምግብ ምርጫዋን ስለሚያውቅ አዞ ጠበቃት። እስከዚያው ቡና እየጠጣ። የቆየ ልማዱ ነው። ቁርስ ከመብላቱ በፊት አንድ ስኒ ቡናና ሁለት ብርጭቆ ውሀ ይጠጣል። ከዚያ በኋላ ነው የመመገብ ፍላጎቱ የሚከፈተው። በሰባት ደቂቃ ልዩነት መጣች። ጥሩ እንቅልፍ እንደተኛች ፊቷን አይቶ አወቀ። መረጋጋት ይነበብባታል። ከወትሮዋ አይን የምትስብ ቆንጆ ሆናለች። በውሃ ሰማያዊ ኦፒር ኮት፣በነጭ ሽሚዝ እና በጥቁር ሱሪ ሽክ ብላለች።

"ጥሩ እንቅልፍ እንደተኛሽ ታስታውቂያለሽ" አላት ቁርሳቸውን እየተመገቡ ሳለ። "በጣም!" አለችው ፍልቅልቅ እያለች። ደስታዋ ወደእሱም ተጋብቶ ከኢህቱሲን ጋር ስለያዙት ቀጠሮ አጫወታት። የሶስና ደስታ የእሱም ደስታ መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል። ታሳዝነዋለች። ልጇን ለብቻዋ የምታሳድግ ነጠላ እናት ስለሆነችም ይሆናል። ግን እኮ ልክ እንደእሷ ያውም ከአንድ ልጅ በላይ የሚያሳድጉ እናቶች ብዙ ናቸው። ታዲያ እሷ ላይ ምን የተለየ ነገር አይቶ ነው.....?

ከሃሳብ አለም መለሰችው "እሱም ሊያናግረኝ ፈልጓላ!? እሱ በጣም ደስ ይላል። መጽሃፉን በጣም ነው የወደድኩለት። ከበቂ በላይ የሆነ መረጃ አግኝቼበታለሁ"

ከቁርስ በኋላ የቀጠሮአቸው ሰአት እስኪደርስ በየክፍላቸው ሆነው የየግላቸውን ስራ ለመስራት ተስማሙ። በትላንትናው እለት የተሳተፉበትን ስብሰባ አጀንዳ እና የተሳታፊዎችን ውይይት በየእራሳቸው መንገድ ማጠናቀር ይኖርባቸዋል። አሊክሲስ ከዚያ የሚተርፍ ሰአት ካገኘ የጣለውን የኤች.ፒ.አልባራሉ "A TERRIBLE MISTAKE" መጽሃፍ ለማንበብ ጓጉቷል። "ስምንት ሰአት ላይ እዚሁ እንገናኝ" አላት ወደየክፍላቸው በማምራት ላይ ሳሉ።

በተጠሯቸው ሰአት ዳንኤልን ወደተጠሩበት ካፍቴሪያ አመሩ። የስነምህንድስና ጥበብ ጎልቶ በሚታይባት ጋሊሪያ አካባቢ ከምትገኝ ሞር ያለች ካፍቴሪያ ነበር የቀጠሯቸው። የመረጃ ምንጮቹን እና ልዩ እንግዶችን የሚቀጥራቸው ከዚህች ሰው ከማይበዛባት ካፍቴሪያ ውስጥ ነው። ሶስና ኢስቴሊንን ከእርቀት አየችው። ሰውነቱ ላይ ጥብቅ ብሎ ቅርጹን የሚያሳይ ጉርድ ሰማያዊ ቲሸርት እና ጂንስ ሱሪ ለብሷል። ጸጉሩን እንደወትሮው ወደኋላው አስተኝቶ ጫፉ ላይ ቋጥሮታል። ፊት ለፊቱ ካለው ጠረጴዛ ላይ በርካታ መጽሃፎች ተከምረዋል።

ሲዘልቁ ከተቀመጠበት ተነስቶ ተቀበላቸው። የሶስናን እጅ እንደጨበጠ በፊግማታ እየተመለከታት "Glad to meet you" አላት። ስለተዋወቃት ተደስቶ ነበር። አጸፋውን መለሰችለት። ወደ ወንበሩ ከተመለሰ በኋላ ስለኢትዮጵያ ያነበበውን እና ካስትሮ ስለዚህች ተአምረኛ ሃገር ያጫወቱትን ነገራት። ደስ አላት። ሰዎች ስለሃገሯ፣ በእርቀት ስለምታውቃት፣ አባቷ ፈጽሞ እንዳትዘነጊያት ስላላት ኢትዮጵያ አድንቀው ሲያወሩላት ይሄው ናት። በደስታ የምትሆነውን ታጣለች። "ግን" አላት ኢስቴሊን ንግግሩን በመቀጠል "ግን ሀገርሽን ከሚፈታተኑ የምስጢር ማህበር አባላት ቁንፅል ሰዎች ጋር ለመስራት የተስማማሽበት ምክንያት አልገባኝም?"

ቶሮንቶ ስታር በገጹ ላይ ያሰፈረው "አባላቱ መግልገያ አሻንጉ ሊቶች" የሚለው ቃል ታወሳትና ሽምቅቅ አለች። ኢስቴሊንም ባነሳላት ጥያቄ ውስጥ ቃሉን የደገመው መሰላት። "ፈልጌ ሳይሆን ተገድጄ ነው" አለችው በፊቷ ላይ ንዴት እና ብስጭት እየታየ። "ፈልጌ አይደለም በልጄ መጡብኝ። ካገቱት በኋላ እንገድለዋለን ብለው አስፈራሩኝ" ታሪኩን ከሀ እስከ ፐ አጫወተችው። ዮናታን ምን ብሎ እንዳስፈራራት ሞምር ነገረችው። አዘነላት። ያውቃቸዋል። አም የለየላቸው አረመኔዎች ናቸው።

"ልክ ነሽ። በማስፈራራት ሰውን የዘለአለም ባሪያ አድርጎ መግዛት ይቻላል ብለው የሚያምኑ ናቸው። ሁሌም ፈሪ ሆኖ የእነሱ ባሪያ ከመሆን ይልቅ እውነትን ይዞ ርዕስ ስራቸውን

እየጋለጡ በጥንቃቄ መኖር ይቻላል፡፡ እራት ሳትሄጂ እኔን ተመልከቺ፡፡ ለበርካታ አመታት ስታገላቸው ኖራያለሁ፡፡ ወደፊትም እታገላቸዋለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ሊያስወግዱኝ ቢሞክሩም አልተሳካላ ቸውም፡፡ አካሄዳቸውንና ማንነታቸውን እስከተረዳሽ ትጠነቀቂያ ለሽ፡፡ በህዝብ ዘንድ እውቅናሽ እየጎላ ሲሄድ አንቺን ማጥፋት ይፈራሉ፡፡ ህዝቡ እንደሚጠይቃቸው ስለሚያውቁ ይጠነቀቃሉ፡፡

"ተንኮላቸውን በምስጢር መከወን ስለሚፈልጉ ፊኪሻኛ መባልን አይፈልጉም፡፡ አመኔታን ማግኘት ይሻሉ፡፡ ዋናው ነገር በህዝብ ዘንድ እውቅናን ለማግኘት ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ይህን ስልሽ ግን እውቅና ማግኘቱ ብቻ በቂ ነው ማለቱ አይደለም፡፡ ወሳኙ የእራስሽ ጥንቃቄ ነው፡፡ እኔን ጨምሮ እነሱን ለሚጋለጥ የሚሞክሩ ጋዜጠኞችን ሁሉ ለማጥፋት ከማሴር ወደኋላ አይሉም፡፡ ያጠፉናል ብለን ግን ወደኋላ አንልም፡፡ መሰዋእትነትን ከፍሎ አለምን ማዳን መታደል ነው፡፡ ለጥቂቶች ብቻ የሚሰጥ ጸጋ፡፡ እውነቱን ነው ከጉራ አትቁጠሪብኝ፡፡ ለእዚህ እድል ለመበቃት መታደል ያስፈልጋል፡፡ እንደ ዊሊያም ኩፐር መሰዋእትነትን እስከመክፈል ድረስ እንሂዳለን" የዊሊያም ኩፐርን ማንነት እና እነሱን ለመዋጋት ሲል የከፈለውን መሰዋእትነት አጫወታት፡፡

"ይሄም አለ?" አለች በውስጧ እየተገረመች፡፡ እነሱን መዋጋት ቀላል እንዳልሆነ፣ ግን እንደሚቻል ኢስቱሊን ነግሯታል፡፡ ያውም እራሱን እና የሚያውቃቸውን ጋዜጠኞች ምሳሌ አድርጎ፡፡

‹እነሱን ታግሎና ተዋግቶ በህዝብ ዘንድ ከበሬታን ማግኘት የላቀዋጋ አለው› ስትል ውስጧን አሳመነች፡፡ ‹ለህዝብ የሚጠቅም ተግባር መፈጸም ታላቅነት ነው፡፡ ህዝብን በባርነት ሊገዙት ስለሚፈልጉ ሃይሎች ግንዛቤን ማስጨበጥ ደግሞ ከታላቅነትም በላይ ነው፡፡ ወደጀግንነት ይጠጋል፡፡ ጀግንነትን ስለተመኙት ብቻ አያገኙትም፡፡ መሰዋእትነትን ይፈልጋል፡፡ ይህ መሰዋእትነት ህዝብን ከጥፋት፣ ሀገርን ከመፈራረስ የሚታደግ ነው፡፡›

ጀግና መሆን አማራት፡፡ ጀግና ብትሆን አባቷ ሁሌም አስታውሻት ያላትን ሀገሯን እየተሸረበባት ካለ ሴራ እና ተንኮል

ታድናታለች፡፡ ከእራሷ ጋር እየተወያየች ባለችበት ሰአት አስዘሲን ሊላም ጥያቄ አስከተለ፡፡

"ልጅን ይገድለብኛል ብለሽ በሙፍራትሽ ሁሌም አገልጋያቸው ሆነሽ ለመገለት ወስነሻል ማለት ነው?"

"በፍጹም!" አለች ፊሞና፡፡ "የተሻለ አማራጭ ባገኝ እንደውም የእናንተን መንገድ ተከትዬ...." ደስ አለው፡፡ የእሱንና የመሰሎቹን አርማ የምታነግብና የምስጢር ማህበራቱን ሰዎች እያላደደች የምታጋልጥ ልምድ ያላት ጋዜጠኛ በማግኘቱ ደስታ ተሰማው፡፡

"ትችያለሽ!" አላት በእርግጠኝነት፡፡ "ትችያለሽ ሶስና፡፡ ውስጥሽን እስካሳመንሽው እና እስከጠነከርሽ ድረስ ያሰብሽውን ከማድረግ ወደኋላ የሚመልስሽ ምንም አይነት ሃይል አይኖርም"

"ልክ ነህ፡፡ ውሳኔ ላይ ስደርስ ግን የማጣቸው ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ዋንኛው ሙተዳደሪያዬ የሆነው ስራዬ ነው፡፡ ስራዬን እጣሁ ማለት ደግሞ እኔና ልጄ....." አላስጨረሳትም፡፡ ስጋቷ ገብቶታል፡፡

"በዚያ ላይ ስጋት አይግባሽ፡፡ ከሰዎቻችን የአንዱ ረዳት ሆነሽ ትሰጠሪያለሽ፡፡ የጋዜጠኝነት ልምዱ ስላለሽ እጅሽን ስመው ነው የሚቀበሉሽ፡፡ ውሳኔ ላይ ድረሺ እንጂ የሚቀበሉሽን ሰዎች አገናኝሻለሁ፡፡" ቃል ገባላት፡፡ በሀልም አለም ውስጥ ያለች መሰላት፡፡ ደስታዋ መጠን አጣ፡፡ አማራጭ የምታገኝ ከሆነማ ሀገርሽን ልንበጠብጣት ነውና ተባበሪን ብለው ካስገደዷት አውሬዎች ጋር የምትተባበርበት ምክንያት አይኖርም፡፡

በገርገር ጉዳዮች ላይ በስፋት ተነጋገሩ፡፡ የምስጢር ማህበራቱን ተግባራት የሚያጋልጡ እንቅስቃሴዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ ለመሆን ተስማማች፡፡

"ከዚህ በኋላ" አለ አስዘሲን እየሳቀ "አባል ሆነሽ ተመገማበሻ ልና ቶሎ ቶሎ ታገኚኝ፣ በአባላቱ ስብሰባዎች ላይ አብረሽን ትሬሂ እና እነሱን የሚቃወሙ ጽሁፎች ታዘጋጂ ዘንድ ተፈርዶብሻል"

"በደስታ" አለች እየተጥለቀለቀች፡፡ በዚህ ቅጽበት አንድ ሃሳብ ብልጭ አለላት፡፡

"አሊክሲስ ስፔን እንደምትኖር ነግሮኝ ነበር?"

"እም ምነው?"

"ሁኔታውን የምታመቻችልኝ ከሆነ ዓዜን ጠቅልዩ....." አላመነም።

"ስፔን መኖር ትፈልጊያለሽ?"

"ይሻለኛል። የተውኒቸው ሰምች ከዛራ ነገ መጥተው ከነልጇ ያጠፉኛል ብዬ ከምጨናነት ብርቅ ይሻለኛል። ከአንተ ጋር በትርበት ለመንቀሳቀስም ይመቸኛል" ወደ ስፔን ሊወስዳት ቃል ገባላት።

ውሎዋ እጅግ አስደሳች ነበር። ካደነቀችው ጸሃፊ ጋር ተዋውቃለች። ጠቃሚ ነገሮችን መከሯታል። ሁኔታውን እመቻችቶ ወደ ስፔይን እንደሚወስዳትም ቃል ገብቶላታል። ሊለያዩ ሲሉ "እስክትገላገያቸው ድረስ እንዳትፈሪያቸው። ግን ተጠንቀቂያቸው። በዘዴ ያገርያቸው። የሚሉሽን ሁሉ እሺ በያቸው። የሰጡሽ የቤት ስራ ረሽሮም ጊዜ የሚወስድ ነውና ሃሳብና ስጋት አይግባሽ። እስከዚያ ብዙ ነገሮች ይቀያየራሉ። በፍጹም የከወደት ምልክት እንዳያዩብሽ ተጠንቀቂ"

"ያልከኝን ሁሉ አደርጋለሁ"

በወዳጅነት ስሜት ተሰነባበቱ።

****

በሶስተኛው ቀን ከአሊክሲስ ጋር ከተማውን ዝንኙች። አራተኛው ቀን ላይ ወደሰብሰባው አዳራሽ ሄዱ። በስብሰባው መጀመሪያ እለት ለተነሱት እጅንዳምች የመፍትሄ ሃሳቦች ናቸው የተባሉት በሰፋት መነጋገሪያ ሆኑና ጉባኤው ተጠናቀቀ ተባለ። እነሶስና ውለው አላደሩም፣ ወደመጡበት ተመለሱ። የስብሰባውን እጀንዳ ለሀገብ ማድረስ ነበረባቸው።

በነጋታው ቢሮዋ እንደገባች ከአለቃዋ አሊክሳንደር ጋር ተገናኙ።

"የቶሮንቶ ቆይታሽ እንዴት ነበር?" አላት የምትለውን ለመስማት በመጓጓት።።

"በጣም ቆንጆ ነበር" አለችው የሆዷን በሆዷ ይዛ። በስብሰባው ወቅት ተነስተው ስለነበሩ አጀንዳዎች ተወያዩ። አጀንዳው ተቀናብሮና በምስል ተሞሀዶ በቴሌቭዥን ሲተላለፍ ሶስና እና አሌክሲስ አድናቆት ተቸራቸው። በአድናቆቱ ደስተኞች አልነበሩም። ያላመኑበትን እና ሃሰተኛውን አጀንዳ እንዳስተላለፉ ያውቃሉ።።

ሶስና ኢስቱሊን እንደመከራት የከሀዲት ምልክት ሳታሳይ ስራዋን በአግባቡ መስራቷን ቀጠለች። ደብቃ ያስቀመጠችውን እውነት እጅግ ለምትወደው ልጇ እንኳን መናገር አልፈለገችም። ከጅምሩ ምስጢሩ ይፋ መውጣት የለበትም።።

- 10 -

ጣሊያን፣ ስትሬሳ

በመጀመሪያ ደረጃ የምስጢር ማህበር አባልነቱና ታማኝነቱ ጣሊያን፣ስትሬሳ ውስጥ የሚካሄደውን ስብሰባ ለመካፈል የተገኘው ዮናታን ወልዴ ከስብሰባው በኋላ በሲ.ሲ.ሊ ገጠራማ መንደሮች በሚካሄደው የአምልኮ ስነስርአት ላይ መገኘት ይኖርበታል፡፡ ቤንጃሚን ፓተርሰን አብሮት አለ፡፡ በቆይታው ደስተኛ ነው፡፡ ከእውቅ የሃገራት መሪዎችና ፖለቲከኞች ጋር ስብሰባ በመቀመጡ ክብር ተሰምቶታል፡፡ የካናዳ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ባንኮች ገገርዎች፣ ፎርድ ካምፓኒን ወክሎ የመጣው ዶናልድ ኢ. ፒተርሰን፣ ሂንሪ ኪሲንጀር፣ ቱጃሩና ቢልደርበርግን እንዳሻው የሚያሽከረክረው ዴቪድ ሮክፌለር እና ሌሎችም በስብሰባው ላይ ነበሩ፡፡ ስብሰባው ሁለት ቀናትን ፈጅቶ በመጠናቀቁ ለገጠራማው መንደር ጉዞ ተዘጋጁ፡፡ ወደስፍራው የሚወስዳቸው እና የሚከብድ አይነት ፊት ያለው ሰው ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት እንዲህ አላቸው፡-

"በቅድሚያ እራሴን ላስተዋውቃችሁ፡፡ ራቬራ እሚንቶሪ እባላለሁ፡፡ የራንቬርሶው ቅዱስ አንቶኒ ገዳም (ደብር) ሽፈርና የግምገባ ቤት ሃላፊ ነኝ፡፡ በአስጎብኚነትም አገለግላለሁ፡፡ ተወልጄ ያደግሁት በዚሁ ስፍራ በመሆኑ አካባቢውን የእራሴን ያህል አውቀዋለሁ፡፡ እንድወስዳችሁ የታዘዝኩት ወደሲ.ሲ.ሊ ገጠራማ መንደር ነበር፡፡ ትእዛዝ በመለወጡ የምንሄደው ወደ የራንቬርሶው ቅዱስ አንቶኒ ገዳም ነው"

ሲናገር አራት ነጥብ አያውቅም፡፡ሎጭን እና የሚስቀጥጥ ድምጽ አለው፡፡ ነጭ መስቀል ያለበት ረዥም ቀይ የመነኩሴዎች ቀሚስ ለብሷል፡፡ መለፍለፉን ቀጠለ፡፡

"ግላሙ የሚገኘው ከብሪን ወደፊደረንላይበሚያመራው ጎዳና ላይ ነው፡፡ በጎዳናው ላይ ስትነዙ ከትዱስ አንቶኒ በተጨማሪ በቲጅሲራ አልታ የተባለውንም ሀገር ታገኛላችሁ፡፡ የራንቪርሶው ቅዱስ አንቶኒ ገዳም መች እና በማን እንደተመሰረተ ታውቃላችሁ? ግደለም እኔ እነግራችኋለሁ፡፡ ለእንግዶች ማብራሪያ መስጠት የኖርኩበት መሥያዬ ነው"

የተውላላው ሪቪራ አሚንዮሪ ልፍለፋ የሰለቸው ቤንጃሚን ፓተርሰን፡

"ግደለም ትነግረናለህ፡፡ ግን ጉዞ ከጀመርን በኋላ አይሻልም?" አለና ዮናታንን ጠየሰው፡፡ በሃሳቡ መስማማቱን በምልክት አሳየው፡፡

"እው! መልካም ሃሳብ፡፡ ግቡ....ግቡ" የመኪናዋን በር ከፈተላቸው፡፡ አሮጌ እና የቆየች ባለሁለት በር ፎርድ ፌይሪሞንት መኪና፡፡ በጉዞ ላይ ሪቪራ መለፍለፉን አላቆመም፡፡ የጣሊያንኛ ዘይቤ በሚንጸባረቅበት እንግሊዘኛ ነበር የሚያወራላቸው፡፡

ዮናታን ሁኔታው ግርሞት ዘወር ብሎ ሲመለከተው ከላይኛ የፊት ጥርሶቹ ሁለቱ ያለመኖራቸውን ልብ አለ፡፡ ከቅጥነቱ የተነሳ ተንቀሳቃሽ ሬሳ እንደሚመስል የታዘበው ደግሞ ፓተርሰን ነው፡፡ ሪቪራ ቀጠለ

"እም....ምን ላይ ነበር ያቆምኩት? አም አስታወስኩት፡፡ የራንቪርሶው ቅዱስ አንቶኒ ገዳም መች እና በማን እንደተመሰረተ ታውቃላችሁ? ስል ነበር የጠየቅኋችሁ፡፡ ከመልሱ እጀምራለሁ"

ዮናታን እና ፓተርሰን ተያይተው ተሳሰቁ፡፡ ሪቪራ ቀጠለ

"ይህ ገዳም የተመሰረተው በ1188 ዓ.ም ሲሆን የመሰረተውም የሳቮዩ አምበርቶ ሰስተኛ ነው፡፡ የሚገርማችሁ ይህ ደብር ቱሪኖ፣ ቨርሲሊ ውስጥ ከምትገኘው የማርያም በተክርስትያን ጋር የሚመሳሰልበት ብዙ ነገር አለው፡፡ የቨርሲሊዋ የማርያም በተክርስትያን የቫይንያርድስ ወይዘሮ ቅዱስ ስፍራ በመባልም ትታወቃለች፡፡ ጥንቅላና ሰይጣናዊ ተግባራት እንደሚከናወንባት ከተመለከትኩ

በኋላ በቅዱስ ስፍራ ስያሜ በምትጠራ የድንግል ማርያም ቤተክርስትያን ውስጥ እንዴት እንዲህ አይነት ርኩሰ ተግባር ይፈጸማል?" ስል ፎከርኩ። ያኔኅናአፍላ ጎረምሳ ነበርኩ። ውስጥ ስለሚከናወነው ድብቅ ሴራ የማውቀው ነገር አልነበረም። የገዳመ. አስተዳዳሪ ጠሩኝና "ተናግረሃል የተባለውን በእኔ ፊት ድገመው?" አሉኝ። ደገምኩላቸው። ያኔ የደብሩ ተላላኪ አገልጋይ ነበርኩ።

"ለሌሎችም ማስተማሪያና መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ወደ ሰምቹ ውሰዱት› የሚል ትእዛዝ አስተላለፉ። ተወሰድኩ። ሰምቹ ግላዲዮ ማፍያ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ቅጥር ነፍሰ ገዳዮችና የገዳመ. ሃላፊዎች መተማመኛዎች እንደሆኑ የተገነዘብኩት ቆይቹ ነው። እንዳልሞት እንዳልሽር ከቀጠቀጡኝ፣ ጥርሶቹን ካወለቁና ሰብርብር ካደረጉኝ በኋላ ባዶ ክፍል ውስጥ ዘጉብኝ። ከድብደባው ይልቅ እጅግ የጎዳኝ ጠኔ ነበር። ርሃብና ጥማቱን መቋቋም አቃተኝ። ሰቃዬ ከፋ። ከሰሀተቴ ተምሬያለሁ ይቅርታ ይደረግልኝ ብዬ በመማጸኔ ምህረት ተደረገልኝ። አስተዳዳሪው ዳግም ጠሩኝና "መሰል ስህተት ብፈጽም በሞት ልቀጣ" የሚል ወረቀት አስፈረሙኝ። ከዚያ በኋላ ቢያዩኝ፣ ቢሰልሉኝና ቢያሰልሉኝ ከገባሁት ቃል የማልዛነፍ ሆኜ በመገኘቴ ቀስ በቀስ ሃላፊነት እና ቋሚ ስራ ተሰጠኝ። የደብሩ ሾፌርና የግምጃ ቤት ሃላፊ ሆንኩ። በሃሳባቸው ባልሰማማስ የት እደርሳለሁ? ከማንበብ እና ከመጻፍ የገፋ ትምህርት የለኝም። ከትውልድ መንደሬም ወጥቼ አላውቅ። ዘመዶቼ ሁሉ አልቀዋል። የምጠጋበት ዘመድ እና ሰው የለኝ። ስለዚህ ታዛጉቸው ሆኜ መኖር አማራጭ የሌለው ግዴታዬ በመሆኑ ይሄው ብዙ አመታት ያገለገልኩበትን ደብር መስሪያ ቤቴም፣ መኖሪያዬም አድርጌው እኖራለሁ"

ዮናታን እና ፓተርሰን ዳግም ተያዩ። ቢሰለቻቸውም ወሬው ደስ ብሏቸዋል። አሮጌዋ ፎርድ ፌይሪሞንት ብሶት ሳታሰማ መንገዱን ቀጥላለች። ሪቪራም ወሬውን።

"በቤተክርስትያኗ እና በቅዱስ አንቶኒ ገዳም የሚፈጸመውና ሲፈጸም የኖረው ተግባር ከላይ የነገርኳችሁ ብቻ አይደለም።

በተለይ በማርያም ቤተክርስትያን ጥንቶላና ሰይጣናዊ ተግባራት ይፈጸሙ እንደነበር ከ1684 ዓ.ም ጀምሮ ይፋ የሆኑ ዶክመንቶች አጋልጠዋል። ቤተክርስቲያኒቱን ያገለግሉ የነበሩት የአካባቢው ልጃገረዶች ሲሆኑ ልጃገረዶቹ ዘወትር ምሽት ተሰብስበው ሰይጣንን በመጥራት አብረውት ይጨፍሩና በደስታ ይፈነጥዙ ነበር። ለነገሩ የቤተክርስትያኒቱ ህንጻ የተዘጋና እንደበፊቱ ይፋዊ የሆነ አገልግሎት መስጠት ያቋረጠ ቢሆንም ለአካባቢው እንግዳ የሆኑ ሰዎች ምሽት ላይ በስፍራው በመገኘት ሰይጣናዊ ስነሰርአቱን ማካሄዳቸውን ቀጥለዋል....."

እንደለፈለፉ ምሽት ላይ የራንቪርሶው ቅዱስ አንቶኒ ገዳም ደረሱ። የደብሩ አስተዳዳሪ፣ ጥቂት ካህናት እና በጣት የሚቆጠሩ የP2 ቅርንጫፍ የምስጢር ማህበር አባላት ደማቅ አቀባበል አደረጉላቸው።

በገዳሙ ውስጥ ያሉት ካህናት እና የምስጢር ማህበር አባላት በጠቅላላ "ወንድም" እተባባሉ እንደሚጠራሩ ዮናታን ልብ ብሏል። ገዳሙ ጭር ያለ ስፍራ የተሰራ በመሆኑ ከገዳሙ ሰዎች በቀር ሌላ ሰው አይታይም። የደብሩ ሃላፊ የነበሩትን ሁሉ እንዲሰበሰቡ ካደረጉ በኋላ ንግግር አደረጉ።

"አላማችንን የሚደግፉና ሃሳባችንን የሚቀበሉ ወንድሞች በእንግድነት በገዳማችን ተገኝተዋል። አላማችንን ስለደገፉና ስለተቀላቀሉን እናመሰግናቸዋለን። ሃይልና ስልጣን፣ ሀብት እና ንብረት የሚሰጠውን የመሪያችንን የሉሲፈርን ተአምር ለመመልከት ብዙ ኪሎሜትሮች ተጉዘው በመምጣታቸው በአምላካችን በሉሲፈር ስም እናመሰግናቸዋለን። በተለይ የቃልኪዳን ሀገር እንደሆነች የተመሰከረላትን ኢትዮጵያ እምነት ለመፈታተን እና ለመሸርሸር በምናደርገው እንቅስቃሴ ላይ አብይ አስተዋጽኦ ለማድረግ ተስማምቶና ያን ለማድረግ የሚያስችለውን ትእዛዝ ከእኛ ለመቀበል ፈቅዶ የመጣውን ዮናታን ወልዴን እጅግ እናመሰግነዋለን። የሰይጣን እምነትን ለማስፋፋት ካሰብናቸው እና ኩተንቀሳቀስን ባቸው የዓለም ሀገራት እጅግ አስቸጋሪ ፈተናና ከባድ ተቃውሞ

የገጠመን ከኢትዮጵያ እንደሆነ ሁላችሁም የምታውቁት ሀቅ ነው። ከመሬት ተነስቼ ይህንን አላልኩም። ሁላችሁም እንደምታስታውሱት በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ1970ዎቹ ሙሉ እመታት እና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ በሃገሪቱ ዋና ዋና ስፍራዎች ቦሌ የተባለውን ሰፈር ጨምሮ የግለሰቦችን ቪላዎች ተከራይተን የ666 ሰይጣናዊ አምልኮን ለማስፋፋት የሞከርን ቢሆንም አልተሳካልንም ነበር። ህዝቡ የአንድ ሰሞን የመነጋገሪያ እጀንዳ ካደረገን በኋላ የተከራየነውን ቤተ አምልኮ በድንጋይ እሩምታ እንዳልነበር እንዳደረገና አባሎቻችንንም ከስፍራው እንዳባረረ አስተማማኝ መረጃ ደርሶናል።

"ይህ ህዝብ ለሃይማኖቱ ቀናኢ እንደሆነና በሃይማኖቱ ቀልድ እንደማያውቅ እናውቃለን። ለዚህም ነው አስፈላጊውን መስዋእትነት ከፍለን፣ ይበጀናል ብለን ያመንበትን ዘዴ ሁሉ ተጠቅመን በቁጥጥራችን ስር ልናውለው፣ የሰይጣን እምነት ተከታይ ልናደርገው ቆርጠን የተነሳነው። አሁንም ከባድና አስቸጋሪ ፈተና እንደሚያጋጥመን እትጠራጠሩ። አድገዋል፣ በልጽገዋል ከተባሉት ሃገራት ዜጎች ይልቅ የማይጨበጥ እሳት የሆነብን የዚህች ምስኪን ህገር ዜጋ ነው። ድሃ ቢሆንም በእምነቱ፣ በባህሉና በሃገሩ ቀልድ አያውቅም። ሃብታሞች ናቸው የተባሉትን አብዛኞዎቹን ሀገራት በቁጥጥራችን ስር አውለናቸዋል። የእምነታችን ተከታዮች አድርገናቸዋል። ኢትዮጵያን ግን አልቻልንም። በቀጥታ እምነታችንን እንድትቀበል ለማድረግ ቢያዳግተን እንኳን በተዘዋዋሪ መንገድ ህዝቡን በቁጥጥራችን ስር ማዋል ይኖርብናል። ለጊዜው ተዘዋዋሪ መንገድ ብለን ያሰብነው ግብረሰዶማዊነትን ማስፋፋት እና የአምልኳችን ተከታዮች የሆኑ ዝነኛ ድምጻውያንን በእምነቱ ስፍራዎች ሰርገው እንዲገቡ ማድረግ ነው። ተከታዮቻችን የሆኑት ድምጻውያን በኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ደግሞ በወጣቱ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት እንዳላቸው አረጋግጠናል።

"በተለያዩ ጊዜያት እነዚህን ዝነኛ ድምጻውያን ወደሃገሪቱ በመላክ ምልክቶቻችንን፣ አላማችንን እንዲሁም መልእክታችንን በዘፈን አማካይነት ማስተላለፍ እንችላለን ብለን እናምናለን።

ድምጻውያን ስላችሁ አላማችን በደንብ ግብታቸው ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱትን እንጂ ሳንቲም ለማግኘት እና ህዝቡን በተራ የዘፈን መልእክት ለማስጨፈር የሚንቀሳቀሱትን ማለቱ አይደለም፡፡ ህዝቡ ጨፈረ አልጨፈረ፣ ተዝናና አልተዝናና ምን አገባን? የእኛ ጉዳይ በእራሳችን ተከታይ ድምጻውያን አማካይነት ወጥመዳችን ውስጥ ማስገባት ነው፡፡ ህዝቡ በተከታዮቻችን ሙዚቃ ከመደሰትና ከመጨፈር ውጭ በመልእክቱ ላይ ትኩረት እንደማያደርግ ከዚህ ቀደም ተግባራዊ ካደረግናቸው ተሞክሮዋቻችን ተገንዝበናል፡፡ ለጊዜው በዚህ አይነት ሁኔታ መልእክታችንን ማስተላለፍ ከቻልን ወደፊት ደግሞ ሃሳቡን ተረድቶና ተቀብሎ እጁን የሚሰጥበትን መንገድ እናመቻቻለን፡፡ መንገዱን ለማመቻቸት ከጎናችን ከሚሰለፉት ቅን ተባባሪዎች መሃል አንዱ ዮናታን ወልዴ በመሆኑ አሁንም ምስጋናችን ወደር የለውም፡፡ ዮናታን ዝነኛ ድምጻውያንን ወደ ኢትዮጵያ ወስዶ ከሃይማኖት አባቶች ጋር በማገናኘት፣ ህዝቡ እንዲቀበላቸው በመገፋፋት፣ የእምነት ተቋማት ውስጥ ሰርገው እንዲገቡ በማድረግ እና ግብረሰዶማዊነትን በማስፋፋት ተልእኮውን በድል ይወጣል ብለን እናምናለን፡፡ ዛሬ እዚህ የተገኘበት አብይ ምክንያትም ይሄው ነው፡፡ ስራውን ለመጀመር የሚያስችለውን ትእዛዝ መቀበል፡፡ ስራ እና ተልእኮ እንደሚበዛበት ብናውቅም ትእዛዛችንን ፈጽሞ የምንጓጓለትን ውጤት በአይናችን ያሳየናል ብለን እናምናለን፡፡ በድጋሚ እናመሰግናለን"

ንግግራቸውን ጨረሱ፡፡ መጽሃፍ ቅዱስ ረግጦ አባልነቱን በተግባር ላረጋገጠው ዮናታን ይሄ ምንም ማለት ባይሆንም ጫናው አስፈርቶታል፡፡ ቤንጃሚን ፓተርሰን ጀርባውን በወዳጅነት ስሜት ቸብቸብ እያደረገ "ወንድም ዮናታን የተሸከምከው ሃላፊነት ቀላል ስላልሆነ ወገብህን ጠበቅ" አለው፡፡ ጫናው ከወዲሁ ታውቆታል፡፡ እድሜ ለሃሪማን ፓሌይ፡፡ የእሱ ስራ ነው፡፡ ‹ስንት ቦታ ሊገነጣ ጥለኝ ይፈልጋል?› ሲል በውስጡ ተነጫነጨ፡፡ የተላከበት ምክንያት ግልጽ የሆነለት አሁን ነው፡፡ የኢትዮጵያን እምነት ሸርሽሮ ህዝቡን የሰይጣናዊ እምነት ተከታይ ለማድረግ የሚያስችለውን ትእዛዝ ለመቀበል ነው የመጣው፡፡ በእይሁዳውያኖቹ ጥንዶች እና በሶስና

አማካይነት ተግባራዊ ሊያደርገው የጀመረውን ተልእኮ ሳይጨርስ ተደራቢ ትእዛዝ መቀበሉ አበሳጭቶታል።

"የእራት ሰአት ደርሷልና ወደመመገቢያው ክፍል እንሂድ" የሚለው የለፍላፊው ሪቬራ አማንቶሪ ድምጽ ከገባበት ጥልቅ የሃሳብ ዓለም መለሰው። ክፍሉ ከቤተ-አምልኮው (ገዳሙ) ህንጻ በስተግራ በኩል የሚገኝ ትልቅ አዳራሽ ነው። ሁሉም ወደዚያው አመሩ። ዮናታን የአዳራሹን በር አልፎ እንደገባ ፊት ለፊት የተመለከተው ስእል ለሰከንዶችም ያህል ቢሆን አስደንግጦታል። ከገደል አፋፍ ላይ የቆመና ጨቅላ ህጻናትን በሁለቱም እጆቹ ጨፍልቆ የያዘ ግዙፍ ሰይጣን ምስል። በርካታ የሰይጣን ምስሎች በአዳራሹ ግድግዳ ላይ ተሰቅለዋል።

የተመደበላቸው ቦታ ላይ ተቀመጡ። በህንጻው ውስጥ ያላያቸውን እንግዶች በምግብ አዳራሹ ውስጥ ተመልክቶ ዮናታን ሌሊት በሚካሄደው ስነስርአት ላይ ለመታደም የመጡ እንደሆኑ ገምቷል። የP2 የምስጢር ማህበር ቅርንጫፍ አባላት ነበሩ። ለእራታቸው የቀረበላቸው የአሳማ ስጋ፣ ፓስታ፣ ዳቦ እና ወይን ነበር። እየተመገቡ ሳለ አጠገባቸው የተቀመጠው ሪቬራ የአሳማውን ስጋ ወደአፉ ልኮ በሽኩሽኩታ እንዲህ አላቸው

"ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ላይ ስነስርአቱ ይጀመራል። ታዋቂዎቹ የሰይጣን መልእክተኞች ዊሊያም ቢሪዚ፣ አልቤርቶ ሞስካቶ፣ ማሲሞ ኢንትሮቪፕ እና የግልዲዮ ማፍያ አባላት ይገኛሉ። በምትመለከቱት ነገር እንደማትደነግጡና እንደማትሸበሩ እምነቴ ነው።"

የተሰላቸው ፓተርሰን ወደ ዮናታን ጆሮ ጠጋ ብሎ "ምነው ይሄን ቀውላላ ራሳ የሚገላግለን ሰው ጠፋ?" አለው። እራቱ ላይ ብዙም አልቆዩ። ንቁ ሆነው ለመገኘት በጊዜ ወደመኝታቸው ሄዱ።

ደውል ሲደወል ሁሉም እየተነሳ የእምልኮው ስነስርአት ወደ ሚካሄድበት ህንጻ ተሯሯጠ። አስተዳዳሪው ስነስርአቱን ለማስጀመር የሰውን ተጠቃሎ መግባት እየተጠባበቁ ነበር። ዮናታን የህንጻውን በር አልፎ እንደገባ ለሁለተኛ ጊዜ ያስደነገጠውን ነገር በቤተ-አምል

ኮው ግድግዳ ላይ በእንግሊዝኛ ተጽፎ ተመለከተ፡፡ ርእሱ ጎልቶ ታየው፡፡ "የሰይጣን ዘፈን" ይላል፡፡ ስንኞቹን ለማንበብ ሞከረ፡-

ሰይጣንን ለመጥራት አብሮ ለመጨፈር
ጨቅላ ሀጻናትን አስገድዶ መድፈር
ስልጣን ከሚሰጠው...
ሀብትን ከሚከሰጠው.....
ዓለምን ለመግዛት ሃይልን ከሚያድለው
ከሉሲፈር ጋራ አብሮ ለመቀመጥ
ጨቅላ ሀጻናትን በስል ድንጋይ መቁረጥ
ጨቅላ ሀጻናትን በስል ድንጋይ መፍለጥ

የስነስርአቱ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አልከበደውም፡፡ የደብሩ አስተዳዳሪ ስነስርአቱን አስጀመሩ፡፡ ሁሉም ድምጹን ከፍ አድርጎና ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ እየጨፈረ መዝፈን ጀመረ፡፡ ክብ ሰርቶ የሚጨፍረው የሰው መንጋ ዘፈን በግድግዳው ላይ የተጻፈው ዘፈን ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ የተከሰተው ነገር ዮናታንን ብቻ ሳይሆን ቤንጃሚን ፓተርሰንንም አደንዝዞታል፡፡ ፓተርሰን በስክል ኤንድ ቦንስ አባልነቱ ብዙ ጊዜ ያሳልፍ፣ በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ ይገኝ እንጂ በእንደዚህ አይነት ሰይጣናዊ ስብሰባዎች ላይ ሲገኝ የመጀመሪያው ጊዜ ነው፡፡ ወንዶች እርስ በእርሳቸው ወሲባዊ ተራክቦ መፈጸም ጀመሩ፡፡ ከቤተ-አምልኮው የጓሮ በር በኩል በግላዲዮ ማፍያ አባላት ከንድ እየታቀፉ የሚገቡት ጨቅላ ሀጻናት አቅላቸውን በሳቱ የስነ-ስርአቱ ተሳታፊዎች ተደፈሩ፡፡ በያዙት ስል ድንጋይ እየቆራረጡ ደማቸውን የሚጠጡም ነበሩበት፡፡ አካባቢው የምድር ሲኦል ሆነ፡፡ ፓተርሰን እና ዮናታን በፍርሃት ተንቀጥቅጠው የሚገቡበት ስፍራ ቢጠፋቸውም ከቁብ ቆጥሮ የተመለከታቸው አልነበረም፡፡ ስነስርአቱ እስከ አስራ አንድ ሰአት ድረስ ቀጠለ፡፡ የፕሮግራሙ ማሳረጊያ በፕሮግራሙ መጀመሪያ ላይ የተዘፈነው ዘፈን ነበር፡፡

አስተዳዳሪው እጃቸውን ከፍ ሲያደርጉ ጸጥታ በመስፈኑ እንዲህ አሉ፡-

"በሉሲፈር ስም ለተከናወነው ሰነስርአት ሉሲፈር ይመስግን!" አባላቱ ተቀበሏቸው "አሜን!"

የግልዲዮ ማፍያ አባላት የሀጻናቱን እራሳ በጓሮ በር በኩል ማውጣትና ክፍሉን ማጽዳት ጀመሩ፡፡ ዮናታን እና ፓተርሰን ወደ መኝታቸው ቢያመሩም እንቅልፍ በአይናቸው ሳይዞር ነጋ፡፡ ለግንዘብ፣ ለስልጣን እና ለምድራዊ ክብር ከፍተኛ ፍላጎትና ፍትር ያለው ዮናታን ከስክል ኤንድ ቦንስ አባልነቱ ለማፈግፈግ የሚያስገድድ ፍላጎት በውስጡ አልተፈጠረም፡፡ የሚሆነውን ሁሉ በጸጋ እየተቀበለ ኢትዮጵያዊ ባህል እና ወጉን እንዲሁም እምነቱን ሸሮ የእድሜ ልክ አገልጋያቸው ለመሆን ዝግጁ ነውና፡፡

- 11 -

ኢሊኖይስ፣ አሜሪካ

አለታዋ አሌክሳንደር ሱልዝበርገር የሶስና የሰራ ፍላጎት መቀዛቀዝ አሳሰቦታል። የጤና ችግር አልነበረባትም። የሰራ ፍላጎቷን ያቀዘቀዘው፣ ሰሜቷን የሰረቀው ሌላ ነገር ነው። ከነኢሰ ቱሊን ጋር ተግናኝታ የምስጢር ማህበራቱን ሴራ የምታጋልጥበት አለት ናፍቋታል። ሀገሯን ሊያፈራርሱ፣ እምነቷን ሊሸረሽሩ ታጥቀው የተነሱ ሃይሎችን የምትዋጋበት አለት አልደርስ ብሏታል። ነፍሱን ይማረውና አባቷ ሁልጊዜ ሰለሃገሯ ይነግራት ነበር። የአባቷን አባባል ዛሬም ቃል በቃል ታስታውሰዋለች።

"ሶሲ አሜሪካ ውስጥ ተወልደሽ ብታድጊም፣ ተምረሽ ለቁም ነገር ብትበቂም፣ የድሎት ኑሮ ብትኖሪም ሀገርሽ፣ መሰረትሽ እና የእውነተኛ ማንነትሽ መገለጫ በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ላይ የምትገኝ ድሃ ሃገር ናት፣ ኢትዮጵያ የሚሏት። ታሪክሽን ጠንቅቀሽ ማወቅ ይኖርብሻል። <ታሪኩን የማያውቅና ስር የሌለው ዛፍ አንድ ነው> የሚለውን የማርከስ ጋርቬይ አባባል ዘወትር አስታውሺ። እድሜ የዜጎቻቸውን ህይወት ከውሾቻቸው ህይወት አሳንሰው ይመለከቱ ለነበሩ ንጉሶቻችን፣ እድሜ በውይይት ሳይሆን በጠብመንጃ አፈሙዝ ህዝብን ማስተዳደር ይቻላል ብለው ያምኑ ለነበሩ አምባገነን ገዢዎቻችን፣ እድሜ በዘረፋ፣ በአድሎ እና በዘረኝነት ለተጨማለቁት መሪዎቻችን በስደት የምንኖር ዜጎች አልነበርንም። ድንግል ሀብታችን እንኳን ለእኛ ለሌሎችም ይተርፍ ነበር። ግና በርሃብ እያለቅን እልቂታችን ግድ ሳይሰጣቸው ለውሾቻቸው ህውልት ባሰሩ ግፈኛ ንጉሶቻችን፣ ነጻነት ስንጠይቅ የጥይት አረር በሰጡን አምባገነኖቻችን፣ የሃገራችንን ሃብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እኩል እንጠቀም ባልን በርሃብ እና በችጋር አለንጋ

በገረፉን መሪዎቻችን ምሬት የባእድ ሀገር እንግዳ ለመሆን ተገደናል። እውቀታችንንም፣ ጉልበታችንንም ለሰው ሀገር እየገበርን እንድንኖር ተፈርዶብናል። ያም ሆኖ ልጄ ሺህ ጊዜ የሰው ሀገር ቢደላሽ ያንቺ አይደለምና ምስኪኗ ሀገርሽን፣ ምስኪኗ እናትሽን እንዳትረሺያት። ለዚህም ነው ከልጅነትሽ ጀምሮ ቋንቋዋን፣ ባህሏን፣ ታሪኳን....እንድታውቂ ጥረት ሳደርግ የኖርኩት።

"እናት ደኸየች፣ አጣች፣ ነጣች፣ ተጎሳቆለች ተብላ ትተዋለች? አትተውም! ስለዚህ ሁሌም እውነተኛ ሀገርሽን፣ እውነተኛ እናትሽን አስታውሻት። ያንቺ መገኛ የመጀመሪያዋ የሰው ልጅች መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ ናት። በሰው ሀገር ኑሮሽን ብታመቻቺም፣ ሀገር ያለሽ መሆኑን፣ ወገን ያለሽ መሆኑን አትርሺ።" የአባቷ ንግግር እና ምክር ባሳደረባት ተጽእኖ "እኔም ሀገር አለኝ" የሚለውን የአስቴር አወቀን ዘፈን ከልቧ ትወደዋለች።

ከኢሰቱሊን ጋር የምትግናኝበትን መንገድ አሰላሰለች። በትእግስት የምትጠብቅ እስከ መቼ ይሆን? ቢሮዋ ሆኖ የሆነችውን ነገር ለማወቅ ሲነዘንዛት የነበረው አሌክሳንደር ፍንጭ ሲያጣ ወደቢሮው ተመለሰ። የቢሮዋ ስልክ በድጋሚ ጮኸ። ዮናታን ወልዴ ነበር።

"ሶስና እንዴት ነሽ? ዮናታን ነኝ። የቶሮንቶ ቆይታሽ አስደሳችና ፍሬያማ እንደነበር እገምታለሁ። ያስተላለፍሽውን ፕሮግራም ተመልክቼዋለሁ። እጅግ ውጤታማ ነበር። አብረሽን ለመስራት ፍቃደኛ በመሆንሽ እናመሰግንሻለን። ለወደፊትም የተሻለ ሰራ እንደምትሰሪ እምነታችን ነው። ሃሪማን ፓሌይም በስራሽ እንደተደሰተ እንድነግርሽ ነግሮኛል"

"አመሰግናለሁ" አለችው በተሰላቸ፣ ነገር ግን እንደተሰላቸ በማያስታውቅ የድምጽ ቃና።

"ኖ-ኖ.....ሶስና ውጤታማ ስራ ስለሰራሽልን ማመስገን የሚኖር ብንማ እኛ ነን። ኢትዮጵያ ውስጥ ያሰብነውን እንቅስቃሴ በተሳካ ሁኔታ ግብ ልታደርሽልን እንደምትችይ ስራሽ አሳይቶናል። በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ነገውኑ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ መምጣት

ይናርብሻል። አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ የሚጠብቅሽን ሰውም አዘጋጅተንልሻል"

ስልኩ ተዘጋ።

"ደግሞ ሌላ ፈተና?" አለች ብስጭት ብላ። በጉዳዩ ላይ የራሷን አስተያየት ሳትሰነዝር ስልኩ በመዘጋቱ ተናዳለች። የሚያውሉላት አለቆቿ ሁሉ ያው ናቸው። የተመሳሳይ ችግር ባለቤቶች። ሃሳቧንና አስተያየቷን ሳይጠይቁየራሳቸውን ፍላጎትና ሃላፊ ብቻ ማስተላለፍ የሚፈልጉ እንደመጥ ባዮች።

ስልኳ ዳግም አንቃጨለ። አሌክሳንደር ነበር።

"በነገው አለት ወደዋሽንግተን ዲሲ ትበሪያለሽ። ከነዮናታን ወልዴ ጋር የምትወያይው ነገር ይኖራል"

"አውቄያለሁ። ዮናታን ደውሎልኝ ነበር"

"ነይና የአውሮፕላን ትኬትሽንና መሰል ዶክመንቶችሽን ውሰጂ"

ጊዜ አላጠፉችም። ሄደች። ትኬቷንና ቀሪ ዶክመንቶቿን እየሰጣት፣ "በሮናልድ ሬጋን ብሄራዊ አየር ማረፊያ የሚጠብቅሽ ሰው ተመድቦልሻል። በረራው ከጠዋቱ 3:00 ሰአት ላይ ነው" አላት።

በእሺታ እራሷን ነቀነቀችለት። "መልካም መንገድ" አለና አሰናበታት። ለጉዞ መሰናዶወደቤት እየሄደች እንደሆነ ነገረችው። ቢሮዋ መቆየት አልፈለገችም። በድጋሚ "መልካም መንገድ" አላት። ቤቷ ደርሳ ትንሽ መተኛት ፈልጋ ነበር። አልቻለችም። በሃሳብ ስትዋትት ቆይታ ሰለሞን ሲመጣ መጠነኛ መረጋጋት አገኘች።

"ሃኒ፣ በነገው አለት ለስራ ጉዳይ ወደ ዋሽንግተን እንድሄድ ትእዛዝ ደርሶኛል" አለችው በስስት እየተመለከተችው። ምንም አልመሰለውም። የለመደው ነው። በተረበሸ ስሜት ውስጥ ሆና ወደአልጋዋ አመራች።

እንደ ምንም ነጋላት፡፡ መኪናዋን በድ ትታ ልጇን በታክሲ ትምህርት ቤት አደረሰችና ወደ አውሮፕላን ማረፊያው አመራች፡፡ አስር ደቂቃ ቀድማ ደረሰች፡፡ ከአንድ ሰአት በኋላ ሮናልድ ሬጋን ብሄራዊ አየር ማረፊያ ትደርሳለች፡፡ አስከዚያው የኒክ ብራያንትን "ዘ ፍራንክሊን ስካንዳል" መጽሃፍ በተመስጦ ማንበብ ቀጠለች፡፡ አንድ ሰአት ከአስራ ዘጠኝ ደቂቃ የተጓዘው አውሮፕላን ከማረፊያው ሲደርስ መጽሃፉን አጥፋና ሻንጣዋን አንጠልጥላ ወረደች፡፡

ሰሚ የተጻፈበትን ወረቀት ከፍ አድርጎ ይዞ መንገደኞች ላይ አይናቹን የሚያቅበዘብዘውን ሰው በፈገግታ ቀረበችው፡፡ ጥቁር ወጣት ነው፡፡ አማርኛ ለመናገር በቸገረው እንደበት "ሚስ ሶሲና አሌማዮሁ?" አላት ለፈገግታዋ አጸፌታውን እየመለሰ፡፡ በአምንታ ራቧን ነቀነቀችለት፡፡ "ፒተር ዋሽንግተን እባላለሁ፡፡ ጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ እንዳደርስሽ የተመደብኩ ሾፌር ነኝ፡፡ እባክሽን ተከተይኝ?" ያንጠለጠለችውን እነስተኛ ሻንጣ ተቀብሎ ወዳቆማት መኪና መራት፡፡ ጥቁር ቮልቮ መኪና ውስጥ ገብተው ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ ታዋቂ ሆቴል ወይም ደግሞ ግዙፍ ቢሮ ውስጥ የሚጠብቋት መስሏት ነበር፡፡ ወደ ጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ የምታመራበት ምክንያት ግልጽ አልሆነላትም፡፡

"ወደ ሆቴል የምንሄድ መስሎኝ ነበር?" አለችው ጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ የተቀጠረችበትን ምክንያት ቢነግራት ብላ፡፡

"ለጊዜው እንድወሰድሽ የታዘዝኩት ወደ ዩኒቨርሲቲው ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የሚዲያ ሃላፊውን ሃሪማን ፓሌይን ጨምሮ በዩኒቨርሲቲው የታሪክ ፕሮፌሰር የሆኑት ቤንጃሚን ኪዩግሌይ እና ሌሎች ታዋቂ ሰዎችም ይጠብቁሻል"

የመሃል ከተማውን መንገድ ተጠቅመው ወደ ዩኒቨርሲቲው አመሩ፡፡ እግረ-መንገዷን ሊንከንን መታሰቢያ፣ ነጩን ቤተመንግስት (Capitol)፣ ከኋይት ሀውስ በስተደቡብ የሚገኘውን የዋሽንግተንን ሃውልትና የጀፈርሰንን ምስል እንዲሁም ሌሎችንም ታሪካዊ ቦታዎች ተመለከተች፡፡ ትኩረቷን የሳበው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የተሰዉ የኮርያና የቬትናም ዘማቾች መታሰቢያ ሀውልት ነበር፡፡ በእድሜ ጠና ላለች ሴት አስረከቧት ሄደ፡፡

"ሃይ ሚስ ሶስና፣፣ ሂላሪ ማልተን እባላለሁ፣፣ በዩኒቨርሰቲው ውስጥ የፍልስፍና፣ የታሪክ እና የሳይንስ ትምህርት መምህርት ነኝ፣፣ እባክሽን ተከተይኝ?"

ሶስና ያረጀ ጉጉት የምትመስለዋን ሂላሪ ማልተንን ተከትላ ወደአዳራሹ አመራች፣፣ አምስት ሰዎች ብቻ ነበሩ፣፣ ከተቀመጡበት ተነስተው ተዋወቋት፣፣

"ዮናታን ወልዴ የስክል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር አባልና ተወካይ"

"የሰው ሰይጣን አንተንማ እስከሞት ድረስ አስታውስሃለሁ" አለች በውስጧ የሃሰት ፈገግታ እያሳየችውና እጇን ለሰላምታ እየዘረጋችለት፣፣ ሌሎቹም ቀጠሉ፣፣ ሮበርት አዳምስ የኤቢሲ ቴሌቭዥን ጣቢያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ሃሪማን ፓሌይ የሲቢኤስ ቴሌቭዥን ጣቢያ የሚዲያ ሃላፊ፣፣ ይህን ሰው በአካል ለመጀመሪያ ጊዜ ትየው እንጂ ድምጹን በስልክ ሰምታዋለች፣፣ ዮናታን ወልዴን እንደእንዝርት የሚያሾረው ይሄ ሰው ነው ማለት ነው፣፣ ዮናታንን ብቻ ሳይሆን አሌክሳንደር ሱልዝበርገርንም የሚያዘው ይህ ሰው እንደሆነ ታውቃለች፣፣ ቤንጃሚን ኪዩግሌይ በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ፕሮፌሰር፣ ኮናብልስ ውድስ የኒውዮርክ ሪዘርቭ ባንክ ፕሬዚዳንት አንቶኒኤም. ሶሎሞን ተወካይ፣፣ ጉጉት መሳይዋ አሮጊት ሚስ ሂላሪ ማልተን ቀደም ብላ እራሷን አስተዋውቃለች፣፣

እሷን ጨምሮ በአዳራሹ ውስጥ የተገኙት ተሰብሳቢዎች ቁጥር ሰባት ደረሰ፣፣ የክብ ጠረጴዛውን ስብሰባ ሮበርት አዳምስ ከፈተው፣፣ "እራሴን በድጋሚ ለማስተዋወቅ ያህል ሮበርት አዳምስ እባላለሁ፣፣ የኤቢሲ ቴሌቭዥን ጣቢያ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልና የጄ.ፒ. ሞርጋን፣ የሚትሮፖሊታን ላይፍ እንዲሁም የሞርጋን ጋራንቲ ትረስት ዳይሬክተር ነኝ፣፣ የዛሬው ስብሰባችን ዋና ምክንያት ሚዲያዎቻችንና የሚዲያዎቻችንን አላማ ከእኛ ጋር በጋራ ለመስራት ለተስማማችው ሶስና አለማየሁ ማሳወቅ ነው" አለና በዝርዝር ስለሚዲያዎቻቸው፣ ስለአላማቸውና በኢትዮጵያ ውስጥ

ሊያደርጉት ሰላሰቡት እንቅሰቃሴ በሰፈው ማብራሪያ ሰጠ፡፡ ንግግሩን ከማብቃቱ በፊት እንዲህ አላት፡-

"ማንነታችንንና አላማችንን በሚገባ የተገነዘብሽ ይመስለኛል፡፡ ከማጠቃለሌ በፊት ግን ዓላማችንን በአጭር ቃል የሚገልጸውን የቀድሞውን የሲቢኤስ ኒውስ ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ሳላንት አነጋገር ልጠቀም፡፡ <ተግባራችን ሰምች የሚፈልጉትን ሳይሆን እኛ እንዲያ ውቂትና እንዲገነዘቡት የወሰንላቸውን መረጃ መሰጠት ነው፡፡>"

የንግግር መድረኩን የታሪክ ፕሮፌሰሩ ኪዮግሌይ ተረከቡ፡፡ ጉሮሯቸውን ከሞረዱ በኋላ፡-

"ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን መላውን አለም ልናስተዳድርበት የምንፈልገው የአዲስ ዓለም ህግና ስርአት በአንድ ጀምበር ተግባራዊ ይሆናል ብለን የምናስበው አይደለም፡፡ በአዝጋሚ ለውጥ እውን እንደሚሆን ስላመንን ነው በአውሮፓ ውህደት እና መሰል ተሞክሮዎች ወደፊት እየገፋን ያለው፡፡ በ1948 ዓ.ም ሂይግ ላይ ተካሂዶ የነበረውን ጉባኤ ካስታወስን ለአባባላችን አይነተኛ ማስረጃ ይሆነናል፡፡ የ1948ቱ የሂግ ጉባኤ አይነተኛ አላማ ምን ነበር? አንድ የሆነች አውሮፓን መፍጠር ነበር፡፡ ይህ ጅማሬ ወደፊት ለምንፈጥራት አንድ አለም ጥርጊያ መንገድ እናምናለን፡፡ በወቅቱ ተካሂዶ በነበረው ጉባኤ ላይ ከጸደቁት ሰባት የውሳኔ ሃሳቦች መሀል ሰባተኛው አሁን እየተጋገርንበት ያለውን የአዲስ አለም ስርአት ይወክላል ብዬ አምናለሁ፡፡ ሰባተኛው የውሳኔ ሃሳብ 'እንድ የሆነች ዓለም መመስረት' የሚል ነበር፡፡ የምናስባትን አይነት ዓለም ለመፍጠር ብዙ መሰዋእትነትን መክፈልና ህዝብን የማሳመን ስራ መሰራት ይኖርብናል፡፡ የኢትዮጵያን ህዝብ የማሳመኑን ስራ ለመስራት ከጎናችን ስለተሰለፍሽ እናመሰግንሻለን፡፡ በነገራችን ላይ ሶስና እኛ ወደድንም ጠላንም የአንድ አለም አስተዳደር ስርአት መመስረቱ አይቀርም፡፡ ዋናው ጥያቄ ይህን ወጥ የሆነ የአንድ አለም አስተዳደር ስርአት በፍቃደኝነት ወይንስ በአስገዳጅ ሁኔታ እንመስርት የሚል ነው"

ትኩር ብለው ተመለከቷት፡፡ የመጨረሻው፣ በፍቃደኝነት ወይንስ በአስገዳጅነት እንመስርተው? የሚለው ሃሳብ የፕሮፌሰሩ

እንዳልሆነ አውቃለች፡፡ የአሜሪካ የምክር ቤት አባል የነበረው የጀምስ ዋርበርግ እንደሆነ እንብባለች፡፡ ሃሳቡ የማንም ይሁን የማን ሰዎቹ ከበፊት ጀምሮ የእንድ አለም አስተዳደርን ለማስፈን ጽኑ ፍላጎት እንዳላቸው የሚያመለክት ነው፡፡

ሃሪማን ፓሌይ በተራው በቶሎ ወደ ኢትዮጵያ ሂዳ ከምታገኛቸው ሰዎች ጋር ጥናት እንድታካሂድና ውጤቱን እንድታሳውቅ ነገራት፡፡ ዮናታን ደግሞ ሪፖርቱን በየጊዜው እንድትልክለት አሳሰባት፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰአት ላይ በዋሽንግተን ፕላዛ ሆቴል የመሸኛ የእራት ግብዣ እንደሚኖር ተነግሯት ሰብሰባው ተበተነ፡፡

ለእሷ ተብሎ በተዘጋጀ የእራት ግብዣ ላይ ያለመገኘት የማይታሰብ ነው፡፡ ወደ ቤቷ ተመልሳ ከልጇ ጋር ማደር ፈልጋ ነበር፡፡ አልቻለችም፡፡ ለፒተር ዋሽንግተን ደወለችለትና ከተማውን መጎብኘት ጀመረች፡፡ በቅድሚያ ያስጎበኛት የአሜሪካ የሰነ ምህንድስና ኢኒስቲቲዩት እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም የአሜሪካ ምርጥ አስር የሰነ-ህንጻ ውጤቶች ብሎ ደረጃ ከሰጣቸው መካከል ስድስቱን ነው፡፡ ጓይት ሀውስን፣ የዋሽንግተንን ብሄራዊ ታላቅ ደብር፣ የቶማስ ጀፈርሰንን መታሰቢያ፣ ነጩን ቤተመንግስት፣ የሊንከንን መታሰቢያ እና የቬትናም ዘማቾችን መታሰቢያ፡፡ የተወሰኑትን ወደ ዩኒቨርሲቲው በመምጣት ላይ ሳለች የተመለከተቻቸው ቢሆንም ዳግም ስለጎበኘቻቸው ደስ ብሏታል፡፡ አንዳንዶቹ በቅርብ ርቀት የተመለከተቻቸው ናቸው፡፡

ይህች ከተማ ከአስራ አራት ሃገራት እህት ከተሞች ጋር በተለያዩ ዘርፎች ስምምነት መፈራረሟን ነገራት፡፡ ከአስራ አራቱ እህት ከተሞች መሃል አንደኛዋ የኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ እንደሆነችም አልደበቃትም፡፡

"ሌሎቹስ እህት ከተሞች?" አለችው እውነተኛ አስጎብኚነቱን በልቧ እያደነቀች፡፡

"ባንኮክ፣ ዳካር፣ ቤጂንግ፣ ብራስልስ፣ አቴንስ፣ ፓሪስ፣ ፕራቶሪያ፣ ሴኡል፣ አክራ፣ ሰንደርላንድ፣ ሮም፣ አንካራ እና ብራሲሊያ ናቸው ሲል ዘረዘረላት፡፡ አብራው እያሳለፈች ያለውን ጊዜ ወደደችው፡፡

ባለብሩህ አእምሮው ፒተር ዋሽንግተን ዲሲን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃዎችን ነግራት፡፡ "የዋሽንግተን ዲሲ ህዝብ ቁጥር ከሰድስት መቶ ሺህ በላይ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ከተማዋ ከአሜሪካ ከተሞች በህዝብ ቁጥር ብዛት የሃያሰባተኝነትን ደረጃ የያዘች ሲሆን ታዋቂ የሆኑ ሃውልቶችና ሙዚየሞች ይገኙባታል፡፡ አንድ መቶ ሰባ ስድስት ያህል የውጭ ሃገራት ኤምባሲዎችንና የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ዋና መስሪያ ቤቶችን የያዘችው ዲሲ በዩናይትድ ስቴትስ ምስራቃዊ ዳርቻ የመካከለኛው አትላንቲክ ግዛት የምትገኝ ከተማ ነች፡፡ አጠቃላይ የቆዳ ስፋቷ ሰልሳሰምንት ነጥብ ሶስት ስኩዌር ማይልስ (177 ኪሎሜትር ስኩዌርድ) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ሰድስት ነጥብ ዘጠኝ ስኩዌር ማይልሱ (18 ስኩዌርድ) በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡"

ከምሳ በኋላም ያልጎበኟቸውን ቦታዎች ጎበኙ፡፡ ምሳ የበሉበትና የምሽት ፕሮግራሙ የተዘጋጀበት ሆቴል በእነሱ አቆጣጠር በ1962 ዓ.ም እንደተሰራና የሰራውም ዓለም አቀፍ እውቅናን የተጎናጸፈው የስነ ምህንድስና ባለሙያ ሞሪስ ላፒደስ እንደሆነም ነግሯታል፡፡ ደስ የሚል ጊዜ በማሳለፍ የፕሮግራሙ ሰአት እስከሚደርስ አብረው ቆዩ፡፡ የፒተር በሽኝት ፕሮግራሙ ላይ መገኘት ደስታዋን እጥፍ ድርብ አደረገው፡፡ ደመቅ ያለ ግብግ ነበር፡፡ ጠዋት በስብሰባው ላይ ያገኘቻቸው ሁሉም ነበሩ፡፡ በግብግቡ መጠናቀቂያ ላይ በጎ ምኞታቸውን ተመኝተው ተሰናበቷት፡፡ ጎኗ አልጋ እንደነካ እንቅልፍ ወሰዳት፡፡

ጠዋት ስትነሳ 1፡30 ሆኖ ነበር፡፡ የቀኑ ድካም ሊሆን እንደሚችል ገምታለች፡፡ ዲሲን ተሰናብታ ወደ ኢሊኖይስ በረረች፡፡

- 12 -

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ቄስ በቹ ከሁሉም በላይ እጅግ የሚታወቅበት ባህሪው ሴት ወዳድነቱ ነው። በቅርብ የሚያውቁት በርካታ የሃብታም ሚስቶች ውሽሞቹ እንደሆኑ ይናገራሉ። ጸበል ደርሳ የምትመለስን ሴት ከጸበል መልስ ቤቴ ጎራ በይና ጸበል ጸዲቅ ቅመሽ በሚለው ብዙዎች እውነታውን ስለሚያውቁት በሚገረሙበት ብሎም በሚስቁበት አባባሉም ይታወቃል። የእሱ ጸበል ጸዲቅ፣ እሱና ውሽሞቹ እንዲሁም የቅርብ ምስጢር አዋቂዎች ብቻ ናቸው የሚያውቁት። አሉባልታ ይሁን እውነት አልተረጋገጠም እንጂ ውሽሞቹ ሁሉ ቄስ በቹ ሲናፍቃቸው የሚዘምሩት የጋራ መዝሙር አላቸው አሉ። እንዲህ የሚል፦

ግድግዳ አስደግፎ አለም የሚያሳየኝ
ድግምታሙ ጠቢብ ቄስ በቹ ናፈቀኝ

ጥንዶቹ ሃጊ እና ጁዲ ሜናሂም አብሯቸው እንዲሰራ የተመደበው መልከመልካም ኢትዮጵያዊ ቄስ አብሯቸው መንቀሳቀስ ይጀምር እንጂ ከሮበርት አዳምስ ጋር እንዴት እና በማን በኩል እንደተገናኘ አልተነገራቸውም። አስፈላጊአልነበረም። ቄሱ በሮበርት አዳምስ በኩል እንደተመደበ ነግሯቸዋል። ከዚያ ወዲያ ያለውን ምስጢር ነው ብሏቸዋል። አትናገር ተብያለሁ ነው መልእክቱ። የምስጢር ማህበራቱ አንደኛው መገለጫ ባህሪ ይሄ አይደል? ለአባሎቻቸውና ለተከታዮቻቸው እንዲሁም ሰራተኞቻቸው መነገር ያለበት ነው ብለው ያመኑበትን ብቻ መንገር። ሌላውን መደበቅ። ሁሉን ያለመናገር ለጥንቃቄና ምስጢርን ለመደበቅ መፍትሄ ነው ብለው ያምናሉ።

ኢትዮጵያ መመላለስን እንደ መደበኛ ስራ ለቆጠሩት ጥንዶች ዋናው ነገር ተነጋግሮ መስራቱ ነበርና የቄስ በቹ ከሮበርት አዳምስ

ጋር እንዴት እና በማን በኩል መገናኘት ብዙም አላሳሰባቸውም፡፡ በቤተክርስትያናት አካባቢ ላሉ ሰዎች ትርብ መሆኑና በእሱ በኩል ሂዮንሴ ኖውልስን መሰል የሰው ሰይጣኖች አሰርጎ ለማስገባት እና ከሃይማኖት አባቶች ጋር በቀላሉ ለማገናኘት እንደሚያስችል በማመናቸው ስራቸው ቀለሞላቸዋል፡፡ በዚህም ተደስተዋል፡፡ በሃገ በኩል ትንሽም ቢሆን ችግር የፈጠረው ቄሱ፣ ሚስቱን ጆዲን ባየበት ጊዜ ሁሉ ብልቱ እንደፍየል ቀንድ የመቆመና የመቅበጥበጡ ነገር ነው፡፡ ደጋግሞ ታገበታል፡፡ መጨረሻ የተገናኙ ቀንማ ሱሪው ላይ ፈላሽ ነገር ለማየቱ እርግጠኛ ነው፡፡ በወቅቱ ስሜቱን መቆጣጠር የማይችል ሴሰኛ አጋሰስ ብሎ ሰድቦታል - በቋንቋው፡፡ "በሃገርና በሚስት እንዲሁም በእናት ቀልድ የለም፡፡ መሸኛውን ቆርጨስት በላስቲክ ቱቦ ባላሸናው እኔ ሃጊ አይደለሁም" ሲልም በልቡ ዝቶበታል፡፡ ቄስ በቹ በሃይማኖቱ ውስጥ ሰርጎ ለመግባት የሚያስችል ጥሩ የጥቅም ቱቦ ሆኖ በመገኘቱ ነበር በአንድሪው ግርሃም አማካይነት ከሮበርት አዳምስ ጋር እንዲተዋወቅ የተደረገውና ጥንዶቹ ዘንድ እንዲመደብ የተደረገው፡፡ የስነመለኮት ትምህርቱን በእስራኤል እና በአሜሪካ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በእስራኤል እና በአሜሪካ መንግስት ወጪ መከታተሉንም የሚያውቁት እጅግ የቅርብ የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ትምህርቱን እንደጨረሰ ወደሃገሩ በመምጣት ሁነኛ ስፍራ ተመደበ፡፡ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ከመስጠት ይልቅ ሴት ማሳደዱን፣ ማጭበርበሩን እና አየር በአየር መነገዱን ተካነበት፡፡ በድርጊቱ እርር ያሉ ለሚመለከተው አካል አንድ በሉትየሚል ስሞታ ቢያሰሙም የሰማቸው አልነበረም፡፡ ጭራሽ በሰልጣን ላይ ስልጣን እንደጃኖ እየተደረበለት ዘለቀ፡፡ ይባስ ብሎም ከውጭ ሀገር ሃያላን ጋር ለመስራት ታጨ፡፡ ለሮበርት አዳምስ የጠቆመው እንድሪው ግርሃም የቄስ በቹን የዩኒቨርሲቲ ቆይታና ባህሪ ያስታውሰዋል፡፡

ጥቅመኛ፣ መሰሪ፣ ተለዋዋጭ፣ ፍጥነቱ ከሰይጣን የሚቀድም፣ አንደበተ ርቱእ ቢሆንም ብዙ ጊዜ ገምታ የሚያዘወትር፣ አስማታዊ አይናቹ በሴቶች ላይ የሚንከራተቱ፣ ብሩህ ጭንቅላቱን ለመጥፎ ተግባር የሚያውል፡፡ ሮበርት አዳምስም እንዲህ አይነቱን ሰው ነበር የሚፈልገው፡፡

- 13 -

ኢሊኖይስ፣ አሜሪካ

ጊዜ የላትም፡፡ መመሪያ ለመስጠት እና አላማቸውን እንድትገ ነዘብ ለማድረግ ዋሽንግተን ድረስ ያስጠሯት የበላዮቿ ውላ ሳታድር ወደ ኢትዮጵያ ሂዳ ጥንዶቹን አይሁዳውያን እንድታገኝ እና አጠቃላይ ጥናት እንድታካሂድ አዘዋታል፡፡ ለዚህም የሚረዷትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተውላታል፡፡ የምታርፍበት ሆቴል፣ ጥናት የምታካሂድበት ትምህርት ቤት፣ በቆይታዋ ወቅት ትራንስፖርትን ጨምሮ የሚያስፈልጋት ወጪ....ሁሉም ነገር ዝግጁ ነው፡፡ ለነገሩ ከሰባት አመታት በላይ በሲቢኤስ የቴሌቭዥን ጣቢያ ያገለገሉት እና ከበቂ በላይ ልምድ ያላቸው ጥንዶች አጠገቧ አሉ፡፡ ሃሪማን ፓሌይ ጥንዶቹን ወደኢትዮጵያ የላከበትን ምክንያት ለመገመት ሞከረች፡፡ አንድም ከበቂ በላይ የሆነውን ልምዳቸውን ፈልጎት፣ ሁለትም በምትልክለት ሪፖርት ላይ እርግጠኛ ለመሆንና ለሃገሯና ለወገኗ አድልታ ውጤቱን በተቃራኒ አቅጣጫ እንዳታስኬደው አጠገቧ ተቆጣጣሪ ለማድረግ እንደሆነ ገመተችና "ውሻ!" ስትል በውስጧ ተሳደበች፡፡ ለፍርፋሪ ሲል ህሊናውን ሽጦ ወገኖቹን የሚከዳ እና በበላበት የሚጮህ ውሻ ብቻ ነው፡፡ እንደውም ውሻ ታማኝነቱ ያይላል፡፡ ይሄ ግን.....እነሃጊ እግረመንገዳቸውን የተመደቡባት ተቆጣጣሪዎች መሆናቸውን ጠርጥራለች፡፡

ወደ ኢትዮጵያ.....ወደ ወላጆቿ ሀገር.....አባቷ ደጋግሞ ያነሳላት ወደነበረችዋ ምድር እንድትሄድ የተቆረጠላት ቀን ከነገ-ወዲያ ነው፡፡ አስቀድሞ ፎቶዋ በሃሪማን ፓሌይ አማካይነት የተላከላቸው ጥንዶች ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተገኝተው እንደሚቀበሏትና ወደተያዘላት ሆቴል እንደሚወስዷት በሽኝት ግብግቡ ላይ ተነግሯታል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ

እንደምትቆይ አላወቀችም፡፡ ፓሊይን ጠይቃው ነበር፡፡ "አሁን እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም፡፡ የምትመለሺበትን ቀን የሚወስነው የምትልኪው የጥናት ሪፖርት ነው፡፡ የጥናት ሪፖርቱ ውጤት ለጊዜው በቂ ነው ብለን ባመንበት ሰአት እንድትመለሺ እናደርጋለን" ነበር ያላት፡፡ የጥናት ሪፖርቱ ውጤት በቂ ነው ካልተባለ ልትቆይ ምናልባትም ልትከርም ነው ማለት ነው፡፡ ልጇስ? በሰው ሀገር ካለእሷ ማንም የሌለው ሰለሞንስ? ተጨነቀች፡፡ ተጨንቃ የምታመጣው ለውጥ እንደሌለ አልጠፋትም፡፡ ጥናቱ በእስቸኳይ ተጠናቆ በፍጥነት ወደልጇ ትመለስ ዘንድ ፈጣሪ እንዲረዳት ተማጸነች፡፡

በነጋታው ሁሉንም ነገር ለልጇ ሰለሞን አስረዳችው፡፡ "ታዲያ ምን ችግር አለ ማም? እንዲያውም ሁሌም የምታነሺያትን እና ልታያት የምትጓጊላትን ሀገር ለማየት እድሉ ስለተመቻቸልሽ ልትደሰቺ ይገባል" አላት፡፡

"ልክ ነህ ሃኒ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ መሄዴ አይደለም ስጋት ላይ የጣለኝ፡፡ ለምን ያህል ጊዜ እንደምቆይ ያለማወቄ እንጂ"

የስጋቷ ምክንያት ተገለጸለት፡፡ እናቱ የተጨነቀችውና የተጠበበችው በእሱ ምክንያት ነው፡፡ ብቻውን ይሆንብኛል የሚለውን ፍርሃት የወለደው ጭንቀቷ ሰላም እንደነሳት አወቀ፡፡

"ማም፣ ለእኔ አትጨነቂ፡፡ ምንም አልሆንም"

ኢትዮጵያ የምትሄደው ከምትሰራበት ቴሌቭዥን ጣቢያ ስራ ጋር በተያያዘ ምክንያት እንደሆነ ስለነገረችው አምኖ ተቀብሏታል፡፡ የሚልኳት ከዚህ ቀደም እሱን ያገቱት እና አብራቸው እንድትሰራ ያስገደዷት ሰዎች እንደሆኑ ነግራ ጭንቀት ልትለቅበት አልፈለገችም፡፡ ካገቷት ሰዎች ጋር በሃሳብ መስማማቷን አድበስብሳ ነግራዋለች፡፡ በሰለሞን እምነት እናቱ ወደ ኢትዮጵያ የምትሄደው PWSIL-TVን ስራ ለመስራት ነው፡፡

"ሃኒ ብቻህን ስትሆን የባይተዋርነት ስሜት አይሰማህም አይደል?" በስስት ተመለከተችው፡፡

"ነገርኩሽ እኮ!.....የስራሽን ባህሪ ሰለማውቀው ውሰጢን ከሳመንኩት ቆይቻለሁ፡፡ የፈለግሽውን ያህል ጊዜ ብትቆዪ ከናፍቆት በስተቀር የሚሰማኝ ነገር አይኖርም፡፡ ናፍቆቱን በተመለከተ ምን ማድረግ ይቻላል? እንጂራ ነው" የተልድ ፈገግታ አሳያት፡፡

"እወድሃለሁ" አለችና አቀፈችው፡፡ አጸፋውን መለሰላት፡፡ እቅፏ ውስጥ እንደያዘችው በሃሳብ ወደእሩቅ ሀገር ተጓዘች - ወደ ኢትዮጵያ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ሊገጥማት እንደሚችል እርግጠኛ ባትሆንም እስክታያት ቸኩላለች፡፡ አባቷን አስታወሰችው - ያውም እስከ ንግግሩ፡፡ *"እናት ደሽየሽ አጣች፣ ነጣች፣ ተጎሳቆለች ተብላ ትተዋለች? አትተውም! ሁሌም እውነተኛ ምስሊን እናትሽን አስታውሻት"* ያላትን አስታወሰች፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የመሄድ አጋጣሚ እንዳገኘሁ ቢያውቅ ምን ይሰማው ነበር? ሰትል አሰበች፡፡ በይበልጥ ለማወቅ የጓጓችው ግን የምትሄድበትን ምክንያት ካወቀ በኋላ ሊሰማው የሚችለውን ስሜት ነው፡፡ ያለጥርጥር ያዝንባታል፡፡ ማዘንም ብቻ አይደለም፤ ያፍርባታል፡፡ ሊረግማትም ይችል ይሆናል፡፡

"ግን እኮ ወድጄ አይደለም" አለች በውስጧ፡፡ "ወድጄ አይደለም፡፡ ተገድጄ ነው"

"ሃሳቤን እቀይራለሁ ብትይ የልጅሽን ሬሳ ትምህርት ቤቱ በር ጋ ተዘርግቶ ታገኚዋለሽ" ያሏትን አስታወሰችና ዘገነናት፡፡ ኢስቱሊንን አስታወሰችው፡፡ ነጻ የምትወጣበትን ቀን ናፈቀች፡፡ የስፔን ኑሮዋን ለማመቻቸት ቃል ገብቶላታል፡፡ እጠገቡ ሆና የምስጢር ማህበራቱን ሴራ እስክታጋልጥ ቸኮለች፡፡ ነጻ ህይወትን አንድ ብላ የምትጀምረው ያኔ ነው፡፡ እስከዚያው ግን በሽቦ ጎጆ ውስጥ የተቆለፈባት ወፍ ከመሆን አትድንም፡፡

- 14 -

ጣሊያን፣ ራንቬርሶ ቅዱስ አንቶኒ ገዳም

በP2 ሎጅ አባላት ሰይጣናዊ ስነስርአት ላይ ተገኝተው የሚዘገንን እውነት የተመለከቱት ዮናታን ወልዴ እና ቢንጃሚን ፓተርሰን ቁርስ ለመብላት ምግብ አዳራሹ ውስጥ ከነበሩት ጋር ሲቀላቀሉ በተመለከቱት ነገር ተገረሙ፡፡ ማታ እንደዚያ አቅሉን ስቶ ሲያብድ የነበረ ሁሉ ምንም እንዳልተፈጠረ "ወንድም" እየተባባለ ቁርሱን ለመመገብ ተዘጋጅቷል፡፡ በተመሳሳይ ደቂቃና ሰከንድ በዮናታን እና ፓተርሰን ጭንቅላት ውስጥ ተመሳሳይ ሃሳብ ተመላለሰ፡፡ "ይህች አለም ከብዙሃኑ የተደበቁ ስንት ጉዶችን በውስጧ ደብቃ ይዛለች? የምስጢር ማህበር አባላት ይሁኑ እንጂ እንዲህ አይነት ተግባር ይፈጸማል ብለው አስበው አያውቁም፡፡ የላይኛዎቹ፣ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ አባላት ብቻ የሚያውቁት "ጉድ" የተደበቃቸው ምናልባትም በጀማሪ ደረጃ ላይ ያሉ አባላት ስለሆኑ ይሆናል፡፡ ዛሬ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ የታሰበውን ተልእኮ ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል ከስነስርአቱ ልምድ ይቀስሙ ዘንድ በስፍራው መገኘታቸው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በቦታው ተገኝተው ስነስርአቱን ተከታትለዋል፡፡

ቁርስ እንደበሉ ወደመጡበት ለመመለስና የደብሩን አስተዳዳሪ ለመሰናበት ሲዘጋጁ የዮናታን አይኖች ከግላዲዮ ማፍያ አባላት መሃል በአንዱ ላይ ተተክለው ቀረ፡፡ የት እንደሆነ ጠፋው እንጂ የሆነ ስፍራ እንደሚያውቀው እርግጠኛ ነው፡፡ ለፍላፊውን ሪቬራን ጠራውና ቀስ ብሎ የሰውዬውን ማንነት ጠየቀው፡፡ ሪቬራ ተተረተረ፡-

"ጆቫኒ ፋንፋኒ ታላቪያ ይባላል፡፡ የግላዲዮ ማፍያ አባላት አለቃ ነው፡፡ በእሱ ፊት እንደፈለግሁ እሆናለሁ ማለት ፈጽሞ

የማይታሰብ ነው።። አባቱ ጣሊያናዊ ይሁን እንጂ እናቱ ኢትዮጵያዊት ናት።። ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አመታት ከቤተሰቦቹ ጋር ኖሯል።። ሶስት እህቶች አሉት።። ሚች አባቱ ጉልበቱ ሲደክም ቤተሰቦቹን ይዞ ወደ ቱሪን እንደመጣ ይነገራል።። ታላት ወንድሙ ሚካኤል ፋንፋኒ በመኪና ሽያጭ ንግድ ላይ ተሰማርቶ ሃብታም ቢሆንም ማፍያዎች ንብረቱን ለመዝረፍ ሲሉ....."

ዮናታን አልተሳሳተም አውቆታል።። እራሱ ነው።።

"አመሰግናለሁ ሪቬራ።። በቃ በቂ ማብራሪያ ሰጥተኸኛል" ሪቬራ አላቆመም።። ቀጠለ፦

"እህቶቹ ደጋግመው የግላዲዮ ማፍያ እልቅናህን ትተህና ቤተሰብ መስርተህ ከእኛ ጋር ኑር ቢሉትም አልሰማቸውም።። የታናሽ እህቱ ማሪያ ባል ሳልቫቶሬ ሮማኖም ለምን የእኔን የስጋ ማምረቻ ድርጅት በስራ አስኪያጅነት አትመራም ብሎት ነበር።። እሱ ግን....." ትእግስቱ ወደ መሟጠጡ የደረሰው ዮናታን፦

"በቃ አልኩህእኮ ሪቬራ።። ሰውዬውን የማውቀው ስለመሰለኝ ነው ማንነቱን የጠየቅሁህ።። አሁን ስላወቅሁት መረጃህ አያስፈልገኝም" ሪቬራ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ማብራራቱን ቀጠለ፦

"ልታውቀው ትችላለህ።። በአባቱ ጣሊያናዊ ቢሆንም በእናቱ ኢትዮጵያዊ ነው ብዬህ የለ? ኢትየጵያ ውስጥ እንደኖረም ነግሬሃለሁ....." ዮናታን ሪቬራን ባለበት ትቶት ወደጆቫኒ ፋንፋኒ አመራ - አብረው ያሳለፉትን የልጅነት ዘመን እንደማይዘነጋው እርግጠኛ በመሆን።።

ጆቫኒ እና ዮናታን ከቀሪ ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የማይረሱ ጊዜያትን አዲስ አበባ ውስጥ አሳልፈዋል - 1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ።። ኮልፌ መብራት ሃይል እየተባለ በሚጠራው ሰፈራቸው የማይረሱ የወጣትነት ጊዜያትን ሲያሳልፉ ጆቫኒ ፋንፋኒ የሚታወቅበት መለያው በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎችን ሳይቀር በላስቲክ እና በባላ ወንጭፍ በመታገዝ አነጣጥሮ የመምታትና የመጣል ጀብዱው ነው።። ጆቫኒ ለፊልም የነበረውንም ፍቅር

ዮናታን ያስታውሳል፡፡ ከሽማግሌ አባቱ ሳምንቱን ጠብቆ በሚቀበለው ገንዘብ ቅዳሜ ቅዳሜ ጓደኞቹን በሙሉ ሰብስቦ ሲኒማ አዲስ ከተማ የሚጋብዘው ጆቫኒ ፋንፋኒ ታላቪያ እንደነበረም ዮናታን አይረሳም፡፡ የሚያስታውሰው ይህንን ብቻ አልነበረም፡፡ የጆቫኒ ፋንፋኒ የሰፈር ስም ማሙሽ እንደነበርም ትዝ ይለዋል፡፡ የወጣትነት ጊዜው ትዝታ ተቀሰቀሰ፡፡ "ቴክሳስ" ብለው በሚጠሩት ገደል ላይ የሚጫወቱትን የሸርተቴ ጨዋታ አስታወሰ፡፡ ያ ተጫዋች ወጣት ዛሬ የሚፈራ የግላዲዮ ማፍያ አለቃ መሆኑ አስገርሞታል፡፡

ፋንፋኒ ጋር እንደደረሰ፡-

"ጆቫኒ ፋንፋኒ የጥንት ጓደኛህን እና አብሮ አደግህን ታስታውሰው ይሆን?" ሲል ትኩር ብሎ ተመለከተው፡፡ ፋንፋኒ ዮናታንን አላስታወሰውም፡፡ ኮስተር ብሎ ተመለከተው፡፡ አብረው የነበሩትም የፋንፋኒ ተከታዮች ዮናታንን በጥንቃቄ እና በጥርጣሬ መከታተል ጀመሩ፡፡ "ንቁ ወፎች" እንደሆኑ ዮናታን ልብ ብሏል፡፡

"ማሙሽ፣ የከልፌ መብራት ሃይል የልጅነት ዘመን ትዝታችንን፣ የቴክሳስ ገደል ሸርተቴ ጨዋታችንን፣ የሲኒማ አዲስ ከተማ ትውስታችንን፣ ሳንጌታ እያልን የምንራገጠውን ልፊያና ድብድባችንን አላስታውስም፣ ረስቼዋለሁ ብትለኝ እምኜ ለመቀበል ይቸግረኛል"

የጆቫኒ ፋንፋኒ ታላቪያ አይኖች አዲስ ብርሃን መርጨት ጀመሩ፡፡ ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሰው ማንነት ለማስታወስ ተፍጨረጨረ፡፡ ይህ ከፊት ለፊቱ የቆመ እንግዳ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነው፡፡ አንድም ሃሰት የለበትም፡፡ ያላለፈውን የልጅነት ጊዜ እና የኢትዮጵያ ቆይታውን አስታወሰ፡፡ ጆቫኒ ያን ጊዜ ከዮናታን በብዙ እድሜ የሚያንስ ቢሆንም ጓደኞቹ በሙሉ ከእሱ እድሜ በላይ ነበሩ፡፡

"እባክህን ስምህን አስታውሰኝ?" ፋንፋኒ ከፊት ለፊቱ ቆሞ ላለፈ ዘመን ትዝታ የዳረገውን ሰው እንደመለማመጥ ቃጣው፡፡

"ጨኒ ልበልህ ብሬሎ፣ ቀበሮ ልበልህ ወይስ ድራኩላ?" ዮናታን ፋንፋኒን እየተመለከተ ከት ብሎ ሳቀ፡፡

"ዮናታን ወልዴ!?" ጆቫኒ ፋንፋኒ ታላቪያ አካባቢውን በጨኸቱ አደባለቀው፡፡ በፍጹም ማመን አልቻለም፡፡ በህልም አለም ውስጥ ያለ መሰለው፡፡ የልጅነት ጓደኛው የምስጢር ማህበር አባላት የለይጣናዊ አምልኮ ስነስርአት በሚያካሂዱበት ስፍራ ምን ያደርጋል? ዘሎ ተጠመጠመበት፡፡ ተቃቅፈው ተሳሳሙ፡፡ ሁለቱም እያለቀሱ ነበር፡፡ ከበው የሚመለከቷቸው ሁሉ በድርጊቱ ተገርመዋል፡፡ በተለይ የግላዲዮ ማፍያ አባላት አለቃቸው እምባ አውጥቶ ሲያለቅስ አይተውት ስለማያውቁ ግራ ተጋብተዋል፡፡ በየልቦቻቸው ጨካኙና የሚፈራው ፋንፋኒም ለካስ እምባ ይወጣዋል ሲሉ ተደንቀዋል፡፡

"ጩኒ ምን እግር ጣለህ?"

ፋንፋኒ ዮናታንን ድሮ በሚያውቀው የሰፈር ስሙ እየጠራ ጠየቀው፡፡

"ማሙሽዬ በቅድሚያ የአንተን ብትነግረኝ እያሻልም?"

"ይህንንማ እንደዋዛ አይደለም የምንጨዋወተው፡፡ ለእንግድነትህ ክብር መገለጫ በማዘጋጅልህ ፕሮግራም ላይ በስፋት እናወጋዋለን፡፡ አብረኸኝ ወደምኖርበት ፓርሌሞ ትጓዝና የልጅነት ጊዜያችንን እያስታወስን ትሰነብታለህ፡፡"

"ያ ቢሆን ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ነገር ግን በርካታ የምፈፅማቸው ተግባራት ስላሉ በፍጥነት መመለስ ይኖርብኛል፡፡ አለቆቼም ቢሆኑ ቅር ሊሰኙብኝ ይችላሉ፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ እንግዳ አብሮኝ አለ" ዮናታን ፓተርሰንን እና ጆቫኒን አስተዋወቃቸው፡፡

"አልሰማህም" አለው ፋንፋኒ ዮናታንን፡፡ "ምንም ብትለኝ አልሰማህም፡፡ እንግዳህ እንግዳዬ ነውና አብሮን ይቆያል፡፡ ለአለቆችህም ስልክ ደውለን እንነግራቸዋለን፡፡"

ፋንፋኒ ወደ ደብሩ አስተዳዳሪ ሂደና በጆሯቸው የሆነ ነገር ሹክ አላቸው፡፡ በእሺታ እራሳቸውን ከነቀነቁ በኋላ የሆነ ቦታ ስልክ ደወሉ፡፡ ብዙም ሳይቆይ የዮናታን ስልክ ጮኸ፡፡ አለቃው ሃሪማን ፓሌይ ነበር፡፡ ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፈለት፡፡

"ዮናታን፣ ለጊዜው ምንም የሚያስቸኩል ጉዳይ የለምና እንተም ፓተርሰንም ለሁለት ሳምንታት ያህል ቆይታችሁ ተመለሱ፡፡ ካገኛችኋቸው ሰዎች ጋር የሚኖራችሁ ቆይታ ከሰዎቹ ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በይበልጥ ያጠብቀዋልና ትእዛዛቸውን እንዳትጥሱ፡፡ የግላዲዮ ማፍያ ቡድን አንድ ቀን ያስፈልገን ይሆናል፡፡"

ሰልኩ ተዘጋ፡፡

የአለቃ ፍቃድ ከተገኘማ ረፍት እና መዝናናትን ማን ይጠላል? ዮናታን ለፓተርሰን የፓሌይን ትእዛዝ ነገረው፡፡ ፓርሌሞን ለመጎብኘት እድል በማግኘቱ ደስተኛ ነበር፡፡

"ማሙሽ ለጥያቄህ እጄን ሰጥቻለሁ" አለ ዮናታን የጥንት ጓደኛውን በስስት እየተመለከተው፡፡ በፊትም ከልቡ ይወደው ነበር፡፡ ብዙ ነገሮችን አብረው አሳልፈዋል፡፡ ወንዝ ወርደው ውሃ እየተራጩ ተጫጫኸዋል፡፡ ወፍ አድነዋል፡፡ አጋምና ቀጋ ለቅመዋል፡፡ ጭቃ እድበልብለው ተወራውረዋል፡፡ ቡሄ ጨፍረዋል፡፡ በቡሄ ዋዜማ አንድ አልጋ ላይ ተኝተዋል፡፡

"ወደህ! አለቆችህ ባይፈቅዱልህም አለቅህም ነበር" አጠገባቸው ሆኖ የሚያወሩትን ያደምጥ የነበረው ሪቬራ አማንቶሪ ጣልቃ ገባ፡-

"ይህን እድል በማግኘትህ ልትደሰት ይገባል፡፡ ፓርሌሞ ከጣሊያን ውብ ከተሞች መሃል አንዷናት፡፡ ልጃገረዶቿም የከተማዋ ውበት የተጋባባቸው ይመስል ያያቸውን ሁሉ ያማልላሉ፡፡ ነገር ግን አደራህን ውበታቸውን ከማድነቅ አልፈህ እተናከላለሁ ብለህ እንዳትሞክር፡፡ የሲሲሊን ደም የማያጣው የፓርሌሞ ወጣት ደምህን ደመ-ከልብ ያደርገዋል፡፡"

ዮናታን እና ፓተርሰን ሳቃቸውን ማፈን አልቻሉም፡፡

"ይሄ ቀውላላ ራሳ ተው ቢባልም አይሰማ፡፡ ለንግግሩ እኮ አራት ነጥብ የለውም" ፋንፋኒ እና ተከታዮቹ በሳቅ ተቀላቀሏቸው፡፡

ውለው አላደሩም፣ የደብሩን አስተዳዳሪ ተሰናብተው ወደ ፓርሌሞ ተጓዙ፡፡

****

ፓርሌሞ እንደብዙዎቹ የኢጣሊያን ከተሞች ውብ ከተማ ናት፡፡ የደስ ደስ ያላትና ትታችሁኝ አትሂዱ ብላ የምታባብል፡፡ ፋንፋኔ በከተማዋ እምብርት ላይ ብቻውን ትልቅ ውብ ቪላ ሙሰጥ እንደሚኖር የተገነዘበው ዮናታን፡-

"አላገባሁም እንዳትለኝ?" አለው፡፡

"እዎ አላገባሁም፡፡ አንተስ?"

"እኔም አላገባሁም"

"የአራስህን ወደጎን ትተህ ነው እንዴ ‹አላገባሁም እንዳትለኝ› የምትለኝ?"

ያላገቡበትን ምክንያት ተነጋገሩ፡፡ ከሚስት ይልቅ ለቆሙለት አላማና ለማህበራቸው ቅድሚያ በመስጠታቸው ነው፡፡

- 15 -

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ከኢሊኖይስ ተነስቶ አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የደረሰው ልዩ አውሮፕላን ልዩ እንግዳውን እንዳወረደ ያቺ ልዩ እንግዳ እጅብ ብለው ዘመዶቻቸውን እና ወዳጆቻቸውን ወደሚጠብቁት ሰዎች አመራች፡፡ የባልና ሚስቱ አይኖች አረቃባት፡፡ ወንድየው እጁን ከፍ አድርጎ ምልክት አሳያት፡፡ ምልክቱን ወደተመለከተችበት አቅጣጫ ሄደች፡፡ ሶስና ከፎቶዋ ለውጥ የሌለው ገጽታ እንዳላት ልብ ብለዋል፡፡

"እንኳን ደህና መጣሽ" አሉና ራሳቸውን አስተዋወቋት፡፡

"እንኳን ደህና ቆያችሁኝ" አለች እየጨበጠቻቸው፡፡

ሀጊ ሻንጣዋን እየገፋላት ወደመኪናቸው አመሩ፡፡ ምኞት ያለው ነጭ ቼቭሮሌት ጥንዶቹን እና ሶስናን ይዞ ወደራዲሰን ብሉ ሆቴል ሲከንፍ ሶስና አይኖቿን በመስኮት ወደውጭ ልካ የወላጆቿን ሃገር ከተማ በተመስጦ እየተመለከተች ነበር፡፡ ውበትም ጉስቁልናም ተመልክታለች፡፡ የሚያማምሩ ቤቶችን እና ሀንጻዎችን ባየችበት አይኗ ያረጁና የተጎሳቆሉ መኖሪያዎችን እና ሀንጻዎችንም ልብ ብላለች፡፡ በመኪናዎች እና በሰዎችም ላይ የሚታየው እውነት ተመሳሳይ ነው፡፡

ምርጥ እና ውድ መኪኖችን በሸገር ጎዳና ላይ ሲፈሱ የተመለከተ ሀገር ጎብኚ "ዋው!" ብሎ በአድናቆት ከአንደበቱ ያወጣውን ቃል ሳይጨርስ ፋብሪካዎቻቸው እስከመፈጠራቸውም የዘነጓቸውን ከርካሳ ተሽከርካሪዎች ሊመለከት ይችላል፡፡ ምኞትና ድሎት የሚታይበት ፊት ያላቸው ነዋሪዎች የሚታዩትን ያህል እጦትና ያልተላላ ኑሮ አጥንታቸውን ብቻ አስቀርቶ ተንቀሳቃሽ ሬሳ

ያለመሰላቸውም በርካታ ናቸው። መኪና ለመኪና እየተሹለከለኩ ባለመኪኖችን በመስታወት በኩል ሳንቲም የሚለምኑ ሕጻናትንና እናቶችን የተመለከተችው ሶስና በዘመናዊ የካፍቴሪያ በረንዳዎች ላይ ተቀምጠው ዓለማቸውን የሚቀጩ ታዳጊ ወጣቶችንም አይታለች። በውስን ደቂቃዎች ውስጥ የተመለከተቻቸው "ምንዱባኖች"ም ይሁኑ ቅንጡ ታዳጊ ወጣቶች መሰሎቻቸውን መወከል መቻል ያለመቻላቸውን እርግጠኛ ባትሆንም በዜጎች መሃል ያለውን ሰፊ ልዩነት ታዝባለች።

ይህንና ሌላ ሌላውንም እያሰላሰለች በነበረበት አፍታ መኪናው ከሆቴሉ ደጃፍ በመድረሱ ርቃ ከሄደችበት ሃሳብ ትመለስ ዘንድ ተገደደች። ባለዘጠኝ ፎቁ አምስት ኮከብ ሆቴል ዓይኗን ማርኮታል። አርባ አራት ያህል አንደኛ ደረጃ ክፍሎችን እና አስራ ስድስት ያህል የተለየ ምቾት ያላቸውን ክፍሎች ጨምሮ በአጠቃላይ ሁለት መቶ አራት ክፍሎች እንዲሁም ዘጠኝ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ባሉት ውብ ሆቴል መልካም ቆይታ እንደሚኖራት እርግጠኛ ሆናለች። ወደተያዘላት ክፍል አመራችና ንብረቶቿን አስቀመጠች። ከአስራ ስድስቱ የተለየ ምቾት ያላቸው ክፍሎች አንዱ ነበር።

****

በኢትዮጵያውያን ሰአት አቆጣጠር ከቀኑ አስር ሰአት ከአርባ ስምንት ደቂቃ ሆኗል። የክፍሏን በር በእርጋታ ያንኳኳው ሃኒ ሜናሂም ወደ ውስጥ ሣይገባ "ምግብ ቢጤ ብንቀምስ ምን ይመስልሻል?" አላት ከውጭ እንደቆመ። ከክፍሏ ወጣች። "እንደውም ርቦኛል" ጥንዶቹና ሶስና ተከታትለው ወደሆቴሉ ምርጥ እና ልዩ የፈረንሳይ ሬስቶራንት "verres en vers" አመሩ። ጣፋጭ ምግባቸውን በወይን ካወራረዱ በኋላ በሃገር ውስጥ ምርጥ የተባለውን የቶሞካ ቡና አዘዙ። ሰፊው ትውውቅ የተጀመረው ከዚህ በኋላ ነው። ሲቢኤስ ውስጥ ለምን ያህል አመታት እንደሰሩ፣ እንዴት እንደተዋወቁና ፍቅር እንደጀመሩ በኋላም ትዳር እንደመሰረቱ ነገሯት። እሷም የት እንደተማረች፣ የት እንደሰራችና

አሁን እያገለገለችበት ወዳለው የWSIL-TV መስሪያ ቤት እንዴት እንደመጣች ነገረቻቸው፡፡ የሁለቱም ትውውቅ "ታሪኬ በአጭሩ" አይነት ነበር፡፡ እነሱም ሆኑ እሷ ያላሰፈላጊ ወሬ ትርተራ ውስጥ መግባት አልፈለጉም፡፡ የሃሪማን ፓሌይ ጆሮ ጠቢ መሆን ያለመሆናቸውን በምን ታውቃለች? ሃሪማን ፓሌይ በላያቸው ላይ የላካት ሰላይ መሆን ያለመሆኗን በምን ያረጋግጣሉ? ለጊዜው የሚያዋጣው ትእዛዝ እና መመሪያ እየተቀበሉ ሪፖርት መላክ ነው፡፡ ከዚህ የዘለለ ድፍረት እና ወሬ ማብዛት አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል፡፡ እርስ በእርሳቸው አልተማመኑም፡፡ በጋራ የሚያውቁት ነገር ቢኖር በኢንቨስተር ስም ኢትዮጵያ መግባታቸውን ነው፡፡

ለትውወቅ ያህል የሚሆናቸውን ሃሳብ ከተለዋወጡና በቂ ቆይታ ካደረጉ በኋላ ወደየከፍላቸው ሄዱ፡፡ ሶስና ልብሷን ከቀየረች በኋላ ወደስኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት አስተዳደር ስልክ ደወለች፡፡ ርእሰ-መምህሩን አገኘችው፡፡ ማንነቷን ካስተዋወቀችው በኋላ በነገው እለት ከተማሪዎቹ ጋር ስብሰባ ማድረግ እንደምትፈልግ ነገረችው፡፡ እየተሽቆጠቆጠ ነበር ያናገራት፡፡

"እው ይቻላል.....ይቻላል ወይዘሮ ሶስና፡፡ ስንት ሰአት ላይ ቀጠሮ እንያዝ?"

"ጠዋት አራት ሰአት"

ተስማምተው ስልኩ ተዘጋ፡፡ ርእሰ-መምህሩ የሚያስተዳድረው ትምህርት ቤት ከጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ጋር ባለው ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቤቱ ስም ከሚላከው እርዳታ በአብዛኛው ተጠቃሚ ስለነበር "ከጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ" ሲባል እንደኳስ መንጠር፣ እንደወፍ መብረር ይጀምራል፡፡ የአለቆቹ ታማኝ አሽከር ነው፡፡

ሶስና ቀጠሮውን ከያዘች በኋላ ሀኒ ሜናሂም ጋር ስልክ ደወለች፡፡ "ስራችንን (ጥናታችንን) ወደምንጀምርበት ትምህርት ቤት ስልክ ደውዬ ነበር፡፡ ርእሰ መምህሩን አነጋግሬ ለነገ ቀጠሮ ይዣለሁ፡፡ ከጠዋቱ አራት ሰአት በፊት መድረስ ይኖርብናል"

"ተስማምተናል" አላት ሃጊ ባለቤቱን ጁዲንም ወከሎ፣፣ አያያዘናም "ከሰአታት ቆይታ በኋላ ከሆቴሉ ባር ተገናኝተን በወይን ብናመሽ ምን ይመስልሻል?" አላት፣፣

"አይ ይቅርብኝ እመሰግናለሁ፡፡ ጠዋት ንቁ ሆኜ ለመገኘት በጊዜ መተኛት ይኖርብኛል"

"እንግዲያውስ መልካም ምሽት እና አዳር ይሁንልሽ"

"ለእናንተም" ተሰነባበቱ፡፡ ሶስና ለሃጊ በጊዜ መተኛት እፈልጋለሁ የሚል ምክንያት ትስጠው እንጂ በጊዜ አልተኛችም፡፡ የጽሞና ጊዜ አስፈልጓት ነበር፡፡ ከተማሪዎቹ ጋር ስለምታደርገው ቆይታ፣ ስለምታቀርብላቸው ጥያቄ፣ ስለምታጠናቅረውና ለዮናታን እና ለሃሪማን ስለምትልከው ሪፖርት ብዙ ብዙ ነገር አሰላሰለች፡፡ ሃሳቧ ወደልጇ ወደ ሰለሞን እየሸፈተም አስቸግሯት ነበር፡፡ ጠቃሚ ናቸው ያለቻቸውን ሃሳቦችና ለተማሪዎቹ ባቀርባቸው ይመጥናሉ፣ ይጠቅማሉ ያለቻቸውን ጥያቄዎች በማስታወሻ ደብተሯ ላይ አሰፈረች፡፡

የምታነሳቸው ጥያቄዎች እና የምታገኛቸው መልሶች የነሃሪማን ፓሌይ ግብአቶች፣ የነዮናታን ወልዴ ቀጣይ እቅድ መንደርደሪያ ዎች ሆነው ቢያገለግሉም፤ ከእነኢስቱሊን ጋር መስራት ስትጀምር የምትጠቀምባቸው ወርቃማ ሃሳቦች እንደሚሆኑም አልጠፉትም፡፡ እነዚህን ሃሳቦች በግብአትነት በመጠቀም ፊር እየለቀቀ በመሄድ፣ የምስጢር ማህበራቱ የአዕምሮ ቁጥጥር ሰለባ በመሆን ላይ ያለውን ሃይል በተቃራኒው ወደማንነቱ የሚመለስበትን፣ የሃገሩን ታሪክ የማወቅ ዝንባሌ የሚያሳድርበትን ስልት ትቀይስበታለች፡፡ ከወጣቱ የምታገኘውን ሃሳብ እና አስተያየት በመጠቀም ጠቃሚ የሆነ ጽሁፍ ታዘጋጅበታለች፡፡ እነዴቪድ አይክ፣ ዳንኤል ኢስቱሊን አሌክስ ጆንስም ሆኑ ሌሎች የምስጢር ማህበራቱን ሴራ ለማጋለጥ ተግተው የሚሰሩ ጸሃፍት ጠቃሚ ሃሳቦቻቸውን ከየትም አላገኟቸውም፡፡ ከጥናት፣ ከምርምር እና ከግለሰቦች ጋር ካደረጓቸው ቃለምልልሶች ነው፡፡ በድንገት በሰውነቷ በተሰራጨ የደስታ ስሜት ተዋጠች፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁት ለበጎ ነው ስትል አሰበች፡፡ ያስገደዷት

ሃይሎች ለክፋት ሊያውሉት ያሰቡትን ሃሳብ እቧ ወዶ ሰናይ ሃሳብ ልትቀይረው እንደምትችል እርግጠኛ ሆነች፡፡ ኢስቱሊን ለመጽሃፍቱ የሚሆነውን ግብአት ከምስጢር ማህበራቱ የቅርብ ሰዎች እንደሚያገኝ የነገራትን አስታወሰች፡፡ እቧስ ከተማሪዎቹ የምታገኘውን ሃሳብ፣ አስተያየት እና ጥቅል መረጃ ነገ በተቃራኒ ጎዳና ስትሰለፍ እንዳትጠቀምበት ማን ይከለክላታል? በቂ መሰናዶና ዝግጅት ካደረገች በኋላ በጋለ ስሜት ወደአልጋዋ አመራች፡፡ ሌላ ጊዜ እምቢ ብሎ የሚታገላት እንቅልፍ ዛሬ አላስቸገራትም፡፡

- 16 -

ጣሊያን፣ ፓርሌሞ

ፓርሌሞ በገቡ በነጋታው ለዮናታን እና ለፓተርሰን ክብር ሲባል በፋንፋኒ ውብ ቪላ ውስጥ ትልቅ ዝግጅት ተዘጋጀ። ምግብና መጠጡ በገፍ ቀረበ። ምግቡን ያዘጋጁት የከተማዋ እውቅ የምግብ ባለሙያዎች ሲሆኑ፤ መጠጦቹም የተገዙት በከተማዋ ውስጥ እውቅና ካላቸው የመጠጥ መደብሮች ነው። በዝግጅቱ ላይ በርካታ እንግዶች የተገኙ ሲሆን አብዛኛዎቹ የከተማዋ ነዋሪዎች ናቸው። ደስ የሚል ዝግጅት ነበር። ፕሮግራሙ ተጠናቆ እንግዶች ከተሸኙ በኋላ፦

"ለክብራችን ብለህ ላዘጋጀኸው ዝግጅት ከልብ እናመሰግናለን" አሉት ዮናታን እና ፓተርሰን።

"የወዳጆቼ ደስታ ደስታዬ ነው።"

ተከታዮቹ የሙሉ ጊዜ አጃቢዎቹ እንደሆኑ ልብ ብለዋል። ከአጃቢዎቹ አንዱ ቀረብ ብሎ መኝታ እንደተዘጋጀላቸው ተናገረ። ዮናታንም ሆነ ፓተርሰን ለመተኛት ፍቃደኞች አልነበሩም። ከፋንፋኒ ጋር ሲጫወቱ ለማንጋት ወስነዋል። ፋንፋኒ በውሳኔያቸው ደስተኛ ነበር። አጃቢውን ካሰናበቱ በኋላ ወይናቸውን እየተጎነጩ ስላሳለፉት የወጣትነት ዘመን ማውጋት ቀጠሉ።

"ወይ ጩኺ!.....ያ ሁሉ ጸጉር የት ሄደ?" አለ ፋንፋኒ እየላቀና የዮናታንን በራራስ እየተመለከተ። ዮናታን ለፋንፋኒ መልስ ሳይሰጥ ጥያቄውን በጥያቄመለሰ::

"አንተስ እንዲህ ያወፈረህ ምንድነው?" የዮናታን ጸጉር በሚገርም ሁኔታ የሸሸውን ያህል የፋንፋኒም ሰውነት በማይታመን መልኩ ወፍሯል።

"ትገ ይልሃል ማሙሽ? ያኔ እኮ በጣም ቀጭን ልጅ ነበርክ"

"ያንተም ጸጉር ግንባርህ ላይ ይደርስ ነበር። ለመሆኑ እነቀበሮ፣ ድራኩላ፣ ተስፋዬ ጌሾ፣ ጌቱ ሴሎ፣ ብርቄ ሴንጢ፣ እና ብሬሎ ቀሽት በህይወት አሉ? ወሬያቸውን ትሰማለህ?" ፋንፋኒ ስለልጅነት ጓደኞቹ ለመስማት ጓጓ።

"ሀገር ቤት በነበርኩ ጊዜ አንዳንዶቹን አገኛቸው ነበር። ከሃገር ከወጣሁ በኋላ ግን ስላሉበት ሁኔታ ሰምቼ አላውቅም። ብሬሎ ቀሽት ሀገር ቤት ላለሁ መሞቱን ሰምቻለሁ"

ፋንፋኒ በብሬሎ ቀሽት ሞት ከልቡ አዘነ። እራሱን የሚጠብቅና በቀን አስሬ በውሃ የሚዘፈዘፍ ሽቅርቅር ልጅ ነበር። ቀሽት የሚለውን ስያሜ ያገኘው ከዚህ ባህሪው ነው። ሁሉም የሰፈር ስም ነበራቸው። ጌታነህ "ቀበሮ"፣ ደረሰ "ድራኩላ"፣ ተስፋዬ "ጌሾ"፣ ጌቱ "ሴሎ"፣ ብርቄ "ሴንጢ"፣ ፋንፋኒ "ማሙሽ"፣ ዮናታን "ጩኒ"፣ ብሬሎ "ቀሽት"። የአብዛኛዎቹ ቅጽል ስም በምክንያት የወጣ ነበር። ጌቱ እና ተስፋዬ ጠላ ስለሚወዱ "ሴሎ" እና "ጌሾ" ተባሉ። ጌታነህ የሚያደርገውን ሁሉ እድፍጠ ስለሚያደርግ "ቀበሮ" ተባለ። ፋንፋኒ ከሁሉም በእድሜ ትንሽ ስለሆነ "ማሙሽ" የሚል ስም ወጣለት። ከጸታ አቻዎቿ ተለይታ ከእነሱ ጋር ግንባር የፈጠረችው ቀጭኗና በተንኮል ስራዋ የምትታወቀው ብርቄ "ሴንጢ" ተባለች። የዮናታንን እና የደረሰን ቅጽል ስም ምክንያት ግን አሁን አያስታውሱትም።

ፋንፋኒ ብርቄን ከልቡ ያፈቅራት እንደነበር ያስታወሰው ዮናታን፡-

"የምታፈቅራትን ብርቄን ትተህ ከሃገር ትወጣለህ ብዬ አላስብም ነበር" አለው።

"አንተስ ብትሆን ለአንድ ቀን እንኳን ሳታያት ስትቀር እበድ እበድ ከሚልህ እህቴ ተለያይተህ ቀርተህ የለ?"

ዮናታን የፋንፋኒን እህት ሪታን እንደጣአት ያመልካት ስለነበር ነው ይህን ማስታወሱ።

"ሪታን ዛሬ ብታያት የምታውቃት አይመስለኝም፡፡ የሶስት ልጅች እናት ሆናለች፡፡ ከባለቤቷና ከልጆቿ ጋር ሮምነው የምትኖረው፡፡ ደውዬ እጠራትና ታያታለህ፡፡ ማሪያም አግብታለች" የዮናታን ፊት ተቀያየረ፡፡ ይህን የተገነዘበው ሩንሩኒ፡-

"ዛሬም ድረስ አፈቅራታለሁ እንዳትለኝ ብቻ?" አለና ከት ብሎ ሳቀ፡፡

"ሪታን መቼም ቢሆን ከልቤ አላወጣትም፡፡ የልቤ የዘለአለም ንግስት ናትና በውስጤ እንደነገሰች ትኖራለች፡፡ ወደ ጣሊያን ለመምጣት ቤት ስትለቁ ወር ሙሉ ያፈሰስኩትን እምባ አልረሳውም" ዮናታን ኮስተር ብሎ ነበር የሚያወራው፡፡

"ድሮም አልቃሻ ነበርክ፡፡ እንኳን የምታፈቅራትን አጥተህ ጎል ሲገባብህም ትነጫነጭ አልነበር?" ሩንሩኒ እና ቤንጃሚን ፓተርሰን በዮናታን ላይ እያሾፉ ተሳሳቁ፡፡

"የሆነስ ሆነና እንዴት የግላዲዮ ማፍያ ድርጅት አለቃ ልትሆን ቻልክ?" ዮናታን ቅልዱን ወደቁም ነገር አዘል ጥያቄ ቀየረው፡፡ ይህን ጊዜ በተራው የጆቫኒ ሩንሩኒ ታላቪያ ፊት ተቀያየረ፡፡ ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ ሁኔታውን ተረከላቸው፡፡

"ከኢትዮጵያ ወጥተን ወደቱሪን እንደመጣን አባቴ ጉልበቱ በመድከሙ ታላቅ ወንድሜ ሚካኤል በመኪና ሽያጭ ንግድ ላይ ተሰማርቶ ቤተሰቡን የማስተዳደር ሃላፊነትን ተረከበ፡፡ ሀብታም ለመሆን ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ይህን ጊዜ ሲሲሊ ውስጥ የተደራጀ የማፍያ ቡድን አይን እሱ ላይ አረፈ፡፡ ከማፍያ ቡድኑ አባላት ጋር ግንባር እንዲፈጥርና በገንዘብ እንዲደጉማቸው ቢጠይቁት እምቢ አለ፡፡ ደጋግመው ቢያስፈራሩት እና ሰው ቢልኩበትም አሻፈረኝ አለ፡፡ በአንድ በተረገመ እለት ከስራ ወጥቶ ወደቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ መንገድ ጠበቁትና ተኩሰው ገደሉት....." የሩንሩኒ ድምጽ እየሻከረ ሄደ፡፡ "ነገሩ ዱብዳ የሆነባት እናቱ ጨርቋን ጥላ አበደች፡፡ ዛሬም ድረስ ከአስፓሮ ሀመሚ አልዳነችም፡፡ አቅሙ የደከመው አባታችንም በድንጋጤና በልብ ህመም በሽታ ሳቢያ የዚያኑ ሰሞን ሞተ.....

"በቤተሰቡ ላይ የደረሰውን ውርደት እና ቅስፈት ተቀብዬ መኖር ስላልቻልኩ ቂሜን ለመበቀል የማፍያ ቡድን ሳፈላልግ ከግላዲዮ ማፍያ አባላት ጋር ተገናኘሁ። የምፈልገው አይነት የተደራጀ የማፍያ ቡድን ነበር። በዚህ ቡድን አማካይነት ለወንድሜና ለአባቴ ሞት እንዲሁም ለእናቴ እብደት ምክንያት የሆኑትን የሲሲሊማፍያ ቡድን አባላት ገድዬ ቂሜን ከተወጣሁ በኋላ ለቡድኑ ያለኝ ፍቅር እየጠነከረ መጣ። በቅንነት ላገለግለው ቃል ገባሁ። ቀስ በቀስ ስልጣን ያዝኩ።"

ዮናታን በሰማው ታሪክ ተረበሸ። ቤተሰቡን የቅርብ ዘመድ ያህል ይቀርበው ነበር። ረጅሙና የሰፈራቸው በረኛ የነበረው መልክ-መልካሙ ሚካኤል፣ ከስራ ሲመለሱ ፍራፍሬና ዳቦ ይዘውላቸው ይመጡ የነበሩት ደጉ ሽማግሌ ታላቪያ ጋስፔሪ፣ ትምህርት በማይኖርበት ጊዜ በተለይም ቅዳሜና እሁድ ቁርስ ሰርተው የፋንፋኒን ጓደኞች የሚሰበስቡት የመቀሌ ተወላጁ አደይ ብርሃን.....ሁሉንም አስታወሳቸው። ሚካኤልና ታላቪያ ሞተዋል። አደይ ብርሃን አብደዋል። ቤተሰቡን ያጣ ያህል ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ።

ታላቪያ ጋስፔሪም ሆኑ አደይ ብርሃን እንደልጃቸው ያዩት ነበር። ሪታን ከልቡ እንደሚያፈቅራት ያወቁት ታላቪያ "እንቴ ቲሚርትን ጨሪሰህ ጢሩ ሲራ ሲቲዝ ቱሪን መጢተህ ያኔን ሊጅ ሪታን ታጌባለህ" የሚሉትን አስታውሶመጽናናት አልቻለም።

"ጩኒ በቃ። ከሆነ በኋላ ምን ታደርግዋለህ?" ፋንፋኒ አጽናንቶ ለቅሶውን አስቆመው። ፓተርሰን በሰማውነገር ከልቡ አዝኖ ነበር። ዮናታንም በምን አይነት ሁኔታ የምስጢር ማህበሩን እንደተቀላቀለ አጫወተው። ፋንፋኒ ኢትዮጵያም ላለ ነገረ-ስራው ሁሉ የሰይጣን ነበር። ከሰፈራቸው ትልቅ የአምልኮ የወይራ ዛፍ ላይየሰኒ ቅቤና ግንዘብ ይሰርቅ እንደነበር ዮናታን ያስታውሳል። በልጅነቱም እግዚአብሄር የለም ብሎ ያምን የነበረው ፋንፋኒ የቤተሰቦቹን ደም ለመበቀል በሚል ሰበብ ለሰይጣን አምልኮ ዘብ ሆኖ የተቋቋመውን የማፍያ ቡድን ቢቀላቀል ሊገርም እንደማይችል አሰበ።

****

ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ ጣላቸው፡፡ ግማሽ ቀን ተኝተው ቆዩ፡፡ ከምሳ በኋላ ከተማዋን ለመጎብኘት ወጡ፡፡ ሰው ለጆቫኒ ፋንፋኒ የተለየ አክብሮት ሲሰጠው አስተውለው ፓርሌሞ ውስጥ ታዋቂ ሰው እንደሆነ አምነው ተቀብለዋል፡፡ አጃቢዎቹ ተከትለዋቸዋል፡፡ ሪቬራ አማንቶሪ እንዳለው የሴቶቹ ውበት አፍዝ አደንዝዝ ነው፡፡ ዮናታን ማስጠንቀቂያውን አልዘነጋውም፡፡ "እተናኮላለሁ ብትል የሲሲሊን ደም የማያጣው የፓርሌሞ ወጣት ደምህን ደመ-ከልብ ያደርገዋል" ፈገግ አለ፡፡ ፋንፋኒ ፈገግ ያለበትን ምክንያት ጠየቀው፡፡ ነገረው፡፡

"ወሬኛ ሽማግሌ በለው፡፡ ከእኔ ጋር አስካለህ ድረስዞር ብሎ የሚያይህ አይኖርም፡፡ እንደውም ውቦች የበዙበት መዝናኛ ስፍራ ለምን አልወሰዳችሁም?"

ከተማዋ አሉኝ ብል ከምትኮራባቸው ታዋቂ መጠጥ ቤቶች ወደ አንዱ ጎራ አሉ፡፡ "እውነትም የውቦች መናሃሪያ!" አለ ፓተርሰን ገና ከመግባታቸው፡፡ አስተናጋጆቹም፣ ተስተናጋጆቹም በአብዛኛው ሴቶች ናቸው፡፡

የበርካታ ቆነጃጅት አይን እነሱ ላይ አረፈ፡፡ የግላዲዮ ማፍያው አለቃ ፓርሌሞ ውስጥ ራሱን የቻለ ንጉስ ነው፡ ቆነጃጅቱ እስኪጠሩ ድረስ በጉጉት ተንሰፈሰፉ፡፡ ፋንፋኒ አይን አውጣ ሴቶች ምን ያህል እንደሚንቅ ስለሚያውቁ አደብ ገዙ፡፡

"እህሳ ምርጫችሁ የሚሆኑ ቆነጃጅት የሉም?" ሲል ጠየቀ፡፡ ፓተርሰን ከፊት ለፊቱ የተቀመጠችውን ቆንጆ መረጠ፡፡ አይኖቿ ጎላ ጎላ ያሉ ረጅም እና ዳሌዋ ሰፋ ያለ ወጣት ነች፡፡ ተጠርታ መጣች፡፡ ደስታ እንደተሰማት ያስታውቃል፡፡ ጓደኞቿ ቅናት ቢሰማቸውም እስኪጠሩ መጠበቅ ነበረባቸው፡፡

"የክብር እንግዳዬን ብታጫውቺው ምን ይመስልሻል?" ፋንፋኒ ጠየቃት፡፡

"በደስታ!" ስትል መለሰችለት፡፡ ፋንፋኒም የተመኛትን ቆንጆ ጉያው ሸጉጦ ጨዋታቸው ቢደራም የዮናታን ብቸኝነት

አልተመቸውም፡፡ ስሜቱን የምትሰብ ቆንጆ አላጋጠመችኝም ብሎ ድርቅ በማለቱ "የሶስት ልጆች እናት የሆነችውን እህቴን ከሮም ድረስ ደውዬ አላመጣልህም" ብሎ ተሳለቀበት፡፡ ለጊዜው ነበር የተግደረደረው፡፡ መጠጡ ስራውን መስራት ሲጀምር በመጀመሪያ የተጠራቸውን ቆንጆ ጓደኞች ጠርቶ መሃላቸው ገባ፡፡ ፋንፋኒ እና ፓተርሰን ተጠቃቅሰው ሳቁ፡፡ ለዚህች አቅምህ ነበር? የሚሉ ይመስላሉ፡፡ ያውም ሁለት ቆነጃጅት፡፡ ምሽቱ ከመግባደዱ በፊት ፋንፋኒ ወደ ዮናታን ጆሮ ጠጋ አለና፡-

"ጩኺምረጥና እንሂድ?" አለው፡፡

"ሁ-ሁለቱንም፡፡ ከሁለቱም ጋር መደሰት አልችልም?" በስካር አንደበት መለሰለት፡፡

"ጉልበቱ ካለህማ መብትህ ነው፡፡ ቆነጃጅት ፍቃደኞች ናችሁ?" ፋንፋኒ ጠየቃቸው፡፡

"በደስታ!" ተንጫጩ፡፡ አራቱ ሴቶችና ሶስቱ ወንዶች በፋንፋኒ ጠባቂዎች ታጅበው ወደ ፋንፋኒ ቪላ አቀኑ፡፡

****

ወደ የክፍላቸው አምርተው ፋንፋኒና ፓተርሰን አስደሳች ሌሊት ቢያሳልፉም፤ ዮናታን ጎኑ አልጋ እንደነካ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ስለወሰደው ቆነጃጅቱ ጸማቸውን ለማደር ተገደዱ፡፡ ቁርስ ላይ ፊታቸውን አኩሳትረው የተመለከታቸው ጆቫኒ የሆኑትን ጠየቃቸው፡፡ ነገሩት፡፡ ሆዱን ይዞ ከተንከተከተ በኋላ ከጠየቁት በላይ ከፍሎ አሰናበታቸው፡፡ እሱ፣ ዮናታንና ፓተርሰን ብቻ እንደቀሩ፤

"ነገ ምሳ ሰአት ላይ ከሮም የሚመጣ እንግዳ ይኖረናል" አለ የዮናታንን ገጽታ በጥንቃቄ እያጠና፡፡ ለውጥ አልተመለከተም፡፡ የእንግዳውን ማንነት አልተገነዘበም ማለት ነው፡፡ "የምትመጣው ሪታናት፡፡ ልታይህ ጓጓለች" የዮናታን ምራቅ ደረቀ፡፡ የሚናገረው ጠፋው፡፡ ውቧን ሪታን በአእምሮው ግድግዳ ላይ ሊስላት ሞከረ፡፡

ፈገግታ የማይለየው ፊት፡፡ ረጅምና ደማቅ ጥቁር ጸጉር፡፡ ቀጭንና ረዘም ያለ ሰውነት፡፡ ማራኪ ድምጽ፡፡ የውጭም የውስጥም ውበት የሚንጸባረቅበት ሰብዕና፡፡ አስመሳይነትን ያልተላበሰ ግልጽ ማንነት፡፡ ሪታ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ናት፡፡

የታላቪያ ጋስፔሪን ቃላት አስታወሳቸው "አንቱ ቲሚርትን ጨሪሰህ ጢሩ ሲራ ሲቲዝ ቱሪን መጢተህ ያኔን ሊጅ ሪታን ታጌባለህ" እንደተመኙት አልሆነም፡፡ ህይወት ባልታሰበ መንገድ ተጉዛለች፡፡ ሪታ የሌላ ሰው ሆናለች፡፡ ዳግም አንድ ላይሆኑ ተለያይተዋል፡፡ ለነገሩ ማን ያውቃል አንድ ይሆኑም ይሆናል፡፡ የህይወትን መነሻና መድረሻ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ይሆናል የተባለው አይሆንም፤ አይሆንም የተባለው ይሆናል፡፡ ህይወት እንዲህ ነች፡፡ የመሆን ያለመሆን ድምር ውጤት፡፡ የመለያየትና የመገናኘት አጋጣሚ፡፡ የመገናኘቱ አጋጣሚ የእድለኞች ሲሳይ ሲሆን የመለያየቱ አጋጣሚ ደግሞ እንደዮናታን ላሉ እድለ-ቢሶች መከራ ነው፡፡ እድሜ ልክ እንደጥላ ሲከተል የሚኖር ባለጋራ፡፡

- 17 -

አዲስአበባ፣ ኢትዮጵያ

የስኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተስፋ ተሞልተው እንግዶቻቸውን እየተጠባበቁ ነው። በገጽታቸው ላይ ጉጉት ይነበባል። ርእሰ-መምህሩ ሰብስቦ "ከጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ተወከለው የመጡ እንግዶች ያነጋግሯችኋል። ዩኒቨርሲቲው ከትምህርት ቤታችን ጋር ባለው የቆየ ጥብቅ ግንኙነት ለጎበዝ ተማሪዎቻችን ነጻ የትምህርት እድል ሲሰጥ እንደቆየ የምታውቁት ነው። እንግዶቹ አሁንም ጎበዝ ተማሪዎችን ለማበረታታት እና ወደፊት የሚሰጡትን ነጻ የትምህርት እድል ለማመቻቸት እንደመጡ ተስፋ አደርጋለሁ" ካላቸው ደቂቃ ጀምሮ እየተቁነጠነጡ ነው። ትምህርት ቤታቸው ከሌሎች ትምህርት ቤቶች በተለይ አሜሪካ ውስጥ ከሚገኝ እውቅ ዩኒቨርሲቲ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ስላለው ኩራት ቢጤ የቃጣቸው ተማሪዎችም አልጠፉም። የጥርጣሬ ወጀብ እያንገላታቸው የእንግዶቹን መምጣት የሚጠባበቁት እና "አዲስ አለም" ከተሰኘው የመንግስት ትምህርት ቤት ተወክለው የመጡት ተማሪዎች ግን የተፈለጉበት ምክንያት ግልጽ አልሆነላቸውም።

ርእሰ-መምህራቸው "በስኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት አዳራሽ ከውጭ ከመጡ እንግዶች ጋር ውይይት ይኖራል" ከማለት ውጭ የነገራቸው ነገር የለም። እሱም ቢሆን ስለጉዳዩ የሚያውቀው ነገር የለም። ትምህርት ሚኒስቴር ስለጉዳዩ ይወቅ አይወቅ እርግጠኛ አይደለም። ደብዳቤ ደረሰው። ተማሪዎች መርጠ ላከ። በቃ ይሄው ነው። የውይይቱ አጀንዳ ይዘት ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ግን ገምቷል። ባይሆንማ ኖሮ ከጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ ድረስ የመጡ ባለሙያዎች የሚያስተዳድረውን

ትምህርት ቤት ተማሪዎች ባልጋበዙ፣ አሱም አንደ ሰኩል አፍ ዋን ግሎብ አንዳንድ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱ በአውቅ ዩኒቨርሲቲ ተወካዮች ያውም ከሌሎች የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተመርጠ በመጋበዙ ኩራት ቢጤ ተሰምቶታል፡፡ አዲስ አለም ትምህርት ቤትን ወክለው በስፍራው የተገኙት ተማሪዎች የስኩል አፍ ዋን ግሎብ ተማሪዎች ለሚያገኙት ነጻ የትምህርት እድል ማዳመቂያ መሆን አልፈለጉም፡፡ የስኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር "እንግዶቹ ነበዝ ተማሪዎችን ለማበረታታት እና ወደፊት የሚሰጡትን ነጻ የትምህርት እድል ለማመቻቸት እንደመጡ ተስፋ አደርጋለሁ" ሲል ግምቱን ያስቀምጥ እንጂ እንግዶቹ የመጡበትን ዋንኛ ምክንያት አያውቅም፡፡ ለማወቅም መብት አልነበረውም፡፡ ምክንያቱ ከእሱ የርእሰ-መምህርነት ስልጣን ደረጃ በላይ ነው፡፡ የእሱ ዋንኛ ድርሻ አድርግ የተባለውን ማድረግ ነው፡፡

በጉጉት እና በናፍቆት ሲጠበቁ የነበሩት እንግዶች ሶስት ሰአት ከሃምሳ ስምንት ደቂቃ ሲል ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ደረሱ፡፡ በተማሪዎቹ ደማቅ አቀባበል ተደንቀዋል፡፡ ተማሪዎቹ ሁሉንም እንግዶች ከሰማይ እንደወረዱ መላእክት ነበር የተመለከቷቸው፡፡ "ምስኪኖች" አለች ሶስና በውስጧ፡፡ "የተሸረበባቸውን ሴራ ያላወቁ የዋሆች! ለአንድ አፍታ ልጇን ሰለሞንን አስታወሰችው፡፡ እንግዶቹ በመሰብሰቢያው አዳራሽ ውስጥ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ላይ ከተቀመጡ በኋላ ተማሪዎቹ እንዲገቡ ተፈቀደላቸው፡፡ ርእሰ መምህራቸው በመግቢያ ንግግር እንግዶቹን አስተዋውቆ እንዳበቃም ውይይቱ በይፋ ተጀመረ፡፡ ተናጋሪው ሃኒ ሜናሂም ነበር፡፡ ሶስና እያስተረጎመችለት ከየት እና ለምን እንደመጡ አብራራ፡፡

"እኔና ባለቤቴ የምንኖረው አሜሪካ ውስጥ ሲሆን እዚህ ከመምጣታችን በፊት ለጥቂት ቀናት ካናዳ አንታሪዮ ነበርን፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ላሰብነው ፕሮጀክት የምናማክረው ባለሙያ ነበር፡፡ ከሰባት አመታት በላይ በሲቪኤስ የቴሌቭዥን ጣቢያ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች አገልግለናል፡፡ እዚህ ሀገር ከኢትዮጵያውያን ባለሃብቶች ጋር በመሆን በጋራ ትልቅ የቴሌቭዥን ጣቢያ የማቋቋም ሃሳብ አለን፡፡ ጣቢያው በመዝናኛ ይዘት ላይ ትኩረት

የሚያደርግ ነው፡፡ ምን አይነት የቴሌቭዥን ፕሮግራም እንደሚያስደስታችሁ እና እንደሚያዝናናችሁ ማወቅ እንፈልጋለን"

ዋንኛው ምክንያት እና አጀንዳ የተደበቃቸው ምስኪን ተማሪዎች በየተራ እጃቸውን እያወጡ ፍላጎታቸውን ተናገሩ፡፡

"እኔ በራፕ ሙዚቃ ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ጣቢያ ቢቋቋም ደስ ይለኛል"

"እኔ በአድቬንቸር ፊልሞች ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ጣቢያ ቢሆን እመርጣለሁ"

"ሙዚቃና ፊልሙን ቀላቅሎ የያዘ ጣቢያ ቢሆን ብዙ ተመልካች ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ"

"እኛ ሀገር እኮ የፍቅር ታሪክ ላይ የሚያተኩሩ የህንድ ፊልሞች በጣም ይወደዳሉ፡፡ የህንድ ፊልሞች የሚታዩበትን ጣቢያ ለምን አታቋቁሙም?".....

ሁሉም የመሰለውን ተናገረ፡፡ ሶስና የተማሪዎቹን ምላሽ ለጥንዶቹ ተረጎመችላቸው፡፡ አንድም በሃገራዊ ይዘት ላይ የሚያተኩር ሃሳብ የሰነዘረ ተማሪ በማጣቷ ግን ደንግጣለች፡፡

ሃጊ ንግግሩን እንደጨረሰ እና ተማሪዎቹም ዝም ማለታቸውን የተገነዘበችው ሶስና ከተቀመጠችበት ተነስታ በአዳራሹ ውስጥ ተንጎራደደች፡፡ በጥልቅ ሃሳብ መዋጧ ያስታውቃል፡፡ የሁሉም አይን አረፈባት፡፡ ተማሪዎቹ በተራዋ የምትናገረውን ለማድመጥ ጓጉተዋል፡፡ አየር በጥልቀት ስባ ከተነፈሰች በኋላ መናገር ጀመረች፡፡

"የሁላችሁንም ፍላጎት እና አስተያየት አድምጠናል፡፡ መልካም ነው፡፡ እስኪ እኔ ደግሞ በተራዬ ጥያቄ ላቅርብላችሁ፡፡ ኢትዮጵያን በመላው አለም ያሳወቃት እውቁ አትሌት አበበ ቢቂላ የሞተበትን እለት እና ዓመተ ምህረት የሚነግረኝ አለ?"

ተማሪዎቹ እርስ በእርስ ተፋጠጡ፡፡ ጎን ለጎን ከመንሾካሾክ በቀር ድምጽ አውጥቶ የተናገረ የለም፡፡

"እሺ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የነበሩት አጼ ኃይለስላሴ መቼ ሞቱ?"

አሁንም ዝም።።

"ይህንንም የሚያውቅ የለም? እርግጠኛ ነኝ አጼ ቴዎድሮስና አጼ ዮሃንስ የሞቱበትን ዓ.ም ትነግሩኛላችሁ?"

ተማሪዎቹ ተደነባበሩ።።

"ይሄ ከከበዳችሁ እሺ ማይክል ጃክሰን የሞተበትን አለት እና ዓ.ም ንገሩኝ?"

አንድ ሺህ አንድ እጆች ተቀሰሩ።። ለአንደኛው ተማሪ እድሉን ሰጠችው።።

"እውቁ የፖፕ ንጉሰ ማይክል ጃክሰን የሞተው ጁን (ሰኔ) ቀን 2009 ዓ.ም ነው" ጥያቄዋን ቀጠለች።።

"እሺ ዊትኒ ሂዩስተንስ የሞተችው መቼ ነው?"

አሁንም አንድ ሺህ አንድ እጆች ተቀሰሩ።። ለአንድኛዋ ልጅ እድሉን ሰጠቻት።። ልጅቷ መልስ የምትመልሰው ቃላቶችን እያሰማመረች ነበር።።

"ዘማሪዋ ወፍ ዊትኒ ሂዩስተን ከዚህ አለም በሞት የተለየችው ፌብራውሪ 11 ቀን 2012 ዓ.ም ሲሆን፤ ሞታ የተገኘችው ቤቨርሊ ሂልተን ሆቴል በሚገኘው የመኝታ ክፍሏ ሻወር ቤት ውስጥ ነው።። የዊትኒ ሬሳ ሲገኝ አፍንጫዋ ደምቶ ነበር" እንደማልቀስ ቃጣት።።

ሶስናም ሆነች ሀጊ እና ጁዲ ከቀጣዮቹ ውይይቶች የተገነዘቡት ወጣቶቹ ከሃገራቸው እውቅ ሰዎች ታሪክ በሺህ ኪሎሜትሮች እንደራቁና ለባህር ማዶ ታዋቂ ሰዎች ታሪክ እጅግ ቅርብ እንደሆኑ ነው።። የነሶስና የበላይ አለቆች ፍላጎትም ይሄ ነበር።። ከእራስ ታሪክ አርቆ የሌላ ታሪክ ቀላዋጭ ማድረግ።።

"እሺ ተማሪዎች ለዛሬ ይበቃናል።። ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።። እንደአስፈላጊነቱ ወደፊት እንገናኝ ይሆናል"

ስትል የተበታተነ ሃሳብ ውስጥ የነበረችው ሶስና ስብሰባውን በተነችው።

የውይይቱ አጀንዳ በነጻ የትምህርት እድል (ስኮላርሺፕ) ላይ ያለመሆኑ ያበሳጫቸው በርካታ ተማሪዎች አዳራሹን ለቀው ሲወጡ በኩርፊያ ለምቦጫቸውን ጥለው ነበር። ሶስና እና ጥንዶቹ ወደሆቴላቸው እንደተመለሱ በጉዳዩ ላይ በስፋት ተወያዩበት። ውጤቱ ያመላከታቸው ነገር ቢኖር ለመዝናኛ ፕሮግራሞች የታሰበው ጣቢያ ወጣቶቹን በቀላሉ በቁጥጥር ስር የሚያውል መሳሪያ መሆኑን ነው። ሶስና አለቆቿ በተለይም ደግሞ ሀሪማን ፓሌይ በእጅጉ እንደሚደሰት እርግጠኛ ሆናለች። ዮናታንም ተመሳሳይ ስሜት እንደሚያድርበት አልጠፋትም።

በጋራ ያዘጋጁትን ሪፖርት ውለው ሳያድሩ ለሃሪማን እና ለዮናታን ላኩ። ዮናታንም ሆነ ፓሌይ የጣቢያው መቋቋም እውን እንደሚሆን ብቻ ሳይሆን የታለመለትን ግብ እንደሚመታም እርግጠኞች ሆኑ። የወጣቶቹ ፍላጎት ከታወቀ ለጊዜው እነሶስናን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያቆያቸው ነገር አይኖርም። የመጀመሪያውን አጠቃላይ ጥናት እጅግ በፈጠነ ሁኔታ አካሂደው የተፈለገውን ውጤት ልከዋል። ለቀሪው የቤት ስራ ከተመለሱና አዲስ መመሪያ ከተቀበሉ በኋላ ያደርሳቸዋል። ዋናው ነገር የወጣቶቹ ፍላጎት መታወቁ ነው። ፍላጎታቸውን ተከትሎ ጣቢያውን መቼ እና እንዴት እናቋቁመው በቀጣይነት የሚታይ አጀንዳ ነው። ለነገሩ ከኢትዮጵያ መንግስት ፍቃድ ማግኘቱም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ቢሆንም መላ ይፈለግለታል።

ሃሪማን ፓሌይ ይህንን ሃሳብ ለሶስና እና ለጥንዶቹ ስለነገራቸው በነጋታው ወደ አሜሪካ ተመለሱ። ሶስና ኢሊኖይስን ጥላት ስትሄድ እንደነበረች ስላገኘቻት ደስ ብሏታል። ሁሉም በመልካም ሁኔታ ላይ ነው። ለነገሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አልቆየችም። ሰለሞን እንኳን "ኢትዮጵያ ሳይሆን ከአሜሪካ ከተሞች አንዱ ጋር ደርሰሽ የተመለስሽ ነው የምትመስይው" ብሏታል። ያም ሆኖ ይህ ከልጇ በዚህ ያህል ርቀት ስትለይ

የመጀመሪያዋ ስለነበር ስጋት ገብቷት ነበር። አሁን ግን ሁሉም ነገር በመልካም ሁኔታ ላይ በመሆኑ ስጋቷ ጠፍቷል።

በተመለሰች በሁለተኛው ቀን ዮናታን ወልዴ ደወለና፤

"ከሁለት ቀን በኋላ አስተርቢክ፣ ኒዘርላንድ በሚደረገው ሰብሰባ ላይ መሳተፍ ስለሚኖርብሽ ወደስፍራው እንድታቀኚ ዝርዝር ጉዳዩን አሌክሳንደር ይነግርሻል" አላት። ስልኳን ዘግታ አልቆየችም። አሌክሳንደር ቢሮው ድረስ ጠርቷት በሰብሰባው ላይ ከእነማን ጋር እንደምትሰበሰብ ነገራት። ሁሉም ዓለም የሚያውቃቸው ሃያላን ሰዎች ነበሩ።

"ከስብሰባው መልስ የካናዳው አይነት ፕሮግራም እንድትሰሪልን እንፈልጋለን። ከስብሰባው ውጪ ከአንዳንዶቹ ጋር ቃለ-ምልልስ ብታካሂጂም አይከፋም። ቃለ-ምልልሱን ጣልቃ እያስገባን ፕሮግራሙን እናስተላልፋለን።"

ይህ ሃሳብ የእሱ እንደማይሆን አልጠፋትም። በሃያላኑ ሰዎች ቃለ-ምልልስ ሹመት እና ጥቅም ማግኘት የሚሻው ሃሪማን ፓሌይ ደውሎ "ጃስ" እንዳለው ገመታለች። ለአለቆቹ ጭራውን የሚቆላ ሰው በመሆኑ እነሱን ያስደስታል፣ ለእኔም ሞገስ ያሰጠኛል ብሎ ያመነበትን ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይልምና።

በትእዛዙ መሰረት ከሁለት ቀናት በኋላ ወደ አስተርቢክ፣ ኒዘርላንድ ተጓዘች። አሌክሲስ ሮቢንስ አብሯት ነበር።

- 18 -

ጣሊያን፣ ፓርሌሞ

ከሪታ ውጭ ሌላ ሴት አገባለሁ ብሎ አስቦ አያውቅም፡፡ ህይወት የአጋጣሚዎች ድምር ውጤት እንጂ ምርጫ ባለመሆኗ የመረጣትን እና እድሜ ልኩን በልቡ ያስቀመጣትን ሴት ማግባት አልቻለም፡፡ ህይወት ምርጫ ብትሆን ኖሮ ስንቱ የተመኘውን ባገኘ፡፡ ሳያገባ የኖረው አንድም በሪታ ምክንያት ነው፡፡ ኋላ ላይ የተቀላቀለው ማህበር ሰበብ እና ምክንያት ይሁነው እንጂ ዋንኛዋ ምክንያት ሪታ ናት፡፡ ልቡ ለሌላ ዝግ ነው፡፡ ማንም የማይከፍተው፡፡ የማያፈቅሩትን ከማግባት የሚያፈቅሩትን እያስታወሱ በትዝታ መኖር ይሻላል በሚለው አቋሙ ጸንቶ ብቻውን ይጓዛል፡፡ ለዮናታን ፍቅር አንዴ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የሚፈጠረው ግንኙነት ፍቅር ሳይሆን የብቸኝነትን ስሜት ለማባረር ራስን የሚሸነግሉበት የጋራ ተቋም ነው፡፡ የጋራ ተቋሙ አባል ለመሆን አልተፈጠረም፡፡

ሪታ እና ቤተሰቦቿ በተባለው እለት እና ሰአት ደረሱ፡፡ የሪታ ልጆች ሶስቱም ሴቶች ናቸው፡፡ አሻንጉሊት ይመስላሉ፡፡ መሃከለኛዋ ከእናቷ ጋር ትመሳሰላለች፡፡ አንዳቸውም የአባታቸውን መልክ አልወረሱም፡፡ ዮናታን እድሜያቸውን ለመገመት ሞከረ፡፡ የመጀመሪያዋ ሃያዎቹ ውስጥ፡፡ ሁለተኛዋ አስራዎቹ ውስጥ፡፡ የመጨረሻዋ ከሰምንት እና ዘጠኝ አመት እንደማትበልጥ ገምቷል፡፡ ሪታ መረጃው ደርሷት ነበርና ዮናታንን ለመለየት አልተቸገረችም፡፡ ተጠመጠመችበት፡፡

"በጣም ትልቅ ሰው ሆነሻል፡፡ ወፍረሻል፡፡ ግርጅፍጅፍ ብለሻል" መናገር የቻለው ይህን ብቻ ነበር፡፡

"አንተም መላጣ ሆነሃል" ሳቀችበት፡፡ የሚወደውን ድምጽና ሳቅ በመስማቱ የወጣትነት ዘመኑን አስታወሰ፡፡ ያ ዘመን ከደስታ

በስተቀር ጭንቀት እና መዋከብ የሌለበት የተረጋጋ ዘመን ነበር። ያ ዘመን የሚያስፈራና በትልቅ በትንሹ ዘራፍ የሚል አለቃ የሌለበትና የእራስ ጌታ የሆኑበት ዘመን ነበር። ያ ዘመን ያለይሉኝታ የሚያስቡትን የሚናገሩበት ነጻ ዘመን ነበር። ያ ዘመን ለገንዘብ የማይንገበገቡበትና ያለውን ተካፍሎ የሚበሉበት የጋርዮሽ ዘመን ነበር። ያ ዘመን በበሬ ወለደ ውሸት የሰውን ስጋ የማይቦጭቁበትና ስምን በሃሰት ጥላሸት የማያቆሽሹበት የንጽህና ዘመን ነበር። ዛሬ ተቀይሯል።

ከባለቤቷ ጋር አስተዋወቀቸው። መልከመልካም ጎልማሳ ነው። ተግባቢና ተጫዋች ይመስላል። ሲልቪዮ ካርሎ ሲያምፒ ብሎ ተዋወቀው። ሪታና ዮናታን ስለቀድሞ ህይወታቸው ሲያወሩ ተገርመው ነበር የሚያደምጧቸው። ጆቫኒ ፋንፋኒ የረሳውን ነገር እያስታወሰ ከት ብሎ ይስቃል። ሪታ ነጻ ሆናማውራቷ ለዮናታን ቢከብደውም በባለቤቷ ገጽታ ላይ የተለየ ነገር አልተመለከተም። በተንተባተበ እንግሊዝኛ፦

"ዮናታንያኔ እኮ እኔን ካላየህ ምግብ አይበላልህም ነበር" አለችው ሁሌም ሊመለከተው የሚጓጓለት ላቄን አስቀድማ፣

"የልቤ ንግስት ነበርሽ" የፊቱ ቀለም እየተለወጠ መለሰላት።

"ለመሆኑ አሁንም እንደበፊቱ ታፈቅረኛለህ?"

"ጎግልጽነቷ በዛ። ነው ወይስ እብደት ጀማምሯታል? ሲል ከሰላሰለ በኋላ ባለቤቷን ተመለከተው። እንኳን ሊቀና በጨዋታቸውና በቀልዳቸው ተደስቶ እየሳቀ ነበር።

"እንደማላገኝሽ ባውቅም ከልቤ አላወጣሽም" ርዕሱን ለመቀየር ቢፈልግም ሪታ እሺ አላለችውም።

"ትዝ ይልሃል ቱክሳስ ገደል አጠገብ ካለው ጫካ ወስደህ በግድ ልትደፍረኝ የሞከርከው? እነማሙሽ ባይደርሱልኝ ኖሮ ድንግልናዬን መግሰስህ አይቀርም ነበር" ጆቫኒ ጣልቃ ገባ፦

"መች ቀረልሽ? ያስረከብሽው ለእሱ አይደል?!"

"በፍቃደኝነት ነዋ። በግድ ሊደፍረኝ የነበረ ጊዜ ምን ብሎ ወደጫካ እንደወሰደኝ ታውቃላችሁ? እጋምና ቀጋ እንልቀም፣ ምን

ብዬ ልጠርጥር? እጅሬ ለካ ተንኮል አስቦ ነው" ሳቋን ለቀቀችው፡፡ ልጆቹ እናታቸው የምትናገረው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ሰለጓጉ ጆቫኒ እየተረጎመላቸው ነበር፡፡ ዮናታንን እንደልዩ ፍጡር እያዩት ነው፡፡ ካርሎ ሲያምፒ ሚስቱ በምትናገረው ነገር ከመሳቅ እና ከመገረም በቀር በፊቱ ላይ ለውጥ አልታየም፡፡ መስመር ያለፈ ግልጽነቷን የለመደው ነው፡፡ እንደልቧ ትጫወት እንጂ ትዳሯን አክባሪ ሴት እንደሆነች ያውቃል፡፡

የባጥ የቆጡን ሲቀባጥሩ ቆዩ፡፡ የሪታ ልጆች ዮናታንንና ፓተርሰንን ተላምደው ጨዋታ ጀምረዋል፡፡ የመጨረሻዋ ልጅ ዮናታን ላይ ጥብቅ ብላ አልላቀቅ ብላለች፡፡

"ዮናታን የሆነስ ሆነና ፓርሌሞ ምን እግር ጣለህ?" አለችው ሪታ፡፡

"ለስራ" የሚል አጭር መልስ ሰጣት፡፡ "የተማርኩትና የምኖረው አሜሪካ ቢሆንም በስራ ምክንያት በተለያዩ ሀገራት እዞራለሁ፡፡ ለስራ በሄድኩበት ነው ከጆቫኒም ጋር የተገናኘነው፡፡" ድፍን ያለ መልስ ሰጣት፡፡

ለሁለት ቀናት ያህል አብረው ቆይተው ወደሮም ሊሄዱ ሲነሱ ሲልቪዮ ካርሎ ሲያምፒ ዮናታንን እንዲህ አለው፡-

"ወደ ሮም መጥተህ የክብር እንግዳችን ብትሆን ደስ ይለናል" ሪታ በባለቤቷ ንግግር ስለተደሰተች ከንፈሩ ላይ ሳመችው፡፡

"እጎት ሮማ መጥተህ ብትጠይቀን በጣም ደስ ይለኛል፡፡ የመጨረሻዋ ልጅ ነበረች፡፡ ጸጉሯን እያሻሸ ቃል ገባላት፡፡ እሷ ብቻ በምታውቀው ምክንያት "እጎት" እያለች መጥራት ጀምራለች፡፡ በግዱ የሚያፈቅራትን ሪታን እና ቤተሰቦቿን ተሰናበታቸው፡፡ አድራሻቸውን ሰጥተውት ተሰናበቱት፡፡

****

እነሪታን ከሸኘ በኋላ ያሳለፈው ጊዜ በድብርት ስሜት የታጀበ ነበር፡፡ የልጅነት ጥቅረኛው ሪታ፣ ከልቡ የማያወጣት ሪታ፣ የልጅነት (የሴትነት) ክብሯን አሳልፋ የሰጠችው ሪታ፣ የፈለገችውን

በነጻነት የመናገር ድፍረት ያላት ግልጽዋ ሪታ.....የተዳፈነውን የፍቅር ረመጥ ቆስቁሳ ማቀጣጠል ጀምራለች፡፡ ሲያያት፣ በቅርበት ሲመለከታት ባሰበት፡፡ ግልጽነቷ ያው ነው፡፡ በባለቤቷ ፊት ሊደፍረኝ ነበር፣ በኋላ ግን በፍቃደኝነት ድንግልናዬን ሰጠሁት ብላ ለመናገር አላፈረችም፡፡ ሌላ አጋጣሚ ታወሰው፡፡ ጫካ ወስዶ ሊደፍራት ከሞከረ በኋላ ለሳምንት ያህል ዘግታው ነበር፡፡ ጨክናበት አልቀረችም፡፡ ራሷ አናገረችው፡፡ ጓደኝነታቸው ቀጠለ፡፡ ከሳምንት በኋላ የደነገጠበትን ብቻ ሳይሆን የተደሰተበትንም ጥያቄ ጠየቀችው፡፡

"አሁን ፍቃደኛ ነኝ፤ ወሲብ መፈጸም እንችላለን?"

ምክንያቷን ጠየቃት፡፡

"በግድ ልትደፍረኝ በመሞከርህ ተናድጄ እንጂ እወድሃለሁ"

የሚሆነው ሆነ፡፡ የህመም ስሜት ቢሰማትም እየፈነጠዘች ወደ ቤቷ ሄደች፡፡

"ምን ተገኘ?" ጆቫኒ ጠየቃት፡፡ ነገረችው፡፡

"ምን?" አንቆ ሊደበድባት ሞከረ፡፡

"አፈቅረዋለሁ፡፡ ፈልጌ ለሰጠሁት ምን ቤት ነህ?"

ዮናታንን ፍለጋ ሄደ፡፡ ቴክሳስ ገደል ሸርተቴ ሲጫወት አገኘው፡፡

"እህቴን በጥሰህ ሸርተቴ ትጫወትልኛለህ!?" ይሄው ነው፡፡ በጣም ሲናደድ የሚናገረውን አያውቅም፣ ቃላት አይመርጥም፡፡ ተደባደቡ፡፡ ጓደኞቻቸው በመገላገል ፈንታ በጆቫኒ ንግግር ተገርመው እየተንከባለሉ መሳቅ ጀምረው ነበር፡፡ ሲደክማቸው አቆሙ፡፡ ወሬው ታላቪያ ጋስፔሪ ጆሮ ደረሰ፡፡

"ዋናው ኔጌር በጊድ አሌመሁኑ ነው፡፡ ተስማምቼው ከቴናቶ ሌላው ሚን አጌባው?" አራዳው ሽሜ የወሬኞችን አፍ አዘጋ፡፡ ጆቫኒ እና ዮናታን ተጨካክነው አልቀሩም፡፡ ታረቁ፡፡

ከትውስታው ሲመለስ ፈገግ አለ። ሁለቱ የእረፍት ሳምንታት እንደምንም አለቁ። በቆይታው ደስተኛ ነበር - ሪታ ደርሳ በጠበጠችው እንጂ፣ ጆቫኒን ሲሰናበተው፡-

"ማሙሽ በቆይታችን ደስተኞች ነበርን። ከልጣ እናመሰግናለን። አንጠፋፋም። እንጠያየቃለን።" አቅፎ አቆየው፣

"እኔም እጅግ ደስተኛ ነኝ። ቶሎ እንደምንገናኝ ተስፋ አለኝ።"

ዮናታን ፓርሌሞን ሲለቅ ብቻውን አልነበረም። ያገረሸውን የሪታንም ፍቅር በልቡ ይዞ ነበር።

- 19 -

አስተርቢክ፣ ኒዘርላንድ

እጅግ የደስ ደስ ባለው ነፋሻ ቀን ሽንጠ ረጣዥሞቹ አውቶሞቢሎች የክብር እንግዶቻቸውን እየያዙ አስተርቢክ፣ ኒዘርላንድ ወደሚገኘው የቢልደርበርግ ሆቴል አመሩ። በሆቴሉ ስም የተሰየመ የምስጢር ማህበር (ቡድን) እንዳለ ከኢስቱሊን መጽሃፍ ላይ ማንበቧን ታስታውሳለች። የምታስታውሰው ይህን ብቻ አይደለም። የቡድኑ አባላት ግዙፍ የሆኑ የአለማችንን ባንኮች እና የንግድ ተቋማት የተቆጣጠሩ ሃያላን መሆናቸውንም ማንበቧን ታስታውሳለች። ከእንደዚህ አይነት ሰዎች ጋር ለመሰብሰብ መገኘቷ ህልም ሆኖባታል። አንዳንዶቹን በካናዳው ስብሰባ ላይ አይታቸዋለች።

ዳር ሆኖ ለሚታዘብ ተራ እንግዶች እንዳልሆኑ የትከሻቸው ክብደት ያሳብቅለታል። አካባቢው በደህንነት ሃይሎች ተሞልቷል። ማዳመጫ የሰኩት ሃይሎች አለባበስ ይማርካል። በጥቁር ሙሉ ሱፍ ሸክ ብለዋል። የጸሃይ መከላከያ (ራስን መከለያም ሊሆን ይችላል) መነጽር ከለበሱት ልብስ ጋር ሄዷል - "ማች" አድርጓል።

እንግዶቹ ከውብ መኪኖቻቸው ላይ እየወረዱ ወደስብሰባው አዳራሽ ሲያመሩ ማንነታቸው ለየ። አሌክሲስ ከዚህ ቀደምም ያውቃቸው ነበርና አስተዋወቃት። በግዙት ላይ የሚገኘው ፖላንዳዊ ፖለቲከኛ፣ የኒዘርላንድ ልኡል፣ የቀድሞ የቤልጂየም ጠቅላይ ሚንስትር፣ የወቅቱ የሲአይኤ መሪ፣ የፕሬዚዳንት አይዘንሃወር የቀድሞ አማካሪ.....ሌሎችም ነበሩ። ከአስራአንድ ሃገራት የተውጣጡ ሃምሳ ያህል የልዑካን ቡድን አባላት (አስራ አንድ እውቅ አሜሪካውያንን ጨምሮ) በስፍራው ተገኝተዋል። ሶስና አራሷን ከሃያላኑ ሰዎች ጋር አነጻጸረችና ድምቢጥ ወፍ የሆነች

ያህል ተሰማት፡፡ አሊክሲስ እቧና ሌሎችም ጋዜጠኞች በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀምጠዋል፡፡ ስብሰባው ለሶስት ቀናት እንደሚቆይ አውቃለች፡፡

ተሰብሳቢዎቹ ቦታ ቦታቸውን እንደያዙ ጊዜያዊው የአመራር ኮሚቴ ሊቀመንበር የመክፈቻ ንግግር ለማድረግ ወደመድረኩ አመሩ፡፡ ጸጥታ ሰፈነ፡፡ ከንግግሩ በኋላ ስብሰባው ተጀመረ፡፡ በምዕራብ አውሮፓ ውስጥ እያደገና እየተስፋፋ ስለመጣው ጸረ አሜሪካ እንቅስቃሴ በስፋት ተወያዩ፡፡ በየአመቱ የሚያካሂዱት ዓለም አቀፍ ጉባኤ በተጠናከረ መልክ እንዲቀጥል ተስማሙ፡፡ በዩናይትድ ስቴትስና በምዕራብ አውሮፓ ሀገራት መሃል ያለውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የመከላከያ ሁኔታ በምን አይነት መልክ ማጠናከር እንደሚገባቸው ሃሳብ ተለዋወጡ፡፡ ፊታቸው ላይ የሚነበበው ስሜት ስብሰባው በየአመቱ ቢካሄድ ቅር የማይላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የስብሰባው መሳካት እዘጋጆቹ በአመታዊው ጉባኤ ይቀጥሉ ዘንድ ብርታት ሆናቸው፡፡

በዚህ የተደሰተው የክበቡ ቋሚ ጸሃፊ ፖላንዳዊ ፖለቲከኛ ወደኒዘርላንድ ልዑልና ወደቤልጅየሙ ጠቅላይ ሚንስትር ተጠጋና በቀጣይነት መከናወን አለበት ብሎ ያሰበውን ሃሳብ አዋያቸው፡፡ በደስታ ተቀበሉት፡፡ ሃሳቡን በእጅጉ የወደዱት ልዑሉ ወደ ሲአይኤው መሪ ቀረብ አሉና፡-

"ሃሳቡን በተመለከተ የምታክለው አስተያየት ይኖር ይሆን?" ሲሉ ጠየቁት፡፡

"ጥቂት ይታገሱኝ ጌታዬ" አለ የሲአይኤው መሪ በትህትና፡፡ ፊቱን የአይዘን ሃወር አማካሪ ወደነበረው ሰው በማዞር ምክር ጠየቀ፡፡

"እንከን የማይወጣለት ሃሳብ ነው" የሚል ምስክርነትን አገኘ፡፡ ተያዩና ፈገግታ ተለዋወጡ፡፡

በተጣዮቹ ተከታታይ ሶስት አመታት ፈረንሳይ፣ ጀርመን እና ዴንማርክ የቢልደርበርግ ቡድን አባላትን ስብሰባ ለማስተናገድ

ፍቃደኝነታቸውን አሳዩ። አሜሪካም ከሶስቱ ሃገራት በኋላ ቻንትሊ ቨርጂኒያ ውስጥ በሚገኘው ማርዮት ሆቴል ስብሰባውን ታስተናግድ ዘንድ ፍቃድ አገኘች። በመሃል እድሜው በሃምሳዎቹ መጨረሻ ላይ የሚገኘው የፎርድ ፋውንዴሽን ተወካይ እጁን አወጣ። ቅበረር ጀነን ባለ ድምጽ እንዲህ አለ፦

"የወከልኩት ፎርድ ፋውንዴሽን ለሶስት ቀናት የተካሄደውን ስብሰባ ሙሉ ወጪ እንደሸፈነው ሁሉ የቀጣዮቹንም ጉባኤዎች ወጪ ለመሸፈን ሙሉ ፍቃደኛ ነው። ሌላ ግለሰብም ሆነ ድርጅት እንዳታስቸግሩ። በእኔ ይሁንባችሁ፤ ሙሉ ወጪያችሁ በድርጅቴ ይሸፈናል" ተጨበጨበለት። አጨብጫቢዎቹን በኩራት ከቃኘ በኋላ እጅ ነሳ። ሶስና አባቷ ይደጋግመው የነበረውን የሃገሯን ተረት አስታወሰች። "ወይ ያለው ማማሩ!"

ከሶስት ቀናት በኋላ ስብሰባው ተጠናቀቀ።

ተሰብሳቢዎቹ ወደየመጡበት አልተመለሱም። ሁለት ጉዳዮች ይቀሯቸው ነበር። አንደኛው ለአውሮፓ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት ዕጩ ተወዳዳሪ ለሆኑት የቡድኑ አባል የእራት ግብዣ ማዘጋጀት ሲሆን፤ ሁለተኛው ከ1998-2001 ዓ.ም ቢልደርበርግን በሊቀ-መንበርነት የመሩት እና በቡድኑ ውስጥ ረዥም አመት የቆዩት ባለስልጣን ባዘጋጁት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ መገኘት ነው። ስብሰባውንና ጋዜጣዊ መግለጫውን መቀላቀል ስላልተፈለገ ጋዜጣዊ መግለጫው ለብቻ እንዲዘጋጅ ሆኗል። የእራት ግብዣውም ሆነ ጋዜጣዊ መግለጫው የሚከናወነው በመጨረሻ ሁለት ቀናት በመሆኑ፤ ሶስናም ሆነች አሌክሲስ ተጨማሪዎቹን ቀናት ይቆዩ ዘንድ ግድ ብሏል። የተያዘው የጊዜ መርሃ-ግብር ምሽት ላይ በመሆኑ ጋዜጠኞቹ በቀን ከተማዋን ተዘዋውረው የመጎብኘት እድል እንዲያገኙ በር ከፍቶላቸዋል።

ሶስና እድሉን በአግባቡ ተጠቀመችበት። ቀናቱን ከተማውን በመጎብኘት አሳለፈቻቸው። በእጅጉ ያስደሰታት ከዳንኤል ኢስቱሊን ጋር መገናኘቷ ነው። ከመግለጫው በኋላ እራት እንበላለን ብሏታል። ሰፊ ውይይት ሊያደርጉ እንደሚችሉ

አምናለች፡፡ ሶስና እና አሊክሲስ በእራት ግብግቡ ላይ አብረው ነበሩ፡፡ ለአውሮፓ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት እጩ ተወዳዳሪ የሆኑትን ባለስልጣን በምልክት እየጠቆማት፡-

"እጩ ተወዳዳሪነታቸውን በድል እንደሚወጡ እርግጠኛ ሁኚ" አላት፡፡

"በምን እርግጠኛ ሆንክ?"

"ሽርጉዱ፣ የእራት ግብግቡና የተንዛዛው ወጪ ያለምክንያት መስሎሻል? የቢልደርበርግ አባል ውድድሩን እንደማይወድቅ ከባለፈ ተሞክሮ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሁልጊዜም አሸናፊዎች ናቸው፡፡"

ሃያልነታቸውን ለአፍታም ቢሆን መርሳት አልነበረብኝም፣ አለች በውስጧ፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ዳንኤልን ስታገኘው ተደነቀች፡፡

"ፍቃድ እንዴት ሰጧችሁ?"

"በሽታቸው እኮ ጉባኤው እና ዝግ ስብሰባው ላይ እንጂ ጋዜጣዊ መግለጫው ላይ አይደለም፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ መገኘታችንንማ ይፈልጉታል፡፡ እንደሚወራብን ድብቆች አይደለንም ለማለት፡፡ የሚዲያ ትችትን በጸጋ እንቀበላለን ለማለት፡፡ ጋዜጠኞች ከእኛ ጋር ለመወያየት ነጻነት አላቸው ለማለት፡፡ ይሄ ሁሉ ጭምብል ነው፡፡ እራስን ከተጠያቂነት ለማውጣት የሚከላከሉበት ጭምብል፡፡ በጋዜጠኞች ፊት ክበባችን ለዓለም መልካም ነገርን ለማበርከት የሚተጋ ክበብ ነው ብሎ ለማላገጥ ነው በመግለጫው ላይ እንድንገኝ የፈቀዱልን፡፡ በመገኘታችን ደስተኞች ነን" አላት አብረው የነበሩትን ጓደኞቹን እያስተዋወቃት፡፡

የፖለቲካ ጋዜጠኛው ኬኔዝ ቨጌል፣ ጆን ሮንሰን የ "Them: Adventures With Extremists" መጽሃፍ ደራሲ፣ ሮበርት ኢሪንገር የ "The Global Manipulators" መጽሃፍ ደራሲ፣ ክርስቶፈር ሆዳፕ

የ"Conspiracy Theories and secret Societies For Dummies" መጽሃፍ ደራሲና ሌሎችም.....።

ከታላላቅ ደራሲዎች ጋር በመተዋወቋ እጅግ ደስተኛ ነበረች።

"ይፋዊ ጥሪው ስለቀላቀለን (በእነሱ መልካም ፍቃድ) ያለስጋት ተጫወቺ። አለቆችሽ ከእኛ ጋር በመገናኘትሽ አይቆጡሽምና ነጻ ሆነሽ አውሪ" አላት እየሳቀ።

"ነግሬሻለሁ፣ ይሆን እድል ዳግም ላታገኚው ትችያለሽ" በተቃራኒ ጎዳና ላይ የሚጓዙትን ጋዜጠኞች እና ጸሃፍት በጋራ መድረክ ላይ ያገናኙትን ሃያላን በልቧ አመሰገነቻቸው።

"የሚቃወሙንን ጋዜጠኞች በመግለጫው ላይ ጋብዟቸውና የሚያስቡንን አይነት ሰዎች፣ የሚያስቡንን አይነት ቡድኖች ያለመሆናችንን በተግባር እናሳያቸው" ሲሉ የጋበዟቸው ከ1998-2001 ዓ.ም ቢልደርበርግን በሊቀመንበርነት የመሩትባለስልጣን እንደሆኑ ሰምታለች።

ስብሰባው በመጀመሩ ጸጥታ ሰፈነ። ፖላንዳዊው ፖለቲከኛ "ጋዜጣዊ መግለጫውን የሚሰጡልን....." በማለት ባለስልጣኑን ወደመድረክ ጋበዟቸው፣ ንግግራቸውን ጀመሩ፦

"ብዙዎች በተለይም ደግሞ በይፋ የሚቃወሙን ጋዜጠኞች ከበባችን በሰብሰባ ጊዜ ሙሉ ነጻነት የማይሰጥ፣ ለሚዲያ ትኩት ያጋልጠናል በሚል ስጋት ተወያዮቹ ሃሳባቸውን እንዲገቱ የሚያስገድድና ዓለምን ለማመሳቀል የሚተጋ ክበብ (ቡድን) ነው በማለት ተቃውሟቸውን ያቀርባሉ። ፍጹም ሃሰት ነው። በስብሰባ ጊዜ ሙሉ ነጻነት የሚሰጥ፣ ተወያዮቹ ሃሳባቸውን እንዳይገቱ የሚያበረታታና ለአለም መልካም ነገርን ለማበርከት የሚተጋ ክበብ ነው። የምንወነጀለው ለአንድ አለም አስተዳደር ተግባራዊነት ይተጋሉ በሚል ከሰ ነው። እጅግ የተጋነነ አባባል ነው። ለአንድ አለም አስተዳደር ተግባራዊነት ሲሉ መርነትን ያስነሳሉ፣ ሃገራትን በኢኮኖሚ ድቀት ይጎዳሉ፣ በላብራቶር ውስጥ የፈጠሯቸውን በሽታዎች ያሰራጫሉ፣ በክትባት ስም የህጻናትን እድገት ገትተው

ወደመቃብር አፋፍ ይመራሉ ብሎ ነገር ምንድነው? እጅግ የሚገርመው ብቻ ሳይሆን የሚያበሳጨው ደግሞ በሰይጣን ያምናሉ፣ ከሰይጣን ጋር ተባብረው ይሰራሉ የሚለው ውንጀላ ነው። ምን ለማግኘት ብለን ነው ከሰይጣን ጋር የምንተባበረው? መሰረተ-ቢስ ውንጀላና ስም ማጥፋት ነው……

"ሰዎች እርስ በእርስ እንዲተላለቁ፣ በበሽታ እንዲማቅቁ፣ በችጋር እንዲሳቀቁ አንፈልግም። ለዚህም ተጠያቂ አይደለንም ብለን እናምናለን። አንድ የሆነ ማህበረሰብ እንዲኖር ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው የሚለው ሃሳባችን የተጣመመ ትርጉም እንዲሰጠው አንፈልግም።"

በቂ ሃሳብ ነው፣ በውይይት ይዳብራል ብለውያመኑበትን ተናግረው ከጨረሱ በኋላ ቀሪው ቆይታ በጥያቄና መልስ አካሄድ እንዲቀጥል በማሰባቸው ጥያቄዎች መቅረብ ጀመሩ። የመጀመሪያውን ጥያቄ ያቀረበው በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ብሰለት እንዳለው የተመሰከረለት ኬኔዝ ቮጌል ነበር።

"ቡድናችሁ በዓለማችን ሃያላን ስብስብ የተመሰረተና ለአንድ አለም አስተዳደር የሚተጋ ቡድን መሆኑን ይክዳሉ?"

"በመላው ዓለም አንድ የሆነ ማህበረሰብን መፍጠር ጉዳቱ ምን ላይ ነው?" ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት።

"አንድ የሆነውን ማህበረሰብ ለመፍጠር የተፈለገው ከቅን ልቦና በመነጨ አስተሳሰብ ቢሆን ኖሮ እንደሚሉት ጥቅሙ ያመዝን ነበር። ነገር ግን የአለምን ህዝብ በባርነት ለመግዛት ታስቦ የሚፈጠረው የአንድ አለም አስተዳደር ሀሳና ስርአት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በእጅጉ ያመዘነ ነው"

"ምክንያትህን ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"በሚገባ!" አለ ቮጌል በልበሙሉነት። "በሚገባ ላስረዳዎት እችላለሁ። የሃገራትን ሉአላዊነት፣ መብትና ነጻነት ይጋፋል። ህልውናቸውን ይፈታተናል። ለአንድ አለም አስተዳደሩ ተግባራዊነት በሚተጉ ሃያላኖች መንገድ እንዳይዘጉ ያስገድዳቸዋል። ከመስከረም

12 እስከ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የአሜሪካ፣ ካናዳና ሜክሲኮ ሃገራት ተወካዮች በምስጢር ካናዳ ውስጥ ያደረጉት ስብሰባ ከድጋፍ ይልቅ ተቃውሞ የገጠመው ለምን ይመስልዎታል? ህዝቡ ጉዳዩ እንደሚያመዝን በመገንዘቡና ለባርነት እንደሚዳርገው በማወቁ ነው፡፡ መረጃ የያዘ ማይክሮ ቺፕስ በሰዎች ሰውነት ውስጥ ቀብሮ የአለምን ህዝብ በባርነት ለመግዛት የሚተጋ የአዲስ አለም አስተዳደር ፈጣሪ ለህዝብ እናስባለን ቢል እንዴት ነው ተአማኒነት የሚኖረው?"

ባለስልጣኑ በንዴት እጃቸውን አወናጨፉና፡-

"ለበጎ ታስቦ የተደረገውን ሁሉ በመጥፎ አትመንዝሩት" አሉ፡፡ ሊግባቡ ባለመቻላቸው ለሌሎች ጋዜጠኞች እድል ሰጡ፡፡

ቀጣዩ ጥያቄ አቅራቢ ኢስቱሊን ነበር፡-

"ቡድናችን በሚዲያ ነጻነት ያምናል ብለው ያስባሉ?"

"እንዴታ!" አሉ በኩራት እና በፈገግታ፡፡

"በሚዲያ ነጻነት የምታምኑ ከሆነ በዜና ማሰራጫዎቻችሁ አማካይነት ለህዝቡ የምታቀብሉት መረጃ እናንተ የወሰናችሁለት መሆን አልነበረበትማ?!"

"ጥያቄህን ግልጽ ብታደርገው?"

"መረጃው ህዝብ የፈለገው ሳይሆን እናንተ የወሰናችሁለት ነው"

"አንተና መሰሎችህ የምታስወሩት ወሬ ነው፡፡"

"አባላችሁ የሆነው የቀድሞ የሲቢኤስ ኒውስ ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ሳላንት፤ ‹ተግባራችን ሰዎች የሚፈልጉትን ሳይሆን እኛ እንዲያውቁት እና እንዲገነዘቡትየወሰንላቸውን መረጃ መስጠት ነው› ሲሉ በአንደበታቸው መስክረዋል፡፡"

መፈናፈኛ ስላጡ አላባቸው፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫውን ማዘጋጀታቸውን ሳይረግሙትም አልቀሩም፡፡

"የዚህን ጥያቄ መልስ የሚያውቀው እራሱ ሪቻርድ ሳላንት ነው" አሉ በንዴት፡፡

ቀጭን ሊድ እግር ጋዜጠኛ እጁን አወጣ። ከሰማና ቤጤ ስለነበር ንቀውታል። ፈታኝ እና ሞጋች ጥያቄ ያቀርብልኛል ብለው አልገመቱም። እድሉን ሰጡት።

"ቅድም ‹በሰይጣን ያምናሉ ተብለን እንወነጀላለን። ምን ለማግኘት ነው ከሰይጣን ጋር የምንሰራው?› ሲሉ ተደምጠዋል። ቦሂሚያ ጫካ ውስጥ ስለሚካሄደው ሰይጣናዊ የአምልኮ ስርአት ሳይሰሙና ሳያውቁ ቀርተው ነው? አላምንም የሚሉ ከሆነ ጋዜጠኛ በቦታው ተገኝቶ የቀረጸውን ፊልም ላሳይዎት እችላለሁ"

አማራጭ ስላልነበራቸው "እመሰግናለሁ"ን አስቀድመው መግለጫውን ረግጠው ወጡ። የዘለፋ ድምጽና የሹፈት ሳቅ ተከተላቸው። ሶስና ተገርማለች። ያልሞቀውም ያልበረደውም ኢስቱሊን ነው። ኬሪን እና ቡሽን ጨምሮ በርካታ ፖለቲከኞች በዚህ አይነት ሁኔታ ከማይመልሱት ጥያቄ ጋር ሲላተሙ "እመሰግናለሁ"ን አስቀድመው ስብሰባ ረግጠው ሲወጡ አጋጥሞታል። ሶስና በጋዜጠኞቹ ድፍረት ተማርካለች።

****

ኢስቱሊን ቃሉን ጠብቆ እራት ጋበዛቸው። ሶስናን እየተመለከተ፦

"ሰርፕራይዚንግ! አስደሳች የምሰራች አለሽ!" አላት። የሚነግራትን እስክትሰማ ተቁነጠነጠች። ከወር በኋላ ስፔን ውስጥ ነዋሪ መሆን የሚያስችላትን ቅድመ-ዝግጅት እንደጨረሰ አበሰራት። አብረውት ያሉት ጓደኞቹ የጋራ አቋም ስላላቸው ያለስጋት ነበር የሚያወራው። አላመነችም። በህልም አለም ውስጥ ያለች መሰላት። ተጠመጠመችበት። "ማን" አላት ሲያስጠነቅቃት። "ኢሊኖይስን እስክትለቂ ወሬው ማንም ዘንድ መድረስ የለበትም"

ቃል ገባችለት።

"እመነኝ። ማንም አይሰማም" የነበሩት ሁሉ ደስታዋን ተጋሯት። አንዳንዶቹ አብራቸው እንድትሰራ ጠየቋት። አላታሚ

ድርጅትና የግል ራዲዮ ጣቢያ የነበራቸው ናቸው፡፡ የስራ እጦት እንደማያጋጥማት የሚያረጋግጡ ዋስትናዎች ሆነውላታል፡፡

"በተፋጠነ ሁኔታ እንዴት ተሳካልህ?"

"እውቅናዬ እና መጽሃፎቹ የጠቀሙኝ ይመስለኛል"

በመላው ስፔን ተወዳጅ እና የሚከራበት የምርመራ ጋዜጠኛ ነው፡፡ ትንሽ ትልቁ፣ ተራውም ባለስልጣኑም ያከብረዋል፡፡ ያንኳኳው በር ሁሉ ይከፈትለታል፡፡ የሚናገረው ይደመጥለታል፡፡ ለስናን በሙያ ረዳትነት ስም ወደ ስፔይን አምጥቶ እንድትኖር ያደረገውን ሙከራ ማንም አልተቃወመውም፡፡

"እስከዛሬ እንዴት ደውለህ አልነገርከኝም?"

"በእኳል ይሻላል ብዬ ነው፡፡ ስብሰባ ላይ እንደምንገናኝ እርግጠኛ ነበርኩ"

ወደመኝታዋ ብትሄድም እንቅልፍ አልወሰዳትም፡፡ ስትገላበጥ ነጋ፡፡ ጭንቀት ብቻ ሳይሆን ከልክ ያለፈ ደስታም እንቅልፍ እንደሚያጠፋ በተግባር አረጋገጠች፡፡ ወደ አሜሪካ እየተመለሱ በነበረበት ለአትም የደስታ ስካሯ አልለቀቃትም፡፡ እንደተመከረችው ድምፄን አጥፍታ ወደ ስፔይን ኮበለለች፡፡ ልጇም ደስተኛ ነበር፡፡

ክፍል ሦስት

- 20 -

አማሃ፣ ኒብራስካ

እለተ ሰኞ ማለዳ ቤተሰቦቹን በብሩህ ስሜት ተሰናብቶ ወደትምህርት ቤቱ የሄደው የአስራ አራት አመቱ ታዳጊ ሰለሞን አሽክሮፍት ከወትሮው በመዘግየቱ አሳዳጊ እናቱ ስቴሲ እና የቤት ሰራተኛዋ ክላራ ተጨንቀዋል። ያልተለመደ ክስተት በመሆኑም ግራ ተጋብተዋል። የበላው ጅብ አልጮህ አለ። እየመሸ ነው። የአማሃ ነዋሪ ከሰራው፣ ከመዝናኛ ስፍራና ከየጉዳዩ ወደመኖሪያው እያመራ ቢሆንም ሰለሞን ብቅም አላለ።

የሚይዙ የሚጨብጡትን ያጡት ስቴሲና ክላራ ለፖሊስ አመለከቱ። ፖሊስ ከኢንዲያን ሂል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተለይም ደግሞ ከሰለሞን የክፍል ጓደኛ ጥቆማ ደርሶታል። የክፍል ጓደኛው ጆን አሞንስ እንደተናገረው ነጭ ቼቭሮሌት መኪና አቁሞ የነበረ ግለሰብ ሲያሳፍረው እንደተመለከተ ፍንጭ ሰጠ። ከዚያን ቀን በኋላ ሰለሞን አልተመለሰም። ጥቆማው እንዳመለከተው ግለሰቡጠይም፣ አጠር ያለ፣ ደንዳና ሰውነት ያለው ራሰ በራ ሰው ነው። ፖሊስ በምናቡ የሳለውን ሰው ምስል ወረቀት ላይ አሰፈረና በቴሌቭዥን አሳየ። ውጤት አልተገኘም።

ቀናት ቀናትን እየወለዱ ሄዱ። ሳምንታት በወራት ተተኩ። ስቴሲ እና ክላራ በጥለጋ እየባከኑ ነው። ስቴሲ በቴሌቭዥን ቀርባ

"ተወዳጁ ልጄ የት ይሆን ያለኸው?" ስትል ልብን በሃዘን በሰበረ አነጋገር ያለበትን እንዲጠቁማት ተማጸነች፡፡ ከሰድስት ወር በኋላ ሁለት የአስራ ሶስት ዓመት ታዳጊዎች ከዚያው ትምህርት ቤት በመሰወራቸው በወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ፍርሃትና ስጋት ተፈጠረ፡፡ ሆኖም የሚሰወሩ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ ምክንያት መሆን አልቻለም፡፡ በሳምንቱአራት ታዳጊዎች መጠለፋቸው ተሰማ፡፡

ሁኔታው በሰፊው በማነጋገሩ፣ ወላጆችንም ክፉኛ በማስቆጣቱ ፕሬዚዳንት ባራክ ሁሴን አባማ ጣልቃ ለመግባት ተገደዱ፡፡ ወደትምህርት ቤቱ ርእሰ-መምህር በመደወል ከፖሊስ ጋር እንዲተባበርና ጉዳዩን እንዲከታተል ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ተስፋ ሰጪ ውጤት አልታየም፡፡

ከአመት በኋላ ባለንጭ ጸጉር እንግዳ በወይዘሮ ስቴሲ አሽከሮፍት ቤት ዙሪያ ማንጎበብ ጀመረ፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች አያውቁትም፡፡ ለአራት ቀናት ሲያንጎላብብ ከቆየ በኋላ ምሽት ላይ የተመቸ ጊዜ በማግኘቱ ወደ ቅጽር ግቢው ተጠጋ፡፡ ማንም እንደማያየው እርግጠኛ ነበር፡፡ የያዘውን ፖስታ የሚታይ ስፍራ ላይ ካስቀመጠ በኋላተሰወረ፡፡ ዳግመኛ አልታየም፡፡

ደብዳቤው በክላራ አማካይነት ወይዘሮ ስቴሲ እጅ የገባው ጠዋት ላይ ነበር፡፡ በችኮላ ከፈተችው፡፡ በታይፕ ተጽፏል፡፡ ጸሃፊው በአታላዮች እንደተጠለፈ፣ የጠለፉት ሰዎች በወሲብ እና አደገኛ ዕጽ ንግድ ላይ እንዳሰማሩት፣ እያሰቃዩት እንደሆነ፣ መጠሪያ ስሙን በሌላ እንደቀየሩና የሲኦል ህይወት ውስጥ መሆኑን አትቷል፡፡ ስቴሲን እና ክላራን እሪ ብለው እንዲጮሁ ያስገደዳቸው *"እናቴ ስቴሲና ምግዚቴ ክላራ ሁሌም ትናፍቁኛላችሁ፡፡ እንዴት ብዬ እንደማገኛችሁ ግራ ገብቶኛል፡፡ የእናንተው ሰለሞን አሽከሮፍት"* የሚለው አረፍተ ነገር ነው፡፡

ደብዳቤውን ያመጣው ሰው ማንነት እንቆቅልሽ ቢሆንባቸውም ስቴሲ ደብዳቤውን ይዛ ወደ ከተማዋ ፖሊስ አዛዥ ሄደች፡፡

"እጅግ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ነው የሰጠሽን፡፡ ጥበቅ ከትትል አካሂደን ውጤቱን ይፋ እናደርገዋለን" ሲል አሰናበታት፡፡ ወሬው

ሚዲያዎች ዘንድ ደረሰ። የወላጆች ተስፋ አንሰራራ፣ አዲስ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆነ። ጋዜጦች፣ የሬዲዮና የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ሰፊ ሽፋናቸውን ሰጡ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሰለሞንን መሰወር ይፋ ያደረገውና በነዋሪዎች ዘንድ በስፋት የሚነበበው "The Omaha Bee" ጋዜጣ በፊት ለፊት ገጹ *"በጉዲፈቻ ሰም ወደ ኔብራስካ የመጣው ኢትዮጵያዊ ታዳጊ አስነዋሪ የወሲብ ጥቃት ተፈጸመበት"* የሚል ርእስ ይዞ ወጣ። ስቴሲብዙ ተመልካች ባለው የቴሌቭዥን ፕሮግራም "Crimestoppers" ላይ ቀርባ እያነባች የሰጠችው ቃለ-ምልልስ የህዝቡን ልብ አንሰፈሰፈ።

ዜና ማሰራጫዎች ወሬውን ተቀባበሉት። እነ "The Omaha World-Herald," "The Omaha Daily News," "Omaha Tribune," "Omaha's Christian Talk," "News Radio," "Easy Listening" እና "Bott Radio Network" የወንጀሉ ፈጻሚዎች ህግ ፊት ይቅረቡየሚልመልእክት አስተላለፉ።

የተደናገጡት የአማሃ ፖሊስ ዲፓርትመንት ዋና ሃላፊ ቶድ ስሚዝ ወንጀለኞች ለፍርድ እንደሚቀርቡ ቃል ገቡ። ቻርልስ አንደርሰን፣ አል ቫንዱሰን፣ ሎይድ ኖርጋርድ እና ሩሴል ማርቪን ጉዳዩን እንዲከታተሉ ተመደቡ። ቃለ-ምልልሳቸውን የጀመሩት ከአሳዳጊዋ ስቴሲ እሽክሮፍት ነበር። ከሆሊውድ ስመ-ጥር ተዋናዮች መሃል አንዷ የነበረችውና በጤና እክል እንዲሁም በእድሜ ብዛት ከምትወደው ሙያ የተገለለችው ስቴሲ ይጠቅማል ያለችውን መረጃ ተናገረች። ወላጆቹ ያወጡለት ስም ሰለሞን አምባዬ የሚል ቢሆንም ከእሷ ጋር መኖር ከጀመረበት እለት እንስቶ ሰለሞን አሽክሮፍት እየተባለ መጠራት መጀመሩን፣ በ1919 ዓ.ም ከተማዋ ውስጥ የተቀጣጠለውና "Red Summer" በሚል ስያሜ የሚታወቀው አመጽ ባስከተለው የህይወት እና የንብረት ጥፋት መላ ዘመዶቿን በማጣቷ ለብቸኝነት እንደተዳረገች፣ ሰለሞንን ከኢትዮጵያ አምጥታ ማሳደግ መጀመሯን፣ አብረው መኖር ከጀመሩበት ከዛሬ አምስት አመት ጀምሮ በመሳላቸው የእውነተኛ ወላጅ ፍቅር መኖሩን፣ ብቸኝነቷን ያስረሳት ተወዳጅ ልጅ መሆኑን፣ ከትምህርት ቤት ቆይታው ውጪ ከማንም ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑን፣ ትርፍ ጊዜውን ቤት

ውስጥ ብቻ የሚያሳልፍ መሆኑን፣ በአንዳንድ ታዳጊ ወጣቶች ላይ የሚታየው የግብረ-ሰዶማዊነት ባህሪ ፈጽሞ የማይታይበት መሆኑን እና ሌሎችንም ዝርዝር መረጃዎች ሰጠች።

ሊወጡ በር ላይ እንደደረሱ "የሰለሞንን ፎቶግራፍ ልትሰጪን ትችያለሽ?" አላት ቻርልስ እንደርሰን። ግድግዳው ላይ ከተሰቀሉት ፎቶግራፎች አንደኛውን አቀበለችው።

"አመሰግናለሁ ወይዘሮ ስቴሲ። ቸር ወሬ እንደምናሰማሽ ተስፋ አደርጋለሁ"

"አመሰግናለሁ የእኔ ልጅ፤ ፈጣሪ ከእናንተ ጋር ይሁን"

መርማሪ ፖሊሶቹ ከስቴሲ ቃለ-ምልልስ በኋላ ያልረገጡት ስፍራ አልነበረም። ኢንዲያን ሂል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሀጻናት የወሲብ ጥቃት ይፈጸምባቸዋል ተብለው የሚጠረጠሩ ቦታዎች፣ አደገኛ ዕጾች ሊሸጡባቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ስፍራዎች፣ ጓዳ ጎድጓዳው ሁሉ አልቀራቸውም። ህጻናትን በመጥለፍ ሪከርድ ያስመዘገቡ ወንጀለኞች እና ተጠርጣሪዎች መዝገብ ፍተሻ ተካሂደበት። በስተመጨረሻ የአማሃን ከተማ ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ጉድ ያሰኘ መረጃ ይፋ ሆነ። መረጃውን ይፋ ያደረገው ህጻናትን በመጥለፍ እና በማስጠለፍ ተግባር ላይ ተሰማርቶ ቆይቶ እጁን የሰጠው የሃምሳ አንድ አመቱ ጎልማሳ ዊል ብራውን ነው።

ዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት

ዊል ብራውን ቃሉን ይሰጥ ዘንድ በዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ላይ ቀርቧል። ስቴሲን እና ክላራን ጨምሮ የኢንዲያን ሂል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ወላጆቻቸውም ታድመዋል። ችሎቱ ተጀመረ። ዳኛ ዴቪድ ጀራልድ ተከሳሹ መቅረቡን ካረጋገጡ እና መሰረታዊ ጥያቄዎችን ካቀረቡለት በኋላ የክስ ሃተታውን በንባብ አሰሙ።

"በክስ ሃተታው ላይ ተቃውሞ አለህ?" እንደሌለው ተናገረ። ቀሪውንም እውነት በፍታዲኝነት ተናዘዘ። ሰለሞን አሽክሮፍትን

ያስጠለፈው እሱ እንደሆነ እና በችሎት ውስጥ የሚገኘው ጓደኛው አብሮት እንደነበር ሲናገር ዘለግ ላለ ጊዜ የቆየ ጉሩምርምታ ተሰማ። "ጸጥታ.....እባካችሁ ጸጥታ!" አሉ ዳኛ ጄራርድ ጠረጴዛቸውን በመዶሻ እየደበደቡ። ቀሪውንም እውነት ለመስማት ጓጉተዋል።

ዊል ብራውን ቀጠለ። "ኢልክሆርን፣ ኒብራስካ ውስጥ የተደራጀ እና ሀጻናትን ለወሲብ ተግባር የሚያስጠልፍ (የሚጠልፍ) ምስጢራዊ ቡድን አለ። ቡድኑን ያጨናነቁት ታዋቂ ሰዎች እና ባለስልጣናት ሲሆኑ እብዛኛዎቹ ርካሽ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ናቸው። የወሲብ ባሪያዎቻቸውን የሚገዙት በጨረታ ሲሆን የጨረታው አሸናፊ በተተመነለት ዋጋ ይገዛና የወሲብ ፍላጎቱን ያረካል። ሰለሞን አሽክሮፍትም በተመሳሳይ ሁኔታ በሃያሺህ ዶላር ነበር የተሸጠው።"

የአሮጊት ሴት ለቅሶ ተሰማ። ዳኛው ጠረጴዛቸውን በመዶሻ እየደበደቡ "ጸጥታ" አሉና ሴትዮዋን ተመለከቷት። ስቴሲ አሽክሮፍት ነበረች።

ብራውን ቀጠለ። "ሰለሞንን የገዛው ሚካኤል ሲርስ በሲአይኤ ውስጥ አእምሮን የመቆጣጠር ስራ ከሚሰራው ቅርንጫፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ወታደራዊ የመረጃ ክፍል ሹም ሲሆን፤ በሃያ ሺህ ዶላር ገዝቶ የወሲብ ባሪያው አድርጎታል። የቡድኑ አንቀሳቃሽ ሞተር ጆርጅ ኪንግ ቢሆንም መሪው ቦብ ዋድማን የተባለ ግለሰብ ነው።"

ዳኛው ጣልቃ ገቡ። "ይህን ሁሉ በፍቃደኝነት ለመዘርዘር ምን አነሳሳህ?" መልስ ከመስጠቱ በፊት ፊት ለፊቱ ተቀምጦ የሚመለከተውን ሰው ተመለከተው። ባለጉጭ ጸጉሩ ሰው ቅንድቦቹን ወደላይ ከፍ በማድረግ ቀጥል የሚል ምልክት አሳየው።

"ከምስጢራዊ ቡድኑና መሰል ማህበራት ጋር ብዙ ቆይቻለሁ። እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ለመከታተል ቅርብ ነበርኩ። የሚፈጸመው ግፍ ጭንቀት ቢለቅብኝ ፊት ለፊቱ ለሚገኘው ጓደኛዬ አጫወት

ኑት፡፡ ተመላላይ ስሜት ውስጡ ነበር፡፡ በአንድ ነገር ተሰማማን፡፡ እራሳችንን በፍቃደኝነት ለማግለልና ወንጀሉን ለማጋለጥ፡፡

"በዚህ ምክንያት ነው የተፈጸመውን ወንጀል በመዘርዘር ላይ ያለሁት፡፡ የምስጢራዊ ቡድኑ ተባባሪ ሆኜ ብቆይም የልጆች አባት ነኝና ድርጊቱ እያመመኝ መምጣቱ አልቀረም፡፡ አሁን ከጠቀስኩት ጓደኛዬ ጋር ተነጋገርንበትና እሱ ሰለሞን ደብዳቤ እንዲጽፍ አድርጎ ለቤተሰቦቹ እንዲደርስ ሁኔታዎችን ሲያመቻች እኔ በፍቃደኝነት በቁጥጥር ስር ዋልኩ" ዳኛው የሚሰሙት ነገር ህልም እና ፊልም መስሏቸዋል፡፡ ባለንጭ ጸጉሩን ግለሰብ ወደተከሳሽ ወንበር እንዲቀርብ አዘዙት፡፡

"ተከሳሹ የሚለው ሁሉ እውነት ነው?"

"እውነት ነው የተከበሩ ዳኛ፡፡ አንድም ሃሰት የለበትም፡፡ በምስጢር ማህበራት ውስጥ በወንጀል ስራ ላይ ተሰማርቼ ረዥም ጊዜ አገልግያለሁ፡፡ ድርጊቴ ስላንገፈገፈኝ፣ ጭንቀት ስለለቀቀብኝ፣ የአእምሮ መታወክ ስለደረሰብኝ እና ከህሊና እዳ ነጻ መሆን ስለፈለኩኝ ሰለሞን ያለበትን ሁኔታ ለቤተሰቦቹ ለማሳወቅ ጥረት አድርጌ ተሳክቶልኛል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚጥልብኝን ቅጣት ለመቀበል ዝግጁ ነኝ" አለና ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ ዳኛው ሰውዬው በፈጸማቸው ወንጀሎች ክፉኛ እንደተጸጸተ ከሁኔታው ተረድተዋል፡፡

"ስምህን ልትነግረኝ ትችላለህ?"

"አድሪያን ሮክዌል እባላለሁ"

ክፉኛ ደነገጡ፡፡ ስሙን ያውቁታል፡፡ በተደጋጋሚ እሳቸው ዘንድ ቀርቦ ቅጣት ተወስኖበታል፡፡ ከእስር ቤት አምልጠ እንደተሰወረም ሰምተዋል፡፡ አሁን ግን ፊት ለፊታቸው ቆሞ.....

"ከዚህ ቀደም የምንተዋወቅ መሰለኝ?"

"በደንብ እንተዋወቃለን የተከበሩ ዳኛ፡፡በተደጋጋሚ የፍርድ ውሳኔ አስተላልፈውብኛል"

"ሳውቅህ ባለንጭ ጸጉር...." አላስጨረሳቸውም፡፡

"ወድጄ አይደለም፡፡ ከአደገኛም፡ቦ የምስጢራዊ ቡድን አባላት መደበት የምችለው በዚህ አይነት ሁኔታ ብቻ ነው"ነኖ ጌጉራና የተቀየረው ፊቱ ሰው ሰራሽ መሆኑን ተገነዘበ፡፡

"አመሰግናለሁ" ወዲ ብራውን ተመለሰ፡፡

"ሚል ካቡምከበት ቱጥል?"

"ፆርጅ ኪንግን እናዋያሚንን ጨምሮ ሁሉም ዲላስ ውስጥ በሚዘጋጁ የሪፐብሊካን ስብሰባዎች ላይ ሲገኙ የጠለፏቸውን ታዳጊዎች ይዘዋቸው ይሂዳሉ፡፡ ለስብሰባው አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ተብሎ አንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከስብሰባው በኋላ ወሲብ ሊፈጽሙባቸው እንጂ፡፡ በርካታ ህጻናት ታዋቂ ከሆኑ የሪፐብሊካን ፖለቲከኞች ጋር ወሲብ ፈጽመዋል፡፡"

ጄራልድ የደነዘዙ ይመስላሉ፡፡ በስተመጨረሻ ወሳኝ ነው ያሉትን ጥያቄ ጠየቁት፡፡-

"የአስራ አራት አመቱን ታዳጊ ሰለሞን አሽክሮፍትን እንዳስጠለፍከው ነግረኸናል፡፡ የጠላፊውን ማንነት ልትነግረን ፍቃደኛ ነህ?"

"ፍቃደኛ ነኝ ከቡር ዳኛ፡፡ የናታን ወልዴ የተባለ ኢትዮጵያዊ የስክል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር አባል ነው፡፡"

ኢፕሌይ አውሮፕላን ማረፊያ

የተመሰከረበትን የናታን ወልዴን ከኒውዮርክ ወደኒብራስካ ለማምጣት የትእዛዝ ወረቀት የያዙት መርማሪ ፖሊሶች በኢፕሌይ አየር ማረፊያ ተገኝተዋል፡፡

"ይህን የሰው ሰይጣን ማንቁርቱን አንቀን እንደምናመጣው እርግጠኛ ነኝ" አለ የሃምሳዓ ሎይድ ፕርጋርድ፡፡ በእድሜ ትንሹ ነው፡፡ ቅንነት እና ከፍተኛ የሆነ የሰራ ፍላጎት ይታይበታል፡፡

"የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን" መቶአለቃ ቻርልስ አንደርሰን መለሰለት፡፡ የበላይ መሪ ነው፡፡

ወደ ኒውዮርክ በመብረር ላይ ሳሉ በየእራሳቸው የሃሳብ አለም ውስጥ ገቡ፡፡ ዮናታንን በቀላሉ ማምጣት እንደሚችሉ እርግጠኞች ናቸው፡፡ ያገኙት መረጃ እንደሚያመለክተው የስክል ኤንድ ቦንስ አባል ከመሆኑ ባሻገር፣ ኒውዮርክ ውስጥ የጥብቅና ቢሮ ከፍቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ የቢሮውንም የመኖሪያ ቤቱንም አድራሻ ከዊል ብራውን አግኝተዋል፡፡

ከአውሮፕላን ወርደው ወደ ቢሮው አመሩ፡፡ በከተማው እምብርት ከሚገኝ ህንጻ ላይ ይገኛል፡፡ አሳንሰር ውስጥ እንደገቡ፡-

"ቢሮው ውስጥ ባናገኘውስ?"አለ ሩሴል ማርቪን፡፡

"ይገኝበታል የተባለ ስፍራ ሁሉ እንፈልገዋለን እንጂ ሳናገኘው አንመለስም" አል ቫንዱሰን መለሰለት፡፡ ሎይድ ኖርጋርድ እና ቻርልስ አንደርሰን በሃሳቡ ተስማሙ፡፡ በዘጠነኛው ፎቅ ላይ የሚገኘውን ሰፊ ኮሪደር አልፈው "የናታን ወልዴ የህግ አማካሪ" የሚል ጽሁፍ ወደተለጠፈበት ቢሮ አመሩ፡፡ ወፍራም እና አጭር ጸሃፊ ተቀበለቻቸው፡፡

"መርማሪ ፖሊሶች ነን፡፡ ከአማሃ፣ ኒብራስካ፡፡ አቶ ዮናታን ወልዴን ፈልገን ነበር?" አላት ቻርልስመታወቂያውን እያሳያት፡፡

አሊሰን ግሪንውድ በፍርሃትና በጥርጣሬ ታጅባ፡-

"እንድ ጊዜ ይቅርታ...." ካለቻቸው በኋላ ወደውስጠኛው ክፍል ገባች፡፡ ከረባቱን አላልቶ ካሰረው ዮናታን ጋር ወጣች፡፡

"ምን ነበር?" አለ በየተራ እየተመለከታቸው፡፡ የተረጋጋ ለመምሰል ቢሞክርም አልተሳካለትም፡፡ ለጸሃፊዋ የነገሯትን ደገሙለት፡፡ የመጥሪያ ወረቀቱን አስፈርመው ከሰጡት በኋላ እናመሰግናለን ብለውት ሄዱ፡፡ መረጋጋት ያልቻለው ዮናታን ወደሃሪማን ፓሌይ ደወለና እየሆነ ያለውን ነገረው፡፡

"እትጨነቅ፣ ማንነታችንን ስላላወቁ ነው፡፡ ችሎቱ የሚታየው መቼ ነው?" ቀኑን ነገረውና ስልኩ ተዘጋ፡፡ ፓሌይ እትጨነቅ ቢለውም ውሳኔውን በመገመት መጨናነቁ አልቀረም፡፡

- 21 -

ፓልማ፣ ማሎርካ

ስፔይን ላቶጃ ውስጥ ለሶስት ቀናት ያህል ተካሂዶ የነበረው የቢልደርበርግ አባላት ስብሰባ እንደተጠናቀቀ፤ ለሃገሩ ባዳ የሆነ ጥቁር እንግዳ፤ ሶስና በምትኖርበት ፓልማ ማሎርካ ውስጥ ተከሰተ። ፈልጎ ካገኛት በኋላ ራሱን አስተዋወቃት።

"ረድኤት ሃይላይ እባላለሁ። የመጣሁት ስብሰባውን ለመካፈል ነው። ሮበርት አዳምስ በአንቺና በዮናታን ቦታ የተካኝ ሰው ነኝ። ዲግሪዬን የያዝኩት በጋዜጠኝነት ትምህርት ነው።"

ምን ይለፈልፋል በሚል አስተያየት ተመለከተችው። እንዚያ የሰይጣን ልጆች ሊያጠፉት እንደላኩባት ተገነዘበች። ቀጠለ፦

"ስፔይን ድረስ መምጣቴ ካልቀረ አንቺን ፈልጌ ማግኘት ነበረብኝ። ኒብራስካ ውስጥ ዝነኛ ሆነሻል። የአማሃ ጋዜጦች ከአንቺ በስተቀር ዜና የላቸውም። በየእትሞቻቸው ላይ እንደሃገር ንጉስ የህይወት ታሪክሽን እና አሁን ያለሽበትንም ሁኔታ እየዘገቡ ነው። የሃገር ንጉስ እንኳን ያንቺን ያህል ከበሮ አይመታለትም። ዝነኛ የሆንሽውን ሰው አድራሻ ፈልጎ ማግኘት አዳጋች አልነበረም። የስፔይኑ ስብሰባ ደግሞ መልካም አጋጣሚን ፈጠረልኝ።"

"ሬሳዋን ይዘህልንና አለህ?"

ከት ብሎ ሳቀ። ጥርሶቹ ያምራሉ። እጅግ መልከ-መልካም ሰው እንደሆነ አምና ተቀብላለች። እና ቢሆንስ? አሁንም አልተዋ ትም፤ እያደኗት ነው ማለት ነው። ንግግሩ ከሃሳቧ መለሳት።

"እንደዚያ እንደምታስቢ ገምቻለሁ። ብታስቢም እውነት አለሽ። እየሰራሁ ያለሁት ከከዳሻቸው እና ከሚያጠፉሽ ጠላቶችሽ

ጋር ነው፡፡ እመኚኝ ያን ያህል ጨካኝ አይደለሁም፡፡ ደግሞም የሃገርሽ ልጅ መሆኔን እትዘንጊ፡፡"

"ዮናታን ወልዴም እኮ የሃገሬ ልጅ ነበር፡፡"

"እኔ ወክዬ የምናገረው ራሴን ነው፡፡"

"ሰዎቹ ካልላኩህ ለምን ፈልገሽኝ መጣህ?" የሚያወሩት አነስተኛ ካፌ ውስጥ ነበር፡፡

"እንቺ ከከዳሻቸው ሰዎች ጋር እንደምሰራ አልካድኩሽም፡፡ ትእዛዛቸውን የተቀበልኩት ወደ አሜሪካ ለመምጣት፣ ለሚከፍሉኝ ከፍተኛ ገንዘብ፣ እንዲሁም ለማገኘው ስልጣን ስል እንጂ፤ ሃገሬን ከድቼ እና ህዝቤን ሸጬ፤ የእነሱን አላማ ደግፌ አይደለም፡፡"

"ጣቱን የሚጠባ ህጻን ልጅ እመስላለሁ? ምን ማለት ነው አሜሪካ ለመምጣት፣ ገንዘብ እና ስልጣን ለማግኘት.....ስለፈጠረህ ከእድሜህ ጋር የሚመጣጠን ነገር ለመናገር ሞክር፡፡ ለገንዘብ እና ለስልጣን ብለህ አብረሃቸው ለመስራት እስከፊቀድክ ድረስ ያው ነው፡፡ አላማቸውን ደገፍክም አልደገፍክም ህዝብህን ከድተሃል፡፡ ሀገርህን ሸጠሃል፡፡ ምርጫው የእራስህ ነው፡፡ ድርጊትህን እና ከሃዲነትህን ግን በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አጋልጣለሁ፡፡ ይልቅ ለምን እንደፈለግሽኝ ንገረኝና....."

"ወደ ዋናው ነጥብ መጣሽ፡፡ ቀደም ብዬ እንደነገርኩሽ ለገንዘብ እና ለስልጣን ስል ከእነሱ ጋር ብሰራም ሀገሬን ከሴራቸው ለመታደግ ደግሞ ከእነሱ የማገኘውን መረጃ ላንቺ ላቀብልሽ ለእራሴ ቃል ገብቻለሁ፡፡ ማመን እንደሚያዳግትሽ ባውቅም አላማዬ ይህ ነው"

"ከእነሱ ጋር እየሰራህ በተደራቢ ከእኛ.....ከሴራ አጋላጮች ጋር.....?"

"ትክክል! ደብል ኤጀንት ብለሽ ልትጠሪኝ ትችያለሽ፡፡ የተለመደ አሰራር ነው፡፡ ህይወቴን አደጋ ላይ ጥዬ እንደምተባበርሽ አውቃለሁ፡፡ ያለው ብቸኛ አማራጭ ይሄ ነው፡፡ ከገንዘቡ እና

ከስልጣኑ የሃገሬ ህልውና ሚዛን ይደፋብኛልና አላማቸውን የማደናቅፈው ውስጣቸው ሆኜ ነው። ውስጣቸው ካልሆንኩ እንዴት አላማቸውን አውቀዋለሁ?"

አሁንም አላመነችውም። ሊያሳምናት በጥረቱ ገፋ።

"በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ ሊደረግ እየተጠነሰሰ ያለ ሴራን እነግርሻለሁ። እንድናዘዝ አላስገደድሽኝም። ከአንቺ ጋር መስራት የመፈለጌ ማረጋገጫ ይሁንሽ። እንዳንቺ አባባል ሀገሬን እና ህዝቤን ከከዳሁ የማላውቃቸውን ሰዎች ለመክዳት ምን ይከለክለኛል?"

"ንገረኝ። ሴራው ምንድነው?"

"ኢትዮጵያ ድረስ በመሄድ በተማሪዎች ላይ ካካሄድሽው ጥናት ውጤት ላይ የተነሱት ሮበርት አዳምስና ባልደረቦቹ አለምአቀፍ እውቅናን በተጎናጸፈች ድምጻዊት በኩል የእምነት ተቋማት ውስጥ ሰርገው የመግባት እና ሰይጣናዊ ተልእኮ የማስፈጸም እቅድ ይዘዋል። ተማሪዎቹ ለባህር ማዶ ድምጻውያን እና አርቲስቶች ያላቸውን የጋለ ፍቅር በመግንዘብ ነው የሰይጣናዊ አምልኮአቸው ማስፈጸሚያ አድርገው የመረጧት። የሰይጣናዊ አምልኮዋና ተዋናይት በመሆኗ የነሮበርት አዳምስን ጥያቄ በደስታ ተቀብላ ዋለች፣ ሽፋን ያደረገችው ኮንሰርቷን ነው። ሂዮንሴ ኖውልስ ትባላለች። ቀነ-ቀጠሮ የተያዘላት በኢትዮጵያውያን የአዲስ አመት ዋዜማ ነው። የዘጠኝ እና አስር ቀን እድሜ ብቻ ነው የቀረው።።»

በማመን እና ባለማመን መሃል ሆና እያደመጠችው ነው። እሷን ለማጥመድና አሳልፎ ለመስጠት ያዘጋጀው የፈጠራ ታሪክ ቢሆንስ?

"ዋና ተልእኮዋ ምንድነው?" አለችው የተሻለ አትኩሮት እየሰጠችው። የማድመጥ ፍላጎቷም ጨምሯል።

"ከሃይማኖት አባቶች ጋር መነጋገር፣ በቤተ-እምነት ውስጥ መገኘት እና ወዳጅ መስሎ በመታየት በልዩ አቀባበል ራስን ካስተዋወቁ በኋላ የህዝብን ትኩረት መሳብ።"

"ታዲያ ምን ችግር አለው? ብዙ አርቲስቶች የህዝብን ትኩረት የመሳብ ፍላጎት ስላላቸው ሊሆን ይችላል እሷም ትኩረት ለመሳብ ያሰበችው"

"በፍጹም! የትኛውም ሃገር ጎብኚ ከሚደረግለት አቀባበል በተለየ ሁኔታ እንደታቦት ጓንጥላ ተይዞላት የተጋነነ አቀባበል እንዲደረግላት ነው የታሰበው፡፡ እነሮበርት አዳምስ ህዝቡ ለሃይማኖቱ ያለውን ቀናኢነት ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ የተጋነነ አቀባበል ከተደረገላት በአማኙ እና በሃይማኖቱ መሪዎች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን መከፋፈል ገምቺ፡፡ አንደኛው አላማ በሃይማኖት መሪዎች፣ በህዝቡና በእውነተኛ የሃይማኖቱ ተቆርቋሪዎች መሃል መቃቃርን እና ልዩነትን መፍጠር፡፡ አለማዊ ዘፋኝ ብቻ ሳትሆን ሰይጣንን እያሞገሰች የምትዘፍን የሰይጣን ታዛዥ መሆኗንም እንዳትረሺ፡፡ ለሰይጣን ታዛዥ የሆነ ዓለማዊ ዘፋኝ ዘፈንም ሰይጣንም በተወገዙበት ቅዱስ ስፍራ እንዴት ነው ታቦት ይመስል ጓኝጥላ የሚዘረጋለት? የተጋነነ አቀባበል የሚደረግለት? ህጻናት በሚገኙበት ትምህርት ቤቶች እና መርጃ ድርጅቶችም በመገኘት ሰይጣናዊ ምልክቶችን የማስተዋወቅ ተልእኮ እንዳላትም ከነሮበርት አዳምስ እቅድ መገንዘብ ችያለሁ፡፡

"ግዴለም ልዩነታችንን ወደጎላ እናድርገው እና ሃገራችንን እንታደጋት"

"ከእነሱ ጋር እየሰራህ፣ እነሱን እያገለገልክ ሃገራችንን ከሰይጣናዊ ተልእኮ እንታደጋት.....ማመን ይከብዳል" አሁንም ፊጽሞ እምነት እንዳላሳደረችበት ገብቶታል፡፡

"ነገርኩሽ እኮ፣ ለሁለት የተለያዩ እና ባላንጣ ለሆኑ አካላት መስራት በእኔ አልተጀመረም፡፡ እዚያ ጋር ገንዘቡና ስልጣኑ ያስፈልገኛል፡፡ እዚህ ጋር ደግሞ ሀገሬ፡፡ ብታምኚኝ ደስ ይለኛል፡፡ ካላመንሽኝ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ ማድረግ የሚገባሽን ነገር ጠቁሜሽ አለይሻለሁ፡፡ የሰይጣን አምልኮ ፊት-አውራሪዋ ወደ ሃገራችን ሂዳ ለህጻናቱ የሰይጣናዊ አምልኮ ምልክቶችን ከማስተዋወቋ፣ ቤተ-አምልኮ ውስጥ ገብታ አማኙን እና የሃይማኖት

አባቶችን ከማቃቃሯ፣ በአጠቃላይ የሰይጣናዊ አምልኮ እንቅስቃሴዋን ተግባራዊ ከማድረጓ በፊት አቅጁን በድራገጾች አማካይነት አሳውቆ ተቃውሞ የማስነሳት እና የማሰቆም እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት 'መገመት አይከብድም። ጊዜው ደግሞ እጅግ እየቀረበ ነው.....

"በመካከላችን መተማመን እና መተባበር እስካልተፈጠረ ሃገራችንን ከምስጢር ማህበራቱ ሴራ ማዳን አይቻልም። የምትሰሚኝ ከሆነ ቅርባቸው ነኝና (ያውም ነቅተው እስካስወገዱኝ ድረስ) በሃገራችን የሚዶለተውን ሴራ አሳውቅሻለሁ። ተከታትለሽ የማክሸፉ ተግባር ያንቺ የቤት ስራ ይሆናል።"

ዝም አለችው። ለማመንም ላለማመንም ተቸግራለች። "አስቢበት" ብሏት ሲሄድ አላስቆመችውም። እውነቱን ነው? ወይስ እውነት ከሚመስል ሃሳቡ ጀርባ ምስጢራዊ ተንኮል አለ? እውነቱን ከሆነ ሴራው አሳሳቢ ነው። ".....I follow Lucifer" እያለች ስትዘፍን አድምጣታለች። በሰይጣን አምላኪነቷ ዙሪያ ያደረገችውን በርካታ ቃለ-ምልልሶችም ተከታትላለች። የሰይጣን መልእክተኛ የሃገሯን የተቀደሰ ምድር በተለይም ደግሞ የተቀደሰውን የእምነት ስፍራ ታረክስ ዘንድ ሊፈቀድላት አይገባም።

ከኢስቱሊን ጋር መምከር ፈለገችና ወደ ቢሮው ሄደች። በዝርዝር አሰረዳችው።

"ምንጭሽንማ ሙሉ በሙሉ ማራቅ አይገባሽም። እንደውም መልካም አጋጣሚ ነው። ጥንቃቄ እያደረግሽ ልትጠቀሚበት ትችያለሽ። ስታገኚው እሱ በመረጠበት ቦታ ሳይሆን አንቺ በመረጥሽበት ቦታ ይሁን። የምትቀጣጠሩበትን ሰአት በተደጋጋሚ ማዛባት ትችያለሽ። የሚሰጥሽንም መረጃ ከመጠቀምሽ በፊት ታጣሪያለሽ። መሰል ጥንቃቄዎች ካደረግሽ በደንብ ልትጠቀሚበት ትችያለሽ" አለና የመረጃ ምንጩ ስለሆነ ሩሲያዊ <ደብል ኤጀንት> የመረጃ ሰው ነገራት።

ረድኤት ሃይላይን በጥንቃቄ ልትጠቀምበት ወሰነች። "በነገራችን ላይ...." አላት ኢስቱሊን "ስለ ድምጻዊቷ የኢትዮጵያ

ጉብኝት አንዳንድ ነገሮችን በድረ-ገጾች ላይ ተመልከቻለሁ፡፡ ማረጋገጥ ትችያለሽ፡፡ የሃገርሽ ልጅ ከነገረሽ እውነት ጋር የሚዛመዱ ነገሮችን ካገኘሽ ወደ ሃገርሽ ከመሄዷ በፊት የተቃውሞ ጽሁፎችን በድረ-ገጾች ላይ መልቀቅ ትጀምሪያለሽ፡፡"

- 22 -

አማሃ፣ ኒብራስካ

ዮናታን ወልዴ በዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ተገኝቷል። ክሱ የሚሰማበት እለት ነው። ሃሪማን ፓሌይን ጨምሮ ከሲአይኤ ጋር ቅጥተኛ ግንኙነት ያለው እና ሰለሞንን በሃያ ሺህ ዶላር የገዛው ሚካኤል ሲርስ፣ የኒውዮርክ ከተማ ፖሊስ አዛዥ ጄ. ፎክስ ባልድዊን፣ የሃገሪቱ የምስጢር አገልግሎት ሃላፊ ሚካኤል ካርትራይት፣ የማእከላዊ የመረጃ ክፍሉ ሃላፊ እና ኤፍ.ቢ.አይን እንዳሻው የሚያሽከረክረው ናትናኤል ፍሊቸርም ነበሩ። ችሎቱ መታየት ጀመረ። ከሰው ምስክሮች መሃል ዊል ብራውን እና አድሪያን ሮክዌል የተመለከቱትን እና የሚያውቁትን ሁሉ ተናገሩ። የምስክሮችን ቃል እንዲሁም የተከሳሽ ጠበቃን እና የአቃቤ ህግን ክርክር ሲያደምጡ የቆዩት ዳኛ ዴቪድ ጄራልድ ተጨማሪ የምስክሮች ቃል ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጡ።

የሰለሞን አሽክሮፍትን አሳዳጊ ወይዘሮ ስቴሲ አሽክሮፍትን እና የቤት ሰራተኛዋን ክላራን ጨምሮ በርካታ የኢንዲያን ሂል ተማሪዎች ወላጆች ተገቢውን ፍትህ እንደሚያገኙ ተስፋ በማድረጋቸው ልባቸው በሃሴት ተሞልቷል። ወይዘሮ ስቴሲ ሰለሞንን በቅርብ በአካል እንደምታገኘው እርግጠኛ በመሆኗም ደስታዋ እጥፍ ድርብ ሆኗል። መርማሪ ፖሊሶቹ የፍርድ ቤት ትእዛዝ አውጥተው የተጠለፉ ህጻናት ይገኙበታል የተባለውን ስፍራ በማሰስ ሰለሞንን እና ሌሎቹንም ታዳጊዎች ነጻ እንደሚያወጧቸው ቃል ገብተውላታል።

****

ዳኛ ዴቪድ ጄራልድ ወደ ቢሮአቸው በማምራት ላይ ሳሉ የሚከተሏቸው ሰዎች እንዳሉ የተገነዘቡት ዘግይተው ነው።

በመኪናቸው የፊት መስታወት ተመለከቱ፡፡ አልተሳሳቱም፡፡ መስታወታቸው የተሸፈነ (ቲንትድ የሆነ) ሁለት ጥቋቁር መርሰዲሶች እየተከተሏቸው ነው፡፡ እርግጠኛ ለመሆን ፍጥነት ጨመሩ፡፡ መርሰዲሶቹም ፍጥነታቸውን ጨመሩ፡፡ ፍጥነታቸውን ሲቀንሱም ተመሳሳይ ምላሽ አገኙ፡፡ መኪናቸውን ሲያቆሙ ሁለቱም መኪኖች አልፈዋቸው ቆሙ፡፡ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ግን አልወረዱም፡፡

ቢሮአቸው ገብተው ሰባት ደቂቃ ያህል እንደቆዩ ከዚህ ቀደም መጥተው የማያውቁ እንግዶች ገቡ፡፡ ጀራልድ እንግዳ መቀበያው ክፍል ከጸሃፊያቸው ጋር እያወሩ ነበር፡፡ ግር ብለው የገቡትን ሰዎች ሲመለከቱ ደንግጠው ተነሱ፡፡

"ይቅርታ የተከበሩ ዳኛ ጄ. ፎክስ ባልድዊን እባላለሁ፡፡ የኒውዮርክ ከተማ ፖሊስ አዛዥ ነኝ፡፡ ከስራ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ነገሮችን ልናናግርዎት ነበር?"

የሰዎቹ ሁኔታ ያላማራቸው ጀራልድ፣

"ይቻላል ወደውስጠኛው ክፍል እንግባ?" አሉ ፊት ለፊት እየመሩ፡፡ ቢሮው ፊረስ ያስጋልባል የሚባል አይነት ነው፡፡ ከሚቀመጡበት የቆዳ ወንበር ጀርባ የጆርጅ ዋሽንግተን ፎቶ ተሰቅሏል፡፡ ፊት ለፊት ደግሞ የታላቁ የሚዙሪ ወንዝ ምስል፡፡ እንግዳ መቀበያ ወንበሮቹም ከቆዳ የተሰሩ ናቸው፡፡

"ይቅርታ ምን ይምጣ?" አእምሮአቸው ወደ መርሰዲሶቹ ሄዶ ነበር፡፡

"መልካም ብለዋል የተከበሩ ዳኛ፡፡ ቡና ብንጠጣ እንጠላም" ጄ. ፎክስ ባልድዊን ነበር፡፡

እንግዶቹ ማንነታቸውን አስተዋወቁ፡፡ የሲቢኤስ ሚዲያ ሃላፊ፣ የሲአይኤ የቅርብ ሰው፣ የሃገሪቱ የምስጢር አገልግሎት ሃላፊ፣ የማእከላዊ መረጃ ክፍል ሃላፊ እና ኤፍቢአይን እንዳሻው የሚያሽከረክር ሃያል ሰው፡፡ "አሜሪካ ራሷ ነቻ ተጠቅልላ ቢሮዬ የገባችው?!" አሉ ጀራልድ ለብቻቸው እያልጎመጎሙ፡፡ ከነማን ጋር

እያወሩ እንደሆነ አውቀዋል። የሃገሪቱ የምስጢር አገልግሎት ሃላፊ የሆነው ሚካኤል ካርትራይት ሁሉንም በመወከል ወደ ጄራልድ ጆሮ ቀረብ ብሎ የሆነ ነገር አንሾካሾከላቸው። ግብዶኛል በሚል ሁኔታ እራሳቸውን ነቀነቁ። ካርትራይት ከጆሯቸው ላይ ቀና እንዳለ

"ቅሬታ አለ ዳኛ ጄራልድ?" አላቸው ሚካኤል ሲርስ

"በፍጹም!" አሉ ውስጣቸው እየተንዘፈዘፈ። እጅን እግራቸው መንቀጥቀጥ መጀመሩን ሁሉም ታዝበዋል። አመስግነው ወጡ።

ዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት

ለሁለተኛ ጊዜ ጉዳዩ የሚታይበት እለት በመድረሱ የዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት በሰው ተሞልቷል። የኢንዲያን ሂል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች፣ ስቴሲ አሽክሮፍት እና ክላራ ፍትህ የሚያገኙበት እለት በመሆኑ ፊታቸው በርቶ የዳኛውን መምጣት በጉጉት ይጠባበቃሉ። ሃሪማን ፓሌይ፣ ሚካኤል ሲርስ፣ ጄ. ፎክስ ባልድዊን፣ ሚካኤል ካርትራይት፣ ናትናኤል ፍሊቸርና የሃገሪቱ የማእከላዊ የመረጃ ክፍል ሃላፊም ቀደም ብለው ተገኝተው ቦታቸውን ይዘዋል።

ዳኛ ጄራልድ ወደችሎቱ ሲገቡ ሰው ሁሉ በክብር ተቀበላቸው። ችሎቱ ተጀመረ።

"ተጨማሪ የምስክሮች ቃል ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ መያዛችን ይታወቃል" አሉና ጉሮሯቸውን አጸዳዱ። "ነገር ግን ተጨማሪ ምስክሮች መቅረብ ባለመቻላቸው እና ከዚህ ቀደም የተደመጠው የምስክሮች ቃል በቂ ሆኖ በመገኘቱ ውሳኔ እንሰማለን" መርፌ ሲወድቅ እስኪሰማ ድረስ አዳራሹ በጸጥታ ተዋጠ። ውሳኔውን ማሰማት ጀመሩ።

"የክሱ ቻርጅ እንደሚያመለክተው አቶ ዮናታን ወልዴ የተባሉ ግለሰብ የአሰራ አራት አመቱን ታዳጊ ሰለሞን አሽክሮፍትን ከትምህርት ቤቱ ሲወጣ ሆን ብለው ጠብቀው ልሸኝህ በሚል ሰበብ በእለቱ ይዘውት በነበረ ነጭ ቼቭሮሌት መኪና ካሳፈሩት በኋላ

ወደማይታወቅ ቦታ በመውሰድ ሚካኤል ሲርስ ለተባለና በሲአይኤ ውስጥ አእምሮን የመቆጣጠር ስራ ከሚሰራው ቅርንጫፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላለው ግለሰብ በወሲብ ባሪያነት ሸጠውታል የሚል ክስ ቀርቧል። ግራና ቀኙን በጽሞና ሲመለከት የነበረው ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ በቂ የሆነ ማስረጃ ያልቀረበበት እና የግለሰቦችን መልካም ስም በሃሰት ለማጥፋት ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ሴራ ሆኖ በማግኘቱ ክሱ የቀረበባቸው አቶ ዮናታን ወልዴ በነጻ እንዲሰናበቱና ያሲያዙት የዋስትና ገንዘብ ካለም እንዲመለስ ሲል ወስኗል። መዝገቡ ተዘግቷል"

በፊተኛው መስመር ላይ ተቀምጠው የነበሩት እነሃሪማን ፓሌይ ዮናታን ወልዴን እንኳን ደስ ያለህ እያሉ ሲጨብጡት፣ የኢንዲያን ሂል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ወላጆች፣ ስቴሲ አሽክሮፍትና ክላራ ግን መብረቅ የወደቀባቸውን ያህል በተቀመጡበት ደንዝዘው ቀሩ።

- 23 -

ማድሪድ፣ ስፔይን

በዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድቤት ታዳጊውን ሰለሞን አሽከሮፍትንና ዮናታን ወልዴን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ ሀገርም ድሩን በማነጋገር ላይ ነው። አቃቤህግ ይግባኝ እንደሚጠ ይቅ ቢያሳውቅም፣ የጄራልድን ውሳኔ የተቃወሙ የተማሪዎች ወላጆችና የከተማ ዋነዋሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ቢወጡም ከቁብ የቆጠራቸው የለም። የከተማዋ ፖሊስ በፍርድቤት አሰራር ጣልቃ አልገባም ሲል ማላገጥ የሚመስል አስተያየት ሰጠ። ሚዲያዎች ኡኡታቸውን ጀመሩ። የሚሰማቸው አላገኙም። ወሬው ከሃገር ውስጥ አልፎ ባህር-ማዶ ሚዲያዎችም ዘንድ ደረሰ። በትሪንዴይ አሳታሚ በኩል አስገራሚውን የፍርድቤት ውሳኔ የያዘው "The Omaha daily News" የተላከለት ዳንኤል ኢስቱሊን ለሶስና በብስጭት ጋዜጣውን እያሳያት፣

"የእነዚህን የሰይጣን ልጆች ሃይልና አቅም የት ድረስ እንደሆነ አየሽው አይደል? የፍርድቤት ውሳኔም እስከማስለወጥ ይደርሳል። እርግጠኛ ነኝ ዳኛው ያለምንም ተጽእኖ እንደዚህ አይነት ውሳኔ አልወሰኑም" አላት በእርግጠኝነት። በማግስቱም እጁ የገባው "The Omaha Daily News" እና ሌሎቹም ጋዜጦች ዳኛ ጄራልድ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ተጽእኖ የፍርድ ውሳኔውን አቅጣጫ ሳይቀይሩት እንዳልቀሩ የሚያስረዱ ዘገባዎችን ማስነበብ ጀመሩ።

ከአማሃ ዴይሊ ኒውስ በተጨማሪ አማሃ ትሪቢዩንን የያዘው ኢስቱሊን፣

"አላልኩሽም?! ይሄው ጋዜጦቹ ጥርጣሬዬን ይፋ እያወጡልኝ ነው" አላት። ክፉኛ ተበሳጭታል። እጅግ የተብሳጨ ሌሎች

ስምችም ነበሩ።። መርማሪ ፖሊሶቹ።። የለቃበት ውሳኔ በመቀየሩ ወደ ከተማው የፖሊስ አዛዥ ሄደው፣

"እንዴት ሊሆን ቻለ?" ሲሉ አፋጠጡት።።

"ከአቅሜ በላይ ነው።። ፍርድቤት እንጂ እኔ አልወሰንኩም" የሚል መልስ ስለሰጣቸው ወደ ፖሊስ ዲፓርትመንቱ ዋና ሃላፊ ቶድ ስሚዝ አመሩ።።

"ኤፍ.ቢ.አይ የሰለሞንን እና የሌሎቹን ታዳጊዎች ጉዳይ ችላ ማለቱ ሲገርመን ፍርድቤቱ ያስተላለፈው ውሳኔ በእጅጉ አበሳጭቶናል።። እኛ የማናውቀው እና ያልተረዳነው ጉዳይ ይኖር ይሆን እንዴ?"

ቶድ ስሚዝ በትጋት ከሚሰሩት ስራ ውጪ ያሉበትን እውነተኛ አለም ፈጽሞ የማያውቁትን መርማሪዎች በሃዘኔታ እየተመለከቱ እንዲህ አሏቸው።-

"አዎ! ውዶቼ የማታውቁትና ያልተረዳችሁት ነገር አለ።። ለመግባት እየሞከራችሁ ያለው የተከለከለ ግዛት ውስጥ ነው።። ለመታገል እየሞከራችሁ ያላችሁትም የተከለከለውን ግዛት ሃያላን ነዋሪዎች ነው" ለመጀመሪያ ጊዜ የሚኖሩበትን እውነተኛ አለም ምንነት ተገነዘቡ።።

እውነተኛው ውሳኔ ይተላለፍባቸው ያሏቸው "ሃጢያተኞች" ታዋቂ ፖለቲከኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም አሜሪካ ውስጥ የሚገኘው ስከል ኤንድ ቦንስ የምስጢር ማህበር አባላት ናቸው።። እራሱን ባጋለጠው ዊል ብራውን አስጠላፊነት እና በዮናታን ወልዴ ጠላፊነት አጸያፊው ድራማ ይካሄድ እንጂ ሃሪማን ፓሌይ፣ ጄ. ፎክስ ባልድዊን፣ ሚካኤል ካርትራይት፣ ናትናኤል ፍሊቸርና ጄራልድ ቢሮ ቡና የተጋበዙት ሁሉ በወሲብ ጥቃቱ ላይተ ሳታፊዎች ናቸው።።

ብስጭቱ የተጋባባት ሶስና የሆነ ነገር ማድረግ እንደሚገባት ታውቃታል።። ወንጀል የተፈጸመበት እና ፍትህ የተዛባበት ታዳጊ የሃገሯ ልጅ ነው።። እውነቱ ይፋ እስኪሆንለት ሊጮህለት ይገባል።።

ድምጹን የሚያሰማለት፣ በደሉን ዳር እስከዳር የሚያስተጋባለት ሰው ያስፈልገዋል። መርማሪ ፖሊሶቹ አስበው "የተከለከለ ግዛት ነው" የተባሉትን ግዛት ጥሶ ገብቶ ወንጀሉን ለዓለም ህዝብ የሚያሰማ አንድ ሰው ያስፈልገዋል። ከፍትህ ደጅ ፍትህ የጠፋበትን፣ የዳኛ ውሳኔ የተቀየረበትን፣ ሃያላን ሰዎች ያስፈራሩበትን ምክንያት መርምሮ ይፋ የሚያደርግና የህዝብን ቁጣ የሚያቀጣጥል፣ አቀጣጥ ሎም የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የሚታገል ስው ያስፈልገዋል። ከድርጊቱ ግንባር ቀደም ተዋናዮች መሃል አንዱ ዮናታን መሆኑም እልህ አሲዞታል።

ታጋይዋ እሷ መሆን ፈለገች። ስፔይን ድረስ የመጣችው ለሽርሽር አይደለም። ለወሳኝ ተልእኮ ነው። ሀገሯን በአንድ አለም አስተዳደር ስም ሊያጠፋባት ቆርጠው የተነሱ የሰው ሰይጣኖችን የማጋለጥ ተልእኮ። በሀገሯ ልጅ ላይ የተፈጸመውን ወንጀል እና የፍርድ መዛባት በማጋለጥ ብትጀምርስ? የተብዳይ ቤተሰቦችን፣ መርማሪ ፖሊሶችን፣ ዳኛ ጄራልድን፣ እራሱን ያጋለጠውን ዊል ብራውንን እና በአጠቃላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሁሉ ፊልጋ ብታናግር "ነፍስ ያለው" ነገር መስራት እንደምትችል አመነች።

ጉዳዩን ለመከታተል እና ለመመርመር መወሰኗን ለኢስቱሊን ነገረችው። ቀና ብሎ ተመለከታት።

"ስፔይን ድረስ የመጣሁት ለሽርሽር አይደለም። በሃገሬ ላይ እያሴሩ ያሉትን ሀይሎች ለማጋለጥ ነው። አስቀያሚው ወንጀል የተፈጸመው በሃገሬ ምስኪን ታዳጊ ላይ ነው። ከወንጀሉ ፈጻሚዎች መሃል አንዱም እድሜ ልኬን የምታገለው የሃገሬ ሰው ነው። የታዳጊው አሳዳጊ ፍትህ አገኛለሁ ብላ ተስፋ ብታደርግም ፍትህ ተዛብቶባታል። ይህን ካላጋለጥኩ፣ የምስጢር ማህበራቱን ሰዎች የምታገልበትን ስራዬን ከዚህ ካልጀመርኩ ከምን ልጀምር ነው? መልካም አጋጣሚ ይመስለኛል። ራሴን እፈትሽበታለሁ"

ትኩረቱን እሷ ላይ አደረገ።

"ማለት ያለባቸውን ያህል እኮ ሚዲያዎቹም ብለዋል" ጣልቃ ገባች።

"እኔ ግን አላምንም፡፡ ሌላው ቀርቶ ሰለሞን እና መሰል የጥቃት ሰለባ ሀጻናት የሚገኙበት ትክክለኛ ስፍራ አልተጠቆመም፡፡ ወንጀሉ መፈጸሙ፣ ከወንጀል ፈጻሚዎች መሃል አንድ ሁለቱ ራሳቸውን ማጋለጣቸው እና የፍርድ ውሳኔው መዛባቱ ተነገረ እንጂ እነሰለሞን ከዚያ የሰቆቃ ስፍራ ወጥተው ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበት መንገድ እንኳን አልተጠቆመም፡፡ በእነዚህ እውነታዎች ላይ ከትትል አድርጌ ውጤቱን ይፋ አደርጋለሁ፡፡ መፍትሄ ይሆናሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ለመጠቆም እሞክራለሁ፡፡ በምክክ ተው ድረ-ገጼ የምለቀው የመጀመሪያ ስራም ይሆናል፡፡ የምሰራቸውን ዘጋቢ ፊልሞች በማቀናበር እና በማስተካከል እንደምትረዳኝ ተስፋ አለኝ?"

"እትጠራጠሪ፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን አጠገባችን ያሉ ባለሙያዎች ሁሉ ይተባበሩሻል"

በወኔ ተሞላች፡፡ ጊዜ ማባከን አልፈለገችም፡፡ ወደአማሃ፣ ኒብራስካ ለመብረር ወሰነች፡፡ ውሳኔዋን አሳወቀችው፡፡ በተጨባጭ ማስረጃ ስላሳመነችው በመሄዷ ተስማማ፡፡

"ሰዎቹ ማነፍነፍ መጀመርሽን ካወቁ፣ ያውም አፍንጫችው ስር ሆነሽ ሊያጠፉሽ ይችላሉና ተጠንቀቂ፡፡ እያንዳንዱ እርምጃሽ በጥንቃቄ ላይ የተመሰረተ ይሁን፡፡ እተማመንብሻለሁ፡፡ ሀገርሽን ኢላማ ያደረጉትን የምስጢር ማህበራት ሰዎች ሴራ ለማጋለጥ አንድ ብለሽ መጀመርሽን እንዳትረሺ፡፡ ዛሬ በወኔ ተሞልተሽ የጀመርሽው ወሳኝ ተልእኮ የሰይጣን ልጆችን ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን ነገ አለም በጉጉት የሚያነበውን መጽሐፍ እንደሚወልድም አስታውሺ፡፡ እንደሻማ እየቀለጡ ለሌሎች ብርሃን መስጠት፣ እየሞቱ ሌሎችን ማኖር ማለት ይሄው ነው፡፡ ሌላ አይደለም፡፡"

ለማጋለጥ ቆርጣ ትነሳ እንጂ በምን አይነት መንገድ እንደምታጋልጥ ትኩረት አልሰጠችም ነበር፡፡ ተስፋ ያደረገችው ድረ-ገጿችን ነበር፡፡ ኢስቱሲን ሌላ መንገድ ጠቆማት - መጽሃፍት፡፡ ድንገተኛ ደስታ ሰውነቷን እጥለቀለቀው፡፡ በድረ-ገጿች ላይ ከምትለቃቸው ጽሁፎች እና ዘጋቢ ፊልሞች በተጨማሪ መጻህፍት

ወላኝ መንገዶች እንደሆኑ ተገነዘበች፡፡ ሰፊ ጊዜዋን ለመሰጠት ወሰነች፡፡ እንደ ኢስቱሊን፣ ዴቪድ አይክ፣ አሌክሳንድ ራሮቢንሰ አለም በተመስለ የሚያነባቸውን መጻህፍት መጻፍ የሚከለክላት አይኖርም፡፡ የሰው ልጅ እችላለሁ ብሎ ከተነሳ የማይችለው ነገር እንደሌለ ታምናለች፡፡

"እንደውም የመጀመሪያ መጽሐፌን ርእሰ ልንገርህ?" አለችው እየሳቀች፡፡

"ደስ ይለኛል"

"ከሀዲምቹ የሰይጣን ልጆች"

"የሰዎቹን ባህሪ የሚገልጽ ምርጥ ርእስ!" ደስ አላት፡፡

በነጋታው ሰለሞንን አደራ ሰጥታው ወደ ኒብራስካ በረረች፡፡

- 24 -

አማሃ፣ ኒብራስካ

ጊዜያዊ ማረፊያዋን መሃል አማሃ ውስጥ በሚገኘው ፎንቴኔሊ ሆቴል ያደረገችው ሶስና ስራዋን ከየት መጀመር እንደሚገባት አስላሰለች። በቅድሚያ ፖሊስ ዲፓርትመንት ቢሮ አመራች። ዋና ሃላፊውን ቶድ ስሚዝን አገኘቻቸው። ማንነቷንና የመጣችበትን ምክንያት ነገረቻቸው። መጣሁበት ያለችውን ጣቢያ ያውቁታል፣ ችግር እንደማይኖር በማመናቸው የጠየቀቻቸውን የሞባይል ስልክ ቁጥሮች ሰጧት።

ከWSIL-TV ያለችው ሆን ብላ ነበር። ከተቋማት ለሚመጡ ጋዜጠኞች የሃላፊዎች ቢሮ ክፍት እንደሚሆን ከልምድ ታውቃለች። ከWSIL-TV እያለች ለምን ያህል ጊዜ እንደምትቆይ እርግጠኛ አይደለችም። ቶድ ስሚዝን አመስግና ከቢሯቸው እንደወጣች ለመቶ አለቃ ቻርልስ አንደርሰን ደወለችለት።

"ስልክህን ያገኘሁት ከቶድ ስሚዝ ነው። ሶስና እባላለሁ። ጋዜጠኛ ነኝ። የወሲብ ጥቃት በተፈጸመበት ታዳጊ ሰለሞን አሸከሮፍት ጉዳይ ላይ ላነጋግርህ ፈልጌ ነበር?" በደስታ ተስማማ።

"ይቻላል መቼ እንገናኝ?"

"የሚመችህ ከሆነ አሁንም እችላለሁ። ቢሯችሁ አካባቢ ነኝ"

"ሃያ አምስት ደቂቃ ልትታገሺኝ ትችያለሽ?"

"እችላለሁ"

ተገናኙ፣ ወደቢሮው ይዟት ገባ።

"ምርመራውን ያካሄዳችሁት አንተና ጓደኞችህ እንደሆናችሁ ጋዜጠኞች ላይ አንብቤያለሁ?" በአምንታ ራሱን ነቀነቀላት።

"ወንጀለኛውን ወደኢብራስካ ማምጣትና ችሎት ፊት ማቆም ችላችሁ ነበር?"

"ምን ዋጋ አለው በነጻ አሰናበቱት!"

"ጠላፊው ነጻ የሆነበትን ምክንያት መገመት እንችላለን?"

"ዳኛው በቂ የሆነ ማስረጃ አልቀረበም ባይ ናቸው፡፡ በድርጊቱ ላይ ተሳታፊ ከነበረ የሰው ማስረጃ የተሻለ ማስረጃ ከየት ሊመጣ ነው? ቶድ ስሚዝን አነጋግረናቸው ነበር፡፡ <የተከለከለ ግዛት> እንደገባን ነው የነገሩን"

"የተከለከለ ግዛት?!" አለች በመልሱ ተገርማ፡፡

"እዎ ሃያላን ነዋሪዎች ብቻ የሚኖሩበት የተከለከለ ግዛት፡፡ ማንም ሊደፍረው የማይችል አደገኛ ግዛት፡፡ በሰልጣን የተከለሉ ወንጀለኞች የተንሰራፉበት ግዛት"

በንዴት ነበር የሚያናግራት

"ወደ ሌላ ባለስልጣን ሄዳችሁ ቅሬታችሁን ለማሰማት አልሞከራችሁም?"

"ከዲፓርትመንቱ ዋና ሃላፊ ውጪ የት እንሄዳለን?"

"ሰለባዎቹ የሚገኙበትን ትክክለኛ ስፍራ ለማወቅ ለምን ጥረት አላደረጋችሁም? ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበትን እና ወንጀለኞቹ በቁጥጥር ስር የሚውሉበትንም መንገድ መፈለግ ነበረባችሁ?"

"በሂደት ላይ እያለን ነው ውሳኔውን የሰማነው፡፡ ቶድ ስሚዝ ቢሯቸው ሰብስበውን ከበላይ የመጣ ትእዛዝ ስለሆነ በጉዳዩ ላይ የጀመራችሁትን ክትትል እንድታቆሙ አሉን፡፡ የበላይ ትእዛዝ ጥሰሽ እንዴት ነው ወደፊት የምትሄጂው?"

"እናንተን ማነጋገር እንደምፈልግ ስነግራቸው ለምን አልተቃወሙኝም? ለምን ሰልክ ቁጥራችሁን ሰጡኝ?"

"ምንም እንደማታመጪ አውቀው ይሆናላ!"

‹እንዴት ነው ምንም የማላመጣው?› አለች በውስጧ፡፡ እልህ ያዛት፡፡

"ከትላንት ትታችሁታላ?!" አለችው ከመሰነባበታቸው በፊት፡፡

"አማራጭ የለንም"

ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ተመሳሳይ ታሪኮችን አንብባለች፡፡ አንዱን አስታወሰች፡፡

".....ኬኔዲ የነበሩበት መኪና ከተገደሉ ከሶስት ቀናት በኋላ በፎርድ ሞተር ካምፓኒ አማካይነት ከዋሽንግተን ወደሲንሲናቲ ተወስዶ ነበር - ለምርመራ፡፡ የሃገሪቱ የምስጢር አገልግሎት ሃላፊ ወደፎርድ ሞተር ካምፓኒ የደህንነት አለቃ ካርል ሬናስ ከበረደ በቀዘቀዘ አይታ እየተመለከተ ምን አለ? አፍሀን ዝጋ፡፡ ሬናስ እንደታዘዘው አፉን ዘግቶ ወደመጣበት ተመለሰ፡፡ አፉን ዘግቶ ባይመለስ በድኑን ስድስት ጫማ ርዝመት ባለው ሳጥን ውስጥ እንደሚያገኘው አልጠፋውም....."

እነሙቶ አለቃ ቻርልስ አንደርሰንም ይህን ታሪክ ያውቁ ይሆናል፡፡ እያወቁ አጉል መዳፈር ስድስት ጫማ ርዝመት ባለው ሳጥን ውስጥ መከተትን ያስከትላል፡፡ የሚያዋጣው አላየንም ብሎ ማለፍ ነው፡፡

"አመሰግናለሁ ቻርልስ፡፡ የሰለሞንን ቤተሰቦች እና የዊል ብራውንን አድራሻ እና ስልክ ልትሰጠኝ ትችላለህ?"

ሰጣት፡፡ ዊል ብራውን ኒውዮርክ እንደሚኖር ተገንዝባለች፡፡ እዚያ መሄዱ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከዮናታን ጋር ተገናኝታ አደጋ ላይ መውደቅ አልፈለገችም፡፡ ደውላ ማነጋገሩን መረጠች፡፡ የዳኛ ጀራልድንም የቢሮ አድራሻ ሰጥቷታል፡፡

ከቻርልስ እንደተለየች ዊል ብራውን ሞባይል ላይ ደወለች፡፡ ዝግ በመሆኑ የመኖሪያ ቤቱ ስልክ ላይ ደወለች፡፡ ድምጽዋ የታፈነ የሚመስል ሴት "ሀሎ" አለች፡፡

"ይቅርታ እመቤት ሶስና እባላለሁ፡፡ ጋዜጠኛ ነኝ፡፡ ዊልን ማናገር ፈልጌ ነበር?" ሴትዮዋ እያለቀሰች

"የእኔን ምስኪን ዊል ትላንት ማታ በመርገጫ አጠፉት" አለቻት፡፡ ለጥቂት ሰከንዶች ደርቃ የቀረችው ሶስና ትንፋሿን ሰበሰበችና

"እነማን?" ስትል ጠየቀቻት፡፡

"ምን አውቄ? የህክምና ውጤቱ በመርገጫ እንደተገደለ ያሳያል፡፡ ምስኪን ባሉ....." ለቅሶዋን ቀጠለች፡፡

ወደሆቴሏ በማምራት ላይ የነበረችው ሶስና ድርጊቱ የሃያላኑ ሰዎች ሊሆን እንደሚችል ጠርጥራለች፡፡ ቀሪውን ምስጢር እንዳይና ዘገ ፊጥነው የወሰዱት እርምጃ ሊሆን እንደሚችል ገምታለች፡፡ አብርሃም ሊንከን የተገደለ ሰሞን ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉ ሁሉ ታድነው እንደተወገዱ አንብባለች፡፡ ቀሪ ምንጮቿ ዳኛ ዴቪድ ጀራልድ እና ስቴሲ አሽክሮፍት ናቸው፡፡ ወደ ስቴሲ አሽክሮፍት መኖሪያ አመራች፡፡ የደረቀ ጭራሮ የመሰለችዋ ወይዘሮ ስቴሲ በትህትና ተቀብላ ወደሳሎን መራቻት፡፡ ብስኩት እና ቡና እየጋበዘቻት "በሃገሬ የፍትህ አካል ላይ ተስፋ ቆርጫለሁ" አለቻት፡፡

ሶስና ማንነቷን እና የመጣችበትን ምክንያት ነግራታለች፡፡

"ሁኔታው ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም እስከመጨረሻው መታገል ያስፈልጋል፡፡ ሶስት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ እፈል ጋለሁ፡፡ ወንጀለኞቹ እውነተኛ ውሳኔ በሚያገኙበት ጉዳይ፣ ልጆቹ የሚገኙበትን ስፍራ ማወቅና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ ላይ፡፡" ስቴሲ ያደረገችውን እንትስታሴና የደረሰችበትን ውጤት ተረክችላት፡፡ ሶስናም ጥያቄዎች አቀረበችላት፡-

"ሰለሞን የሚኖርበትን ስፍራ የጠቆመሽ ሰው የለም?"

"ቢኖር ተረጋግቼ እተመጥ ነበር?"

"የምትጠረጥሪውስ ስፍራ አይኖርም?"

"እንዴት ብዬ? ዊል ብራውን ከሰጠው ቃል አማካ ግዛት የሚል ሰለሰማሁ መሃላችን እንደተደበቁ እገምታለሁ፡፡"

ሶስና የመጣችው ልጆቹ ያለበትን ቦታ እንድትጠቁማት ነበር። አልተሳካም። ተሰናበተቻት።

ወደዳኛ ጀራልድ ቢሮ በማምራት ላይ የነበረችው ሶስና የምታቀርብላቸውን ጥያቄ እያሰላሰለች ነበር። የወሰኑት በትክክለኛ መንገድ ነው? ውሳኔውን ይቀይሩ ዘንድ ተጽእኖ ያሳደሩብዎት ሰዎች አሉ? እነማን ናቸው? በድርጊቱ ተሳታፊ የነበረ ሰው ማስረጃ እንዴት ነው በቂ የማይሆነው? መሰል ጥያቄዎችን እያሰላሰለች ከቢሯቸው ደረሰች።

"ምን ልርዳሽ የእኔ እመቤት?" አለች ጸሃፊዋ በትህትና።

"ይቅርታ፤ ዳኛ ጀራልድን ፈልጌ ነበር። ሶስና እባላለሁ። ከWSIL-TV ነው የመጣሁት"

"ቀጠሮ አለሽ?"

"የለኝም አስቸኳይ ጉዳይ ይገፍ ነው የመጣሁት"

"እንዴ ቆይኝ" በውስጥ መስመር ደወለች። ለአፍታ ከተነጋገረች በኋላ ትገባ ዘንድ ጋበዘቻት።

ወንበር እንደያዘች ነበር ወደ ጉዳዩ ያመራችው።

"ሶስና እባላለሁ። ጋዜጠኛ ነኝ። በቅርቡ የታዳጊውን የሰለሞን አሽከሮፍትን ጉዳይ በተመለከተ ባስተላለፉት የፍርድ ውሳኔ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎችን....." ጀራልድ የፊታቸው ቀለም እየተቀያየረ አቋረጧት፦

"ይቅርታ በዚህ ጉዳይ ላይ ከማንም ጋር ለመነጋገር ፍቃደኛ አይደለሁም"

"የሚዲያ ነጻነት ባለበት ሀገር የዚህ አይነት መልስ መስማት.....ያውም ከሀግ አስፈጻሚ አካላት....." አሁንም አቋረጧት፦

"ነገርኩሽ እኮ መኖር ስለምፈልግ..." አቋረጠቻቸው፦

"አሃ! ውሳኔውን የወሰኑት በሆኑ ግለሰቦች፣ ወይም ደግሞ በሆነ ቡድን አባላት ተጽእኖ ነው ማለት ነው?" ብእር መሳይ ድምጽ መቅረጫ መሳሪያዋን ኮቷ የውስጥ ኪስ አድርጋ ነበረ።

"ምናለ ቢሮዬን ለቀሽ ብትወጪ?" በታክሲ ስሚት ለመኛት።።

"ውሳኔውን በምንፈልገው መልክ ካላስኬድክ አናስኖርህም ብለው ያስፈራሩዎትን ሰዎች ማንነት ሊነግሩኝ ፍቃደኛ ነዎት?"

"ምን ያለችው እብድ ናት እባካችሁ?! በጉዳዩ ላይ ምንም ነገር መናገር አልፈልግም አልኩሽ እኮ!"

"ዊል ብራውን የድርጊቱም ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነው።። በምን ምክንያት ቃሉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ የሚሆነው?"

ጠረጴዛቸውን በቡጢ ነርተው ተነሱ።።

"ትሰሚኛለሽ! ከዚህ በኋላ ፖሊስ ለመጥራት እገደዳለሁ።። ሰዎቹ ቢሮዬ ድረስ መጥተው መኖር የምትፈልግ ከሆነ.....ሲሉ አስፈራሩኝ።። አንቺ ደግሞ ማስታወስ ወደማልፈልገው ርእስ ልትነትችኝ ትጥሪያለሽ።። ውጪ!"

በድጋሚ ጠረጴዛውን በቡጢ ነረቱት።።

"ምን ታደርጊ?! ማንነታቸውን አላወቅሽ!?"

"አመሰግናለሁ"

ቢሯቸውን ለቃ ወጣች።። ጠቃሚ ጥቆማ በማግኘቷ ደስተኛ ነበረች።። የተቀረጸ ድምጻቸውን አይክዱም።። ታክሲ ከመያዟ በፊት ድምጽ መቅረጫ መሳሪያዋን አውጥታ ከፈተችው።።

"ይቅርታ በዚህ ጉዳይ ላይ ከማንም ጋር ለመነጋገር ፍቃደኛ አይደለሁም" ከሚለው "ሰዎቹ ቢሮዬ ድረስ መጥተው ‹መኖር የምትፈልግ ከሆነ.....› ሲሉ አስፈራሩኝ።። አንቺ ደግሞ በግድ.....ምን ታደርጊ የሰዎቹን ማንነት አላወቅሽ" እስከሚለው የተቀዳውን ድምጻቸውን አሰማት።።

"አገኘኋቸው!" ስትል ጮቤ ረገጠች።። ጄራልድ በተጽእኖ ስር መሆናቸውን በአንደበታቸው አምነዋል።። ለመጽሃፏ ግብአት እንደሚሆናት አልጠፋትም።። እስከዚያ ድረስ አፍናው ለመቀመጥ አልፈለገችም።። አሁኑኑ ሀገብ መስማት ይኖርበታል።። "ሰዎቹ"ም ጭምር።።

ወደ "The Omaha Bee" አዘጋጅ ደወለች፡፡ ማንነቷን ካስተዋወቀች በኋላ በእጇ ላይ ስላለው መረጃ አወራችው፡፡ "አሁኑኑ ላግኝሽ?" አላት፡፡ ፎንቴኔሊ ሆቴል እንዳረፈች ነገረችው፡፡ ተቀናቃኟቹ መረጃው የደወለችለት ሴት ጋር መኖሩን ቢያውቁ እንዴት እንደሚራኮቱ ያውቃል፡፡ ማንም ሳይቀድመው ሊያገኛት ቸኩሏል፡፡

ወደሆቴሏ ከነፉ፡፡ እንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ተገኙ፡፡ እንዲህ አለችው፡-

"ሰባራ ሳንቲም አልፈልግም፡፡ መረጃውን ሳታካፍሉ ህዝብ ዘንድ እንድታደርሱ እሻለሁ፡፡ በስሜ እንዲወጣም እፈልጋለሁ፡፡ ሀገናቱ እውነተኛ ፍርድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ወንጀለኞቹም ቅጣታቸውን፡፡ ቤተሰቦች ከልጆቻቸው ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ እስኪፈጠር በጋራ መስራት ይኖርብናል፡፡ ፍርሃት መፈንጫቸው ሊያደርገን አይገባም"

ተስማማ፡፡ ድፍረቷ እና ትጉህነቷ ማርኮታል፡፡ "አብረሽን ስራ፡፡ በቋሚነት ልንቀጥርሽ እንችላለን" አላት፡፡ ችኮላው አልተመቻትም፡፡ ስለ WSIL-TV ጋዜጠኝነቷ እና የተወችበትን ምክንያት ከነገረችው በኋላ ልምድ ያላት ጋዜጠኛ መሆኗን ተገንዝቧል፡፡

"ስላሳደርክብኝ እምነት ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች አልችልም ስልህ እያዘንኩ ነው"

ውጤት እስክተገኝ ጉዳዩን እንዴከታተል አደራ አለችው፡፡ ቃል ገባላት፡፡

"እንዴ ቆይኝ" አለና ወደእንግዳ ተቀባይዋ ሴት አምርቶ ካርድ ሰጣት፡፡ በማሽኑ ውስጥ አሳልፋ ደረሰኝ ሰጠችው፡፡ ወደ ሶስና ተመለሰ፡፡

"እስክቆየሽ እንግናኛለን፡፡ የሳምንት ወጪሽ በድርጅታችን ተሸፍኗል" አለና ተሰናበታት፡፡

"ምን አሳሰበህ?" የሚለው ድምጽዋ ከኋላው ተከተለው፡፡

****

ዜና ማሰራጫዎቹ የተመኙትን ውጤት ባያገኙም፣ ጨኸቱ መቀጠሉ አልቀረም። የከተማዋ ባለስልጣናት ጆሮ ዳባ ማለታቸው በእጅጉ ያበሳጫት ሶስና የተለያዩ መንገዶችን ለመሞከር አእምሮዋን አሰጨነቀች። ብቸኛ አማራጭ አድርጋ ያሰበችው ሚዲያዎችን እና የሀጻናቱን ቤተሰቦች ሰላማዊ ሰልፍ ማስወጣት ነው። ለሚዲያዎቹ ባለቤቶች አሳውቃም ተቀባይነትን በማግኘቷ ቤተሰቦች እየተፈለጉ ይዘጋጁ ዘንድ ጥሪ ተላለፈላቸው። ከተባባሪዎቿ ጋር ቤት ለቤት ቀሰቀሱ። እለቱ በሚዲያዎች እንደሚገለጽ ተነገራቸው። ከሃያ ስድስት ቀናት በኋላ በጋዜጦች ይፋ ሆነ። ፖሊስ ለማስተጓጎል ቢሞክርም አልተሳካለትም። የአማሃ ዋና ዋና መንገዶች *"ፍትህ ለሀጻናቱ! ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ! ወላጅች ከልጆቻቸው ተለይተው እንዳይቀሩ፣ ሀጻናቱ ያሉበትን ቦታ የፍትህ አካላት ተከታትለው ያሳውቁን!....."* የሚሉ መፈክሮች ባነገቡ ነዋሪዎች ተጨናነቁ።

ሶስና የአመጽ እንቅስቃሴ እንዳያካሂዱ ስላሳሰበቻቸው በሰላም ተጀምሮ በሰላም ተጠናቀቀ። ሌሎች ችላ ያሉትን በእራሷ ተነሳሽነት ግብ ለማድረስ በመሞከሯ የከተማው ህዝብ ከበሬታን ችሯታል። እንደሰላማዊ መሪያቸው ቆጥረዋታል። ሰላማዊ ሰልፉ እየተካሄደ በነበረበት ሰአት አንድ ሰው ተጠጋትና እንዲህ አላት፡-

"ጠንካራ ሰው ነሽ። ይህን ያመንክት መጀመሪያ ያየሁሽ እለት ነው። ረስተሽኛል መሰል?" አላወቀችውም።

"አልፈርድብሽም። ተለውጫለሁ።"

ፍርሃት ተሰማት። "ሰዎቹ" የትም ቦታ ሊገኙ እንደሚችሉ አስቡሊን ነግሯታል። ህዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ ምን ሊያደርጋት ይችላል? ሊላኛው ሃሳቧ እንዲህ አላት። "አትሞኚ። አጥፍቶ ለመጥፋት የቆረጠ የሚመርጠው ሰው የተሰበሰበበትን ቦታ ነው።"

እንደሪራቸው አውቋል።

"የሰላማዊ ሰልፉን ዜና በማንበቤ ነው ከኒውዮርክ ድረስ ሰባሰማስ የመጣሁት። ቋሚ መቀመጫ ቦት አለኝ ብለሽ ነው? አንዴ

ስፔይን፣ አንዴ አሜሪካ፣ አንዴ ጣሊያን አንዴ ካናዳ፡፡ በፍቃደኝነት እራሴን ጡረታ በማውጣቱ እና ከሰዎቹ ገለል በማለቱ ጊዜያዊ መቀመጪያዬን ኒውዮርክ አድርጌያለሁ፡፡ በዳኛ ጀራልድ ዙሪያ ጋዜጣ ላይ የጻፍሽውን ዘገባ አንብቤዋለሁ፡፡ ጥሩ ዘገባ ነው፡፡ ሰልፉ ላይ እንደማገኝሽ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ሀጻናቱ የታገቱበትን ሰፍራ እነግርሻለሁ፡፡ አድሪያን ሮክዌል ነኝ፡፡ የጸጉሬን ቀለምና የፊቴን ገጽታ የቀየርኩት ለጥንቃቄ ያህል ነው፡፡"

የተበረዘ ስሜት ውስጥ ገባች፡፡ እራሱን ቀይሮ ፍርድቤት በመገኘት ስለሰጠው የምስክርነት ቃል እና ዳኛ ጀራልድ ለውጡን ተመልክተው ስለተናገሩት ነገር ከስቴሲ አሽክሮፍት ሰምታለች፡፡ ፍጹም እስከሚያሳስተኝ ይቀየራል ብላ ግን አላሰበችም፡፡

"አ! ሮክዌል ፍጹም አላወቅኩህም፡፡ ስለአንተና ስለዊል የፍርድ ቤት ቆይታ ሰምቻለሁ፡፡ ወደሰላማዊ ኑሮ ለመመለስ በመወሰንህ ደስ ብሎኛል፡፡" እንዲህም ሆኖ በፍጹም ልቧ መቀበሉ ተስኗታል፡፡ በአንድ ወቅት የመግደል ሙከራ ያደረገባት ሰው ነው፡፡

"በሀጻናቱ ላይ የሚፈጸመው ግፍ፣ በደም የተጨማለቀው ሰብእናዬ፣ አውሬ ያደረጉኝ ሰዎች አውሬነት አንገሽግሾኝ፡፡ ንስሃ ገብቶ ህሊናን ከጭንቀት ማዳን መፍትሄ እንደሆነ አምኜ እራሴን አጋለጥኩ፡፡ ከጭንቀቴ ፋታ አግኝቻለሁ"

"ጥሩ ውሳኔ ነው፡፡ መች ተገናኙትን እናውራ?"

"አንቺን በተመቸሽ ጊዜ"

ስልክ ቁጥር ተለዋውጠው ተለያዩ፡፡

****

"ዘ ኦማሃ ቢ" ጋዜጣ *"ዳኛ ዴቪድ ኤም. ጀራልድ በተጽእኖ መወሰናቸውን አመኑ!"* በሚል ርእስ ሰፋ ያለ ዘገባ ይዞ ወጣ፡፡ በሶስና ስም ነበር የወጣው፡፡ ዝርዝር ሃሳቡ የሚከተለው ነው፡፡

"በሰለሞን አሽክሮፍት ላይ የተፈጸመውን የወሲብ ጥቃት አስመልክቶ በዱግላስ ፌዴራል ክፍተኛ ደረጃ ፍርድቤት ሲታይ

የነበረውን ችሎት የመሩት ዳኛ ዴቪድ ሌም. ጀራልድ ሃሰተኛ ውሳኔ የወሰኑት በፌሽቸው ድረስ በመሄድ ባስፈራሯቸው ሰዎች እንደሆነ አምነዋል። ከዳኛው ጋር ልናደርገው ያሰብነው ታሊምልልስ ባይሳካም በመቅረጸ-ድምጻችን ያስቀረነው ድምጻቸው ግን በተጽእኖ ውሳኔ መቀየራቸውን ያመለክታል" ይልና መ.ሉውን ትርክ መላይ ንግግር ሰፍሯል። ሶስና በዘገባው ደስተኛ ነበረች። እንዳለ ነው የወጣው። ለኢስቴሊን ደወለችለት።

"ከተማዋ ቀውጢ ሆናለች!" አለችው እየተፍለቀለቀች። ምክንያቱን ነገረችው።

"ኮራሁብሽ" አላት ተደሰቶ። "ወደፊት ለምትሰሪያቸው ስራዎች ዝግጁነትሽን አመላካች ነው። ሆኖም የጦርነት አውድማ ውስጥ እየገባሽ ነውና ተጠንቀቂ። በአንቺና በምስጢራዊ ቡድን አባላት መሃከል ይፋዊ ጦርነት ታውጇል"

"እጠነቀቃለሁ" አለችና ስልኳን ዘጋች። የ"ዘአማሃቢ" ጋዜጣ አዘጋጅ ደወለላትና በውጤቱ እንደተደሰ ተነገራት።

"የተለየ አስተያየትስ አልደረሳችሁም?" "ሰዎቹስ አልደወሉም?" ነበር መልእክቱ። ገበቶታል።

"ዛቻዎችና ማስፈራሪያዎች ነበሩ። አወጣጋቢ ታሪኮች ሲወጡ የተለመደ ነውና እንደነቅም" እየሳቀ መለሰላት። አንድ እርምጃ ተራምዳለች። ወደምትፈልገው ውጤት መጠጋቷ የማይቀር ነው። ልታገኘው እንደምትፈልግ ነገረችው። ሾፌር ላከላት። በጋዜጣው አዘጋጅና በባልደረቦቹ የክብር አቀባበል የተደረገላት ሶስና የመጣችበትን ምክንያት አስረዳች።

"አንድ ሰሞን ብቻ አራግበነው ዝም ልንል አይገባም። የከተማዋ ጋዜጦች የጋራ ድምጻቸውን ማሰማት ይኖርባቸዋል። ውጤት እስኪመጣ መሥሀ ይኖርባቸዋል። ሀጻናቱ ያለበት ስፍራ መታወቅ ይኖርበታል። ወንጀለኞቹም ትክክለኛውን ፍርድ ማግኘት አለባቸው። ሀጻናቱ ከወላጆቻቸው ጋር ካልተገናኙ እንቅልፍ ሊወስደን አይገባም። የንግድ ፉክክራችንን ትተን ሁሉም ሚዲያዎች ድምጻቸውን የሚያሰሙበትን መንገድ መቀየስ ይኖርብናል"

የማስተባበሩን ሃላፊነት ለመውሰድ ቃል ገቡላት። እንትስቶሲው ከዛሬ መጀመር አለበት ተብሎ በመወሰኑ ወደሊሎች ሚዲያዎች እየደወሉ ሃሳባቸውን አስረዱ። መልካም ተቀባይነትን ነበር ያገኙት። ጋዜጦች ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን እየያዙ መውጣት ጀመሩ። የግል ራዲዮ ጣቢያዎችም ጥያቄዎቹን ማስተጋባት ቀጠሉ።

****

ጊዜ ማባከን ያልፈለገችው ሶስና ለሮክዌል ደወለችለትና ልታገኘው እንደምትፈልግ ነገረችው። በነገው አለት ምሳ ሰአት ላይ ፎንቴኔሊ ሆቴል ለመገናኘት ቀጠሮ ያዙ። ሁለት ደቂቃዎችን አሳልፎ የተገኘው ሮክዌል እየጨበጣት፦

"ለቡና ተጋባኸኮት የተግደረደረች ሴት ምሳ ጋባኸር ሆና ተገኘች" አለና ቀለዳ።

"ሁለም ነገር መሆን የሚገባው ከጊዜ እና ከቦታ ጋር ሲስማማ ነው" ስትል መለሰች። "ያለትክክለኛ ጊዜና ቦታ የሚከወኑ ነገሮች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል።"

ምሳው ሲጠናቀቅ ወደጉዳያቸው አመሩ። ምንም ነገር አልደበቃትም። የሚያውቀውን እና ከሰዎቹ ጋር በነበረበት ሰአት የፊጸመውን ውንጀል ሁሉ ተናዘዘላት።

"ነጣዜዬ ከሀሊና ጭንቀቱ ይፈውሰኛል ብዬ አምናለሁ" ያላት ሮክዌል፤ ህጻናቱ የሚገኙበትን ቦታ ጠቆማት። ኢልክሆርን፣ ኒብራስካ ከተማ የሚገኝ ግዙፍ ሰማያዊ ቤት ነው። እነሱ <ዘ ሀዩጅ ብለው ሃውስ> እያሉ የሚጠሩት። የጎዳናውን ቁጥር፣ ሊሎች ምልክቶችን እና አስፈላጊ ዝርዝር መረጃዎችን ሰጣት።

ቤቱ ውስጥ ከሃያ የማያንሱ የወሲብ ተጠቂዎች እንደሚገኙም ነግሯታል። እድሚያቸው ከ9 እስከ 21 ይደርሳል። የምስጢራዊ ቡድኑን አባላት ተክትለው ከሰፍራ ስፍራ የሚዘዋወሩ ናቸው።

"ስለመረጃህ ከልብ አመሰግንሃለሁ። በምፈልግህ ጊዜ እንደማገኝህ እርግጠኛ ነኝ"

"እኔም ለምላ መስተንግዶሽ አመሰግናለሁ፡፡ በእርግጠኝነት በምትፈልጊኝ ጊዜ ሁሉ ታገኚኛለሽ"

ተሰነባበቱ፡፡

ወደ"ዘ አማሃ ቢ" አዘጋጅ ደወለች፡፡

"ሃይ ሶስና እጅሽ ከምን?"

"ወሳኝ የሆነ መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ ሀጻናቱ የታገቱበትን ቤት ከሚያውቅ የቀድሞ የምስጢራዊ ቡድኑ አባል ጋር ቃለ ምልልስ አድርጌያለሁ"

በፍጥነት ሾፌር ላክላት፡፡ ተጽእኖ መፍጠር ችላ ነበር፡፡ አዘጋጁና ባልደረቦቹ ቋሚ ሰራተኞቹው እንድትሆን እየወተወቷት ነው፡፡ የመጀመሪያቀን ለአዘጋጁ የነገረችውን ደገመችላቸው፡፡ መረጃውን አስረክባ ወደሆቴሏ ሸኟት፡፡

በነጋታው ገበያ ላይ የዋለው <ዘ አማሃ ቢ> ገበያውን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን የመንግስት ባለስልጣናትንም ቀልብ ሳበ፡፡ "የወሲብ ተጠቂዎቹ መደበቂያ ይፋ ሆነ!" በሚል ርእስ ያወጣው ዘገባ የጎረቤት ከተሞች ነዋሪዎችንም አነጋገረ፡፡ በዘገባው ላይ ኢልከሆርን፣ ኒብራስካ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ግዙፍ ሰማያዊ ቤት የታገቱት ሀጻናት ማንነት፣ ከየትኛው ትምህርት ቤት እና የከተማዋ ክልል እንደተጠለፉ፣ ጠላፊና አስጠላፊዎቻቸው፣ የወላጆቻቸው ስም፣ ወሲብ የሚፈጽሙት ባለስልጣናት ማንነት፣ በግርፊያና በስቃይ ሀይወታቸው ያለፈ ታዳጊ ወጣቶች ማንነት እና ሌሎችም ዝርዝር መረጃዎች ተካተዋል፡፡ የባለስልጣናትን ቀልብ የሳበው መጨረሻ ላይ የሰፈረው *"ባለስልጣናት ይሀን ሁሉ ወንጀልና ግፍ እየተመለከቱ ዝምታን መርጠዋል"* የሚለው አረፍተ ነገር ነበር፡፡ ዘገባው አሁንም የወጣው በሶስና ስም ነው፡፡

በነጋታው ከተማዋ በእራሳቸው ተነሳሽነት ሰልፍ በወጡ ነዋሪዎች ታመሰች፡፡ ቁጣ የሚነበብባቸው ነበሩ፡፡ መንግስት በወንጀለኞቹ ላይ ትክክለኛውን የፍርድ ውሳኔ ካላስተላለፈና ሀጻናቱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ ሁኔታዎችን ካላመቻቸ ርምጃ

ሊወስዱ እንደሚችሉ አስታወቁ፡፡ ከፖሊስ ጋር በተፈጠረ ግጭት አንድ ሰው ህይወቱን ሲያጣ አስራ አንድ ሰዎች ቆሰሉ፡፡ ሁለት የፖሊስ መኪኖች ተቃጠሉ፡፡ ቁጣው ወደሌሎችም ከተሞች እንዳይዛመት የፈራው የአሜሪካ መንግስት ጣልቃ ለመግባት ተገደደ፡፡ የአሜሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ ብለው ወንጀለኞቹ ከህግ በላይ እንደማይሆኑና በድጋሚ ለፍርድ እንደሚቀርቡ፣ ትክክለኛው ውሳኔ እንደሚተላለፍባቸው እንዲሁም ህጻናቱን ከወላጆቻቸው ጋር የማገናኘቱ ስራ በቅርቡ እንደሚሰራ ቃል ገቡ፡፡ ቁጣው በረደ አለ፡፡

ምክትል ፕሬዚዳንቱ ቃላቸውን አላጠፉም፡፡ የወንጀለኞቹ ጉዳይ በሌላ ዳኛ እንዲታይ፣ ትክክለኛ ውሳኔ እንዲተላለፍ፣ የከተማዋ ፖሊስም የተጠቆመው ስፍራ ድረስ በመሄድ የተጠለፉትን ህጻናት እንዲያስለቅቅ፣ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ወንጀለኞች በቁጥጥር ስር እንዲያውል እና ህጻናቱን ከወላጆቻቸው ጋር እንዲያገናኝ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጡ፡፡

****

ችሎቱ በሰው ተሞልቷል፡፡ ጄራልድን የተኩት ዳኛ ሀሮልድ ሰዋንሰን ወደችሎቱ ሲገቡ ሰው በአክብሮት ተቀበላቸው፡፡ እንደ ዳኛ ጄራልድ በተጽእኖ ውሳኔ ይቀይሩ አይቀይሩ የታወቀ ነገር የለም፡፡ ውሳኔው እስኪደመጥ ማንም እርግጠኛ መሆን አልቻለም፡፡ ሰዋንሰን ተከሳሾቹ መቅረባቸውን ካረጋገጡ በኋላ የፍርድ ውሳኔ አስተላለፉ፡፡

"የህጻናቱ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በዋለው ችሎት የታየ እና ውሳኔ የተሰጠው መሆኑ ይታወሳል፡፡ ነገር ግን አቃቤ ህግ ይግባኝ በማለቱ፣ ይሩ በወጡ መረጃዎች እና የህዝብ ቅሬታ የተነሳ ጉዳዩን እንደገና መመልከት ግድ ብሏል፡፡ በዚህም መሰረት ጉዳዩን በጥልቀት ሲመረምር የቆየው ፍርድ ቤት ተከሳሾቹ በሙሉ ጥፋተኛ ሆነው ስላገኛቸው ህጻናቱን አስጠልፈው ወሲባዊ ጥቃት በፈጸሙት እና ለስቃይ እንዲሁም ለግድያ በዳረጉት ላይ የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት የወሰንን ሲሆን ህጻናቱን በመጥለፍ በተባበሩት ላይ ደግሞ

የለበራ አምስት አመት ጽኑ እስራት ወስነናል፡፡ መገገቡ ተዘግቷል"

አብዛኛዎቹ በፍርድ ውሳኔው ደስተኞች ናቸው፡፡ ሰዋንሰን ፖሊስ የተጠለፉትን ህጻናት እንዲያስለቅቅ እና ቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ወንጀለኞች በቁጥጥር ስር እንዲያውል እንዲሁም ህጻናቱን ከወላጆቻቸው ጋር እንዲያገናኝ ትእዛዝ ማስተላለፋቸውን ሶስና አድምጣለች፡፡ ጅማሬዋ አላሳፈራትም፡፡ ለቀጣይ እንቅስቃሴዋ በር ከፍቶላታል፡፡

****

አማሃ ውስጥ ይካሄድ የነበረውን እንቅስቃሴ ከሚላክለት ጋዜጣና ከአለም አቀፍ ቴሌቭዥቦን ጣቢያዎች ይከታተል የነበረው ኢስቱሊን ለሶስና ደወለላትና፡-

"እንኳን ደስ አለሽ" አላት፡፡

"አመሰግናለሁ፤ ውጤቱ የተሻለ ስራ እንድሰራ አነሳስቶኛል" አለችው፡፡

"ሌላም ሰው ሊያናግርሽ ይፈልጋል፡፡ አንዴ ቆይኝ?"

"ሃሎ" አለች ከኢስቱሊን ጓደኞችና የስራ ባልደረቦች አንዱ ሊሆን እንደሚችል በመገመት፡፡

"ማም እጅግ ኮርቼብሻለሁ" ሰለሞን ነበር፡፡ ሰውነቷን ወረራት፡፡ አይኖቿ እምባ አቀረሩ፡፡

"አመሰግናለሁ የእኔ ማር፡፡ ብዙ የምቆይ አይመስለኝም፡፡ እንገናኛለን"

"ችግር የለም፡፡ ተረጋግተሽ መምጣት ትችያለሽ"

ተሰናብታ ስልኳን ዘጋች፡፡ ሞላንሞል እየታያት ነው፡፡ ከጋዜጠኞች ጋር ባደረገችው የጋራ ትግል ህዝብን ለማነሳሳት፡ የመንግስትን ቀልብ ለመግዛት እና የተመኘችውን ውጤት ለማየት መንገዱን ጀምራለች፡፡ ምክትል ፕሬዚዳንቱ የተናገሩትን

እያንዳንዱን ቃል በጥንቃቄ ተከታትላለች፡፡ ለተግባራዊነቱ አልተጠራጠረችም፡፡ ከዚህ በኋላ በአማሃ ብዙ ላትቆይ ትችላለች፡፡ በወንጀለኞቹ ላይ የሚተላለፈውን የፍርድ ውሳኔ ከሰማችና ሀዳጉ ከወላጆቻቸው ጋር ሲገናኙ ከተመለከተች የሚያቆዩት ነገር አይኖርም፡፡

ክፍል አራት

- 25 -

ኢሊኖይስ፣ አሜሪካ

ከኤቢሲ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መሃል አንዱ ለሆነው ሮበርት አዳምስ የሃሪማን ፓሌይና የዮናታን ወልዴ እስር ቤት መወርወር ዱብዳ ሆኖበታል። ኢትዮጵያ ውስጥ የታሰበውን ሴራ የሚያደናቅፍም ሆኖበታል። አሌክሳንደር ቢሮ ተቀምጠ ያነበባቸው የአማሃ ጋዜጦች እስደናቂ ወሬዎችን ነው ያስነበቡት። ያጫቸው ሰዎች በወሲብ ቅሌት ወደእስር ቤት መወርወራቸውን፣ ጉዱን እየተከታተለች የምታስነብበው ተስፋ ጥሎባት የነበረችው ሶስና አለማየሁ መሆኗን፣ ከድርጊቱ ተሳታፊዎች እና ምስክሮች መሃል ዊል ብራውን በመርዝ መገደሉን፣ አድሪያን ሮክዌልም መሰወሩን እና የደረሰበት ያለመታወቁን ሆኖም በሴራ ህይወቱን ሳያጣ አይቀርም የሚሉ ግምቶች እና አስተያየቶች እየተሰጡ መሆናቸውን.....ሌላም ሌላም ጉዶችን አንብቧል።

"ውሾች.....ከንቱዎች ስንት እና ስንት የሚፈጽሙት ወሳኝ ተልእኮ እያለ ከሀጻናት ጋር ተልከስከሰው እስር ቤት ተወረወሩ" ሲል ከተሳደበ በኋላ ሃሳብ ገባው። የኢትዮጵያው እንቅስቃሴ ሊስተጓጎል?! በፍጹም። ሁለት ሰዎችን አስታወሰና ፈገግ አለ። ቄስ በቹን እና ረድኤትን። አማራጭ ተስፋዎቹ ናቸው።

- 26 -

ፓልማ፣ ማሎሮካ

ተልእኮዋን በድል ፈጽማ የተመለሰችው ሶስና እውቅና በተለይ በምስጢር ማህበራት ተቃዋሚዎች እና የሴራ አጋላጮች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። አብረሽን ስሪ የሚለው ጥያቄ እያጨና ነቃት ቢሆንም ለጊዜው የአንዳቸውንም ጥያቄ አልተቀበለችውም። ትኩረት ማድረግ የፈለገችው እራሷ ስራ ላይ ነው። የኑሮዋ ሁኔታ እያሳስባትም። እድሜ ለኢስቱሊን። ድጋፍ እያደረገላት ነው። ከኒብራስካ በተመለሰች ማግስት እቤቷ በመሄድ እንዲህ አላት፡-

"ረፍት አድርጊ፤ የሚያስቸኩልሽ ነገር የለም ያልኩሽን የምትዘነጊው አይመስለኝም። እንደዚያ ብልሽም መንፈስሽ ተረጋግቶ መቀመጥ ባለመቻሉ ኒብራስካ ሄደሽ አስመስጋኝ ስራ ሰርተሽ ተመልሰሻል። ከዚህ በኋላ የብዙ ጓደኞቼ በር ወለል ብሎ ስለተከፈተልሽ....." ሳታስጨርሰው ጣልቃ ገባች።

"የእራሴ የሆኑ እቅዶች እና ስራዎች ስላሉኝ ከማንም ጋር ለመስራት ፍቃደኛ አይደለሁም -ያለአንድ ሰው በስተቀር" ግራ ተጋባ። ያ አንድ ሰው ማነው?

"ያ ሰው ማነው? እሱን በመምረጥሽ ደስታ ሊሰማው ይገባዋል"

"ያ ሰው ማንም ሳይሆን አንተ ነህ። ፍቃደኛ ከሆንክ። ውለታ የዋልክልኝ እና በጨለማ ሰአት ብርሃን የሆንክልኝ ሰው ነህ። ከአንተ ጋር የመገናኘቱ አጋጣሚ ባይፈጠር ኖር የኔም ሆነ የልጄ እጣ ፋንታ ምን ሊሆን ይችል እንደነበር አላውቅም። ከሰራሁ አይቀር ከአንተ ጋር እንጂ....." አላስጨረሳትም።

"ባንዳና!" አላት። የኢስቱሊን ረዳት ሆና ተቀጠረች።

ባለሙያዎችንና ለመረጃ ቅርብ የሆኑ ሰዎችን እያነጋገረችና የምስጢር ማህበራቱ ስብሰባ በሚያደርጉበት ስፍራ እየተገኘች

የተከታተለችውን ለድረ-ገጹ ግብአት ይሆን ዘንድ ታተርብለታለች፡፡ በታታሪነቷ ወዷታል፡፡ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ በመፍጠሯ ህይወቷ ለችግር እንደማይጋለጥ እርግጠኛ ሆናለች፡፡ በመድረክ ገለጻዎችም ላይ ረዳቱ ነች፡፡ የሙያ ተሞክሮዋ ልትጽፈው ላሰበችው መጽሃፍ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ሊያበረክትላት እንደሚችል እምነት አላት፡፡ ከሴራ አጋላጮች ጋር ለመተዋወቅ በመቻሏ ደስተኛ ሆናለች፡፡ በዶክተር ናንሲ ላንክቶት የተዘጋጀው የገለጻ መድረክ ወደ መደበኛ ስራዋ የምትሰማራበት የመጀመሪያ መድረኳ ይሆናል፡፡ በመድረክ ገለጻ ላይ ስትገኝ የመጀመሪያዋ ነው፡፡

****

በድረ-ገጾች ላይ የተመለከተቻቸው መረጃዎች የሂዮንሴ ኖውልስን ጉብኝት እና የሙዚቃ ፕሮግራም ይፋ ስላደረጉላት ወደ ኢትዮጵያ የመሄዱ ዜና እውነት እንደሆነ አረጋግጣለች፡፡ ከሃይማኖት አባቶች ጋር ካልተገናኘችስ? የተጋነነ አቀባበል ካልተደረገላትስ? ለህጻናት የሰይጣናዊ አምልኮ ምልክቶችን ካላስተዋወቀችስ? ስህተት ላይ ላለመውደቅ አርቲስቷ በኢትዮጵያ የምታደርገውን ቆይታ ካጠናቀቀች በኋላ ከምትመለከተው እውነት ላይ በመነሳት ሚዛናዊ የሆነ ጽሁፍ ለማስተናገድ ራሷን አሳመነች፡፡ አርቲስቷ እንደተባለው ሰይጣናዊ እምነትን በሚሰብክ መልኩ በሃገሯ ከተንቀሳቀሰች፣ ህጻናቱን ከምልክቶች ጋር ካስተዋወቀች፣ በተጋነነ ሃይማኖታዊ ስርአት ደጀሰላም ከረገጠች ያ ድርጊት እንዳይደገም የሚያሳስብና በነሃሪማን ፓሊይ ፊት አውራሪነት በስኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት አዳራሽ ውስጥ የተከናወነውን ሁሉ ይፋ ታደርጋለች፡፡ ሀገሩን ከምስጢር ማህበር አባላት ሴራ ለመታደግ የማይንቀሳቀስ ህዝብ እንደማይኖር እርግጠኛ ነች፡፡ የትምህርት ቤቱን እውነታ በምትጽፈው መጽሃፍ ላይ የማጋለጥ እቅድ ቢኖራትም አሁን ግን የሂዮንሴ ኖውልስን ተልእኮ እንድታጋልጥ አቋራጭ መንገድ ሊሆናት ነው፡፡ የሚሆነውን በትእግስት መጠበቅ መርጣለች፡፡ ከዘጠኝ እና አስር ቀናት ላልበለጠ ጊዜ መታገስ አያቅታትም፡፡

- 27 -

ማድሪድ፣ ስፔን

በዳንኤል ኢስቱሊን ጋባዥነት በህክምናው አለም እየተፈጸመ ያለውን ደባ አስመልክቶ ገለጻ ለማድረግ ስፔን ዋና ከተማ ማድሪድ የገባችው ዶክተር ናንሲ ላንክቶት፣ በተደረገላት ሞቅ ያለ አቀባበል ከፍተኛ ደስታ ተሰምቷታል። በትውልድ ሀገሯ ካናዳ ረዘም ላሉ አመታት በህክምና ሙያ ላይ ያሳለፈችውና ጥናትና ምርምር ባደረገችባቸው ሃገራት የተመለከተችውን ደባ <The Medical Cheater> በተሰኘው ድንቅ መጽሃፏ ያጋለጠችው ዶክተር ናንሲ ይህን ያህል ህዝብ ገለጻዬን ለማዳመጥ ይመጣል ብላ አላሰበችም። ኢስቱሊን ስፔን ውስጥ ብዙ ተከታዮችና አድናቂዎች እንዳሉት ብታውቅም ይህን ያህል የህዝብ ቁጥር አልገመተችም። ሰፊው አዳራሽ በህዝብ ተጨናንቋል። ገለጻዋን ለማድመጥ የመጡ መሆናቸውን በማወቋ ስሜትን የሚያሞቅ ደስታ ተሰምቷታል። በስራ አጋጣሚ የተመለከተችውን፣ በጥናት እና ምርምር ላይ ሳለች የታዘበችውን የህክምና አለም ደባ ይፋ ለማድረግ ለእራሷ ቃል ገባች። የዓለም ህዝብ በጠቅላላ ደባውን ቢያውቅ ብላ ተመኘች። ወደ መድረኩ በማምራት ላይ ሳለች ጭብጨባ ተከተላት።

ስሟን እና ሙያዋን አስተዋውቃ ወደ ንጥቧ አመራች።

"በመሃላችሁ በመገኘቴ ታላቅ ደስታና ኩራት ይሰማኛል። ዋነኛ አጀንዳቸውን ከአለም ህዝብ ደብቀው በክፋት ጎዳና በመገስገስ ላይ ያሉት የምስጢር ማህበራቱ አባላት ሴራ እስካልተገታ በህክምናው አለም እየተፈጸመ ያለው ደባ ሊገታ ይችላል ብዬ አላምንም። በደባው ህጻናትንና ሴቶችን ጨምሮ የበርካቶች ህይወት እየተቀጨ ነው። የህክምና ቁሶችና መድሃኒቶች እንደልብ በማይገኙበት ዘመን አማካይ እድሜ በሰማኒያዎቹና በዘጠናዎቹ

መሃል የሚገኝ ነበር። ብዙ ነገር ተሻሽሏል ተብሎ በሚታመንበት በአሁኑ ወቅት ግን ወደስልሳዎቹና ወደሰባዎቹ እየወረደ ነው። ለምን? ከስልጣኔና ከነገሮች መሻሻል ጋር የሰው ልጅች እድሜ መጨመር ሲገባው እየቀነሰ የመጣበትን ምክንያት በጥልቀት ከልመረመርንና ካልተገነዘብን በስተቀር የህክምናው አለም ደባ እንቆቅልሽ ላይ ፈታልን ይችላል። በምስጢር ማህበራቱ ሰዎች የመድሃኒት ፋብሪካዎች እየተመረቱ የዓለምን ህዝብ ቁጥር ለመቀነስ አገልግሎት ላይ የሚውሉት መድሃኒቶች አይነትና ቁጥር ከእለት እለት እየጨመረ ነው። በየትኛውም የእድሜ ክልል ላይ ያለ ግለሰብን ህይወት በአጭር የማስቀረት ሃይል ያላቸው ቢሆኑም ቀነኛ ተጠቂዎቹ ግን ህጻናት ናቸው። መድሃኒቶቹንና ታቅደው የሚመረቱ ለሰላሳ መጠጦችን እንዲሁም የታሸጉ ምግቦችን በብዛት የሚጠቀሙት ህጻናት በመሆናቸው ነው።"

የሶስና ልብ እንደኳስ ነጠረ። ልጇን አስታወሰችው። ጥሩ ስሜት አልተሰማትም። ዶክተር ናንሲ ቀጠለች፦

"የተመረዙት ምግቦችና መጠጦች እንዲሁም መድሃኒቶች የትኞቹ እንደሆኑ እንመለከታለን። ከአስፓርቴም እጀምራለሁ። በለስላሳ መጠጦችና የታሸጉ ምግቦች ውስጥ ይገኛል። በአብዛኛው የሚጠቀሙት ህጻናት መሆናቸው አይጠፉንም። ከጎንዮሽ ጉዳት አንጻር ሰኳርን ለመተካት በሚል ሰበብ እ.ኤ.አ በ1981 ዓ.ም አገልግሎት ላይ የዋለው ይህ ማጣፈጫ የትውስታ ችግርን፣ በሴቶች ላይ የወር አበባ ጊዜ መዛባትን፣ ድብርትን፣ በልጆች ላይ መንተባተብን፣ እይታን መከልከልን እና ሌሎች ችግሮችን የሚያስከትል ነው.....

"ቀጥሎ የምንመለከተው ፕሮዛክ በመባል የሚታወቀውን የመድሃኒት አይነት ነው። በነገራችን ላይ ይህን መድሃኒት የሰከል ኤንድ ቦንስ አባል የሆኑት የተድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ መድሃኒት ኩባንያ <Eli Lilly> የሚያመርተው መሆኑን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። እንደ አስፓርቴም ትውስታን ለመንጠቅ፣ የማየት ችሎታን ለመጋረድ፣ ሰዎችን ለአእምሮ ቁጥር

ለማመቻቸት፣ በድብርት ስሜት ውስጥ ሆነው የተሻለ ነገርን እንዳያስቡ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። ሰዎችን ግልፍተኛ የማድረግ፣ ወደወንጀል የመግፋፋት ባህሪም አለው። ተመራምረዋል የሚባሉ ባለሙያዎች አገልግሎት ላይ እንዲውል ተባባሪዎች ሆነው መገኘታቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው። ከባለሙያዎች መሃል አንዱን በምሳሌነት ማቅረብ እንችላለን። ዴቪድ ደነር ይባላል። የዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ ምሁር ነው። የጆርጅ ቡሽ መድሃኒት ኩባንያ ከአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር በላይ መድቦለት ጥናትና ምርምር ካካሄደ በኋላ ፕሮዛክ ፍቱን ነው የሚል ምስክርነትን ነው የሰጠው። እውነታው ጠፍቶት አይደለም። የሰዎቹ ሃይል እና ገንዘብ ሚዛን ደፍቶ እንጂ። ፍቱንነቱን ያረጋገጠው ደነር ብቻ አይደለም። የአሜሪካ የምግብ እና መድሃኒት አስተዳደርም ማረጋገጫ ሰጥቷል። የመድሃኒቱ ውጤትስ? መሰረታዊው ጥያቄ ይህ ነው.....

"የጆርጅ ቡሽ ሰዎች ለዴቪድ ደነር ገንዘቡን ሲሰጡት በመጀመሪያ መድሃኒቱን በአንድ መቶ ሰዎች ላይ እንዲሞክር እና ውጤቱን እንዲያሳውቃቸው በማሰገንዘብ ነበር። ኤፍዲኤ በ1987 ዓ.ም የአሜሪካ የምግብና መድሃኒት አስተዳደር ለፕሮዛክ ማረጋገጫ ከመስጠቱ ሁለት ወር ቀደም ብሎ ሃያ ሰባት ሰዎች በህክምና ምርመራ ሙከራው ጊዜ ለህልፈት ተዳርገዋል። አስራ አምስቱ አራሳቸውን በእራሳቸው ሲያጠፉ ስድስቱ ከመጠን በላይ መድሃኒት ወሰዱ። አራቱ የጥይት አራት ሲሆኑ ሁለቱ ውሃ ውስጥ ሰጥመው ሞቱ። ውጤቱን ተከትሎ ለምግብና መድሃኒት አስተዳደሩ በርካታ ሪፖርቶች ቢደርሱትም ተቀባይነትን አላገኙም። የልብ ልብ የተሰማቸው የኩባንያው ሰዎች አሁንም ድረስ በሰፋት ለልጆች እያስተዋወቁት ነው።"

የሶስና ልብ ለሁለተኛ ጊዜ ነጠረ። ልጇን በድጋሚ አስታወሰችው። የምትኖርበትን ዓለም እንደማታውቀው እርግጠኛ ሆናለች። የምስጢር ማህበራቱን አባላት ይበልጥ ጠላቻቸው፣ ተጠየፈቻቸው፣ ይበልጥ ልትታገላቸው ቃል ገባች። ዶክተር ናንሲ ላንክቶት ገለጻዎን ቀጥላለች።

"የጉዳት መጠኑን በአሃዝ እንመልከተው፡፡ የደባውን አደገኝነት እንድንገነዘብ ይረዳናል፡፡ እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም ብቻ በፕሮዛክ የተከሰቱ ሁለት ሚሊዮን ሰምንት መቶ ሰልሳ ሺህ ሳጂ ውጤቶች ይፋ ሆነዋል፡፡ <ጅምላ ጨራሽ ጥፋት ያለመሳሪያ> ብላችሁ ልትጠሩት ትችላላችሁ፡፡"

ሶስና አማተበች፡፡ ዶክተሯ በገለጻዋ በጎሩች ቁጥር ፍርሃቷ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በቀጥታ ያገናኘችው ከልጇ ህልውና ጋር ነው፡፡

"ሌሎች እውነቶችን ልንገራችሁ" አለች ዶክተር ናንሲ፣ የዓይን መነጽሯን እያስተካከለች፡፡ "ስኮትላንድ ደንብሌን ውስጥ ህጻናትን የጨፈጨፈውን ቶማስ ሃሚልተንን ፖሊሶች አስመርምረውት ነበር፡፡ ጤነኛ ሰው ህጻናትን አይጨፈጭፍም ብለው በማሰባቸው ነው፡፡ ጥሩ ገምተዋል፡፡ ሃሚልተን ፕሮዛክ የተሰኘውን መድሃኒት መውሰዱ ተረጋገጠ፡፡ የኮሎምቢያን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪው ኤሪክ ሎካ ሃሪስ በታዳጊነት እድሜው በአቻዎቹ ላይ የከፈተው የተኩስ እሩምታ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ነበር፡፡ ሃኪሞች ባደረጉለት ምርመራ <ሉቮክስ> የተሰኘና የፕሮዛክ ይዘት ያለው መድሃኒት መውሰዱ ነው የተረጋገጠው፡፡ ዓለም በፍቅር የሚያነሳሳት የዌልያ ልእልት ዲያና በመኪና አደጋ ህይወቷን እንዳጣች በመኪናዋ ፍጥነት የተደነቁ አስተያየት ሰጪዎች ጤነኛ ፍጡር በዚህ ፍጥነት ሊያሽከረክር አይችልም የሚል አስተያየት በመሰንዘራቸው ጥርጣሬ የገባው ፖሊስ የሹፌሩን ሄንሪ ፖወል ደም አስመረመረ፡፡ ውጤቱ ምን እንዳረጋገጠ ታውቃላችሁ? በደሙ ውስጥ የፕሮዛክ ንጥረ-ነገር መገኘቱን፡፡ ፕሮዛክ ለብዙዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ቢሆንም በምስጢር ማህበራት ውስጥ የተሰገሰጉ ሃያላን ሰዎች ህጻናት ፕሮዛክን ይጠቀሙ ዘንድ አሁንም ድረስ መወትወታቸው አልቀረም፡፡ ሌሎች መድሃኒቶችንም እናንሳ፡፡ ሪታሊንን አስቀድሚያለሁ፡፡ ህጻናትን ኢላማ አድርጎ የሚመረት ነው፡፡ አእምሮን የመቀየር ሃይል አለው፡፡ ሪታሊንን የወሰዱ ታዳጊዎች የባህሪ ለውጥ ቢያሳዩ ልንደነቅ አይገባም፡፡ ለአመጽ ቅርብ እንደሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ የአሜሪካ መንግስት

ሪታሊንን በኒኬይን እና በሄሮይን ምድብ ውስጥ ቢያስቀምጠውም በአሜሪካ ብቻ በየአለቱ ሶስት መቶ ሰላሳ ሚሊዮን ያህል መጠን ያለው ሪታሊን አገልግሎት ላይ ይውላል.....

"ከክትባቶች ጀርባ የሚሰራውም ቅጥፈት የተለየ አይደለም። የምስጢር ማህበራቱ ሰዎች የዓለምን ህዝብ ቁጥር ለመቀነስ ከድሮ ጀምሮ ሲጥሩ ቆይተዋል። ከክትባቶች ጀርባ የሚሰራውን ቅጥፈት ለመረዳት የአውስትራሊያዊውን ተመራማሪ ኢያን ሲንክሌይርን ተሞክሮ መመልከት ይኖርብናል።"

እጇ ላይ ካንጠለጠለችው የውሃ ፕላስቲክ ስትንነጭ ሶስና በተመስጦ ተመለከተቻት። ገለጻው የፍርሃት ዓለም ውስጥ ከታታል። እያንዳንዱን እውነት በሰማች ቁጥር ሃሳቧን ወደ ልጇ ትልከዋለች። በልጇና በመላው አለም በሚገኙ ምስኪን ህጻናት ላይ እየተፈጸመ ያለው ደባ ገዝፎ ይታያታል። ያለሃጢያታቸው እየተቀጡ እንደሆነ ትረዳለች። ሴረኞቹን ለመፋለም ያላት ፍላጎት ይጨምራል። ዶክተሯ ወደ ገለጻዋ ስትመለስ እሷም ሂዳበት ከነበረው የሃሳብ አለም ተመለሰች።

"ኢያን ሲንክሌይር <Health: The Only Immunity>ን ጨምሮ ተከታታይ መጻህፍትንና የምርምር ጽሁፎችን አበርክቶልናል። በር ዘግቶ የደከመበትን የምርምር ውጤት እንደሚከተለው ይገልጽልናል። "ውጤቶቹን በዝርዝር አስቀመጠቻቸው።

*ስእላዊና ስታትስቲካዊ መረጃዎች ክትባት ከመጀመሩ በፊት በተላላፊ በሽታዎች ምክንያት ይከሰት የነበረው የሞት መጠን ዘጠና ከመቶ ያህል መቀነሱን ያመለክታሉ። የህክምና ጆርናሎች የሞት መጠኑ በተጠቀሰው አሃዝ ልክ ያሽቆለቆለው የጤና አጠባበቅ ስርአቱ በመሻሻሉና ጤናማ የአመጋገብ ስርአት ተግባራዊ በመሆኑ እንደሆነ ነው ያመኑት። የሞት መጠኑን የቀነሰው የጤና አጠባበቅ ስርአትና ጤናማ የአመጋገብ ስርአት እንጂ ክትባት አይደለም.....

*ሀ*ለት መቶ ሰልሳ ሺህ ሀንዳውያንን ያካተተ የሳምባ ነቀርሳ ክትባት መከራ ሀንድ ውስጥ ተካሂዶ ነበር። የደረስኩበት የጥናት ውጤት እንዳመለከተው ካልተከተቡት ይልቅ በተከተቡት ላይ

በሽታው መታየቱን ነው፡፡ አሁንም ድረስ በአውስትራሊያና በቀረው አለም የሚገኙ ልጆች ከትባቱን እየወሰዱ ነው.....

"ለላል ተብሎ የሚታዘዘው የክትባት መድሃኒት ዋጋ በ1982 ዓ.ም እ.ኤ.አ ከነበረው የአስራ አንድ ሳንቲም ተመን በ1985 ዓ.ም ወደ አስራ አንድ ነጥብ አራት ዜሮ ዶላር አሻቅቧል፡፡ በሳንቲምና በዶላር መካከል ያለውን ልዩነት መገመት ይቻላል፡፡ ለህዝብ ጤንነት የሚያስብ በአምስት አመታት ውስጥ ይህን ያህል ዋጋ አይከምርም.....

"በሶስተኛው አለም የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ህጻናት ክትባት ይሰጣል በተባለበት ዘመንም ላይ ሆነን በሳምባ ነቀርሳ፣ በኩፍኝ፣ ተላላፊ የጉሮሮ በሽታ፣ መንጋጋ ቆልፍ፣ የልጅነት ልምሻ እና በሌሎችም በርካታ በሽታዎች እየሞቱ ነው፡፡ ክትባት በመፍትሄነት ከቀረበበ በሽታዎቹ የሚከሰተው አሰፈሪ ሞት ለምን አልቆመም? ወይም መጠኑን አልቀነሰም?.....

"የአውስትራሊያዊው ተመራማሪ የምርምር ውጤት ይህን ይመስላል፡፡ ከሲንክሌይርም ሆነ ለሰው ልጆች ህይወት ከሚጨነቁ የህክምና ባለሙያዎች የጥናት ውጤት ላይ ተንስተን የምንደርስበት መደምደሚያ የህክምናውን አለም ሸፍጥና ሴራ የሚያመለክት ነው፡፡ ከማብቃቴ በፊት ዶክተር ሪማ ሌይቦው ለሴራ አጋላጩ ጄሲ ቬንቹራ በዝርዝር ያጫወተችውን ገጠመኟን ቀንጭቤ ልንገራችሁ፡፡ «ብዙውን እውነት // ሚዲሳል ማፍያ በተሰኘው መጽሃፌ ላይ ገልጬዋለሁ፡፡ ለማመንም ሆነ ላለማመን እንደምትቸገር አምናለሁ፡፡ አልፈርድብህም፡፡ ከሰው አብራክ የተፈጠረ እንዲህ አይነት ጭካኔና ግፍ ተሞላበት ጅምላ ጭፍጨፋ ይፈጽማል ተብሎ አይገመትማ! ደጋግሚ የምናገረውን አሁንም ልናገር፡፡ የጠቀስኩልህ መጽሃፌም ሆነ የቀድሞ መጽሃፎቹ ዋና አላማ አንዳንዶች እንደሚያስቡት አንተንም ሆነ አንባቢን ፍርሃት አዘል ጭንቀት ውስጥ መክተት አይደለም፡፡ በህክምና ስም የተፈጸመውንና እየተፈጸመ ያለውን እውነት ማሳወቅ ነው».....

"እውነታውን ሸሽተን የትም አንደርስም። በአሰመሳይ መድሃኒቶች ህጻናትን እና ሴቶችን ጨምሮ ብዙዎች እያለቁ ነው። የሚበጀን ከሴራቸው የምናመልጥበትን መንገድ መፈለግ ነው። ባለሙያዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ቢጮሁም ጆሮ አላገኙም። አደገኛዎቹ መድሃኒቶች የአለም ህዝብ ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ቀጥለዋል፣ አዋጭ የገቢ ምንጭም ሆነውላቸዋል። እየኖርንበት ያለው አለም እውነት ይህ ነው። ካንቀላፋንበት እንንቃ። አመሰግናለሁ።"

በጋለው ጭብጨባ ውስጥ ለሶስና የሚሰማት ድምጽ ሌላ ነበር። ልጅሽን ጨምሮ የሃገርሽ ህጻናት፣ የአህጉርሽ ህጻናት፣ የአለም ህጻናት የከፉ አደጋ ላይ ናቸውና አድኚያቸው የሚል በውስጧ እየጮኸ ነው። ሰላሟን ነሳት። ስሜቷን አደፈረሰው። ጥቂት የሰይጣን መልእክተኞች መንጋውን የዓለም ህዝብ ባሻቸው ጎዳና ላይ እየነዱት ነው። ሃይ ባይ ያሻቸዋል። ሃይ ባይ ለመሆን፣ ያንቀላፋውን መንጋ ለመቀስቀስ መስዋእት መሆን ግድ ይላል። የልጇን ህይወት ማዳን እስካስቻላት፣ የሃገሯን ህዝብ ህይወት መታደግ እስካስቻላት፣ የዓለምን ህጻናት በአጭር መቀጨት ማስቆም እስካስቻላት መስዋእት ትሆናለች። የሚያቆማት ሃይል አይኖርም። የማይታጠፍ ቃልኪዳኗ፣ የማይበጠስ የእምነት ማህተቧ ነው።

- 28 -

ፓልማ፣ ማሎርካ

ከሬድኤት ሃይላይ ጋር ቀጠሮ እንዳላት ያልዘነጋችው ሶስና መሰናዶዋን የጀመረችው ማለዳ ነው። "በመሃላችን መተማመንና መተባበር እስካልተፈጠረ ሀገራችንን ከምስጢር ማህበራቱ ተንኮልና ሴራ ማዳን አንችልም። የምትሰሚኝ ከሆነ ቅርባቸው ነኝና በሃገራችን ላይ የሚዶለተውን ሴራ በምስጢር አሳውቅሻለሁ። የማክሸፉ ተግባር ያንቺ ይሆናል" ብሏታል። ኢስቱሊንም የመረጃ ምንጯን ሙሉ በሙሉ ማራቅ እንደማይገባትና በጥንቃቄ ልትጠቀምበት እንደሚገባት መክሯታል። ታምነዋለች። ታከብረዋለች። ከስራ ልምዱ ብዙ እውቀት ቀስማለች። በስራ ልምድ የሚበልጥን ታማኝ ሰው ምክር መቀበል ጠቀሜታው ሚዛን እንደሚደፋ በማወቋ ሬድኤት ሃይላይን ተቀብላ ለማነጋገር ፍቃደኛ ሆናለች። ስብሰባው ቢጠናቀቅም ለልዩ ተልእኮ ለሃያ አንድ ቀናት እንደሚቆይ ነግሯታል። ለደህንነት ሲባል የቀጠሮ ቦታቸው ሶስና መኖሪያ ቤት ይሆን ዘንድ ወስነዋል። ሶስና ኢስቱሊንም እንዲገኝ ፈልጋ የነበረ ቢሆንም

"ዛሬ ብቻችሁን አውሩ። በመጀመሪያው ቀን ነጻነት ያስፈልጋችኋል። ሌላ ሰው እንዲሰማው የማይፈልገው፣ ለአንቺ ብቻ ሊነግርሽ የሚሻው መረጃ ይኖረው ይሆናል። ፍቃደኛ ከሆነ በቀጣይ ቀጠሯችሁ ላይ እገኛለሁ" ብሎ ተከላክሏታል። ሰለሞንም ትምህርት ቤት ስለሚውል በነጻነት እንደሚያወሩ እርግጠኛ ሆናለች።

ዋነኛ ርእሳቸው ሂዮንሴ ናውልስ ነች። በኢትዮጵያ ቆይታዋና በሙዚቃ ዝግጅት ስም የሰይጣን አምልኮ ተልእኮዋን ከመፈጸሟ በፊት አቅዷ የሚከሽፍበትን መንገድ ለመነጋገር ነው የተቀጣጠሩት።

ሮበርት አዳምስ በሶስና ቦታ ለሚተካው ሰው ያወጣው የብቁነት መመዘኛ በአካዳሚ እውቀቱ የተሻለ፣ የአለቆቹን ትእዛዝ የሚቀበልና የአንድ ዓለም አስተዳደሩን ተግባራዊነት የሚደግፍ የሚል እንደሆነ የተረዳው ረድኤት እጹ የገባውን የጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲ የፋከስ መልእክት ከተመለከተ በኋላ እንደሳቀባቸው ያስታውሳል። የስኩል ኦፍ ዋን ግሎባል ሃላፊዎች ፈጽሞ እንደማያውቁት እርግጠኛ ነው። እንኳንስ ፉዙዎቹ የስኩል ኦፍ ዋን ግሎባል ሃላፊዎች ይቅሩና በሴራ ተግባራቸው የተራቀቁት የመለመሉት ሰዎችም ሊያውቁት እንደማይችሉ እርግጠኛ ነው። ምስጢራዊነት የአስተዳደጉ ውጤት ነው። ያለወላጅ ፍቅር በህጻናት ማሳደጊያ ማእከል ውስጥ ያሳለፈውን ጊዜ አይረሳውም። ያለእናት፣ አባት፣ እህት እና ወንድም መኖር የሚፈጥረውን ስሜት የደረሰበት ብቻ ነው የሚያውቀው። ለአቅመ-አዳም ደርሶ፣ ትምህርቱን ጨርሶ በስራ አለም እስከተሰማራበት ጊዜ ድረስ የተመለከታቸው ውጣ ውረዶች ሰው እራሱን ነጻ አስካላወጣ ድረስ በባርነት ህይወት መኖሩ የግድ እንደሚሆን አሳይተውታል። ከዚህ በኋላ በባርነት ህይወት ላለመኖር የሚይሆነው የለም። ኑሮ፣ የተጎሳቆለ ኑሮ፣ በግለሰቦች በተለይ በባለስልጣናት፣ በቀበሌ ሹሞች በአጠቃላይ በባለወንበሮች የሚፈጸሙ በደሎች ብልጥ፣ ተመሳስሎ የሚኖር፣ ጥቅሙን የሚያስቀድም፣ በተገኘው አጋጣሚ በስልጣን መሰላል ላይ የመንጠልጠል ፍላጎት ያለው ሰው እንዲሆን አድርገውታል። ስልጣን ማለት ገንዘብ፣ ወገን፣ የፈለጉትን ማግኘት፣ ያለመገሩት ማለት እንደሆነ ያሳለፉቸው አመታት አሳይተውታል። ጋሽ ሙደሲርንና መሰሎቻቸውን ያስታውሳቸዋል። "ቀድሞ" ወይም "ይሆ" መገኘት አማራጭ የሌለው የህይወት አቋራጭ መንገድ መሆኑን አምኖ ተቀብሏል። ታማኝነትን እና የዋህነትን የተሰበኩ ሃቀኞች ከድህነት ጠለል በታች እየሰጠሙ ሲሄዱ የዘመኑ ስሌት የገባቸው ደግሞ የዘመኑ የጨዋታ ህግ በሚፈቅደው የመብለጥለጥ ስልት ተጠቅመው ወደላይ ሲመነደጉ ታዝቧል። ምርጫው ሁለተኛው ነው። በግ መሆን አይፈልግም፣ እንዲህም ሆኖ ለሃገሩ ያለው ፍቅር የተለየ ነው። ዐበ ከግለሰቦች እንጂ ከሃገሩ ጋር አይደለም።

ይህን አስተሳሰብ ይዞ ነው አሜሪካ የገባው፣ ከሰምቹ ጋር ለመስራት የተስማማው። ብዙም ወዳጆች ባይኖሩትም የሚቀርቡት ጥቂቶች "ይህን የመሰለ ሞንቅላት ይዘህ ቅን ብትሆን...." ሲሉ የባህሪውን መንጋደድ ሊነግሩት ሲሞክሩ

"የቅንነት ትርጉሙ በደንብ አልገባችሁምና አርፋችሁ ተቀመጡ። ቅንነትን ሲሰብኩ የሚኖሩ ናቸው ቅንነትን ሲያጠፉት የሚታዩት። ሁላችንም በሚያዋጣን የህይወት መንገድ እንሂድ። መካሪ አያስፈልገኝም። የማደርገውንና የሚያዋጣኝን፣ የሚሆነኝን የማውቅ ሰው ነኝ" ሲል እምርሮ ይከራከራቸዋል። ለረድኤት የሚነገረውና በተግባር የሚታየው የሰማይና የምድር ያህል እርቀት አለው። ሁሌም መጓዝ የሚፈልገው ልቡ በመራው የራሱ መንገድ ነው።

መሰል ሃሳቦችን እያሰላሰለ ሶስና ቤት ደረሰ። በምልክት ስለነገረችው አልተቸገረም፣ አቀባበሏ ደስ አሰኘው። ቤቷ አነስ ያለች ብትሆንም ጽድት ያለች ነች። ወደ ሳሎን አመሩ። ብቻዋን ነበረች። ከጠዋቱ 4፡35። የምታቀርበውን አቀራርባ ፊትለፊቱ ተቀመጠች።

"እራስህን አስተናግድ" አለችው ፊግማታዋን አስቀድማ። ሳንዱዊቹን ከገመጠ በኋላ ቡና ቀዳ። ለቡና ፍቅር አለው።

"ቀኑን ሙሉ ምግብ ብላ ከሚሉኝ ቡና ስትጋት ዋል ቢሉኝ ምርጫዬ ነው"

"ከቡና መገኛ ሃገር ስለተገኘህ ይሆናል"

"ያንቺም መሰረት ኢትዮጵያ ናት"

በአምንታ ራሷን ነቀነቀች። የሀገሯ ነገር ሲነሳ ትካዜ ይቀናታል።

"ትዝታ ቀሰቀስኩ መሰለኝ?" አላት የቡና ስኒውን እያስቀመጠ።

"ኢትዮጵያ ውስጥ አልኖርኩም። ለጥቂት ጊዜያት ነው የነበኘኋት። ያም ሆኖ ረጅም ጊዜ የማውቃትን ያህል ነው

የሚሰማኝ፣ የአባቱ ተጽእኖ ሰላረፈብኝ ይሆናል፣ በየጊዜው ስለኢትዮጵያ ይነግረኝ ነበር፣ እንድወዳት፣ ድሃ ሀገር ብትሆንም እናቱ ናትና እንዳልተዋት፣ እንዳልከዳት ያስጠነቅቀኝ ነበር፣ እናት አጣች፣ ነጣች፣ ደኸየች፣ ተጎሳቆለች ተብላ አትተውም" አለችና በሃሳብ አለም ነጎደች፣ ንግግሯ ለአጀንዳቸው ምክንያት በመሆኑ ደስ እያለው ወዳገናኛቸው የጋራ ርእስ አመራ፣

ዋንኛ ርእሳቸው ሂዮንሴ ኖውልስ ብትሆንም አብይ አጀንዳቸው ኢትዮጵያ ናት፣ ከሃሳብ ዓለሟ ተመልሳ በንግግሯ ከመቀጠሏ በፊት ጣልቃ ገባ፦

"ኢትዮጵያ ድሃ አይደለችም፣ ያጣች የነጣች ያደረጓት እየተፈራረቁ የቦጠቦጧት መሪዎቿ እና ባለስልጣኖች ናቸው፣ ለእኔ እና ለቤተሰቤ የሚለውን ራስ ወዳድነታቸውን ትተው ለእኛና ለህዝባችን፣ ለሃገራችን የሚለውን ቅዱስ ሃሳብ ቢተገብሩ ለሌሎችም የምትተርፍ ሃገር ነበረች፣ ከባዱ ፕሮፓጋንዳ አትቁጠሪብኝ እንጂ በአጥንቷ ያስቀሯት መሪዎቿ ናቸው፣

"ከአንቺ በበለጠ ኢትዮጵያን አውቃታለሁ፣ በስራ አጋጣሚ በየቢሮው እየተፈጸመ ያለውን ዘግናኝ ተግባር ለመመልከት እድሉ ነበረኝ፣ ሃምሳዎቹ መጨረሻ የእድሜ ክልል ውስጥ እየገባሁ ነው፣ ትላንት፣ በወጣትነቴ ሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ ሳለሁ የማስታውሳት ኢትዮጵያን እና የዛሬዋን ኢትዮጵያን ባነጻጽር እንኳን ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አላቸው፣ ያቺ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያደረባት፣ ልጆቿ የሚፋቀሩባት፣ ያገኙትን ተካፍለው የሚበሉባት፣ ድሃ ብትሆንም በአምላክ ረድኤት የምትኖር ኢትዮጵያ ዛሬ የለችም፣ የዛሬዋ ኢትዮጵያ አዲስ ኢትዮጵያ ናት፣ የትላንቷ ግልባጭ፣ ዜጎቿ ግራ የተጋቡባት፣ አምባገነን የቀበሌ ሹሞች ዘውድ የጫኑባት፣ በኢኮኖሚ አቅማቸው ሳይሆን አስማት በሚመስል ተአምር የሚኖሩ ዜጎች የበረከቱባት፣ የለፉ የከሰሩባት፣ የሰረቁና ያጭበረበሩ የበለጸጉባት ኢትዮጵያ፣ በወርሃዊ ደሞዛቸው ተመስገን ብለው በእርጋታና በሰላም የሚኖሩ ዜጎችን ሳይሆን በተአምር በአንድ ሌሊት ባለበርካታ ህንጻዎች ባለቤት ሆነው ያለእንቅልፍ የሚያነጉ ዜጎችን በእናትነት ተቀብላ ናላዋ የዞረ ኢትዮጵያ፣ ከእንቅልፉ ስለተጣላ

ራሱን በዊስኪ ሽንግሎ ሌሊቱን በአስረሽ ምቺው ፈንጠዝያ ካሳለፈ በኋላ ንጋት ላይ ወደ ቤተክርስትያን የሚያቀና ሃብታም ከኢትዮጵያ ውጪ በሌላ ሀገርም ይኖር ይሆን?.....

"ዝምታን ምርጫቸው ያደረጉ ዜጎቿ የተቀበሩባት፣ በእጭበርባሪ ምላሳቸው <አለን> ያሉ የተንሰራፉባት ኢትዮጵያ፡፡ ብዙ ነገር ተተረማምሷል ሶስና፡፡ በሰው ልጅ ልብ ላይ ፍቅርና ተስፋን ሳይሆን በተዘረፈ መሬት ላይ ህንጻን የሚያበቅል ራስወዳድ ትውልድ እንደአሸን እየፈላ ነው፡፡ ወሬያም እንጂ ተግባራም ያልሆነ ትውልድ፡፡ ለዚህች ምስኪን ሀገር አዝንላታለሁ፡፡ ትተሃት መጥተህ እንዴት አዝንላታለሁ ትለኛለህ ማለትሽ አይቀርም፡፡ ሃቅ አለሽ፡፡ በየበረሃ ከሞት ጋር እየተፋጨ ለመስደትን ብቸኛ አማራጭ ያደረገ ዜጋ ሀገሩን ጠልቶ ነው? ከቤተሰቡ ተነጥሎ መኖርን ወዶ ነው? በፍጹም! ጥቅም ፈላጊውም፣ ሃቀኛውም፣ ክፉውም፣ ደጉም በደል ያደረሱበትን ሹማምንት ቢጠላ እንጂ ሃገሩን አይጠላም፡፡ ሃገር እኮ ለመጥፎውም፣ ለጥሩውም ከቃላት በላይ የሆነ ትርጉም አላት፡፡ መንፈስ እና የሃገር ትዝታ ሁሌም እንደተቆራኙ ነው፡፡ ያቆራኛቸውን ጠንካራ ሰንሰለት ሃይል እንጂ ምንነቱን ማንም እንዲህ ነው ብሎ ሊገልጸው አይቻለውም፡፡ እንደማንኛውም ዜጋ ሃገሬን እወዳታለሁ፡፡ በሹማምንት ስለተማረርኩና ስልጣን፣ ገንዘብ እና ዝና ስለፈለግሁ ሀገሬን እጠላታለሁ ማለት አይደለም፡፡ ከሰዎች እየዘረፈ የሚኖር ዘራፊ እንኳን እናቱን ማሰብ ሲጀምር ልቡ መሸበር፣ ሆዱ መባባት ይጀምራል፡፡ የእናትን ፍቅር ከምንም ነገር ጋር አታነጻጽሪውም፡፡ ሀገሬ ደግሞ ለእኔ እናቴ ነች፡፡ ለዚህም ነው ደጋግሜ ከልቤ እወዳታለሁ የምልሽ.....

"ስለሆነም የወደፊት እጣ-ፋንታዋ ያሳስበኛል፡፡ የወላድ መሃን የሆነች ሃገር፡፡ ታሪኳን ብቻ በመጽናኛነት ይዛ የቀረች ሃገር፡፡ ያለፉ ታሪክ ብቻውን የህልውና ዋስትና አይሆንም፡፡ የሚጠብቀው ይፈልጋል፡፡ ይህ ትውልድ ደግሞ እንኳንስ ታሪኩን ሊጠብቅ እና ሊንከባከብ ቀርቶ ቅርስ እና ታሪኩን ዘርፎ በሽርፍራፊ ሳንቲም ለባእዳን በመሸጥ መበልጸግ የሚሻ ነው፡፡ ለቁስ ሮጦ፣ ቁስ እካብቶ ከቁስ ጋር የሚሞት....."

ጣልቃ ገባች፡፡

"በጅምላ ትውልዱን መውቀስማ አግባብ አይሆንም፡፡ ቅርስ ሰርቆ መበልጸግ የሚፈልግ ያለውን ያህል ቅርሱን ጠብቆ ሀገሩን የሚያስከብርም ትውልድ ሞልቷል፡፡"

"ለእኔ ሚዛን የሚደፋው ለግል ጥቅሙ የሚሮጠው ነው" ሲል ኮስተር ብሎ ከተናገረ በኋላ "ምን ነካሽ ሶስና፤ ለመበልጸግ ቅርስ መዝረፍ አይደለም ከሰይጣን ጋር አብሮ ከመስራት ወደኋላ የማይል ትውልድ እያየን እኮ ነው" ሲል አከለላት፡፡ አልገባትም፡፡ ግንባሯን ቁጥር እና ሽብሽብ አድርጋ አየችው፡፡

"አጭበርባሪውና አታላዩ የተበራከተውን ያህል ባእድ አምላኪውም ቁጥሩ የትየለሌ እየሆነ ነው፡፡ ስንቱ በአንድ ሌሊት የአስር እና ሃያ ሀንዳዎች ባለቤት የሆነው ሰርቶ መሰለሽ? የአባቱን እጅ ጨብጦ ነው፡፡" ይበልጥ ግራ አጋባት፡፡

"ምንድነው የምታወራው? የእባቱን እጅ ጨብጦስ ማለት ምን ማለት ነው?" ሌላ ቡና እየቀዳ ቀጠለላት፡፡

"እጅ መጨበጥ ማለት በድግምት ከሰይጣን ጋር መገናኘት ማለት ነው፡፡ በሰይጣን አምልኮ ሃብትና ንብረት ለመሰብሰብ የሚሯሯጠው ህዝብ ቁጥር እየጨመረ በአቋራጭ መንገድ ሲንጠራወዝ ሃገር አደጋ ላይ ትወድቃለች፡፡ የሚማር እና የሚሰራ በላቡ ወዝ የሚኖር ዜጋ ይጠፋል፡፡ ሃገር አብራ ትጠፋለች፡፡ የሚያበሳጭሽ ባእድ አምልኮውን የሚከተሉት ተራ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ ታዋቂ አርቲስቶች፣ አትሌቶች፣ ባለስልጣናት፣ የንግድ ሰዎች፣ ጋዜጠኞች ወዘተ ጭምር መሆናቸው ነው፡፡ ሃገርን ከእንደዚህ አይነት ሃጢያት ሳያጸዱ ከምስጢር ማህበራት ሴራ ለመታደግ መሞከር ታጥቦ ጭቃ መሆን ነው" በእጅጉ እየተደነቀች ነው፡፡ ለማመንም አስቸግሯታል፡፡ ለማመን መቸገሯን ነገረችው፡፡

"ያለሽው ርቀሽ ስለሆነ ያላየሽውን ለመቀበል ብትጠራጠሪ አይፈረድብሽም፡፡ የማውቀውን ነው እየነገርኩሽ ያለሁት፡፡ ከመምህርነቱ በፊት ለስድስት አመታት ያህል ጋዜጠኛ ሆኜ

ሰርቻለሁ፡፡ የጋዜጠኝነት ህይወቴ ብዙ ነገሮችን እንድታዘብ ምክንያት ሆኖኛል፡፡ ሶሲ አብዛኛው ሰው በአንደበቱ ያጥላላል እንጂ ሰይጣን አምላኪ ሆኗል፡፡ በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ በቅጽር ግቢው በሰራው የአምልኮ ጎጆ ውስጥ አናቱ ላይ ቅቤ አስቀምጦ ሰይጣንን ሊለማምን የሚውለውን ሃብታም ቤቱ ይቁጠረው፡፡ ዘመናዊ መኪናውን በሰዋራ ገጠራማ ቀበሌዎች አቁሞ በጠንቋዮች ጎጆ የሚሰነብተው ቱጃር ቁጥርስ መች የዋሃ ሆነና? ይሄ ለምስጢር ማህበር አባላት፣ በሰይጣን ለሚያምኑት ሃያላን ሲሳይ ነው፡፡ የመቆጣጠሪያ አቋራጭ መንገድ፡፡"

ሁለት እውነቶች ትገዘ አሉትና ፈገግ አለ፡፡ "ጥርጣሬሽን ብችል ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ካልሆነም በግማሽ ያህል ለመቀነስ የተመለከትኳቸውን ሁለት እውነቶች ልንገርሽ፡፡ ከካዛንቺሱ ገጠመኜ ልጀምርልሽ....

"ከአንድ የቅርብ ጓደኛዬ ጋር በሳምንት አንድ ቀን የምናዘወትረው ቤት አለ፡፡ አልኮል መጠጦች መሸጫ ነው፡፡ ካዛንቺስ ውስጥ አለ የተባለ ቤት በመሆኑ የማይመጣ የሃብታም አይነት የለም፡፡ የእኔንና የጓደኛዬን ብቻ ሳይሆን የቤቱን ጠጪ ሁሉ ትኩረት የሳበ አንድ ጠጪ ነበር፡፡ እድሜው ሃያዎቹ መጨረሻ ላይ እንደሆነ ያስታውቃል፡፡ አቤት የሚቀያይራቸው መኪኖች! አቤት የሚለብሳቸው ዘመናዊ እና ውድ ልብሶች! ቢሞት ከሰው አይቀላቀልም፡፡ ይመጣል፡፡ መኪናውን በር ላይ ያቆማል፡፡ ባንኮኒው ጋር ይቀመጥና ውስኪ አዞ ከመጠጥ ቤቱ ባለቤት ጋር ቆይቶ ይሄዳል፡፡ ባለቤቷ ቆንጆ ወጣት ስለነበረች ጠጪው ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል ገምቷል፡፡ እሷም ብትሆን ዘና ብላ የምትጫወተው ከሃብታሙ ወጣት ጋር ነው፡፡ የዘወትር ምርጫው ብላክ ሌብል ነው፡፡ ይመጣል፡፡ ጠርሙስ ያወርዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ጠርሙሱን ሲጥ ነበር የሚያደርጉት.....

"ወጣቱ ሃብታም የቤቱን ጠጪዎች ትኩረት ቢስብም፣ ምን እንደሚሰራና ከየት እንደሚመጣ የሚያውቅ አልነበረም፡፡ አንድ ቀን ባለቤቷን ጨምሮ በወቅቱ የነበርነውን ሁሉ ከፋኝ ያስደነገጠ

ከስተት ተፈጠረ። ከወትሮው ዘግይቶ ነበር የደረሰው። ፊቱ ላይ መረጋጋት አይነበብም። ከመቀመጡ የተለመደውን መጠጥ አዘዘ። በገምታ እንደተሸበበ ነበር። ባለቤቷ በሁኔታው ግራ ሳትጋባ እንዳልቀረች ያስታውታል። ልታወራው እና ልታጫውተው ብትሞክርም ፍንክች አልልም አለ። በገምታ ውስኪውን ይመጣል። ሰአቱ እየገፋ ሄደ። ዲጄው ሰራውን አጠናቆ ስለሄደ ቤቱ ረጭ አለ። በጣት የምንቆጠር ጠጪዎች ቀረን። ጓደኛሞች በግል ከሚነጋገሩት ድምጽ ውጪ የሚሰማ ድምጽ የለም.....

"በመሃል ሁላችንንም ያስደነገጠ ንግግር መናገር ጀመረ።

"አሁንስ አበባው። በዚህ ሰአት የህጻን ልጅ ደም ከየት አባቴ ነው የማመጣለት!? ህጻን አርደህ ደም አምጣ ይለኛል ንዴ? ከየት አባቴ ነው የማመጣለት?› እንደ እብድ አደረገው። ኪሱ የነበረውን ብር አውጥቶ ባንኪው ላይ ከበተነ በኋላ እየሮጠ ወጣ። መኪናውን አስነስቶ ሲከንፍ ይሰማናል። ከዚያን ቀን በኋላ በአካባቢው ታይቶም አያውቅ። ባለቤቷን በደንበኝነት ብቻ እንደምታውቀው ምላ ተገዝታ ነገረችን። ይሄ የመጀመሪያው ገጠመኟ ነው። ወደ ሁለተኛው ልሸጋገር" አለና ሌላ ስኒ ቡና ቀዳ። ለቡና ያለውን ፍቅር አረጋገጠች።

"ይህኛውን የተዋወቅሁት በወንድሙ አማካይነት ነው። የጓደኛዬን ሱቅ ተከራይቶ ይነግድ ስለነበር እንተራረብ ነበር" ሲል ጀመረላት። የምትሰማቸው ነገሮች ስለመሰሏት በጽሞና ማድመጥን መርጣለች።

"ሱቁን ተከራይቶ ይነግድ የነበረው ልጅ እንዲያግዘኝ በማለት ታናሽ ወንድሙን ከገጠር አምጥቶት አብረው መስራት ጀመሩ። አመት እንኳን አልሰሩም። ታናሽ ወንድም ብቻዬን መስራት እፈልጋለሁ በሚል ሰበብ ከወንድምየው ተለየ። ገበያው ቀዝቅዞበት እና ገንዘቡ ከስሮበት የነበረው ታላቅ ወንድም ነገር ሆድ ሆዱን እየበላው ገንዘብ ከየት አምጥቶ ነው ብቻውን የሚሰራው ብሎ ሲያስብ ቅርብ የሆኑ ሰዎች "ብቻውን መስራት ነው የሚገርምህ? ዓለም ባንክ በሚባለው ሰፊር እንዴት አይነት ቤት ሰርቷል።

የገማድ እና የቤት መኪና ገዝቷል› ሲሉ ነገሩት፡፡ ብር ዘርፎት እገደሃደ እርግጠኛ ሆነ፡፡ የዘረፈውን ገንዘብ ይመልስለት ዘንድ ሸማሌ እንሆነው ዘንድ እኔን እና ሱቅ ያከራየውን ጓደኛዬን ጠየቀን፡፡ ‹እርግጠኛ ሳትሆን? ገንዘብ ከሌላ ቦታ አግኝቶ ሊሆን ይችላል› ብንለውም ሊያደምጠን ፈቃደኛ አልሆነም፡፡

"‹ሌላ ከየትም አያመጣም፡፡ የእኔኑ ገንዘብ ዘርፎ ነው፡፡ እኔ እንደ ካሮት ቁልቁል ሰበቅል እሱ እንደ ሮኬት ወደ ላይ ይወነጨፋል፡፡ ግዴላችሁም በሽምግልና ጠይቁልኝ?› ሲል ሙጭጭ አለ፡፡ ዘርፈሃል ልንለው ሳይሆን ያለውን ሁኔታ ለመጠየቅ ቸስማማን፡፡ ሃብታም ሆኗል፣ ቤት ሰርቷል ሲሉ የነገሩት ቤቱን በእርቀት አሳዩትና በቀጠሮ ይዞን ሄደ.....

"በር የከፈተችልን ታናሽ እህታቸው ነበረች፡፡ ወንድሟን በድንገት ስታገኝ በደስታ የምትሆነው ጠፋት፡፡ ሰፊ የሚያምር ግቢ ነው፡፡ ቪላ ቤት ሰፍሮበታል፡፡ ከዋናው ቤት በስተግራ የሳር ጎጆ ይታያል፡፡ ከተማ ውስጥ የሳር ጎጆ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፡፡ ሳሎን ገብተን ተቀመጥን፡፡ ብንጠብቅ አይመጣም.....

"‹ጥሪው?› አላት ወንድምየው ክስተር ብሎ፡፡ ጎጆ ቤቱ ደርሳ ከመጣች በኋላ በፊቷ ላይ የፍርሃት ምልክት ይታያል፡፡ ዝም ብላ ቆመች.....

"‹ጥሪው እንጂ?› አላት በድጋሚ፡፡

"‹ረስቼው ነው፤ ዛሬ ማንንም አያናግርም› አለች መሬት መሬት እያየች እና ጣቶቿን እርስ በእርስ እያፋተገች፡፡ ሰኞ ቀን ነበር፡፡ ተበሳጨ.....

"‹ማን ሆኖ ነው በዛሬው አለት ሰው የማያናግረው? ቢሮክራት ባለስልጣን ወይስ....? ወሬ ሳታበዛና በይው፡፡›

‹‹በምንኮት ልትፈነዳ የደረሰችው ልጅ፣ ‹ጋሼ ለብቻዬ ታናግረኝ?› አለችና ወንድሟን ወደጓሮ ይዛው ሄደች፡፡ ቆይተው ሊመለሱ ፊት ተለዋውጠ ነበር.....

"‹እንሂድ!?› አለን እንዳቀረቀረ፡፡

"‹የለም፣ ወይስ ሊያናግርህ ፈቃደኛ አይደለም?› ሱቅ አከራይ ጓደኛዬ ነበር የጠየቀው.....

"‹ነገሩ ወዲህ ነው እንሂድ.....እንሂድ› አለን እየተወራጨ፣ ተያይዘን ወጣን። ምስጢሩን የሰማሁት ቆይቼ ነበር። ሱቁን ያከራየው ልጅ ወንድም የሃበት ምንጭ ባእድ አምልኮ እንደሆነ፣ ሰኞ ሰኞ የተመለከትነው ጎጆ ውስጥ ቅቤ ተቀብቶ ዘግቶ ጫት እየቃመ እንደሚውል፣ ስራ እንደማይሰራና ከማንም ጋር እንደማይነጋገር እንደደረሰበት ወንድምየው እንዳጫወተው ጓደኛዬ አጫወተኝ። በባእድ አምልኮ የሚያምን ትውልድ እየተበራከተነው ያልኩሽ ለዚህ ነው። አካሄዱ እጅግ አደገኛ ነው።"

ከብደቱ ታይቷታል።

"ትውልዱ እንዲህ ከተበላሸ እንዴት አድርገን ነው ይህችን ሀገር የምንቀይራት?" ስትል ጠየቀችው።

"ይቻላል!" አላትበእርግጠኝነት። "ይቻላል። ዋናው ቁርጠኝነት ነው። ጥቂት የራእይ ሰዎችን ማፍራት ቢቻል እና እነሱ ትውልዱን ለመቀየር ቆርጠው ቢነሱ የምናስባትን አይነት ኢትዮጵያ መፍጠር እንችላለን። ቁምነገሩ ከቁጥሩ ላይ ሳይሆን ከጥራቱ ላይ ነው። እስከማውቀው በአለም ታሪክ የአይሁዶችን ያህል ስቃይና መከራ የተቀበለ ህዝብ የለም። ስቃይ መከራ ሳይበግራቸው ፈተናውን በማለፍ በትንሽ የህዝብ ቁጥር አለምን መቆጣጠር የቻሉ ህዝቦች ሆነዋል። ግብስብሱንና ራስ-ወዳዱን ትተን ጥቂት የራእይ ሰዎችን ማፍራት ብንችል በእራሷ ሃብት መጠቀም የምትችል የትላንቷን ታላቅ ገር መፍጠር እንችላለን። እንደ ቅርጫ ስጋ በብሄርና በሃይማኖት ያልተከፋፈለች አንድ ኢትዮጵያን። ያለበለዚያ የደም መጣጭ ሸመኛች መጫወቻ ሆነን መቅረታችን ነው። የባለስልጣናት መጫወቻ የሆነ ህዝብ ደግሞ ከኑሮው ጋር ድብብቆሽ ለመጫወት የሚገደድ በስጋት የተከበበ እድለ-ቢስ ዜጋ ይሆናል" አለና ጋሽ መደሲር ትዝ አሉት። ታሪካቸውን አጫወታት።

"ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት ሀገር ሆናለች። የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ዜጎቿ ወደማይጨካከኑባት አዲስ ኢትዮጵያ ለመቀየር ትግል ይጠይቃል።"

ጋሽ ሙደሲርን በምናዊ ሳለቻቸው፡፡ ሌሊት ሰው አየኝ አላየኝ ብለው ከመንደራቸው ጠፍተው ሌሊት የሚመለሱ አሞር፣ ጠቆር ያሉ በሞንተት እና በችግር የፊት ቆዳቸው የተጨማደደ አዛውንት ታዩዋት፡፡ በእሳቸው ውስጥ በሙስና፣ በስልጣን መባለግ፣ በጉሮ ውድነት ተማረው የተንሳቀሉ በርካታ ኢትዮጵያውያንም ታይተዋታል፡፡ ትግሉ ከምስጢር ማህበራት ሴራ ጋር ብቻ ሳይሆን ከተንሰራፋው ሙስና፣ አድሎአዊ አሰራር እና አምባገንንነት እንዲሁም ድህነት ጋር መሆን እንዳለበት ገባት፡፡

ወደዋነኛዋ ርእሳቸው ሂዮንሴ ኖውልስ አመሩ፡፡ አሁንም ተናጋሪው ረድኤት ነበር፡፡ ዝርዝር እውነት ነገራት፡፡ በነገራት መሰረት የሂዮንሴ ኖውልስ የኢትዮጵያ ጉብኝት እውን ሆኗል፡፡ የሙዚቃ ኮንሰርቷን አቅርባለች፡፡ ርዳታ ድርጅት ጎብኝታለች፡፡ በቅድስት ሰላሴ ቤተክርስትያን ቅጽር ግቢ ተገኝታ ከጳጳሱ ጋር ጥላ ተይዞላት ወረብ እና ሽብሸባ ተመልክታለች፡፡ ዘፈን በተወገዘበት ቤተክርስትያን ውስጥ ሰለሰይጣን የምታቀነቅን ዘፋኝ በተካበደ ሁኔታ አቀባበል ተደርጎላት ያሳለፈችው ጊዜ በእጅጉ ያበሳጫት ሶስና ስህተት ላይ ላለመውደቅ በሚል ምክንያት መረጃው እንደደረሳት መውሰድ ያለባትን እርምጃ ባለመውሰዷ፣ ሂዮንሴን በድራገጽ ጽሁፍና ቪዲዮ አማካይነት ባለማጋለጧ የጥፋተኝነት ስሜት ተሰማት፡፡ ኢትዮጵያ ሁለተኛ ቤቴ ስለሆነች ዳግመኛ እመጣለሁ ማለቷንም ረድኤት ነግሯታል፡፡ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን (ቪዲዮ ጨምሮ) ከሃገር ቤት ያስላከው ረድኤት ማስረጃዎቹን እያሳያት

"አላልኩሽም!? ሴትየዋ የመጀመሪያ ተልእኮዋን በድል አድራጊነት ተወጥታለች፡፡ ለቀጣዩ ተልእኮዋም ከወዲሁ እመለሳለሁ በማለት ቃል ገብታለች፡፡ የተታውሞ ዘመቻችንን መጀመር የሚኖርብን ከወዲሁ ነው፡፡ ሃገር ቤት ያለው ህዝብ የሚያውቀው ዘፋኝነቷን ብቻ ስለሆነ ይሆናል ልቡን ከፍቶ ባህሪው በሆነው የእንግዳ አቀባበል ስርአት የተቀበላት፡፡ ከነሮበርት አዳምስ ጋር የወጠነችውን የጋራ ሴራ በትርብ ስለማውቅ የተታውሞ ዘመቻችንን

ውለን ሳናድር መጀመር ይኖርብናል። ዳግም ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ ሰይጣናዊ አምልኮቷን ማስፋፋት አይኖርባትም።"

ካሳያት መረጃዎች መሃል ለኢትዮጵያውያን ሀጻናትን ምልክት የምታሣይበት እና እነሱም ምልክቱን እንዲያሳዩ የምታበረታታበት ቪዲዮ እንዲሁም የእሷን የቤተክርስትያን ቆይታ እና የኢትዮጵያ ጉብኝት አስመልክቶ በአማርኛ የተጻፈው መጽሃፍ ቁልፏን ገዝተውታል። ሁለተኛ ቤቱ ናት ስትል ምን ማለት ፈልጋ ነው? አቅዶቹን እና ተልእኮዎቹን ተግባራዊ የማደርግባት ወይስ? ሀጻናትን ሰብስቦ ሰይጣናዊ ምልክቶችን ማለማመድስ ምን ይባላል? ሀጻናቱ ከጨዋታነት በዘለለ ስለምልክቶቹ ምስጢራዊነትና ትርጉም የሚያውቁት ነገር አይኖርም። አብዛኛው ህዝብ ስለምልክቶቹ ምስጢራዊነት እና ትርጉም የሚያውቀው ነገር የለም። በቅርቡ ያነበቦቸውን "ማጂክ ኢን ቲዮሪ ኤንድ ፕራክቲስ" እና "ኮዴክስ ማጂካ" መጽሃፍት አስታወሰቻቸው። የኢትዮጵያ ህዝብ እንዚያ ሀጻናትን ጨምሮ እነዚህን መጽሃፎች ያነቧቸው ዘንድ ተመኘች። እንብበዋቸው ቢሆን ኖሮ እንኳን በዚያ አይነት አቀባበል ሊቀበሏት ተከትለዋት ምልክቶቹን መልሰው ሊያሳዩ በመቋሚያ ፈንካኩተውና በድንጋይ ወግረው ሊያባርሯት ይችሉ እንደነበር ገመቶች። መጽሃፉቱ የምልክቶቹን ምስጢራዊነት ስለሚያብራሩ፣ ትርጉም ተንትነው ስለሚናገሩ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ቢነበቡ ኖሮ ሂዮንሴ ናውልስ ምሀረት አታገኝም ነበር። ምልክት ከማሳየት እና ከማለማመድ ዳንስ እና እስክስታ ለምን አላስተማሯቸውም? ስትብሰለሰል ቆየችና

"ይህን ነገር ማስቆም አለብን" አለችው።

"በሃላብሽ እስማማለሁ። ተመልሳ የቅድስት ሃገሬን ቅዱስ ስፍራ ማርከስ የለባትም። ጥሎብን በተግባሩ ከሚጸድቅ ድሃ በተግባሩ ለሪክስ እና ለተከነን ሃብታም እና ገነኛ ማሸርገድ እንመርጣለን። ለዚህም ነው እየተቀበልን የምንስተናግዳቸው። ያውም ከሰገራና ከሽንት ለማያልፍ ሆድ። ነትቦ መበጫጨቅ ለማይተር ሰልባጅ። ሀሊናን ማቁሰሉ ለማይተር ሽራፊ ሳንቲም።

ከጊዜያዊ ጥቅሞች ይልቅ ሀገር እንደምትበልጥ በውስጣችን ለበቀሉ ጅቦቻችን እና አሳሞቻችን ማን በነገራቸው? ምንም ይሁን ምን የዚህችን ሰይጣን ተልእኮ እና የሃገር ውስጥ ተባባሪዎቿን ድጋፍ ማውገዝ፣ ተቃውሞ እንዲገጥመው የማድረግ ሃገራዊ ሀላፊነት አለብን፡፡ አትጠራጠሪ፤ ሀገራዊ ሃላፊነታችንን በሚገባ እንወጣለን፡፡"

"አዎ፤ የግድ መወጣት አለብን፡፡ ሴራው ለተራው ህዝብ ገና የተገለጠለት አልመሰለኝም፡፡ አጠገባቸው ነንና፣ እየተደረገ ያለውን በቅርብ እናውቃለንና የህዝቡን አይን መክፈት አለብን፡፡ በተለያዩ ሰበቦች እና ምክንያቶች ሀገር ውስጥ ሰርገው ለመግባት፣ የአዲስ ዓለም ስርአቱን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ሰይጣናዊ አምልኮታቸውን ለማስፋፋት እየጣሩ ነው፡፡ ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት ህዝቡን ማንቃት ይኖርብናል፡፡"

መስማማቱን በድጋሚ አረጋገጠላት፡፡ ከሃገር ቤት ያስመጣው መጽሃፍ ከሁሉም መረጃዎች በይበልጥ ስሜቷን ገዝቶታል እና እንደገና ወደዚያው ተመለሰች፡፡ በዋዛ እንደማትላቀቅ የገባው ረድኤት

"ሶስና መጽሃፉ ላይ ትደርሺበታለሽ፡፡ እኔ መሄድ ስለሚኖርብኝ አሰናብቺኝ" አላት እየተነሳ፡፡ ጊዜው ገፍቷል፡፡ ብዙ ቆይተዋል፡፡ አልታወቃትም፡፡

"ይቅርታ መረጃዎቹ ስሜቱን ሳቡት እና.....ይህን መጽሃፍ ግን አሁን አልሰጥህም፡፡"

"ለአንቺ ነው ያመጣሁት፡፡"

"አመሰግናለሁ" ሸኝታው ተመለሰች፡፡ ከሶስት ቀናት በኋላ ወደመጣበት ይመለሳል፡፡

- 29 -

ፓልማ፣ ማሎርካ

ያን እለት ቡና ለመጠጣት በሚያዘወትራት ካፌ ውስጥ አብሮት የተገኘው የቅርብ ጓደኛው ዳንኤል ኢስቱሊንን እንዲህ አለው፡፡ "አሜሪካ ውስጥ የሚኖር ሳይንቲስት ወዳጄ ሊተዋወቅህ ይፈልጋል፡፡ አሪዞና በሚገኝ ሆስፒታል ውስጥ ህክምናውን በመከታተል ላይ ይገኛል፡፡ ሰዎቹ ከዚያ ከተማ እንዳይወጣ የቁም እስረኛ አድርገው እየተከታተሉት ነው፡፡ ትንሽ ሻል ሲለው ወደ ቤቱ ይሄዳል፡፡ በሽታው ሲነሳበት እና ሲብስበት ደግሞ ወደ ሆስፒታሉ ይመለሳል፡፡ ከዚያ ሆስፒታል ውጪ ህክምናውን ሌላ ሆስፒታል እንዳይከታተል በአሪዞና ግዛት ውስጥ ላሉ ሆስፒታሎች ጥብቅ ትእዛዝ ስለተሰጠ ህክምናውን የሚከታተለው በነገርኩህ ሆስፒታል ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ረጅም እድሜውን ከሲ.አይ.ኤ ጋር አሳልፏል፡፡ የጄሰን ምስጢራዊ የሳይንቲስቶች ቡድን አባልነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፡፡ እንደበርካታ አሜሪካውያን ለሃገሩ ፍቅር ስላለው በእውቀቱ ሃገሩን ለማገልገል በመፈለጉ ነበር የስለላ ድርጅቱን የተቀላቀለው፡፡ ውሎ ሲያድር ግን የሚመለከተው ነገር ሬት ሬት አለው፡፡ የድርጅቱ ፕሮጀክት ከእሱ ሃሳብና ፍላጎት ጋር ተቃራኒ ሆነ፡፡ የሰውን ዘር እደጋ ላይ በሚጥል ተግባር ላይማ አልሳተፍም፣ አብሬያችሁ አልሰራም ሲል ወንዝ የማያሻግር አመጽ ማመጽ ጀመረ፡፡ <ተው> አሉት ሲያስጠነቅቁት፡፡ አልሰማቸውም፡፡ ‘ሽማግሌ ባይልኩም እብሪትህ የትም አያደርስህምና ዳግም አስብበት ሲሉ ማሳሰቢያ መሳይ ማስጠንቀቂያ አደረሱት፡፡ አሻፈረኝ አለ፡፡ የተከሰተው ነገር ዘግናኝ ነበር፡፡ ቀሪውን ታሪክ ለምን ከእራሱ አንደበት አትሰማም?"

ኢስቱሊን ፊታደኛ ሆኖ አድራሻውን ተቀበለ፡፡ ከሳምንት በኋላ ወደ አሪዞና ሲጓዝ ረዳቱን ሶስና አለማየሁን አስከትሎ ነበር፡፡

****

ዳንኤል ኢስቱሊን፣ ሶስና አለማየሁ እና ሳይንቲስቱ በሳይንቲስቱ መኖሪያ ቤት ተገናኙ።

"ሻል ስላለኝ ነው በመኖሪያ ቤቴ የቀጠርኳችሁ" አላቸው ወደ ላሎን እየጋበዛቸው። ሶስና በግቢው ውስጥ ኳስ የሚጫወቱ ሁለት ታዳጊዎችን ስትመለከት ልጇ ትዝ አላት። የሳይንቲስቱ ንግግር ሃሳብ ውስጥ እንድትቆይ እድል አልሰጣትም።

"ከርስቶፈር ስቲቨንስ እባላለሁ" ሲል ንግግር ጀመረ።

"ኢስቱሊን ደፋርና እውነትን ለዓለም ህዝብ ከማድረስ ወደኋላ የማትል ጸሃፊ መሆንህን ስለማውቅ ነው የተመለከትኩትን የሲ.አይ.ኤ ሴራ የምነግርህ" ኢስቱሊን ለምስጋና ጭንቅላቱን ጎንበስ ካደረገ በኋላ ቀጥል አለው በምልክት። ቀጠለ፦

"በሲ.አይ.ኤ ውስጥ እየተፈጸመ እና ሊፈጸም እየታሰበ ያለውን ሴራ ቁንጮ ፖለቲከኞች እንኳን አያውቁትም። ፈጽሞ የማያስቡት ነው። ሴራውን ጠንቅቀው የሚያውቁት እና ያለተግባራዊነቱ የሚተጉት ከፖለቲካ ሹመኞቹ በላይ ሃይል እና ስልጣን ያላቸው ቢልደርበርግ-ኢሉሚናቲዎች ናቸው። ሲ.አይ.ኤን እንዳሻቸው የሚያሽከረክሩ የዘመናችን ጉልቤዎች።" የብሽቀት እና የምጸት ፈገግታ ከቸረው በኋላ ሽሚዙን ከፍቶ ደረቱን አሳየው። በደረቱ ላይ ያለችው አነስተኛ መጠን ያላት ቲዩብ መሳይ ነገር የኢስቱሊንንም፣ የሶስናንም ትኩረት ስባለች። በውስጧ ቢጫማ ፈሳሽ እንደያዘች ኢስቱሊንም፣ ሶስናም ልብ ብለዋል። ቀረብ ብለው ተመለከቷት። "መድሃኒት ነው" ሲል ቀጠለ ሳይንቲስቱ።

"የሰውን ዘር ለማጥፋት በወጠናችሁት ሴራ ላይ አልሳተፍም በማለቴ ሲ.አይ.ኤዎች የሸለሙኝ ነው። ራሴን ስቼ በነቃሁበት ሰአት ነው የተመለከትኩት። አመጽ የማያዋጣኝ ኖሮ እራሴን እንድስት ካደረጉ በኋላ ሸለሙኝ። በቲዩቡ ውስጥ ያለውን መድሃኒት ሰውነቴ እጅግ ስለለመደው ያለእሱ መኖር አልችልም። የግድ በየሰባ ሁለት ሰአቱ መወጋት አለበት። እሱን ካላገኘሁ

በእጅር ጥናት ውስጥ የስታይ ሞት እንደምሞት የሚያውቁት የሲ.አይ.ኤ ሰዎች የሆነ ነገር ሊያሰሩኝ ሲፈልጉ ‹እሀሳ?› ይሉኛል መድሃኒቱን ከማስፈራሪያነት በመዛወር፡፡ አሻፈረኝ ካልኩ መድሃኒቱ ይቆማል፡፡ በከፍተኛ ስታይ ወደሞት አመራለሁ፡፡ ምርጫው የእኔ ነው፡፡ እስከዛሬ ለአራሴም ለበላሰበኩ ምስል የታዘዝኩትን እሸ ስል ኖሬያለሁ፡፡ ተመሩን አሻሽዬ ሰርቼ ለማስረከብ በመስማማቴ ነው ይህን ያህልም ትንፋሽ ያገኘሁት፡፡ እንጂ ሟች ነበርኩ፡፡ በቅዠል፡፡ ተመሩን አልሰጣቸውም፡፡ ሃሳቤን ያወቁ እለት ያጠፉኛል፡፡ ያጥፉኝ እንጂ በሚሊዮን የሚቆጠር የአለም ህዝብ ከሚጠፋ እኔ ብጠፋ እመርጣለሁ፡፡ መጽናኛዬ ይፋ ያወጣሁልህ ምስጢር ነው፡፡ በመጽሃፍችህ አማካይነት ለህዝብ እንደምታደርሰው እምነቱ ነው፡፡ ሁሉ ነገር ስለሰለቸኝ እንደሚከታተሉኝ እያወቅሁ እንኳን ጥንቃቄዬን ችላ ብያለሁ፡፡ መስታወቱ ቲንት የተደረገ (ወደ ውስጥ በማያሳይ ጥቁር መሸፈኛ የተሸፈነ) መኪና በሸፌር የላኩላችሁ ማንነታችሁ እንዳይታወቅ ነው፡፡ በተለይ ኢስቱሊን፡፡ አንተነትህን ካወቁ መጠርጠራቸው አይቀርም፡፡ በተሸፈነ መኪና እንደመጣችሁ በተሸፈነ መኪና ትሸኛላችሁ፡፡ ዛሬውኑ፡፡ ውላችሁ አታድሩም፡፡ ካደራችሁ ነገር ሊመጣ ይችላል፡፡ መኪናው የቤተሰቦቼም መመላለሻ በመሆኑ ላይጠራጠሩ ይችላሉ፡፡

"ሁሉን ነገር ሲያውቁ እንደሚያጠፉኝ አርግጠኛ ነኝ፡፡ ለምን ያህል ጊዜ መኖር እንደሚፈቅዱልኝ አላውቅም፡፡ ከሰአታት በኋላ.....ነገ ወይም ከነገ-ወዲያ ሊያሰናብቱኝ ይችላሉ፡፡ በሞት ከመሰናበቴ በፊት በመላው የሰው ዘር ላይ የጠነሰሱትን ሴራ ልነግርህ ነው ያገኘሁህ፡፡ አትጠራጠር፣ ያደርጉታል፡፡ ተጨባጭ መረጃዎችን ላቅርብልህ፡፡ የወሳኙ ማንነትነት ምክርቤት፣ የቢልደርበርግ እንዲሁም የሮም ክበብ አባል የነበረውና በአሜሪካ የተለያዩ የስልጣን ቦታዎች ላይ የሰራው ሄንሪ ኪሲንጀር በአንድ ወቅት ባደረገው ንግግር እንዲህ ነበር ያለው፡፡ <ስለወሲብ፣ ስለወሊድ መከላከያ፣ ስለውርጃ በአጠቃላይ የህዝብን ቁጥር ስለሚቆጣጠርልን ወሳኝ አጀንዳ በግልጽ መነጋገር ይኖርብናል፡፡

የስነ-ምህዳር ቀውስ ሌላ ምንም ሳይሆን ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የሚከሰት ቀውስ ነው። ዘጠና ከመቶውን የአለም ህዝብ ካስወገድነው የስነ-ምህዳሩን ቀውስ መቆጣጠር እንችላለን።<> የእሱ ደቀመዝሙር የሆነው ሻኪውስ ኮስቲዩም በኖቬምበር ወር 1991 ዓ.ም ከዩኔስኮ ኮሪየር ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ የተናገረውን ልመርቅልህ፣ <አስደንጋጭ አባባል እንደሆነ አልጠፋኝም። የአለምን ህዝብ ለማረጋጋት በየቀኑ ሰላት መቶ ሃምሳ ሺህ ያህል ህዝብ ማስወገድ ይኖርብናል። አሰቃቂ ንግግር ቢሆንም ያለመናገሩ በራሱ መጥፎ ነው> ነበር ያለው። እነዚህ ታዲያ ምንስ ነገር ከማድረግ ይመለሳሉ ብለን እንዴት ነው የምናምነው?.....

"የምንግርህን ለዓለም ህዝብ እንደምታደርስ እርግጠኛ ነኝ። ባንተ ላይ እምነት አለኝ። እንደ እኔ ልዩ ችሎታ ያላቸው በርካታ ሳይንቲስቶች የዓለምን ህዝብ ከሲ.አይ.ኤና ከመሰሎቹ ሴራ ለማዳን፣ ከአንድ ዓለም አስተዳደር ባርነት ነጻ ለማውጣት በመፈለጋቸው፣ ዓለምን ከርሃብ እና ከችግር እንዲሁም ከድህነት ለመታደግ ፍላጎት በማሳየታቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው ያሉት።"

ይህን ብቻ አይደለም የነገረው። በርካታ የሰው አራዊቶችን ድብቅ አለም ገበና ይፋ አድርጎለታል። ቀጣዩ ገጠመኝ ከኢስቱሊን ይልቅ ሶስናን በድን አድርጎ ያስቀረ ነበር።

"ከዚህ ቀጥሎ የምንግርህ ታሪክ የሰማሁትን ሳይሆን በስፍራው ተገኝቼ በአይኔ የተመለከትኩትን፣ በተግባር ያረጋገጥኩትን ነው። በአዜ ኃይለ-ስላሴ ዘመን በኢትዮጵያ ተከስቶ የነበረውን ርሃብ እና ድርቅ ሁለታችሁም በንባብ ታስታውሱታላችሁ ብዬ አምናለሁ። በተለይ ሶስና ኢትዮጵያዊ በመሆንሽ እንደምታስታውሽው ተስፋ አደርጋለሁ። በዚህ ወቅት ወደ ሃገራቸው ካመራው የሳይንቲስቶች ቡድን እና የሲ.አይ.ኤ አባላት ጋር ነበርኩ። ቡድኑ በድርቅ የተጎዳ መሬትን ለማለምለም እና ሰብልን ማብቀል የሚያስችል ቴክኖሎጂን ይዞ ነበር ምድራቸን የረገጠው። የሲ.አይ.ኤ ሰዎች ለዚህ በጎ አላማ አልተጠቀመባትም። እቅዱ በማግኔታዊ ሃይል እህል ማብቀል የሚያስችለውን ንጥረ-ነገር አውሮፕላን ላይ ሆኖ ወደ ምድር

መርጨት ነው፡፡ አፈሩን ወደለምነት ቀይረው እህል እንዲያበቅል ከማድረግ ይልቅ ቴክኖሎጂውን በሰው ልጆች ላይ ለመሞከር በመፈለጋቸው የበርካታ ንጹሃን ዜጎች ህይወት ተቀጠፈ፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለህልፈት ተዳረጉ፡፡ ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ በማምራት ላይ በነበረችው አውሮፕላን ውስጥ ስለነበርኩ እየሆነ ያለውን ነገር ለመመልከት ወደፊት ለፊት ተጠጋሁ፡፡ የተመለከትኩት መሬትን ለም እድርጎ እህል የሚያበቅል ቴክኖሎጂ ሳይሆን የሺዎችን ህይወት የበላ ቴክኖሎጂ ነው፡፡"

"የድርጊቱ ተዋናዮች?" አለች ሶስና ደምስሮጅ ተገታትረው፡፡

"ከሲአይኤ ጀርባ ሆነው ድርጅቱን የሚያሽከረክሩት ቢልደርበርግ-ኢሉሚናቲዎች፡፡" ክርስቶፈር መልስ ሰጠ፡፡ ቢልደርበርግ-ኢሉሚናቲዎች ለአንድ ዓለም አስተዳደር እውን መሆን የሚተጉ ዘመናዊ የምስጢር ማህበር አባላት እንደሆኑ ኢስቱሊን ነግሯታል፡፡ አንብባለችም፡፡ ቀና ብላ ኢስቱሊንን ተመለከተችው፡፡ አይን ለአይን ተጋጩ፡፡

ሳይንቲስቱን ተሰናብተው የተመለሱት ዳንኤልና ሶስና ፓልማ ማሎርካ እስኪደርሱ ብዙም አልተነጋገሩም፡፡ በድብርት ስሜት ውስጥ ሆነው ከእራሳቸው ጋር እየተወያዩ ነበር፡፡ የድብርታቸው ምንስኤ ሳይንቲስቱ የነገራቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸመው ዘግናኝ ሴራ እንደሆነ አልጠፉቸውም፡፡

- 30 -

ፓልማ፣ ማሎርካ

በሂዮንሴ ኖውልስ የኢትዮጵያ ጉብኝት ላይ በሚያተኩረው መጽሃፍ በእጅጉ የተመሰጠችው ሶስና አለማየሁ፣ ዛሬም በድጋሚ በተመስጦ እያነበበችው ነው። ከምትፈልጋቸውና ለማወቅ ከምትሻቸው የኖውልስ እውነቶች መሃል አብዛኛዎቹ በመጽሃፉ ውስጥ ሰፍረዋል። እነከሬዚላቭን፣ ዘ ላስት ግሬት ሴዴክሽንስን፣ ሃሎን ከእርቃን ባልተናነሰ ሰውነት ሰይጣናዊ ምልክቶች በሚታይባቸው መድረኮች ላይ ያቀነቀኑች አርቲስት በቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ዜማዎች መሃል ተቀምጣ የሃገራችንን መንፈሳዊ ስርአት የመመልከት ሞራላዊ ብቃት ሊኖራት ይችላልን?" የሚለው አረፍተነገር ስሜቷን ወጥሮ ይዞታል። "በፍጹም አይኖራትም። ሊኖራትም አይችልም" ስትል በስሜት ተናገረች። ለብቻዋ ነበር ያወራችው።

በ2010 ዘፈኗ <ስዊት ድሪምስ> ላይ የተካተቱትን የግጥም ስንኞች አስታወሰቻቸው። ስለ ሂዮንሴ ኖውልስ ታሪክና ስራዎች የሚናገሩ መረጃዎችን መቆፈር እንዲሁም የቪዲዮ ስራዎቿን በተመስጦ መከታተል ከጀመረች ሰነባብታለች። የእለት ከእለት ጉዳይዋ ሆናለች። ስንኞቹን ዳግም አስታወሰቻቸው።

I am worthy.....Hail Satan.....I follow Lucifer.
I'm Stuck in the fast living.....
I'm Sorry for the end of your Sins.

ለሲፈርን እከተላለሁ ብላ የዘፈነች ድምጻዊት በየመድረኩ ላይ የምታሳየው ምልክት ጥቂት የሰይጣን ተገዢ ነኝ፣ ለሰይጣን እገዛለሁ ማለት እንደሆነ ያነበበቻቸው መጻህፍት ነግረዋታል። ሰይጣንን

የምትከተል፣ ለሰይጣን የምትገዛ የዚሳዊው አለም <ንግስት> ለሁለተኛ ጊዜ ሃገሯ ተመልሳ የምትሄድበት ምክንያት አልታያትም። እጅጉን ወደእግዚአብሄር እንደምትዘረጋ በተመሰከረላት ሃገር የተለየ ሰይጣናዊ አጀንዳ ከሌላት በስተቀር መመላለሱን ለምንፈለግችው?

ዘፈኖጅን የትኛውም መድረክ ላይ የማቅረብ መብት አላት ስትል አሰበች። ነገር ግን ሰይጣናዊ ምልክቶችን በሀጻናት ዘንድ ማስተዋወቁን ምን አመጣው?

ወደንባቢ ተመለሰች። ስሜቷን ወጥሮ የያዘ ሌላ አረፍተነገር አጋጠማት።

"የሰጋ ሰራዎች የተገለጡ ናቸው ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ገላቲ ያመልእክቱ ላይ ከዘረዘራቸው ውስጥ አንዱ ዘፋኝነት ነው። ዘፋኝ መንግስተ-ሰማያትን አይወርስም መልእክት ያላቸው ትእዛዛት አሉ። ሰው የተፈጠረው እግዚአብሄርን ለማመስገን ነው። ከዚያ ውጪ እንደዘፋኝነት ባለመንገድ መሰማራት ከሃጢያት የሚመደብ ነው። በእኛ ቤተክርስትያን ይሄ አቋም እያለ ዘፋኞችን የምንቀበልበትና የምናስተናግድበት መንገድ የተሳሳተ ሆኖ እናያለን።"

በተወጠረ ስሜቷ የሚከተለውንም አረፍተነገር አነበበች።-

"ወደ ሃገሯ ከተመለሰች በኋላ የምናያቸው መረጃዎች እያንዳንዱ እንቅስቃሴዋ ተልእኮ እንዳለው የሚያመላክቱና የሚጠቁሙ ናቸው። ባታስበው እንኳን ሰይጣን የሚያስበው ነገር ሊኖር ይችላል። የእምነት ቦታዎች ፈተና ይበዛባቸዋል። ኢትዮጵያ የፊላሪ ሀገር እንደሆነች አለምም የመሰከረው እውነት ነው። ከዚህ አንጻር ሰይጣን የሚያስበው ነገር ሊኖር ይችላል። ከእኛ ጋር ተያይዛ መነሳቷ "ታላ" መደረጓ ጥሩ አይደለም። .....ቅድም ሀጻናትን ሰብስባ ምልክቶችን ስለማስተዋወቋ አውርተናል። ያአራሱ ጥርጣሬ ላይ የሚጥለን ምልክት ነው። ከዚያ ውጪ የሰይጣኒዝምን እምነት የሚያራምዱ ወገኖችን ከዚያ በፊት አግኝታቸው ከሆነ የእሷ እዚህ መምጣት ምንም ሳይታሰብ

የተደረገ ነው ለማለት ይቸግራል። እና ለእንዲህ አይነት ሴት በመንፈሳዊ ቤት ውስጥ ያንን ማእረግ መስጠቱ ትልቅ ስህተት ነው.....

"በፍታት ስርዓት ላይ ጥንጥላ ተይዞላት ከጳጳሱ ጎን መቀመጥ አልነበረባትም። በወቅቱ ብዙ አርቶዶክሳውያን በሊላ ሃይማኖት ተዘቃዮች ፊት ምንም ማውራት እንዳይችሉ አድርጓል። ያ ነገር በዜና ሲታይ አጠገበህ ያለ ሰው ይዘብትብሃል። ለዚህ ነው ዋጋ አስከፍሎናል ያልኩት። ቅዱስ ዳዊት ስለእስራኤል ሲናገር ለጎረቤቶቻችን መሳለቂያ ሆንን ብሏል። እኛም ላይ የታየው ይህ ነው። ወደፊት ካላስተካከልነው አደገኛ አካሄድ ነው። ዓለማዊው እና መንፈሳዊው ነገር ተደበላልቋል። በሁለት ዓለም መጓዝ አይቻልም። አንዱን መምረጥ አለብን። ኤልያስም እኮ መጽሃፍ ቅዱስ ላይ እስከ መቼ ድረስ በሁለት ሃሳብ ታነከሳላችሁ? ያለው ለዚህ ነው። እግዚአብሄር መሃል ሰፋሪ ክርስትያኖችን አይወድም። ወይ ጭልጥ ብለን አልካድንም፣ ወይ በሙሉ ልባችን ፈጣሪን አልተከተልንም። መሃል ላይ ነው የምንዋልለው። ለዚህም ነው ለነሂዮንሴ አይነት ክስተት ክፍተት የምንፈጥረው።"

"እም!" አለች በሰሜት። "እም ወደፊት ካላስተካከልነው አደገኛ አካሄድ ነው። ዳግም የጎረቤቶቻችን መሳለቂያ መሆን አይኖርብንም። በጥቂት ራስ-ወዳዶች ስህተት አንገታችንን መድፋት የለብንም። ማንም ሊዘባበትብን አይገባም። የሂዮንሴ እና የጌቶጀ ሴራ መጋለጥ ይኖርበታል። ተጨባጭ መረጃዎች ያለው ሪድኤት ሃይላይ አጠገቧ አለ። እንደሚረዳት ቃል ገብቶላታል። ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመር ይኖርበታል። የስኩል አፍ ዋን ግሎብን ትምህርት ቤት ገጠመኝ እና የሂዮንሴን እቅድ በድረ-ገጽዋ ላይ ትለቀዋለች። ኢስክሊንም ያግዛታል። በድረገጹ አማካይነት ለአለም ህዝብ ያደርስላታል። በሚሰጠው ሙያዊ ገለጻ ላይ ያነሳላታል። ብዙ ህዝብ እንዲያውቀው ያደርግላታል። ስሜቷ ተነቃቃ።

- 31 -

ኢሊኖይስ፣ አሜሪካ

የሃሪማን ፓሌይ እና የዮናታን ወልዴ በተልካሻ ነገር እስርቤት መወርወር ዱብዳ የሆነበት፣ እቅዱ ሊከሽፍ በመሆኑ ከፍተኛ ብስጭት ውስጥ የገባውና "ውሾች! ከንቱዎች!!" ሲል በስድብ የከረመው ሮበርት አዳምስ፤ ከሰኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት ባስመጣው ረድኤት ሃይላይም እምብዛም ‹ሙቀት› አልተሰማውም፡፡ በችሎታው እና በንቁነቱ ቅንጣት ጥርጣሬ የለውም፡፡ ግን እባብ ነገር እንደሆነ ደመነፍሱ ነግሮታል፡፡ አብረውት የሚሰሩትን የቅርብ ሰዎች በጥንቃቄ እንዲያሰሩት ትእዛዝ ካስተላለፈ በኋላ ምክትል የሚዲያ ሃላፊውን አንድሪው ግርሃምን፡-

"ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ እቅዳችንን ለማሳካት እንዲተባበረን ያጨነውና ተልእኮ የሰጠነው አብሮህ የተማረው ቄስ የሚያስፈልገን አሁን ነው፡፡ ፈልገው?" አለው ሃሳብ በገባው ሰው እንደበት፡፡

"የስኩል አፍ ዋን ግሎቡ ሰውዬስ?"

"ችሎታና ንቁነት ሳያንሰው እባብ ቢጤ ነው፡፡"

አንድሪው ግርሃም ከት ብሎ ሳቀ፡፡ "እንዲህ እንድትል ያስገደደህ ምክንያት ምንድነው?"

አዳምስ አልሳቀም፡፡ እንደተኮሳተረ መልስ ሰጠ፡፡ "እስካሁን ድረስ ምንም ባላይበትም ለምን እንደሆነ እንጃ እባብነቱን ደመ-ነፍሴ እየነገረኝ ነው፡፡"

ግርሃም ለደቂቃዎች ያህል የተመሰጠ መሰለና "ደውዬ አገኘዋለሁ" አለ፡፡ ወሳኙ የቤት ስራ ተሰጠው፡፡

- 32 -

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የዘወትር ጥቁር ቆቡን የደፋውና ጥቁር ቀሚሱን ያጠለቀው ቄስ በቹ ዛሬም ከጊዮርጊስ ስጋ ቤቶች በአንደኛው ተገኝቷል። እለተ ማክሰኞ። ከቀኑ 6፡45 ደቂቃ። ዶሮ ማነቂያ እንደወትሮው ነው። ጸሃዩ እናት ይተረክካል። ሙቀቱ ምኞታቸውን ያጓደለባቸው የለበሱትን እያወለቁ ትከሻቸው ላይ ጣል ለማድረግ ተገደዋል። ለአት የረፈደባቸው የገዙትን ጫት ብብታቸው ውስጥ እየሸጎጡ ወደመቃሚያ ቤታቸው ይከንፋሉ። "ልንፋህ!" ና "እናትህን ልንፋ!" የሚሉትን ስድቦች እለታዊ መግባቢያቸው ያደረጉ አንዳንድ የአካባቢው ወጣቶችና ሊስትሮዎች እየተዘላለፉ ንብረቶቻቸውን ይናጠቃሉ። ጅምር ወፈፌዎች የጫት ገራባ እየለቀሙ አሮጌ ፌስታሎች እና ላስቲኮች ውስጥ ይከታሉ። ይህን ሁሉ ትእይንት እየታዘበ ከስጋ ቤት በረንዳ ላይ የተሰየመው ቄስ በቹ አስር ጊዜ ለአቱን ይመለከታል። ሁለት ወሳኝ ቀጠሮዎች ነበሩት። አንደኛው መስተፋቅር ከሰራለት አስቀያሚ መልክ ያለው ወጣት ገንዘብ የሚቀበልበት ቀጠሮ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከእመት በፊት የገዛትን መኪና ለመሸጥ በማሰቡ የሚያሻሽጥለትን ደላላ የቀጠረበት ነው። የባህር ማዶውን አዲሱን ስራውን ታሳቢ በማድረግ ገንዘብ እና ሃይል ወደእሱ እየመጣ እንደሆነ እርግጠኛ ሆኗል።

በመሃል ነበር "ልንፋህ!" የሚለው ጸያፍ ቃል ጆሮው ጥልቅ ያለው። ፈገግ አለ። ሰው ለይምሰል በየአደባባዩ ያወግዘዋል እንጂ እንደመነፋፋት ደስታ እና እርካታ የሚሰጥ ምን ነገር አለ? ሲልም ራሱን ጠየቀ። አይ ሃበሻ! ተግባሩና አፉ ለየቅል ሆኖ የሚያደርገውን እየደበቀ እንጂ የጓዳ ምስጢር ለደቂቃ የመጋለጥ አጋጣሚ ቢያገኝ ስንቱ ጨዋ መሳይ፣ ስንቷ እንግት ደፊ በተጋለጠ፣

በተጋለጠች አለና ከውሽሞቹ አንዱ ትዝ አለችው፡፡ የታወቀ ወርቅ ነጋዴ ሚስት ነች፡፡ ባሏ ሃብት እና ጉራ ብቻ እንጂ ስሜት አልነበረውም፡፡ እሷ ደግሞ ቅንዝንዝ ያደረጋት የሃያ አራት አመት ቆንጆ፡፡ የንስሃ (የነፍስ) አባታቸው ሆኖ ቤታቸው ከገባበት ቀን አንስቶ ቀልቧን ጣለችበት፡፡ እንኳን ቀልብ ተጥሎበት.....ጸበል ልርጭ በሚል ሰበብ እየተመላለሰ ሃጢያቱን ይረጭባት ጀመር፡፡ ጣማት፡፡ ስፍስፍ አለችለት፡፡ ሱስ ሆነባት፡፡ የማይጠቅማት ጉድ ነበረች፡፡

ድርጊቷን አስታወሰና ፈገግ አለ፡፡ ከቀረበለት ጥሬ ስጋ ይልቅ በምናቡ የሳለው ፍም የመሰለ ታፋዋ ምራቁን አመጣው፡፡ ቀጠሮ ባይኖረው ተነስቶ በበረረ፡፡ ስፍስፍ እያለች ደረቱ ላይ ልጥፍ ብላ "እንተ እናትህን ንፋኝ እንጂ!" ስትለው ታወሰውና መንከትከት ጀመረ፡፡ ከእርካታ በኋላ ያለችውን ሲነግራት በሃፍረት የምትገባበት ይጠፋታል፡፡ የበርካታ የሃበሻ ባህሪ ነው፡፡ ሲሰክር እና ወሲብ ላይ እያለ የሚለፈልፈውን አያውቅም፡፡ ቢያውቅም ግድ የለውም፡፡ ከእብደት እና ከስካር መልስ የሚገባበት ይጠፋዋል፡፡

"አባ.....አባ እንደምን ዋሉ?" የአስቀያሚው ወጣት ድምጽ ከሃሳብ አለም መለሰው፡፡ መስተፋቅር የሰራለት ወጣት ነበር፡፡

"መጥተሃል እንዴ? ሃሳብ ውስጥ ገባሁና....ቁጭ በል" ከመቀመጡ "ምን ይምጣ?" አለ ያንን ፍም የመሰለ ታፋ ከአይኑ ለማባረር የፊለገ ይመስል የቀኝ እጁን ወዲያና ወዲህ እያወናጨፈ፡፡

"ያለውን እንብላ፡፡" ወጣቱ አጨበጨበና ቢላዋ ጠየቀ፡፡ ወደጉዳያቸው ገቡ፡፡

"እሺ እንዴት ነው ጉዳያችን? ሰራ?" ሲል ቄስ በቹ ጠየቀ፡፡

"በደንብ እንጂ አባ! መንከራተት፣ በቀን አስሬ ወደቤቴ መመላለስ ጀምራለች፡፡ ስንት ዓመት ሙሉ አሳሬን ነበር ያበላችኝ፡፡ በተራዋ አሳሯን መብላት ጀመረች፡፡ ስንት ነበር ያሉኝ?" ወጣቱ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ነበር የሚያወራው፡፡ ቄስ በቹም ማንሾካሾክ ጀመረ፡፡

"ተነጋግረን የለ? በወዳጆቹ በኩል ስለመጣህ እንጂ ሰባት ሺህ ብር እያዋጣም"

"ለማስታወስ ያህል እንጂ በዛ ብዬ አይደለም፡፡ አመሰግናለሁ"

የታሰረ ብር አቀበለው፡፡ ቄሱ ሰው እንደማያየው ካረጋገጠ በኋላ ቆጥሮ ጨረሰ፡፡

"እኔም አመሰግናለሁ" ደላላው ስለመጣ ተሰነባበቱ፡፡

"እሺ?" አለ ቄስ በቹ ወደተረኛው ባለጉዳይ እየተመለከተ፡፡

"ለገጠው ሁሉንም ነገር ነግሬዋለሁ አባቴ፡፡ መንፈሳዊ ሰው እንደሆኑ፣ ተቸግረው እንጂ ለትርፍ እንደማይሸጡ፣ በደንብ የተያዘ መኪና እንደሆነ....."

"ጥሩ፡፡ ምን አለ?"

"ደስ ብሎታል፡፡ መንፈሳዊ አባት መሆንዎን ሲያውቅ የተባረከ መኪና ሊገዛ እንደሆነ እርግጠኛ ነው የሆነው፡፡ መኪናውን አስፈትሸነዋል፡፡ ስለዋጋው እና ስለቀሪ ጉዳይ በስልክ ሊያወራዎት ይፈልጋል፡፡ ስራ በዝቶበት እንጂ በአካል ሊያገኝዎት ነበር የፈለገው"

"ችግር የለም፤ በስልክ እንጨርሳለን፡፡ መልካም ብለኸዋል፡፡ የተባረከ መኪና ነው ፈጣሪ የጣለለት፡፡ እንደውልለታ?"

ደላላው የግንዘብ ጉዳይ ሆኖበት እንጂ የተባረከ እና የተረገመ መኪና እንደሌለ አልጠፋውም፡፡ ኮሚሽኑን እያሰበ ደወለ፡፡ ቄስ በቹና ገጠው መነጋገር ጀመሩ፡፡

"እንደምን ዋሉ አባ?"

"እግዚአብሄር ይመስገን፡፡ እንደምን ውለሃል ልጄ?"

"እግዜር ይመስገን፡፡ ሁሉንም ነገር ደላላው ነግሮኛል፡፡ ከመንፈሳዊ አባት ጋር በዚህ አጋጣሚ በመተዋወቄ ደስተኛ ነኝ፡፡ አባ ሰው አጭበርባሪ ሆኗል፡፡ መኪናቸውን የሚሸጡ መንፈሳዊ

አባት አሉ ሲሉኝ እግዜር ችግሬን አይቶ ነው አሳቸውን የጣለልኝ አልኩ፡፡ ለእግዜር ያደሩ ሰዎች የሰው ሃቅ አይፈልጉም....."

"በስመአብ...ወወልድ.....ወመንፈስ ቅዱስ፡፡ ምን አልኩህ ልጄ? የሰው ሃቅማ እሳት ነው፡፡ የእራስንም ይዞ የሚጠፋ፡፡ ያለንን ይባርከልን"

"ይባርከልን የሚል ጠፍቶ እኮ ነው ግለኝነት የሰፈነው፡፡ እና ስንት ነው የሚሉት?"

"እልነገረህም? ግዴለም ተጎድቼም ቢሆን ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ እሸጥልሃለሁ"

"እንደዚያማ አይሆንም አባ፡፡ መኪናውን አስፈትሸነዋል፡፡ ወጪ አለው"

"ይህች ዋጋ ማራከሻ ዘዴ ነች፡፡ አንተ የምትገዛበትን ዋጋ ተናገራ?"

"እንቀራራባ አባ፡፡ እርሶ እኮ በጣም ራቁ"

"እሺ...መቼስ ሁለት ክሰባ ይሁንልህ"

"እንደዛም አይሆንም"

"እና ስንት ነው የምትለው?" ቄስ በቹ እንደመበሳጨት አለ፡፡ ገጠርው እየፈራ እየቸረ መናገር ጀመረ፡፡

"እኔ ልጎዳ.....ያውም እርሶን ፈርቼ እና አክብሬ ነው፡፡ አይጎዱም፡፡ መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር ልስጥዎት"

"እንተን ብሎ መኪና ገጪ፡፡ የብስክሌት ሳይኖርህ መኪና ላይ ምን አንጠለጠለህ?"

ገጠርው የሰማውን ማመን አልቻለም፡፡ ምቀኛ ሰይጣን በቄሱ አንደበት የሚናገር መሰለው፡፡

"ምን?"

"ያንተን መቶ ሰማኒያ ሺህ ብር ቂጥህን ጥረግበት"

"ስነ-ስርአት! አስመሳይ ቄስ! ያንት ቢጤዎች ናቸው አማኙን ከእውነተኛ አባቶች የሚያታልሩት፡፡ ካልተስማማህ ይቀራል እንጂ ዘለፋና ስድቡን ምን አመጣው?"

"ሰን ኦፍ ኤቢች!"

"ምን?"

"ፋከዩ!"

ስልኩ ተዘጋ፡፡ ደላላው የሰማውን ማመን ተስኖት ቄስ በቹን በአትኩሮት እያየ ፊዞ ቀረ፡፡ አእምሮው የሚያሳየው ልብሰ-ተክህኖ የለበሰ፣ የመልካም አባቶችን ስም የሚያጎድፍ የከተማ ጹርዬ ነበር፡፡

****

ከመኪናው ሽያጭ ላይ ሊያገኝ ያሰበው ትርፍ እንዳሰበው ባለመሆኑ ብስጭትጭት ያለው ቄስ በቹ ሙሉ ትኩረቱን እነሮበርት አዳምስ በሰጡት የቤት ስራ ላይ ማድረግን መርጧል፡፡ የመኪናውን ሽያጭ ከአእምሮው አውጥቶታል፡፡ ሃያላኑ ሰዎች ለስራ ማስኬጃ ብለው የላኩለት ገንዘብ አስር መኪናም ቢሸጥ የማያገኘው ነው፡፡ ሙሉ ትኩረቱ ከፍተኛ ትርፍ ካለው ተልእኮ ላይ ሆኗል፡፡ ተልእኮው የሂዮንሴ ኖውልስ ቀጣይነት ያለው ተልእኮ እውን እንዲሆን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡ ሰይጣናዊ አምልኮን ማስፋፋት አንደኛው ነው፡፡ በጠንካራ የእምነት ሃገር ውስጥ ገንዘብ እና ዝና የሚያታልለው ጥቂት ሆዳም እና አላማ ማግኘት አይቸግርም፡፡ ጥቂቱ ሆዳምና አላማ ውሎ ሲያድር ጤናማውንም ሀዝብ መበከሉ አይቀርም፡፡ ለጊዜው ወጥመዱ ውስጥ የሚገባ ጥቂት አላማ ከተገኘ ቀሪውን በጊዜ ሂደት ማየት ይቻላል፡፡ እነሮበርት አዳምስ ጥቂት የስኬት ምልክት ከተመለከቱ ከረድኤት ሃይላይ የተሻለ እምነት ማሳደራቸው አይቀርም፡፡

ባያት ቁጥር እንትኑን እንደቀንድ የምትቀስር ይሁዳዊት ቆንጆ አጠገቡ አለች - ጁዲ ሚናሂም፡፡ ከእሷ ጋር መስራቱም አንድ ነገር ነው፡፡ ስሜትን ከምታቀጣጥል ውብ ሴት ጋር የሚሰራ ወንድ ለስራ

አይሰንፍም የሚል አመለካከት አለው። ችግር ሲፈጥር የሚችለው ያግልፍተኛ ባሏ ነው። ፊሱን እያንዛረጠ ወደ ሃገሩ እንዲሽመጥጥ ማድረግ እያቅተኝም ሲል አሰበና ሃሳቡ ስላሳቀው ሆዱን ይዞ ተንከተከተ። ሰይጣን እየኮረኮረው ነው ይሉ ነበር የሚጠሉት ባልደረቦቹ ቢያዩት። ሲናይ በረሃ ሲደርስ መቅዘኑን ያቆመው ባለስልጣን ትዝ አለው። የዚህኛው ግን ያስቸግራል። እየሰራ ያለው የገንዘብ ምንጩ ለሆኑት ሃያላን ሰዎች ነው። እያስፈሱ ከሃገር ከማባረር ይልቅ በድግምት የወሲብ ስሜቱን መስለብ ሳይሻል አይቀርም። ይሄኛው ተመራጭ መንገድ ነው። ያቺ ወንድ የምትፈታተን ሚስቱ ባሏ ሲቀዘቅዝባት እሱ ዘንድ መጥታ "እባክህን.....?" ማለቷ አይቀርም። የወርቅ ነጋዴውን ሚስት አስታወሳት። ይህችንም እንደ እሷ ካላንሰፈሰፍኳት እኔ በቁ አይደለሁም ሲል ዛተ።

- 33 -

ኢልከሆርን፣ ኒብራስካ

እለተ ረቡእ ከንጋቱ 11፡55። "ወደተከለከለው ግዛት" እንዳይገቡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የነበሩቱ አራት መርማሪ ፖሊሶች ውሳኔው ተለውጦና ማስጠንቀቂያው ተነስቶላቸው ኢልከሆርን፣ ኒብራስካ ውስጥ የሚገኙትን ወንጀለኞች በቁጥጥር ስር ለማዋል የፍርድቤት ትእዛዝ ይዘው ወደዚያው በመጓዝ ላይ በመሆናቸው ፍንጥዝጥዝ ብለዋል። ቶድ ስሚዝ "ከመበታተናቸው በፊት ደርሳችሁ በቁጥጥር ስር አውሏቸው!" ስላሏቸው ነበር በማለዳ በቦታው የተገኙት። ዋና ዋና ጎዳናዎችን እና የሰውና የተሽከርካሪ መተላለፊያዎችን ከዘጉ በኋላ መሳሪያቸውን በጥንቃቄ በመያዝ ወደግዙፉ ሰማያዊ ቤት ተጠጉ። ተጨማሪ ሃይል በመታዘዙ አካባቢው በፖሊስ መኪኖች ተጨናንቋል። ከአስር በማያንሱት የፖሊስ መኪኖች ተከልለው የአካባቢውን እንቅስቃሴ በንቃት የሚጠብቁት ተጨማሪ የፖሊስ ባልደረቦች ከውስጥ ሊሰነዘር የሚችለውን ጥቃት ለመከላከል ትንፋሻቸውን ዋጥ አድርገው እየጠበቁ ነው።

አራቱ መርማሪ ፖሊሶች በፍርግርግ ብረትየ ተሰራውን የግዙፉን ቤት አጥር በቀላሉ ዘለው ወደቤቱ ተጠጉ። አንድም ሰው አላጋጠማቸውም። የጠረጠሩት ዘበኞችን ነበር። በአጥሩና በቤቱ መካከል ሰፊ እርቀት አለ። ግቢው የመዋኛ ስፍራና ለምለም መስክ አለው። ድንገት ከመኪኖች ቤት አካባቢ ብቅ ካለ ወፍራም አጭር መላጣ ሰው ጋር ግጥምጥም አሉ። ወደየትም የማምለጥ እድል አልነበረውም። እየተብረከረከ ተመለከታቸው።

"ፖሊሶች ነን። አላስፈላጊ እንትስቃሴ አደርጋለሁ ብለህ እንዳታስብ። እጅህን ወደላይ!" ሙቶ አለቃ ቻርልስ አንደርሰን

ነበር የተናገረው። እንደታዘዘው አደረገ። ፈጠን ብሎ የተንደረደረው ሃምሳ አለቃ ሎይድ ፕርጋርድ ሰውዬውን በደረቱ መሬት ላይ አስተኛውና እጆቹን አዙሮ በሰንሰለት አሰራቸው።

"ሀጻናቱ የት ናቸው?" አለ ቻርልስ አፍጥጦ እየተመለከተው።

"የምን ሀጻናት?"

ድንገት ከቤቱ ዋና መግቢያ በር በስተግራ ካለው መስኮት ተኩስ ተከፈተ። ፖሊሶቹ መሬት ላይ ተኝተው አጸፋ መስጠት ጀመሩ። ተጨማሪ ሃይሎቹ እየተታኮሱ ወደቤቱ ቀረቡ። ታስሮ የነበረው ሰው ሊያመልጥ በሙከራ ላይ ሳለ ከሃምሳ አለቃ ሎይድ በተተኮሰ ጥይት ተመትቶ ሀይወቱ አለፈ።

ቅጽር ግቢው በተኩስ እሩምታ ቀውጢ ቢሆንም ተኩሱ ከሰባት ደቂቃዎች በላይ አልወሰደም። እጃቸውን እራሳቸው ላይ ያደረጉ ስድስት ሰዎች ከውስጠኛው ክፍል ወጥተው ፖሊሶቹ ፊት ቆሙ። ሃምሳ አለቃ አል ቫንዱሰን ግራ ክንዱ ላይ በጥይት በመመታቱ ደሙን ለማቆም ጥረት እያደረገ ነው። ይህን የተመለከተው አንድ ፖሊስ ቫንዱሰንን ደግፎ ውጭ ከተደረደሩት መኪኖች ወደአንዱ ወሰደው እና ለሹፌሩ "በአስቸኳይ ወደሆስፒታል" ሲል ትእዛዝ ሰጠ። ሾፌሩ አል ቫንዱሰንን ይዞ ወደሆስፒታል ሲከንፍ ትእዛዙን የሰጠው ፖሊስ ወደውስጥ ተመለሰ። ሶስቱን መርማሪ ፖሊሶች ጨምሮ ሁለት ረዳት ሃይሎች ሽጉጣቸውን ደግነው እጃቸውን ራሳቸው ላይ ወዳደረጉት ሰዎች ተጠጉ። እጆቻቸውን ካሰሩ በኋላ በርከት ያሉት የፖሊስ አባላት በሮች እየበረገዱ ፍተሻ ማካሄዳቸውን ቀጠሉ። ምድር ቤት ውስጥ ድምጽ የሰማ የመሰለው መቶ አለቃ ቻርልስ ሃይል አስከትሎ ወደዚያው አመራ። የሚያለቅሱና የሚንጫጩ ሀጻናት ድምጽ ይሰማ ነበር። በሩ ላይ ተለጥፎ ሲያደምጥ ከቆየ በኋላ ለሃምሳለቃ ሩሲል ማርቪን ምልክት አሳየው። በተመሳሳይ ፍጥነት በሩን በርግደው ገቡ። ያዩትን ማመን ተሳናቸው።

ሃያ ሶስት ሀጻናት ተጠጋግተው ተቀምጠዋል። ቤቱ ሰፊና በውድ እቃዎች የተሞላ ነው። በጎልማሳነት እድሜ ላይ የሚገኝ

እና የቆዳ ሶፋ ላይ የተቀመጠ መልከ-መልካም ሰው ከወገቡ በላይ እርቃኑን ሆኖ ቮድካ ይጠጣል። ጥምብዝ ብሎ እንደሰከረ ያስታውቃል። ከተቀመጠበት ሳይነሳ በንቀት ተመለከታቸው። በስካር የተያዘ አንደበቱ ሊያናግረው አልቻለም።

"ተነስተህ ልብስህን ልበስ?" አለው መቶ አለቃ ቻርልስ። ሹራቡን ለበሰ። ሩሴል ማርቪን እጆቹን አሰራቸው።

መቶ አለቃ ቻርልስ ሀጻናቱን በሃዘኔታ እየተመለከታቸው፣

"አይዟችሁ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር እናገናኛችኋለን" አላቸው። ፖሊሶች መሆናቸውን የተገነዘቡት ሀጻናት በደስታ ተንጫጩ። ወንጀለኞቹ እና ሀጻናቱ በፖሊስ መኪኖች ታጅበው ሲወጡ ነዋሪው በግርምት ተመለከታቸው።

****

የዱግላስ ፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድቤት ዳኛ ሃሮልድ ሰዋንሰን በቁጥጥር ስር የዋሉትን ተከሳሾች ጉዳይ መርምረው ብይን ለመስጠት በሰው በተጨናነቀው ችሎት ተሰይመዋል። ቦታ ያጡ ውጭ ሆነው ውጤቱን እየተጠባበቁ ነው። ለምስክርነት ከተመረጡት የወሲብ ተጠቂ ሀጻናት መካከል ሰለሞን አሽክሮፍት እና ዊሊ ካሪንግተን ተገኝተዋል። ጉዳዩ መታየት ጀመረ። ዳኛው ተከሳሾቹ መገኘታቸውን አረጋገጡ። ሁሉም ተገኝተዋል። ተከሳሾቹ ትሮይ ቦነር፣ ጆርጅ ኪንግ፣ ሚካኤል ሲርስ፣ አለን ባኢር፣ ፒተር ሲትረን፣ ቦብ ዋድማን እና ሃሮልድ አንደርሰን ነበሩ። በክስ ፋይሉ ላይ እንደተጠቆመው ሚካኤል ሲርስ በሲ.አይ.ኤ ውስጥ አእምሮን የመቆጣጠር ስራ ከሚሰራው ቅርንጫፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የወታደራዊ መረጃ ክፍል ሹም ሲሆን፣ ጆርግ ኪንግ ደግሞ የሪፐብሊካኑ ደጋፊና ቀንደኛ ገንዘብ አሰባሳቢ ነው።

የምስክሮች ቃል መሰማት ጀመረ። የማህበራዊ አገልግሎት ክፍል ሰራተኞችም በችሎቱ ፊት ቆመው የሚያውቁትን ተናገሩ። ከሁሉም ቀልብን የሳበው ምስክርነት የሰለሞን አሽክሮፍትና የዊሊ ካሪንግተን ነበር። የመጀመሪያው ምስክር ሰለሞን በነጭ ቼቭሮሌት

መኪና እንዴት እንደተጠለፈ፣ የጠለፉት ሰዎች በወሲብ እና በአደገኛ እጽ ንግድ ላይ እንዳሰማሩት፣ እንዳሰቃዩት፣ መጠሪያ ስሙን በሌላ እንደተየሩት እና ሲኦል ሀይወት ውስጥ እንደቆየ እምባ እየተናነቀው ተናገረ፡፡ ቀጣዩ ምስክር ካሪንግተንም ካሊፎርኒያን፣ ዋሽንግተን ዲሲን፣ ዴስ ሞይንስን፣ ፓሴዳን፣ ታምፓን እና ሚኒያ ፖሊስን ጨምሮ ከአስር ባላነሱ ከተሞች ከባለስልጣናት እና እውቅ የንግድ ሰዎች ጋር እየተዘዋወረ የግዳጅ ወሲብ ይፈጽም እንደነበር ተናገረ፡፡ በ<YNR> እና <Kam> አየር መንገዶች ወደሚጠሩት ሰዎች ይመላለስ እንደነበር የተናገረው ዊሊ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በመንታዎቹ ማማዎች ላይ በሚገኘው የግል አፓርትመንቱ ከአለን ባኢር ጋር በሃያ ዶላር ክፍያ ወሲብ መፈጸሙን ተናገረ፡፡ በግዳጅ ወሲብ እና በድብደባ ህይወታቸው ካለፈ ጓደኞቹ መሃል አሌክሳንደር ሌስተርን፣ ሃሮልድ ብራውንን፣ ማይከል ፓስካልን እና ዴቪድ ክራግን እንደሚያስታውሳቸው እያለቀሰ ተነገረ፡፡

ወንጀለኞቹ እጅ ከፍንጅ ስለተያዙ ማስተባበል አልቻሉም፡፡

ተጨማሪ ማስረጃ ያላስፈለጋቸው ዳኛ በሁሉም ወንጀለኞች ላይ የእድሜ ልክ እስራት ወስነው ፋይሉን ዘጉት፡፡ ወላጆቻቸውን ያገኙ ህጻናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲቀላቀሉ ለጊዜው በቦታ እርቀት እና በሌሎች ምክንያቶች ቤተሰቦቻቸውን ያላገኙ ህጻናት በማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት እንክብካቤ እየተደረገላቸው እንዲቆዩ ተደረገ፡፡

- 34 -

ካናዳ-ሴንት ካስቲን

ሃያላኑ ስብሰባ ለማካሄድ ካናዳ-ሴንት ካስቲን ተገኝተዋል። ጸንኤል ኢስቱሊን፣ ሶስና አለማየሁን አስከትሎ ከቅርብ ምንጮቹ መረጃ ለማነፍነፍና ስብሰባቸውን ለመቃወም በስፍራው ተገኝቷል። ሶስና አንድ ነገር ትውስ አላት። የደብሊው.ኤስ.አይ.ኤል-ቲቪ ባልደረባ ሆና ብትቆይ በ"አሻንጉሊት"ነት በስብሰባው ላይ መገኘቷ አይቀርም ነበር። ረድኤት ሃይላይ ቦታዋን እንደሚተካ አልተጠራ ጠረችም። ልታገኘው እንደምትችልም ገምታለች። እንዴት፣ መች እና የት እንደሆነ ባታውቅም። በመጀመሪያው ቀን ከጋዜጠኞች፣ ከራሳቸው አሻንጉሊቶች ጋር ይፋዊ ስብሰባ ያደረጉት ሃያላን በሁለተኛው ቀን አሻንጉሊቶቻቸውን ለዛሬ አትፈለጉም፤ ሀጻናት እና አገልጋዮች የማይሰሙት፣ ሊሰሙትም የማይገባ የግል ምስጢር አለን። በመዝጊያው እለት ነገ እንጠራችኋለን ሲሉ አሰናበቷቸው።

ረድኤት ሃይላይ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሴንት ካስቲንን ከእግር እስከ እራሷ ሊጎበኛት ወሰኗል። አልጋ በተያዘለት ሆቴል ቁርሱን በልቶ ወጣ። ሱቆችን፣ መዝናኛ ስፍራዎችን፣ ታዋቂ ቦታዎችን እየጎበኘ እና በሚያየው ነገር እየተዝናና በእግር መጓዙን ቀጠለ። እብድ ሃገር ቤት ብቻ ያለ ይመስለው ነበር። እንደሃገር ቤቶቹ ልብሳቸውን አውልቀው መለመላቸውን በትልቅ ድንጋይ ሰው እያባረሩ አፏራ የሚያስነሱትን አይነቶቹን ባይሆንም የጸዳ ልብስ ለብሰው ከእራሳቸው ጋር እያወሩና እየሳቁ ሰው ትኩር ብለው የሚያዩ ጥቂት እብዶችን ተመልክቷል። ይህንን እና ሌላ ሌላውንም እየታዘበ ሲጓዝ ከኋላው የደረሰችበት ሴት፣

"አይ ዋንት ድሪንክ ኮላ?" አለችው ጎርነን ባለድምጽ። ዘወር ብሎ ተመለከታት። ጸጉሯን ወደኋላ ልምጥ አድርጋ አሰተኛታ ጆሮዋ ላይ ትልልቅ ክብ ጌጦች አንጠልጥላለች። አለባበሷ

አይስብም፡፡ አይናቿን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ፍሬሙም መስታወቱም ጥቁር የሆነ ትልቅ መነጽር አድርጋለች፡፡ ትልቅ ታኮ ጫማዋ ቁመቷን ያለቅጥ አንቀዋሎታል፡፡ ምኗም አላማረውም፡፡ እስካሁን የተመለከተው የወንድ ወፈፌዎችን ነበር፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ወፈፌ አጋጠመችው፡፡ ገላምጧት ጉዞውን ቀጠለ፡፡ እየተከተለችው "አይ ዋንት ድሪንክ ኮላ?" አለችው በሚያስጠላ ጎርናና ድምጽዋ፡፡ ሀገር ቤት ቢሆን እግዜር ይስጥልኝ ይላት ነበር፡፡ እዚህ ምን እንደሚባል አያውቅም፡፡ አፉ እንዳመጣለት

"አይ ሃቭ ኖ ታይም" አላት፡፡ የዋዛ አልነበረችምና አልለቀቀችውም፡፡

"አኬ ጀስት ጊቭ ሚ መኒ?" በብስጭት እርምጃውን አፋጠነ፡፡ በፍጥነት ከጎኑ እየተራመደች

"ረድኤት ይሀን ያህል ቆንቋና ነህ እንዴ - ያውም ለአንድ ኮካ?" ጎርናና ድምጽዋ ተቀይሯል፡፡ ማመን ተሳነው፡፡ አፍጥጦ ተመለከታት፡፡

"እኔ አላምንም ሶስና እንዲህ አይነት ተዋናይ ነበርሽ እንዴ?!"

"ስራዬ ለጥንቃቄ ስል ተዋናይ እንድሆን ያስገድደኛል፡፡ የግድ ነው፡፡ እንደነኢስቱሊን እጅግ ታዋቂ እስክሆንና ከለላ እስካገኝ በእዚህ አይነት ሁኔታ ከአለቆችህ መደበቅ ይኖርብኛል፡፡ እንደዚህ አይነት ስብሰባዎች ላይ እንደሚገኙ አውቃለሁ፡፡ ጸባችን እየከረረ መሄዱ ስለማይቀር ዱካዬን ማግኘት አይኖርባቸውም፡፡ ሱቅ ውስጥ ሆነን ስለተመለከትኩህ ነው የተከተልኩህ፡፡ አብረኸን ልትቆይ ፍቃደኛ ነህ?"

"በጣም ሶስና.....በጣም፡፡ አብሬያችሁ ብውል እና ባመሽ ደስታውን አልችለውም"

"ተከተለኝ? ኢስቱሊንን ካገኘነው በኋላ ከአካባቢው መራቅ ይኖርብናል፡፡ በተለይ ለአንተ ደህንነት"

"ትክክል ነሽ ሶስና፣ በነጻ መንፈስ ለማውራት ሴንት ካስቲንን ለቀን መራቅ ላይኖርብን አይቀርም፡፡ ከእናንተ ጋር መገናኘቴ በተለይ ከኢስቱሊን ጋር መታየቴ ሊያስጠረጥረኝ ይችላል"

ኢስቱሊንን ካገኙ በኋላ ወደከተማዋ ዳርቻ ነዱ፡፡ ያረፉት በከተማዋ ዳርቻ ላይ በሚገኝ ሰው የማይበዛበት ሆቴል ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ረድኤት ከኢስቱሊን ጋር በሰፊው ለመወያየት እና ስለሃያላኑ የማያውቀውን ለማወቅ እድል አገኘ፡፡

ኢስቱሊን ብዙ ነገሮችን ነገረው፡፡ በእጅጉ የተገረመው "ሃያላኑ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ በኢየሱሳውያኑ አማካይነት ኢትዮጵያን ለመውረር እና እምነታቸውን ሊያስፋፉባት ያደረጉት ሙከራ ነው፡፡ ሙከራው ዛሬም ድረስ ዘልቆ በሌላም መልክ ቢሆን ሃገራችሁን መመኘታቸው አልቀረም" በሚለው ንግግሩ ነው፡፡ በሌላ መልክ ማለቱ በድምጻውያን ሰርጎ-ገቦች አማካይነት ባእድ አምልኮ ማስፋፋትን፣ ሃገሪቱ በእጅጉ የምትጠየፈውን ግብረ-ሰዶማዊነት ማዛመትን፣ በስልጣኔ ስም ወጣቱን የባህርማዶ ባህልና እምነት ጥገኛ ማድረግን ወዘተ ማለቱ እንደሆነ አብራርቶለታል፡፡ የከሰአት በኋላውን የውይይት መድረክ የተቆጣጠረው ረድኤት ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ላይ የታሰበውን ሴራ ሶስና በጽሞና እንድታደምጠው ፈልጓል፡፡

"ሰዎቹ ባስተላለፉልኝ ትእዛዝ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ከሸሙት ቄስ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳደርግ ነግረውኛል፡፡ በየጊዜው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚመላለሱት ጥንድ አይሁዶች ጋር በጋራ እንዲሰራ የተመደበ ሰው ነው፡፡ አብረኸው ስራ ከተባልኩበት ጊዜ ጀምሮ ወደሚያገለግልበት ደብር ደውዬ ታሪኩን ለማጥናት ሙከራ አድርጌ ነበር፡፡ የሚገርማችሁ ግን በቅርብ የሚያውቁት ሁሉ የነገሩኝ በልብሰ-ተክህኖ የተደበቀ የከተማ ዱርዬ መሆኑን ነው፡፡ በእስራኤል እና በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ባገኘው የነጻ ትምህርት እድል ሁለቱም ሃገራት የስነ-መለኮት ትምህርቱን ተከታትሎ የተመለሰ ነው፡፡ የሞሳድ እና የሲ.አይ.ኤ ሰላይ ለመሆኑም ጥርጣሬ አለ፡፡ የግል ባህሪውም ለሰዎች፣ በተለይም ደግሞ አጠገቡ ላሉት የሚመች አይደለም፡፡ ቄስ በቹ ይባላል....."

ሶስና ጣልቃ ገባች፡፡

"በስልጣንና በደሞዝ የበለጣቸው ያስወሩበት የምቀኝነት ወሬ ቢሆንስ?" ረድኤት በፍጥነት እንጉቱን ነቀነቀ፡፡ የሚያወሩት

በእማርኛ ስለነበር ኢስቱሊን ያሚሉት ባይገባውም በተመስጠ ነበር የሚያደምጣቸው፣፣ አልፎ አልፎ ሶስና ትተረጉምለታለች፣፣

"መጀመሪያ እኔም እንደዚያ ገምቼ ነበር፣፣ ግን የምቀኞች ወሬ አይደለም፣፣ አብሯቸው እንዲሰራ የተመደቡት ጥንዶቹ አይሁዲ ችም ከጅምሩ በርከት ያሉ የስሞታ ሪፖርቶች አቅርበዋል፣፣ ሪፖርቶቹ ሰውዬው ለጥቅም የቆመ እንጂ ፈጽሞ ስራውን የማያውቅ (ለስራው የማይመጥን)፣ ቀጠሮ ሰአት ላይ ግድ የሌለው፣ ሶስት ሰአት ተቀጥሮ እምስት ሰአት የሚመጣ እንደሆነና ሌሎችም አሰቸ ጋሪ ባህሪያት እንዳለው የሚናገሩ ናቸው፣፣ የተጠራጠርኩት የሞሳድ እና የሲ.አይ.ኤ ሰላይ መሆኑ ያጠራጥራል የሚለውን እንጂ የተባ ለው ሁሉ የማይሆንበት ምክንያት የለም፣፣ የሃገሩ ልጆች በምቀኝነት አወሩበት ብንል እንኳን ጥንዶቹ የት አውቀውት ነው እንደዚያ አይነት ሪፖርቶች ለሮበርት አዳምስ የሚልኩት? በተለይ ከሃጊ ጋር ጥርስ ያናከሳቸው ሚስቱን አላስወጣ አላስገባ ስላሳት ነው፣፣ ሃጊ በአንደኛው ሪፖርት ላይ ይህንን ምሬቱንም አስፍሮታል" አለና ሳቀ፣፣

አሁንም ሶስና ጣልቃ ገባች፣፣

"የሞሳድ እና የሲ.አይ.ኤ ሰላይ ሊሆን ይችላል የሚለውን ጥርጣሬ በምን ተጠራጠርከው? ደግሞስ ይሁዶቹ ይህን ያህል ከተማረሩበት እነሮበርት አዳምስ ከእነሱ ጋር እንዲሰራ ለምን መደቡት?" ረድኤት መልስ ሰጣት፣፣

"ሰላይ ለመሆን፣ በተለይም የሁለቱ ታላላቅ የስለላ ድርጅቶች ሰላይ ለመሆን እኮ ችሎታ እና የስለላ ስነ-ምግባር እንዲሁም ጊዜ የፈጀ ስልጠና ያስፈልጋል፣፣ እንዳለኝ መረጃ ከሆነ ቂሉ ዩኒቨርሲቲዎቻቸው ስነ-መለኮትን አጠና እንጂ ለስለላ ብቁ የሚያደርግ ስልጠና አልወሰደም፣፣ እንደመሸታ ቤት ዘው ብለው የሚገቡበት ቦታ እና ሙያ አይደለም፣፣ በስልክ እንዳወራሁትም ባዶ ጉራ እንጂ ብቃት ያለው አይመስለኝም፣፣ እነሮበርት አዳምስ የመደቡትማ በሃይማኖቱ አካባቢ በተለይም በአብያተ-ክርስትያናት

አካባቢ ለታሰበው ዘፋኞችን አሰርጎ የማስገባት ሴራ ዋና ሞተር ሆኖ እንዲያገለግላቸው ነው። እንድሪው ግርሃም ነው የጠቆመው.....

"ጉንዶቹ ይሁዶች የተመደበላቸው ሰሞን የአብያተ-ክርስትያናቱ አካባቢ ተልእኮ ያለችግር ይሳካል ብለው ተደስተው ነበር። ውሎ ሲያድር ነው ጉድ የተከሰተው። እንዴ ሰውዬው እኮ ሃጊን በድግምት ወንድነትህን ሰልቤ ሲያዩዋት ብልት የምትቀስር ሚስትህን ያላንበጫበጭኳት እንደሆነ በቹ ብለህ አትጥራኝ ብሎ ዝቶበታል አሉ። ሃጊበላከው ሪፖርት ላይ የተናገረው ነው" ሶስና እየተገረመች ረድኤት የነገራትን ሁሉ ለኢስቱሊን ነገረችው።

"ሮበርት አዳምስ ለምን እሱን አሰናብቶ ሌላ ሰው አይተካም?" ስትል ጥያቄ አቀረበች። ኢስቱሊን ድግምት ስለሚባለው ነገር ማብራሪያ ስለፈለገ አስረዱት።

ረድኤት ምላሽ መስጠት ጀመረ።

"ባህሪው.....መሰሪነቱ.....አምታችነቱ ለሮበርት አዳምስ ላይስማማው አልቀረም። በዚያ ላይ ሃይማኖቱ አካባቢ እንደእሱ አይነት ማተብ በጣሸ፣ ያጎረሰውን ነካሽ እንደማይገኝ እርግጠኛ ሆኗል። አላማቸውን እስካሳካላቸው አምታች፣ አተራማሽ መሆን አይደለም ምንም ቢሆን ምን ቸግሯቸው!?"

ሶስና ዱርዬውን ቄስ በምናቧ ስላው ሳቀች። ስለ በቹ የተነገረው ኢስቱሊንም በማያውቀው ኢትዮጵያዊ ቄስ አስገራሚ ባህሪ ተደንቆ ሳቁን ማባራት አልቻለም። ረድኤት በቀጣይነት ለነሶስና የነገራቸው በአለቆቹ በኩል የተነገረውን እና እንዲያስፈጽም ትእዛዝ የተላለፈለትን የሴራ ታሪክ ነው።

"ሶስና ይህ ታሪክ ለድረ-ገጽሽ እጅግ ይጠቅምሻልና በደንብ ስሚኝ። ሰምቹ ከኖውልስ ተልእኮ ጎንለጎን ተግባራዊ ሊያደርጉ ያሰቡት የአእምሮ ቁጥጥር ስራውን ነው። ተጋባሽ በሆንኩበት ሙያዊ ገለጻ ላይ ስለአእምሮ ቁጥጥር ተግባር ገለጻ ሊያደርጉልኝ ሞክረዋል። በሌላው አለም ተግባራዊ የሆነውን ይህንን ሰይጣናዊ ሴራ በሃገሬ ወጣቶችም ላይ ተግባራዊ ሊያደርጉ ተዘጋጅተዋል።

"በምን እይነት ሁኔታ?" የሶስና ልብ ባልተለመደ አኳኋን መምታት ጀመረ፡፡ በመድሃኒት የሰው ዘር ለማመናመን ወደኋላ ያላሉ እኩዮች ምንም ነገር ከማድረግ እንደማይመለሱ ታውቃለች፡፡ ረድኤት ቀጠለ፡-

"ሲሰራባቸው የቆዩ የተለያዩ የአእምሮ ቁጥጥር ቴክኒኮችና ዘዴዎች ቢኖሩም ለጊዜው ኢትዮጵያ ውስጥ የታሰበው የድግምት፣ የአስማት እና የጥንቆላ መጽሃፍትን በብዛት በማስገባት የወጣቶችን አእምሮ እንደፈለሙና እንደሙዚቃው ሁሉ በአስማታዊ መጽሃፍት አደንዝዞ በቁጥጥር ስር ማዋል ነው፡፡ ልብ አድርጊ የአስማታዊ መጽሃፍት አላማ ወጣቶቹ እንብበዋቸው በተመሰጡባቸው ታሪኮች እየናወዙ ሌላውንና ወሳኙን የሃገራቸውን ታሪክ እንዲረሱ ማድረግ ብቻ አይደለም፡፡ ዋናው አላማ አስማታዊ ሃሳቦችን ወደ አእምሯቸው አስርጾ በማስገባት የጥንቆላው አለም ዋና ተዋናይ፣ የሰይጣናዊ ዓለም ግንባር ቀደም ተሳታፊ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚበተኑ የ1900ዎቹዓ.ም የአስማት መጽሃፍት በብዛት እና በተለያየ ይዘት ተዘጋጅተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ፣ እንደውም ሁሉም ማለት ይቻላል በ1940ዎቹ ማገባደጃ ላይ ለኢሉሚናቲ የመረጃ (ኢንተለጀንስ) ማህበረሰብ አባላት ሞንቅትን እና ፍርሃትን መሰረት ያደረገ የአእምሮ ቁጥጥር ተግባራዊነት አገልግሎት ላይ የዋሉ ናቸው፡፡ እነሱ "ትራውማ ቤዝድ ማይንድ ኮንትሮል ፕሮግራም" ለሚሉት ማለት ነው.....

"የቲዮዞፊካል ማህበር አባል የነበረው ጠንቋዩ ባውም የሆነ መንፈስ የአስማቱን ቁልፍ ስለሰጠው <Wizard of Oz> የተሰኙ ተከታታይ መጽሃፍትን እንዳዘጋጀ በሙያዊ ግለጻው ላይ ተነግሮኛል፡፡ እነዚያ መጽሃፍት አስራ አራት ተከታታይ ክፍሎች ያሏቸው ሲሆኑ ሁሉም ስለሰይጣን፣ መድሃኒተኝነት፣ ድግምት፣ ጥንቆላ፣ መተት ወዘተ የሚያወሩ ናቸው፡፡ The Wizard of Oz፣ The Land of Oz፣ Ozma of Oz፣ Dorothy and Wizard In OZ፣ The Road to Oz፣ The Emerlad City of Oz እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል.....

"እና ሶስና ይህንን እንዴት ነው በዝምታ እና በቸልተኝነት የምናልፈው? የሀገሬ ወጣቶች በእንደዚህ አይነት ሰይጣናዊ አስተሳሰብ እንዲበከሉ አልፈልግም። የተጠነሰሰውን እና ተግባራዊ እንዳደርገው የተነገረኝን ሴራ ነግሬሻለሁ። አንድ ነገር አድርጊ። ቢያንስ በድረ-ገጽሽ አማካይነት ሴራው የተደገሰላቸው ወጣቶች እውነቱን አውቀው ራሳቸውን እንዲከላከሉ የማድረግ የዜግነት ግዴታ አለብሽ።"

ረድኤትን በማመን እና በመጠራጠር መሃል ላይ የነበረችው ሶስና የእምነት መጠኗን ከፍ እያደረገች ሄዳለች። ሌላው ቢቀር ህይወቱን አደጋ ላይ ጥሎ የተነገረውን መረጃ እያደረሳት እና እርምጃ እንድትወስድ እየገፋፋት ነው። ያም ሆኖ ሙሉ በሙሉ እምነቷን አልጣለችበትም። ለነገሩ ኢስቱሊን ለገንዘብም፣ ለሃገርም የሚሰሩ <ደብል ኤጀንቶች> እንዳሉ በተደጋጋሚ ነግሯታል።

ኢስቱሊን የረድኤትን ገለጻ ተከትሎ ስለአእምሮ ቁጥጥር ጥቂት ነጥቦችን ጨመራላቸው።

"የአእምሮ ቁጥጥር ሳይንስ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ አገልግሎት ላይ የዋለ ጨካኝ ሳይንስ ነው። ረድኤት እንዳለው ከአስማት መጽሃፍት በተጨማሪ በኤሌክትሪክ ንዝረት፣ አእምሮን በሚለውጡ ሃይለኛ መድሃኒቶች እና በሌሎችም ቴክኒኮች አእምሮን በቁጥጥር ስር ማዋል ከተጀመረ አመታት ተቆጥረዋል። ጀርመንን፣ ስኮትላንድን፣ ጣሊያንን እና እንግሊዝን ጨምሮ በሌሎች በርካታ ሃገራት በሚገኙ የኢሉሚናቲ ቤተሰቦች አማካይነት ተፈጥረው በየጊዜው እየተሻሻሉ ዛሬ ላይ የደረሱት የተለያዩ የአእምሮ ቁጥጥር ዘዴዎች ዛሬም በተለያዩ ሃገራት ተግባር ላይ እየዋሉ ነው። ይህን ቴክኒክ ተግባራዊ ካደረጉ ጨካኝ የሰው ልጅ አእምሮ ቁጥጥር ፕሮግራመሮች አንዱ ጆሴፍ ሚንግል ነው። በማጎሪያ ካምፕ ውስጥ የነበሩ በርካታ እስረኞችን አእምሮ በተለያዩ ቴክኒኮች በቁጥጥር ስር እንዲውል ያደረገ ጭራቅ ነው።"

የሶስና ጭንቅላት ሊፈነዳ ደረሰ። ይህማ አይሆንም፣ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት እንድ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል ስትል በውስጧ

ዛተች። ረድኤት ‹በቀሚስ ተከልሎ የሚያጭበረብር› እያለ የሚጠራውን ቁስ በቹን እኩይ ተግባር ጨምሮ የሂዮንሴ ኖውልስን ቀጣይ ሰይጣናዊ የተልእኮ እቅድ እንዲሁም በስኩል አፍ ዋን ግሎብ ትምህርት ቤት ቆይታዋ የተመለከተችውን እውነት በማዘጋጀት በድረ-ገጽ ለመልቀቅ መንፈሷ አቆበቆበ። ሃሳብ ሲለዋወጡ አምሽተው ወደ ሴንት ካስቲን ተመለሱ። ረድኤትን ሲሰናበቱት በሌላ ጊዜ እንደሚገናኙ ቃል በመግባት ነበር።

- 35 -

ፓልማ፣ ማሎርካ

ሶስና አለማየሁ በቅጡ ያጠናቀረቻቸውን መረጃዎች ደጋግማ ተመለከተቻቸው፡፡ በእሷ እምነት ሁሉም ሚዛን የሚደፋና ህዝቡ ሊያውቃቸው የሚገባ ናቸው፡፡ ህዝቡ እውነታውን ከተገነዘበ በኋላ ራሱን የመከላከል አርምጃው የአራሱ የቤት ስራ ይሆናል፡፡ እነሮበርት አዳምስን ሊያስቆማቸው እና ሴራችሁ ታውቋል አርፋችሁ ተቀመጡ ሊላቸው የሚገባውም እራሱ ህዝቡ ነው፡፡ ማድረግ የሚገባትን አድርጋለች፡፡ ከእሷ ቅስቀሳና ከሰዎቹ የሴራ ሃይል የቱ ሚዛን እንደሚደፋ ወደፊት የምታየው ይሆናል፡፡ በዜግነቷ ማድረግ የሚገባትን ነው ያደረገችው፡፡ ሴራውን ተናግራለች፣ አሳውቃለች፡፡ ካንቀላፋችሁበት ንቁ ብላለች፡፡ መንቃት እና ከሰይጣን አምላኪዎች ወጥመድ አልወድቅም ማለት የህዝቡ ፋንታ ነው፡፡ ቁልፉ ያለው እሱ ዘንድ ነው፡፡ የሴራውን በር ለመክፈትም ሆነ ለመዝጋት እድሉ ያለው ህዝቡ ዘንድ ነው፡፡ ዛሬ ባይሳካ ነገ ይሳካልና፣ ዛሬ ባይነቃ በሂደት ይነቃልና ጥረቷን እንደማታቋርጥ ለእራሷ ቃል ገባች፡፡

በመጀመሪያው ምእራፍ ላይ ያስቀመጠችው የናውልስን ዳግመኛ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ መሄድ እና በአብያተክርስትያናት ውስጥ ሰርጋ በመግባት ምእመኑን ከሃይማኖት እባቶች እና በመሪነት ደረጃ ላይ ካሉት ጋር ለማቃረን እና ሰይጣናዊ አምልኮን በተለያዩ መንገዶች ለማስፋፋት የያዘችውን እቅድ ሲሆን፣ ከዚህ ቀጥሎ እነሮበርት አዳምስ ኢትዮጵያ ውስጥ የቴሌቭዥን ጣቢያ በማቋቋም ሽፋን የወጣቶችን አእምሮ በቴጥር ስር ለማዋል በጥንዶቹ አማካይነት እየሸረቡ ያሉትን ሴራ ዘርዝራለች፡፡ የስኩል አፍ ዋን ግሎባ ትምህርት ቤት ገጠመኟ ተነስቷል፡፡ ረድኤት

ሃይላይ የነገራት ኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ ሊደረግ የታሰበው የአእምሮ ቱጥጥር ተግባር እና አተገባበሩም አልቀራትም፡፡ መጨረሻ ላይ ያሰፈረችው ክስክል ኤንድ ቦንስ አባላት ጋር ግንባር ፈጥሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሰቡትን እቅድ ለማሳካት ቀኝ እጃቸው ሆኖ የተሾመውን ቂስ በቹን ጉዳይ ነው፡፡ መረጃዋን ለሰምንተኛ ጊዜ አነበበችው፡፡

"እንደ ኢትዮጵያዊነቴ....እንደ ባለሙያነቴ የእራሱን መንግድ እና ሰበብ ፈጥሮ እንዳጋልጥ መሳሪያ ያደረገኝን ልዑል ፈጣሪዬን እግዚአብሄርን አመሰግነዋለሁ፡፡ ሰሚያደርገው ሁሉ ምክንያት አለው፡፡ በጋዜጠኝነት ሀይወቴ ባሳለፍኳቸው አመታት የምስጢር ማህበራት ወጥመድ ውስጥ እወድቃለሁ ብዬ አሰቤ ቀርቶ ትዝ ብሎኝ አያውቅም፡፡ ለበጎ ነው፡፡ በምክንያት እዚህ ወጥመድ ውስጥ እንድገባ ያደረገኝን ዓምላክ በድጋሚ አመሰግነዋለሁ፡፡ መሳሪያ ሊያደርገኝ አሰበ ይሆናል.....

"እነዚህ የሰይጣን ልጆች በሃገሬ ምድር ላይ የተንኮል ድራቸውን ማድራት ከጀመሩ አያሌ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከአሰራ ሰድስተኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ አይናቸውን በሃገሬ ላይ እንደጣሉና በኢጣሊያን ወረራ ጊዜም በኢየሱሳውያን ቄሶች ተመርቀው ለም መሬቴን ለመውረር እንደተንቀሳቀሱ መጻህፍት ነግረውኛል.....

"በሃገሬ ላይ ያደረባቸው ፍላጎት ቅርጹን ይቀይር እንጂ ዛሬም እንዳለ ከምመለከተው ነባራዊ እውነታ ላይ በመነሳት መመስከር እችላለሁ፡፡ በተለይም ከሴረኞቹ ጋር እስከቅርብ ጊዜ አብሬ ነበርኩና ስለእውነታው ጥርጣሬ አይግባችሁ፡፡ የምስጢር ማህበራት ከፍተኛ ባለስልጣናት በሆኑት በነሮበርት አዳምስ እየተመሩ ሀገሬን እና ዜጎቿን በተለያየ መንገድ በቁጥጥር ስር ለማድረግ እየተንቀሳቀሱትና የሃገሬ ዜጎች በተለይም መጣቶች በላያቸው ላይ የተቃጣውን የሴራ ድርጊት በመገንዘብ ራሳቸውንና ሀገራቸውን ይከላከሉ ዘንድ ጥሪዬን ለማስተላለፍ እገደዳለሁ.....

"የሃገሬ ዜጎች በተለይም መጣቶች ሂዮንሴ ናውልስ በሃገር ቤት መድረክ ላይ ያቀረበችውን የሙዚቃ ዝግጅት፣ በሀዳናት ማላደጊያ

ድርጅት ያደረገችውን ጉብኝት፣ በሰይጣናዊ የእጅ ምልክት ምንም ከማያውቁ ሀጻናት ጋር የተነሳችውን ፎቶ፣ በቅድስት ሰላሴ ካቴድራል ቅጽር ግቢ ተገኝታ በነበረ ጊዜ የተደረገላትን ደማቅ አቀባበል እንደማይረሱት እተማመናለሁ፣ ይህች ሴትዮ ዘፈን እና ዘፋኝነት በሚወገዙበት ቅዱስ ስፍራ ጥላ ተዘርግቶላት ለመቀመጥ ለፍረት ያልያዛት ርቃን ደናሽ ጉድ ከምስጢር ማህበር ባለስልጣናት በተላለፈላት ልዩ ትእዛዝ መሰረት ዳግመኛ ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ አብያተክርስትያናት ውስጥ ሰርጋ ለመግባትና በአማኙ ህዝብ እና በሃይማኖት አባቶች መካከል መቃቃርን ለመፍጠር፤ ከተሳካላትም ሰይጣናዊ አምልኮን ለማስፋፋት በዘገጅት ላይ ትገኛለች። የሃገሬ ወጣቶች የጥበብ ሰውነቷን ለማድነቅ አትከለከሉም። ነገር ግን በጥበብ ሰውነቷ ተታላችሁ የነሮበርት አዳምስ ኢላማ ማረፊያ ላለመሆን ተጠንቀቁ። አይናችሁን ክፍታችሁ ንቁ.....

"ጥበብን እና ሰይጣናዊ ተልእኮን ለዩ። እደግምላችኋለሁ። የጥበብ ሰውነቷን ለማድነቅ አትከለከሉም። ከሰይጣናዊ መልእክት ይዘት ውጪ የሆኑ ዘፈኖቿን አታድምጡ የሚል ግትር አቋም የለኝም። ነገር ግን በእግላይ ዘፈኖች ተታላችሁ የማንነታችሁ አሻራ የሆነች ሀገራችሁን ለሰይጣናዊ አምልኮ አራማጅች አሳልፋችሁ እንዳትሰጡ አደራ። ከሰይጣናዊ ሴራ ተጠንቀቁ። ጥበብን እና ሰይጣናዊ ተልእኮን ለመለየት አይናችሁን ክፈቱ። እናንተ ኢትዮጵያዊ እንጂ አውሮፓዊ አይደላችሁምና ግብረ-ሰዶምን ለመደገፍ የሚከፈት አንደበት አይኖራችሁም። እናንተ የቴምድሮስ፣ የምኒልክ፣ የዮሃንስ የልጅ ልጆች ናችሁና ጨዋነታችሁ ወግ እና ባህላችሁ ኩተመሳሳይ ጸታ ጋር ጋብቻ ትፈጽሙ ዘንድ አይፈቅድላችሁም። የጨዋነታችሁን ማተብ በእፍኝ የእርዳታ ሰንዴ ላለመለወጥ ተጠንቀቁ። ያ ማተብ እናንተ ዘንድ እስካለ ድረስ ብቻ ነው ለሃገራችሁ ጨዋነታችሁን በተግባር ማረጋገጥ የምትችሉት። ከእጅችሁ ከወጣ ማተባችሁ ብቻ ሳይሆን እናንተም የሌላ ሆናችኋልና ለምስኪን ሃገራችሁ፣ የእይዘሽ ላይ ልጅች እጥረት ለገጠማት እድለ-ቢስ እናታችሁ ማልቀስ ይምሩ። ከእርዳታ ሰንዴ

ከርሰን ለመሙላት የጨዋነት ማተቡን ከሚበጥስ ይልቅ በጨዋነቱ ጸንቶ፣ የአባት የእያቶቹን ቃል ጠብቆ በርሃብ የሚሞት፣ በርሃብ መሞትን የሚመርጥ ምንኛ የተባረከ ነው!? አሞ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚወክለው እንዲህ አይነቱ የተባረከ ዜጋ ነውና የተባረካችሁ ሆናችሁ እንድትዘልቁ እናታችሁ ሁሌም እጆጅን የምትዘረጋለት አምላክ ብርታቱን ይስጣችሁ.....

"የምናገረው በስሜታዊነት አይደለም፡፡ የማውቀውን እና በውስጡ ያለፍኩበትን እውነት ነው፡፡ በምስጢር ማህበሩ አባላት ወጥመድ ወድቄ በነበርኩበት ሰአት ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ ያከናወነውን ተግባር አላማ ስነግራችሁ በስሜታዊነት እየተናገርኩ እንዳልሆነና በሃገራችን ላይ እየታሰበ ያለውን አደገኛ ሴራ ትረዳላችሁ ብዬ አምናለሁ....."

የስኩል አፍ ዋን ግሎብ ገጠመኟን በዝርዝር ከገለጸች በኋላ ረድኤት ሃይላይ ስለ አእምሮ ቁጥጥር ያወራትን በስፋት አብራራች፡፡ ማሳረጊያዋ ቁስ በቹ ነው፡፡

"ብዙውን ጊዜ ይህችን ምስኪን ሀገር አደጋ ላይ የሚጥሏት ለሆዳቸው ያደሩ፣ ሀገራዊ ራእይ የሌላቸው፣ እኔ ጠግቤ ሌላውን ጠኔ ይጣለው፣ ርሃብ እና ችጋር ይጋጠው የሚሉ ሀሊናቢሶች፣ የማይጠረቁ አሳሞች መሆናቸውን አንብቤያለሁ፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ በተግባርም አረጋግጫለሁ፡፡ በተግባር ያረጋገጥኳቸው እውነቶች ባልፈልግም ሁለት ለግል ጥቅም ያደሩ ኢትዮጵያውያን አሳሞችን አሰተዋውቆኛል፡፡ አንደኛው የስኩል ኤንድ ቦንስ ማህበር አባል እና በስልጣን ደረጃ የነበረ ኢትዮጵያዊ ሲሆን በሃገሩ ታዳጊ ሀጻን ላይ በፈጸመው ወንጀል የእጁን አግኝቶ ወህኒ ውስጥ ይገኛል፡፡ ዮናታን ወልዴ ይባላል፡፡ ፈጣሪ ባያጋልጠው ኖሮ ከምስጢር ማህበሩ አባላት ጋር አሲሮ ኢትዮጵያን የሰይጣን ልጆች ፅቅድ ማስፈፀሚያ ለማድረግ ቆርጦ የተነሳ ነበር.....

"ሁለተኛው በቅርቡ የተሾመ እና ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር እና ደላላ ሆኖ የተመደበ ሰው ነው፡፡ ሀጢ እና ጅዲ ሜናሂም ከተሰኙ ባል እና ሚስት ይሁዲዎች ጋር እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ቁስ በቹ

ይባላል። እስራኤል እና አሜሪካ በሚገኙ ዩኒቨርሲዎች የሥነ-መለኮት ትምህርቱን ተከታትሎ እንደተመረቀና ወደ ሀገር ቤት ተመልሶ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድቦ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ታማኝ ምንጮች አረጋግጠውናል። በምዕመኑ እና በሃይማኖት አባቶች መሃል መቃቃርን ለመፍጠር፣ የታቀደውን ሴራ ለማቀጣጠል በዝግጅት ላይ መሆኑን መናገር እፈልጋለሁ.....

"ስለዚህ የሃገሬ ዜጎች በተለይ ወጣቶች እነዚህን የሰይጣን ልጆች ሴራቸውን በማጋለጥ እግዚአብሄር የሚወደውን ሰራ እንድንሰራና እንድናሳፍራቸው እንዲሁም ሃገራችንን ሊቃጣባት ከታሰበው የሰይጣን ልጆች ጥፋት እንድንታደጋት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ። ማድረግ ያለብኝን በጥቂቱም ቢሆን አድርጌያለሁ ብዬ አስባለሁ። ቁልፉ፣ የሴራውን በር የሚዘጋው ወሳኝ ቁልፍ ያለው በእናንተ እጅ ነውና ለሴራው ክሽፈት ተግባራዊነት ተንቀሳቀሱ። እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር ይሁን!!"

የሶስና መረጃ በድረ-ገጽዋ በኩል ይፋ ከሆነበት እለት አንስቶ ዓለም አቀፍ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆነ። በባህር ማዶ የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያውያን አብረንሽ ነን ሲሉ በጎ ምኞታቸውን አስተላለፉላት። ከሃገር ቤት የደረሳት መልእክትም ነበር። በርካታ ዜጎች በተለይ ወጣቶች የሴራውን አራማጆች፣ ኖውልስን እና ቄስ በቹን የሚያወግዙ ጽሁፎቻቸውን በማህበራዊ ድረ-ገጾች ላይ በስፋት አሰራጩ። ጫናው በፊጠረው ግፊት በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሎ ድርጊቱ በምርመራ ስለተረጋገጠ ከስራው የተባረረው ቄስ በቹ በሃገር ክህደት ወንጀል ክስ ተመሰረተበት። እውነቱን እየመረራቸውም ቢሆን የተቀበሉት እነሮበርት አዳምስ እስቸኳይ ስብሰባ ተቀመጡ።

- 36 -

ኢሊኖይስ፣ አሜሪካ

"እርግጠኛ ነኝ ጉያችን ውስጥ አስገብተን ከያዝነው የሀገሯ ልጅ በስተቀር ለዚያች ተኩላ ምስጢር እያወጣ የሚበትን ከሃዲ አይኖርም" አለ ሮበርት አዳምስ እጅግ ተበሳጭቶ። አሌክሳንደር ሱልዝበርገር፣ አሌክሲስ ሮቢንስ እና አንድሪው ግርሃም በጽሞና እያዳመጡት ነው። የአሌክሲስ ሮቢንስን ደረት ከፍቶ ልቡን ማየት አይቻልም እንጂ ወንዳታ! ድሮውኑ ኢትዮጵያዊ አይደለሽ!? የሚል ሃሳብ ባነበቡበት። አዳምስ ንግግሩን ቀጠለ፦

"ሱልዝበርገር የስሜት ለውጥ ሳታሳይ ስራውን እንዲሰራ አድርግ። እንደተጠራጠርነው በፍጹም ማወቅ አይኖርበትም። ግርሃም ፈረንሳዊቷ አጋራችን እንድታገኝኝ አድርግ። ሮቢንስ ደግሞ.....ግዴለም መደበኛ ስራህ ላይ ብቻ አተኩር። የሁላችሁም የጋራ ተልእኮ ረድኤት ሃይላይ የተባለን እባብ በጥንቃቄ መከታተል እና ከተቻለ አድፍጦ እጅ ከፍንጅ መያዝ ነው። ግልጽ ነው?"

በእምንታ ራሳቸውን ነቀነቁ። ስብሰባው ይሄው ነበር።

****

"እኔ የምልህ?" አለው አሌክሳንደር ሱልዝበርገር አንድ ቀን ከWSIL-TV ህንጻ ስር ካለው ካፌ ሻይ-ቡና እየተባባሉ ሳለ።

"የሃገርህ ልጅ የመረጃ አነፍናፊነት አይገርምም? አሁንማ የተነጋገርነውን ሳይሆን እያሰብን ያለውንም የምትደርስበት እየመሰለኝ መደንገጥ ጀምሬያለሁ"

"መግረም ብቻ?! የምትደንቅም ፍጡር ናት። ፎቶዋን እንዳሳየኸኝ አይነት ፈጣን እና ምላጭ ሰው አትመስልም"

"ፎቶን አይቶ የሰውን ባህሪና ማንነት መረዳት ቢቻልማ ኖሮ....."

"ፎቶን በማየት የሰውን ባህሪ ማወቅ እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ላይንስ እንዳለ መጽሃፍ ላይ ማንበቤን አስታውሳለሁ"

"ይሆን ይሆናል። ከእሷ ይበልጥ አስገራሚ እና እንቆቅልሽ የሆነብን ግን መረጃዎቹን አሳልፎ የሚሰጣት ሰው ማንነት ነው" አሌክሳንደር ትኩር ብሎ ረድኤትን ተመለከተው።

"ሌትዬዋ የነዳንኤል ኢስቱሊንን፣ ዴቪድ አይከን እና የመሳሰሉትን ሰዎች ጎዳና መከተሏን አትርሳ። ይህንን የነገርከኝ ደግሞ አንተ ነህ። እነዚያን ይሁዳዊ ጥንዶችስ ምን ያህል ታምናቸዋለህ?"

ከወንጀሉ ነዳ ነኝ በሚል አይነት አነጋገር ኮስተር ብሎ ተናገረ። ግማሽ ሃሳቡ ፊትለፊቱ ተቀምጣ በፈገግታ የምትመለከተው ቆንጆ ጋር ቀርቶ ነበር። አሌክሳንደር ይህን ልብ ብሏል። አይቶ እንዳላየ ሆነ።

"ወደፊትም መረጃዎቻችንን ለአየር ላለመበተኗ ምንም አይነት ዋስትና ስለሌለን በሆነ መንገድ ልናስቆማት ግድ ይላል" አሌክሳንደር ረድኤትን የጎንዮሽ እየተመለከተ ተናገረ።

"ልክ ነህ። የግድ መሆን ያለበት ነው። ያለበለዚያ እቅዳችን....." ወጣቷ የጠቀሰችው መሰለው። ነው ወይስ በቁሙ መቃዠት ጀመረ? በጣም ታምራለች። የሞዴል ሰውነት አላት። አይኖቹን ማንሳት ተስኖታል።

"እኔ ቁምነገር እያወራሁ አይኖችህ እና መንፈስህ ያለው....." አሌክሳንደር እየሳቀ አናገረው።

"አታያትም እንዴ ውበቷ እኮ እንኳን የእኔን የትኛውንም ብርቱ ጎኛ ባይ ወንድ ልብ ቶጥ የሚያደርግ ነው!"

"አሌክሳንድራ ፓምፒዱ ትባላለች። ታዋቂ አለምአቀፍ ሰአሊ ነች። እየተዘዋወረች ኤግዚብሽን በማሳየት ትታወቃለች። ሁለት ጊዜ የጣቢያችን እንግዳ ነበረች"

"ታዲያ ለምን ፈገግታዋን አሳየችኝ? ሲል በውስጡ ካሰላሰለ በኋላ

"ወንበር ብንጋራት ቅር አይላትማ?" ሲል ጠየቀው።።

"ችግር የለም" ወደነበረችበት ጠረጴዛ አመሩ።። በፈገግታ ተቀበለቻቸው።።

"ሃይ አሌክሳንድራ እንደምን አለሽ? አሌክሳንደር ሱልዝበርገር እባላለሁ።። ከአንዴም ሁለቴ የጣቢያችን እንግዳ....."

"እረሳሁህም።። አስታውሼሃለሁ"

"ስለሙያሽ ስለነግርኩት ጓደኛዬ ሲተዋወቅሽ ፈለገና.....ሰአሊዎችን በጣም ያደንቃል...."

"ስለተዋወቅሁት ደስተኛ ነኝ።። አሌክሳንድራ ፓምፔዱ እባላለሁ" አለችና እጇን ለሰላምታ ዘረጋች።። በመቀጠልም እንዲህ አለችው።-

"ፈረንሳይ ተወልጄ ባድግም የጥበብ ሰው ሃገር የለውም በሚል እምነቴ ከሃገር ሀገር እየዞርኩ የስእል ስራዎቼን አቀርባለሁ" ረድኤት ደስ ብሎታል።። በቅርበት ሲመለከታት ደግሞ ክንፍ አልባ መልአክመስላ ታየችው።።

"ስላወቅሁሽ ደስ ብሎኛል።። ረድኤት ሃይላይ እባላለሁ።። በቅርቡ ነው ከሃገሬ ከኢትዮጵያ የመጣሁት።። የWSIL-TV ባልደረባ ነኝ።። አላገባሁም።። ወንደ-ላጤ ነኝ።።" ተሳሳቁ።።

"ልክ እንደኔ።። ጋዜጠኞች እና የጥበብ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሌሎችን ኑሮ ስለሚኖሩ የእራሳቸው ህይወት አይታያቸውም።።" ያልታሰበ ደራሽ ደስታ ሰውነቱን ወረረው።።

"እርግጠኛ ነኝ አንድ ቀን ስዕሎችሽን ታስነበኚኛለሽ?" አሌክሳንደር በፈረንሳዊቷ ቆንጆ አፍዝ አደንግዝ ውበት እንደተዝረከረከ ገብቶታል።።

"አንተም መኖሪያ ቤትህን ካስነበኘኸኝ?" ረድኤት የሰማውን ማመን አልቻለም።። ውብ ብቻ ሳትሆን ግልጽና ነጻ የሆነችው ፈረንሳዊት ቤትህን አሳየኝ እያለችው ነው።።

"በደስታ! አንቺ በፈለግሽው ቀን" ስልክ ቁጥር ተለዋወጡ፡፡ ወደቢሯቸው ከተመለሱም በኋላ የረድኤት ሃይላይ ወሬ ፈረንሳዊቷ ፓምፔዱ ሆና ነበር፡፡

በሶስተኛው ቀን ደወለችለትና

"ከቻልክ ለምን ዛሬ ቤትህን አታሳየኝም?" አለችው፡፡

"ይቻላል!" አላት በደስታ ትንፋሽ እያጠረው፡፡ እናትህ ሞተች ቢሉት እንኳን ቀጠሮውን እንደማይሰርዘው እርግጠኛ ነበር፡፡ ከስራ ሲወጣ ሊገናኙ ተስማሙ፡፡ በተቀጣጠሩበት ካፌ ውስጥ ያገኛት ረድኤት አለባበሷና ውበቷ መብረቅ ሆኖበታል፡፡ ልብን ትርክክ አድርጎ ሁለት ቦታ የሚከፍል ምትሃታዊ መብረቅ፡፡ የለበሰችው ነጣ ያለ ጂንስ ሱሪ የሰውነት ቅርጽዋን አጉልቶ አውጥቶታል፡፡ ከነጭ ሸሚዟ ውስጥ አፈትልከው ለመውጣት የተዘጋጁ የሚመስሉ ልከኛ መጠን ያላቸው ጡቶቿ ምራቁን እያስዋጡት ነው፡፡ ካፌ ውስጥ ጊዜ ማባከን አልፈለገም፡፡ ስጋ እንዳገኘ ጭልፊት ቆንጆዋን ጉያው ከቶ ወደመኖሪያው መብረር አሰኝቶታል፡፡

"ወደቤት እንሂድ፡፡ ልትወጂያቸው ትችያለሽ ብዬ የማስባቸው የመጠጥ አይነቶች አሉ፡፡ ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን፡፡" አደንዛዥ ፈገግታዋን አስቀድማ መስማማቷን በራስ ንቅናቄ ገለጸችለት፡፡ መሃል ኢሊናይስ ወደሚገኘው የመኖሪያ አፓርትመንቱ አመሩ፡፡ ጽድት ያለ ነው፡፡ ሰፋ ያለ ሳሎን፣ ምግብ ማብሰያ፣ ሁለት መኝታ ቤቶች እና ከአንደኛው መኝታ ቤት ጋር ተያይዞ የተሰራ መታጠቢያ ቤት፡፡ ሳሎኑ ውስጥ በስተ-ጥግ በኩል የቆመው ቄንጠኛ የመጠጥ መደርደሪያ ሙሉ ነው፡፡ ጉድ-ጉድ ብሎ ምግብ እስከሚያዘጋጅ የሃገሯን የፈረንሳይን ምርጥ ቪኖ ይዛ ፊልም ትመለከት ነበር፡፡

"ምርጥ የምግብ ሰራ ባለሙያ ነኝ፡፡ ሀገር ቤትም ሳለሁ ምግቤን የማዘጋጀው ራሴ ነበርኩ" አላት ምግቦቹን ጠረጴዛው ላይ እየደረደረ፡፡ አሳ፣ ፓስታ እና የተለያዩ አትክልቶች፡፡ ጎንለጎን ተቀመጡ፡፡ ወደመጠጥ ሲዞሩ

"ይህን የመሰለ ውበት ይዘሽ እንዴት እስከዛሬ አላገባሽም?" አላት

"ውብ ስለሆኑ ብቻ ባል ይገኛል እንዴ?" ስትል ከቀለደች በኋላ "እጅግየ ማፈቅረው ጋዜጠኛ ፍቅረኛ ነበረኝ፡፡ በኢራቅ ጦርነት ወቅት የጦርነት ዘገባ ሊሰራ ወደሰፍራው ተጉዞ....." ሲቃ አላናግር አላት፡፡ መጨረሻውን ባይሰማም የሆነውን መገመት አላቃተውም፡፡ ፍቅረኛዋን የኢራቅ ምድር እንዳሰቀረው እርግጠኛ ሆኗል፡፡ አዘነላት፡፡ በማያውቀው ጋዜጠኛ ቅናት እንዳደረበት መደበቅ አልቻለም፡፡

ሊያጽናናት አጠገቧ ተቀመጠ፡፡ እየፈራ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገ፡፡ አልከለከለችውም፡፡ ይልቁኑ ራሷን ትከሻው ላይ ዘንበል አድርጋ ወሲብ ቀስቃሽ በሆኑት አይኖቿ ፍዝዝ ብላ ተመለከተችው፡፡ ሰውነቱ ሲነቃቃ እና ሲፍታታ ታወቀው፡፡ ደምስሮቹ ተወጣጠሩ፡፡ ሙቀት በሙቀት ሆነ፡፡ ጎንበስ ብሎ ከንፈሯን ሳመ፡፡ የያዘችውን የመጠጥ ብርጭቆ ወለል ላይ ጥላ በሁለቱም እጆቿ አንገቱ ላይ ተጠመጠመች፡፡ ተስገብግቦ ሸሚዟን አወለቀ፡፡ እየተስገበገበች የሱሪውን ዚፕ ለመፍታት ሞከረች፡፡ አንዳቸው የአንዳቸውን ልብስ ለማውለቅ ተሽቀዳደሙ፡፡ ሳሎን ውስጥ እንደአውሬ የተጫጫሁበትን ወሲብ ፈጸሙ፡፡ በችሎታቸው ተደናነቁ፡፡ ርቃኗን ወደመታጠቢያ ክፍል እያመራች

"ከያዝክ የማትለቅ ጉንዳን ኖረሃል?!" አለችው፡፡

"አንቺም የወሲብ ንግስት ብትባይ እያንሰሽም" ፡

ከዚያን ቀን ጀምሮ ሚዜዎች መርጠው ከበሮ እያስደለቁ በሰማኒያ ጋብቻቸውን ባያውጁም ያልተፈራረሙ ባልና ሚስት ሆኑ፡፡ የፓምፔዱ መዋያና ማደሪያ የረድኤት ሃይላይ ቤት ሆነ፡፡ አልከፋውም፡፡ እንደውም እጅግ ደስተኛ ነበር፡፡ ፓምፔዱ ከስእል ስራ የሚተርፋትን ሰዓት ምግብ ትሰራለታለች፡፡ ልብሶቹን ትተኩስለታለች፡፡ ከልቡ አፈቀራት፡፡ ከልቡ ማፍቀርም ብቻ ሳይሆን ልቡንም፣ ያለውን ሁሉ አስረከባት፡፡ በፍቅሯ እፍ ብሎ በነበረበት ሰአት ይሆናል ብሎ ያልጠረጠረው ዱብዳ ተከሰተ፡፡ ከሶስና አለማየሁ ጋር የተለዋወጠውን የድምጽ፣ የጽሁፍ እና የቪዲዮ መረጃ ሁሉ ከያለበት በርብራ ለነርበርት አዳምስ አላልፋ

ለጠች፡፡ የሰዎቹ ሰላይ መሆኗን የተረዳው ከረፊደ ነበር፡፡ በተቀነባበረ ሴራ በመኪና እደጋ አጠፉት፡፡

****

የረድኤት ሃይላይን መወገድ ከአሌክሲስ ሮቢንስ የሰማችው ሶስና እጅጉን ብታዝንም ከተልእኮዋ አልተዘናጋችም፡፡ ያሰባሰበች ውን መረጃ በመጽሃፍ መልክ አዘጋጅታ ለህዝብ ልታደርስ ተዘጋጀች፡፡ ይህ ስራ የምስጢር ማህበር አባላት የሆኑት የሰይጣን ልጆች ወይ ከሴራቸው እስካልታቀቡ (ይህ እንደማይሆን ታውቃለች) ወይ ጥርግርግ ብለው ከምድር እስካልተወገዱ (የዚህም ምኞቷ እውን መሆን አጠራጣሪ ነው) የሚቀጥል ነው፡፡ ይህ የስራዋ የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው፡፡ ሰው እስከሚያውቅ እና ሙሉ በሙሉ ከእንቅልፉ እስከሚነቃ የማያቋርጥ ይሆናል፡፡ ከነኔ ሊቆም ቃል የገባላትን ረድኤትን ሙሉ በሙሉ እምነቷን አሳሳደረችበትም ነበር፡፡ አውነቱ ሳይለይ በእጭሩ ተቀጨ፡፡

ጠቃሚ መረጃዎችን አቀብሏታልና ስታመሰግነው ትኖራለች፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ እያለች የ"ዘአማሃቢ" ጋዜጣ አዘጋጅ ደወለላትና የተጠለፉት ህጻናት የታገቱበት ቦታ መታወቁን፣ ወንጀለኞቹ የፍርድ ውሳኔ ማግኘታቸውን እና ህጻናቱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር መገናኘታቸውን፣ ለጊዜው ከወላጆቻቸው ጋር ያልተገናኙትም በማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ እንዲቆዩ መወሰኑን እና የሃገሯ ልጅ የሆነው ሰለሞን አሽከሮፍትም ከአሳዳጊው ጋር መገናኘቱን ነገራት፡፡ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ውስጥ ገባች፡፡ የዮናታን ወልዴ መታሰር.....የረድኤት ሃይላይ መወገድ..... የሰለሞን አሽክሮፍትና የሌሎቹም ህጻናት ከወላጆቻቸው ጋር መገና ኘት.....የወንጀለኞቹ የፍርድ ውሳኔ.....ትላቅ ታልቅስ ግራ ገባት፡፡ መንታ ስሜት፡፡ እየሳቀች እነባች፣ እያነባች በሳቅ ተንከተከ ተች፡፡ የመጀመሪያው የፍላጎቷ ምእራፍ በድል ተጠናቋል፡፡ ለቀጣዩ በእጅጉ የምትተማመንበት እግዚአብሄር ያውቃል፡፡

ጽሞናዋን ለመሰብሰብ ሞከረች፡፡ የተረጋጋች ሲመስላትም የመጽሃፏን ርእስ በጉልህ ፊደል አሰፈረች፡፡ "ከሀዲዎቹ የሰይጣን

ልጆች!" ርዕሱ በሃገሯ ላይ ሴራ ሸርበው እና ተንኮል ጎንጉነው ለመንቀሳቀስ ሰፊ የሆነ እቅድ የያዙትን የምስጢር ማህበር አባላት እንደሚወክል እርግጠኛ ሆናለች፡፡ "እንደመግቢያ" ብላ ከጻፈችው ርዕስ ስር ደግሞ የሚከተለውን አሰፈረች፡-

"የምስጢር ማህበር አባላት በሃገሬ ላይ ማሴር ከጀመሩ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ዛሬም ኢላማቸው ነች፡፡ ርሃብ ያንገላታቸው ወገኖቼን ምድር በሚያለማ ቴክኖሎጂ ሰም ጨርሰዋል፡፡ በኢየሱሳውያን ቄስ ቡራኬ ሃገሬን ለመውረር ሞክረዋል፡፡ የሰይጣን መልዕክተኛ የሆነች አቀንቃኝ በተቀደሰ ስፍራ አሰርገው አስገብተዋል፡፡ አማኙንና የሃይማኖት አባቶችን ለማቃቃር ሞክረዋል፡፡ የሰይጣናዊ አምልኮታቸው ቅኝ-ተገዢዎች እንሆን ዘንድ ብዙ ጥረዋል፡፡ አይሳካላቸውም፡፡ ወገኖቼ ከተንኮላቸው ተግባራዊነት በፊት ቀድመው ይነቃሉና ምኞታቸው እንደ ማለዳ ጤዛ ይረግፋል፡፡ እንደ መስከረም እና ጥቅምት ጉም ይበናል፡፡ ለምን ቢሉ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ የትኛውም ሃያል ሃገር ሳይሆን ወደ ፈጣሪ ትዘረጋለችና.....!"

እጥር ምጥን ያለው መግቢያ መልዕክትም ተስማምቷታል፡፡ ወደ ዋናው የመጽሃፉ ርዕስ ተሸጋገረች፡፡ ምዕራፍ አንድ *"የሰይጣን ልጆች ሴራ በኢትዮጵያ በፈጣሪ ሃይል ሲከሽፍ....."*

በመጨረሻም በድል እንደምታጠናቅቀው ፍፁም እርግጠኛ ነበረች፡፡

ድህረ-ታሪክ

ሂዮንሴ ፍውልስ በአለቆጅ እቅድ እና ትእዛዝ መሰረት ኢትዮጵያ ከደረሰችበት፣ ቤተክርስትያን ውስጥ የተለየ አቀባበል ከተደረገላት፣ ጎንጥላ ከተያዘላትና ሀጻናት መርጃ ድርጅት ከጎበኘች እለት አንስቶ በህዝቡ ዘንድ የተለያዩ ስሜቶች ተፈጥሩ። የቤተ-ክርስትያን ሰዎችም በቁጣና በንዴት አስተያየታቸውን ሰጡ። ከእነሱ መሃል አንዱ የሆነው ዲያቆን ብሩክ ሃይሌ ጉብኝቷን አስመልክቶ በተዘጋጀ መጽሃፍ ላይ የሚከተለውን አስተያየት ሰጠ።

"ቤተክርስቲያን በተናጠል ሂዮንሴን ብቻ ላይሆን ዘፋኝን የምትቀበልበት መንገድ ላይ የተወሰኑ ነጥቦችን ላንሳ። "የሥጋ ስራዎች የተገለጡ ናቸው" ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ገላቲያ መልዕክቱ ላይ የዘረዘራቸው ውስጥ አንዱ ዘፋኝነት ነው። በተጨማሪ ዘፋኝ መንግስተ ሰማይን አይወርስም የሚል መልእክት ያላቸው ጠንከር ያሉ ትዕዛዛት አሉ። ሰው የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው። አንደበቱ የተዘጋጀው እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው። ከዚያ ውጭ እንደዘፋኝነት ባለ መንገድ መሰማራት ከኃጢያት የሚመደብ ነው። በእኛ ቤተክርስቲያን በሃይማኖቱ ደረጃ ይሄ አቋም እያለ ዘፋኞችን የምንቀበልበት እና የምናስተናግድበት መንገድ የተሳሳተ ሆኖ ይታያል። ወደ ሂዮንሴ ከመምጣቴ በፊት የተወሰኑ ነጥቦችን ላንሳ። አንደኛው ነገር በዓለማዊ ዝናቸው ወይም በዘፈን ባላቸው ታዋቂነት ቤተክርስቲያን የተለየ ቦታ እንድትሰጣቸው መደረግ የለበትም፣ ዘፋኞች በተለየ ስነ-ስርዓት ሲቀበሩ ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ ተራ ሰው እድሜውን ሙሉ ሃይማኖቱን፣ ምግባሩን ጠብቆ ኖሮ ሲሞት የዘፋኙን ያህል ቦታ ሲያጣ እንመለከታለን። ዘፋኙ እንደ ጀግና ተቆጥሮ፣ ታላላቅ አባቶች ተገኝተው የቀብር ስነ-ስርዓቱ ሲከናወን ሲንመለከት ስህተት እየተሰራ እንደሆነ እንገነዘባለን። እንደውም ይሄ ምን ያመለክታል?

ቤተክርስቲያኗ የዘፈን አድናቂ የሆነች ነው የሚያስመስላት። ያ ሰው ዘፋኝ ስለሆነ ብቻ የተለየ አክብሮት የሚሰጠው ከሆነ በተዘዋዋሪ ዘፈን እየተበረታታ ነው ማለት ነው። ብዙ ዘፋኞች ኦርቶዶክስ ሆነው ይቆዩና ዘፈን የሚያቆሙት ወደ ፕሮቴስታንት ሃይማኖት ሲሄዱ ነው። ለምን? ብንል ዘፈናቸውን ሳያቆሙ ቤተክርስቲያን መልካም አቀባበል እያደረገችላቸው ነው የቆየችው እና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውስጥ እያሉ ዘፈንን እንደ ኃጢያት እያዩትም። አንድ ዘፋኝ መዝሙር አውጥቶ ለዚህ ቤተክርስቲያን ማሰሪያ ብሎ ቢሰጥ ይበረታታል፣ ከዚህ ሰው የሚገኘውን ገቢ እንጂ ሰውዬውን አንፈልገውም ማለት ነው። እገሌ ጴንጤ ሆኖ ዘፈን አቆመ የሚል ነባር በተደጋጋሚ ይሰማል። ኦርቶዶክስ እያለ ዘፈን ይፈቀድ ነበር እንዴ? በመፅሐፍ ቅዱስ ደረጃ አይፈቀድም። በተዘዋዋሪ ግን እየደገፍነው ነው። በጣም ጥቂቶች ናቸው ከዘፈን ወደ ቤተክርስቲያን ህይወት ተመልሰው መዝሙር አወጡ ሲባል የምንሰማው፣ ከዚያ ውጭ ግን ብዙዎቹ እዚያው ሆነው ነው በመንታ መንገድ ላይ ሲጓዙ የምንመለከተው።

"ቤተክርስቲያናችን ዘፋኝነትን ትቃወማለች። ዘፋኙ ንሰሃ እንኳን ቢገባ እንደመጣ ወደ መዝሙር አትመልሰውም። የአመክሮ ጊዜ የሚባል አለ፣ ዘፋኝነት በአደባባይ የተሰራ ኃጢያት ነው። ስለዚህ በአደባባይ ነው ንሰሃ መግባት ያለበት። የመድረክ አገልግሎት የዋዛ አይደለም። ብዙ ፈተና አለው። ዘፋኝነት ላይ ያለ ስኬት መንፈሳዊው ህይወት ጋር ሰመምጣት ክሬዲት ሊሆን አይገባም፣ እዚህ እንደተመጣ ወድያው መድረክ ላይ የሚወጣ ከሆነ ይሄ መድረክ እውቀት አያስፈልገውም ወይ? ያስብላል።

"ሃይ ባይ ስለጠፋ በዘፈን ውስጥ ሃይማኖታዊ ሀሳቦችን እና ቃላቶችንም መጨመር ፋሽን እየሆነ መጥቷል፣ በእመቤቴ... በአማላጇ የሚሉ ቃላት በዘፈን ግጥሞች ውስጥ እየተሰሙ ነው። የአብይ ፆም ሰሞን የባህል ሙዚቃ ተጫዋቾች የሚዞሩት ወደ በገና ነው፣ እነዚህ አርቲስቶች ሙሉ በሙሉ ወደ መንፈሳዊ ህይወት ቢመለሱ መልካም። ሳይመለሱ ነው ወቅት እየጠበቁ መንፈሳዊ ዜማ የሚያሰሙት፣ ይህ ትክክለኛ አካሄድ አይደለም። የቲያትር

ቤት የሙዚቃ ተጫዋቾች ቅዳሜና እሁድ መንፈሳዊ ጉባዔ ላይ ይወጣሉ። ስርዓት ያጣ የመሳሪያ አጨዋወት ይታያል። ምክንያቱም ወሰኑ ጠፍቷል። የመንፈሳዊውና የዓለማዊው ሀይወት ወሰን ተደበላልቋል። በዚህ የሚቀጥል ከሆነ ደግሞ ዘፋኝና ዘማሪ፣ ኮሜዲያንና ሰባኪ፣ መንፈሳዊ ሚዲያ እና ዓለማዊ ሚዲያ እየተደበላለቀ ነው የሚሄደው። ይህ ደግሞ በእርግጠኝነት ነው የምናገረው ዋጋ ያስከፍለናል። እኛ እነሱ ጋር እየሄድን እንዘባርቃለን፣ እነሱ እኛ ጋር መጥተው ይዘባርቃሉ። ይሄ ወሰን (ቦርደር) መጥፋቱ ሰዎች ወደ መንፈሳዊ ሀይወት ጠቅለው እንዳይመጡ እንቅፋት ይሆናል።

"የእንድ ድምፃዊ ገጠመኝ ላንሳ። ስሙን ማንሳት አስፈላጊ ስላልሆነ ነው። በቀብሩ እለት የህይወት ታሪኩ ሲነበብ ምን ተባለለት? "ይህ ሰው መረዋ በሆነ ድምፁ ሲዘፍን ነበር... ህዝቡን ሲያገለግል ነበር።" በሙዚቃ ችሎታው፣ በድምፃዊነቱ በህዝብ ዘንድ ሊደነቅ ይችላል። ህይወቱ ጥሩ እንዳልነበረ ግን እርሱ ራሱ በህይወት ሳለ በሰጠው ቃለ-ምልልስ ተናግሯል። በዚህ አይነት ህይወት ውስጥ አልፎ ይፀድቃል ብለን ከመሰከርን በስፍራው የነበረው ህዝብ የሚረዳው እሱ በእዚህ አይነት ህይወት ውስጥ አልፎ የሚጸድቅ ከሆነ እኔ ምን አጠፋሁ! የሚል ድምዳሜ ላይ ይደርሳል። እዚህ ላይ አንድ አስተያየት ሊሰነዘር ይችላል። ዘፋኝም ንሰሃ ሊገባ ይችላል የሚል። አዎ! ንሰሃ ሊገባ ይችላል። ንሰሃ ሲገባ ግን ሌላው ሰው "ትሪት" በሚደረግበት መንገድ ነው "ትሪት" የሚደረገው እንጂ ከዓለማዊ ዝናው አንፃር አይደለም። የእሱ ዝነኛ መሆን ቤተክርስቲያን ላይ የሚያመጣው የተለየ ነገር አይኖርም። ዘፋኝም ይሁን ንጉሥ ያው እንደተርታ ሰው ነው። ንጉሰ ዳዊት እንኳን ምንድን ነው ያለው? "በእግዚአብሄር ቤት መጣልን መረጥኩ" ነው ያለው። ልብ እናድርግ! ንጉስም ቢሆን በእግዚአብሔር ቤት እንደሌላው ተርታ ሰው መሆኑ አልጠፋውም።

"የትንሳኤ እለት ያጋጠመኝን ነገር ልናገር። እንድ ጉባዔ ነበር ሩፋኤል ቤተክርስቲያን። በእለቱ አስተምር ነበር። እርቲስቶች መገኛር ሊያቀርቡ በስፍራው ተገኝተው ነበር። ትምህርቱ ላይ

ግን አልተሳተፉም፡፡ እነዚህ ሰዎች መዝሙር በሚያቀርቡበት መድረክ ላይ ለመግር ዝግጁ አልነበሩም፡፡ እዚያ ሆነን የሆነ ነገር አስተዋፅኦ ካደረግን እንደፀደቅን ይሰማናል፡፡ እግዚአብሔር በእርዳታ ከምንሰጠው ገንዘብ በፊት እኛን ነው የሚፈልገን፡፡ አንድ ሰው መቶ ሺህ ብር ከሚሰጥ በንፁህ ልቡ መቶ ቢሰግድ እግዚአብሄር ይደሰታል፡፡ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር የምንገዛው በሰውነታችን ነው፡፡ ያሙም፣ ፀሎቱም፣ ንሰሃውም አያስፈልገንም እያልን ገንዘብ ብቻ የምንለግስ ከሆነ ጨዋታ ነው የሚሆነው - ያውም አደገኛ ጨዋታ፡፡ ዋጋ የሚያስከፍል ጨዋታ፡፡ ይህ ነገር እናስታውስ እንደሆነ ከአሜሪካ ነው የተጀመረው፡፡ አንድ ሰሞን ዘፋኞች መዝሙር እወጡ ተብሎ በጣም ተናፍሶ ነበር፡፡ ቀደም ብዬ እንዳልኩት ወሰኑ ተቀላቅሏል፡፡ ብርሃን ከጨለማ ምን ህብረት አለው? ዘፋኝነት ከመዝሙር ምን ህብረት አለው? ቀልድና ስብከት ምን ህብረት አለው? በሂዮንሴ ደረጃ ብቻ ላይሆን በሀገር ደረጃም ተቀላቅሏል፡፡ እነዚህ አሁን መዝሙር አወጡ ያልናቸው አርቲስቶች መዝሙር ላይ የመግቢያ ንግግር የሚያደርጉት ሊቃነ-ጳጳሳት ናቸው፡፡ ማንኛውም ዘማሪ (በተለይ እውቅና የሌለው) መዝሙር አውጥቶ አንድ ጳጳስ ንግግር ያድርግልኝ ቢል አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ምንድነው ይህን ያደረገው ታዋቂዎች መሆናቸው ነው፡፡ መንፈሳዊ የምንለው ሰው እነሱን በማግኘቱ፣ ከእነሱ አጠገብ ሆኖ በመታየቱ የተለየ ክብር የሚሰማው ከሆነ አደገኛ አካሄድ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን እኮ የማይታዩ መላዕክት አሏት፡፡ ከሁሉ በላይ የማይታዩ ቅዱሳን አሏት፡፡ ያ ነው የሚያስከብራት፡፡ በእነሱም፣ በዘፋኞቹም በኩል ይሄ ክብር አይገባኝም የሚለውን ነገር መልመድ አለባቸው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ጠፍቶ ቆይቶ ወደ አባቱ የተመለሰው ልጅ "አባቴ ሆይ ልጅህ ልባል አይገባኝም ከባሪያዎችህ አንዱ አድርገኝ" ነው ያለው፡፡ ዘፋኞቻችንም ይህንን ትህትና መልመድ አለባቸው፡፡

"ወደ ዋናዋ ርዕሳችን ወደ ሂዮንሴ ስንመጣ ህዝብ መገንዘብ ያለበት ቤተክርስትያን ተግኝታ በልዩ አቅባበል ጥላ የተዘረጋላት ለእሷ ክብር ተብሎ እንዳልሆነ ነው፡፡ ያ ዝግጅት የጳጳሳት ፍታት

ነው.....የፓትሪያርኮች ፍታት ነው፡፡ ያረፉ ፓትሪያርኮች በየዓመቱ ፍታት ይደረግላቸዋል፡፡ መታሰቢያ ዐሎት አለ፡፡ የመታሰቢያ ቀን አለ፡፡ ያ ቀን ማለት ሂዮንሴ የተገኘችበት እለት ነው፡፡ በጣም የተዘነጋው ነጥብ እሱ ነው፡፡ እዚያ ላይ ወረብ ያቀረቡ የሰንበት ተማሪዎች፣ ወረብ ያቀረቡ አባቶች እና ካህናት ቪዲዮው ላይ በደንብ ለሚሰማ የሚሉት ነገር ሰለ እነዚህ ብፁዓን አባቶች ነው፡፡ ዜማው እራሱ ያንን የሚገልፅ ነው፡፡ በእርግጠኝነት እዚያ ሰነ-ስርዓት ላይ ወረብ እና መንፈሳዊ ዜማ ያቀረቡ ወጣቶችም ይሁኑ ካህናት ስለ እሷ መምጣት የሚያውቁት ነገር አልነበረም፡፡ ወረብ እኮ ከምንም ነገር ተነስተን የምንለው ነገር አይደለም፡፡ ሊቃውንቱ እንኳን ሲማሩት የኖሩት ስለሆነ ያለዝግጅትም ሊያቀርቡት ይችላሉ፡፡ ወጣቶች ግን ለዚያን እለት ምንድን ነው የምናቀርበው ብለው ሊያጠኑ ከርመው ነው የሚያቀርቡት፡፡

"ስለዚህ መዝሙር ጥናቱ ላይ ሂዮንሴ ስለምትመጣ አጥና ተብሎ የሚታዘዝ ወጣት አይቀበለውም፡፡ ሊቃውንቱም ቢሆኑ ፈፅሞ አያደርጉትም፡፡ ሌላው ቢቀር በቅኔ እንኳን ይጎሸማሉ፡፡ የእኛ ሊቃውንት የማይጥማቸው ነገር መድረክ ላይ ሲኖር ምን ያደርጋሉ? በቅኔ ተችተው ነው የሚወርዱት፡፡ እና ያ ስርዓት ለሂዮንሴ ተብሎ የተዘጋጀ ሳይሆን የሊቃነጳጳሳቱ ፍታት መሆኑን ሊታወቅ ይገባል፡፡ ከቅዱስ ፓትሪያርኩ ጋር የተገኙትም ሊቃነ-ጳጳሳት በእርግጠኝነት መናገር አችላለሁ ሰለ ሂዮንሴ መምጣት የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ የሂዮንሴን ፕሮግራም ማን አስተካከለው? ከትትል እና ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ አንድ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ሰው ያደረገው ሙሉ በሙከርስቲያኗን ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል፡፡ ማረጋገጥ የምንችለው ግን ፓትሪያርኩ ሳይፈቅዱ መሆን የማይችል መሆኑን ነው፡፡ እዚህ ጋር ወሳኝ ነጥብ ማንሳት እንችላለን፡፡ ጥምቀት ላይ ብዙ ቱሪስቶች ወደሀገራችን ይመጣሉ፡፡ እነዚህን ሰዎች ታሪካቸውንና ሃይማኖታቸውን አጥንተን አይደለም የምናመጣቸው ስርዓቱ ደስ ስለሚላቸው ይመጣሉ፡፡ በደስታና በመልካም የእንግዳ አቀባበል ስሜት እናስተናግዳቸዋለን እንጂ የቪአይፒ ቦታ ጥላ ተዘርግቶላቸው ከፓትሪያርክ አጠገብ

አይቀመጡም፡፡ ትልቁ ስህተት ያለውም እዚህ ጋር ነው፡፡ ስነ-ስርዓቱ ለእሷ አይደለም ሁሉም ነገር (ዝግጅቱ) እራሱን የቻለ ምክንያት አለው፡፡ ይህ አያከራክረንም፡፡ ጥያቄው ማንኛውም ቱሪስት ሲመጣ ከፓትሪያርክ አጠገብ ይቀመጣል ወይ? የሚለው ነው፡፡ አይቀመጥም! እሷ የተገኘችበት እለት የተሰራው አሳፋሪ ስህተት ጥላ ተይዞላት ከቅዱስ ፓትሪያርኩ ጎን መቀመጫ ነው፡፡

"ይህች ሴት የኢትዮጵያ ፓትሪያርክን ሳሳገኝ አልሄድም ብትል እንኳን ማንኛውም ግለሰብ እንደሚያደርገው በግል ሊያነጋግሯት ይችላሉ እንጂ በሚዲያ ፕሮሞት በሚደረግ ደረጃ ማስተናገድ ከባድ ነው፡፡ የትኛውም ቱሪስት ይህን መብት አግኝቶ አያውቅም፡፡ ለእሷ ይህ መብት በተለየ ሁኔታ ለምን ተሰጣት? ዘፋኝ ስለሆነች!? እዚህ ጋር ተቃርኖው መጣ ማለት ነው፡፡ በእኛ ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜ ለዘፋኝ የሚሰጠው ቦታ በጣም አስጊ ነው፡፡ ለዘማሪ የማይሰጥ ነው፡፡ በእግራቸው ገጠር ድረስ እየሄዱ እየዘመሩ ህይወታቸውን በአገልግሎት ያሳለፉትን እነተስፋዬ ኢዶን ማስታወስ እንችላለን፡፡ ዘማሪዎች የዘፋኞችን ያህል....ወደ ሂዮንሴ እንመለስ፡፡ እርግጠኛ ሆኜ መናገር የምችለው ያን እለት፣ ሂዮንሴ ቤተክርስትያን ቅጥር ግቢ ተገኝታ ጥላ የተዘረጋላት እለት እዚያ የነበሩት በሙሉ በሁኔታው ደስተኞች ያለመሆናቸውን ነው፡፡

"ከዚያ በኋላ የፃፉም፣ የተቃወሙም፣ በጋዜጣ አስተያየታቸውን ያሰፈሩም ብዙ አሉ፡፡ የዚህችን ሴት አቀባበል በተመለከተ የተለየ ነገር ባይደረግላትም በቪ.አይ.ፒ ቦታ ላይ መቀመጫ አግባብ አይደለም፡፡ ማንኛውንም ቱሪስት ማተብ ካላሰርክ አትገባም እያልን አይደለም የምናስገባው፡፡ [እንዲያውም በእንባሩ] እዚህ መጥታ በነበረበት ወቅት ያናገሯት የሃይማኖት አባቶች ሊነግሯት፣ ሊገስፅዋት እና ሊያስጠነቅቋት ይገባ ነበር፡፡ የተከተልሽው መንገድ የማያዋጣ ነው ሊሏት ይገባ ነበር፡፡ ያለመናገር እራሱ ያስጠይቃል፡፡ ነብዩ ኢሳያስ ሃያ ሰባት ዓመት ከንፈሩ በለምጥ ተመቶ ትንቢት መናገር ሳይችል ቆይቷል፡፡ ለምን? ንጉሥ አዝያን ጥፋት ሲያጠፋ ባለመናገሩ ነው፡፡ [እኛስ] ይህችን ሴት ወደ ትክክለኛ መንገድ ለማምጣት ምን ነግረናታል?

«ይህች ልጅ አሁን የኢሉሚናቲ አባል መሆኗን በእንደበቷ እየመሰከረች ነው። እሷ ወደሀገሯ ከተመለሰች በኋላ የምናያቸው መረጃዎች እያንዳንዱ እንቅስቃሴዋ ተልዕኮ እንዳለው የሚያመለክቱና የሚጠቁሙ ናቸው። ብዙ ጊዜ የእምነት ቦታዎች ፈተና ይበዛባቸዋል። ኢትዮጵያ የፈጣሪ ሀገር እንደሆነች አለምም የመሰከረው እውነት ነው። ከእዚህ አንባር ሰይጣን የሚያስበው ነገር ሊኖር ይችላል። ከእኛ ጋር ተያይዛ መነሳቷ.....“ታግ” መደረጓ ጥሩ አይደለም። ሀፃናትን ሰብስባ ምልክቶችን ስለማስተዋወቋ በይፋ ተመልክተናል። ያ እራሱ ጥርጣሬ ላይ የሚጥለን ምልክት ነው። ከዚያ ውጭ የሰይጣኒዝምን እምነት የሚያራምዱ ወገኖችን ከዚያ በፊት አግኝታቸው ከሆነ የእሷ እዚህ መምጣት ምንም ላይታሰብ የተደረገ ነው ለማለት ይቸግራል። እና ለእንዲህች አይነት ሴት የቪ.አይ.ፒ ቦታ መስጠቱ ትልቅ ስህተት ነው።

“የተደረገላት መስመር ያለፈ አቀባበል በወቅቱ ብዙ ኦርቶዶክ ላውያን በሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ፊት ምንም ማውራት እንዳይችሉ አድርጓል። ያ ነገር በዜና ሲታይ አጠገብ ያለ ሰው ይዘብት ብናል። ለዚህ ነው ዋጋ አስከፍሎናል ያልኩት። ቅዱስ ዳዊት ስለ እስራኤል ሲናገር “ለጎረቤቶቻችን መሳለቂያ ሆንን” ብሏል። እኛም ላይ የታየው ይህ ነው። ወደፊት ካላስተካከልነው አደገኛ አካሄድ ነው። እግዚአብሔር መሃል ሰፋሪ ከርስቲያኖችን አይወድም። ወይ ጭልጥ ብለን አልካድንም፣ ወይ በሙሉ ልባችን ፈጣሪን አልተከተልንም። መሃል ላይ ነው የምንዋልለው። ለዚህም እኮ ነው ለጎሂዮንሴ አይነት ከስተት ከፍተት የምንፈጥረው።

“በሃይማኖት ዙሪያ ያለንውም ሰዎች ከሚዲያው ተፅእኖ መውጣት ይኖርብናል። ለሂዮንሴ ለምን የተለየ አክብሮት ሰጥተን ጋበዝናት? ሚዲያው ከሰጣት የተጋነነ ከብር ላይ ተነስተን ነው። በሃይማኖቱ ሰዎች ዘንድ ከዓለም ምንም አልፈልግም የሚለው ሀሳብ ይሰርፅ ዘንድ ያስፈልጋል። ያለበለዚያ ወሰኑን እናደባልቀውና የሂዮንሴ አይነት ሰው ሲመጣ መነታረኪያ አጀንዳ እንሆናለን። መነታረኪያ አጀንዳ ከመሆን ደግሞ እሱ ይጠብቀን።”

በመቅቱ ይህን የዲያቆኑን አስተያየት ያነበቡና ከሶስተኛ ወገን የሰሙ በርካታ ኢትዮጵያውያን በአንድ ድምጽ እንዲህ አሉ፡- "አሜን፡፡ ቅድስት ሃገራችንን ኢትዮጵያን ሂዮንሴን ከመሰሉ የሰይጣን ተላላኪዎች ጠብቅልን!!"

ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!